እሺ አሁን በጥሞና ታዳምጣላችሁ ፍ/ቤቱ የክስ ቻርቱን ያሰማል አስተርጓሚው ያስተረጉማል ንገራቸው ለማታውቁት በአስተርጓሚ በኩል እየተተረጎመ ትሰማላችሁ ስለዚህ ማሾክሾኩን ወረቀት ማምታታቱን ታቆማላችሁ እሺ ክሱን እናነባለን አንደኛ ክስ በአንደኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ የቀረበ ነው 1ኛ ተከሳሽ 1ኛ ክስ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ የቀረበ የክስ ቻርት ነው በአብዱረህማን ባሌ ጎጆ እየሰማህ ነው 1ኛ ክስ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስቦ ቀኑ እና ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅበት ታህሳስ ወር 1997 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቦሎ ኦዶ ወረዳ የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ የሚኖሩትን የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችን ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ተደራጅተው እንዲታገሉ እና እንዲደግፉ በመገፋፋቱ በፈጸመው የመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው። እና 1ኛ ክስ የቀረበው ያው 257ለ ላይ የተመለከተውን ተላልፈሃል በማለት የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑትን ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ኦነግ ብሎ ለሚጠራ ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ተደራጅተው እንዲታገሉ እና እንዲደግፉ በመገፋፋት በፈጸምከው የመገፋፋትና ግዙፍ የሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰሃል የሚል ነው አስተርጉምለት ግልጽ ነው ገብቶሃል

አዎ

እሺ 2ኛ ክስ በ1ኛ፣ 8ኛ እና 14ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ክስ ነው 1ኛ ተከሳሽ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ 14ኛ ተከሳሽ ኢብራሂም ሁሴን ጉራቾ እና 8ኛ ተከሳሽ ፋጤ አሜ ሳዲቅ ፋጤ የታለች እሺ

2/18

1ኛ፣ 8ኛ እና 14ኛ ማለት አብዱረህማን፣ ፋጤና ኢብራሂም ሁሴን ጉራቾ 2ኛው ክስ እናንተን የሚመለከት ነው ክሱን እናሰማለን ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 321ሀ 27/1 እና 238/1ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስና አደጋ ላይ ለመጣል አስበው ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1996 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቦሎ ኦዶ ወረዳ ቡርቃ ከተማ ልዩ ቦታው ቀጠና 2 ጤና ጣቢያ አካባቢ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ብሎ የሚጠራውን አሸባሪና ፀረ-ሰላም ቡድን በመደገፍ የተነሳውን ረብሻ በማነሳሳታቸው እና በመምራታቸው በፈጸሙት በህገ መንግስት እና በህገ መንግስት ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው።

የቀጠና 2 ጤና ጣቢያ አካባቢ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ኦነግ ብሎ የሚጠራውን አሸባሪ ፀረ-ሰላም ቡድን በመደገፍ የተነሳውን ረብሻ ለማነሳሳታቸው እና በመምራታቸው በፈጸሙት በህገ መንግስት እና በህገ መንግስት ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ስለሆነ ግልጽ ነው እሺ 3ኛ ክስ በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 4ኛ፣ 6ኛ፣ 8ኛ፣ 10ኛ፣ 44ኛ፣ 57ኛ፣ 60ኛ እና 69ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ የክስ ቻርት ነው 1ኛ ተከሳሽ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ እጅህን አውጣ

ስትጠሩ እጃችሁን አውጡ

2ኛ ሸሪፍ አሊ መሀመድ፣ 4ኛ አመዲን ኢብራሂም ሀሰን፣ 6ኛ መሀመድ ኢብራሂም አደም፣ 8ኛ ፋጤ አሜ ሳዲቅ፣ 10ኛ ጣሃ አህመድ፣ 44ኛ ሀጂ ጣሃ ሀሰን ቡሌ፣ 57ኛ ሼክ ከዲር ቱራ ሊዮ፣ 60ኛ ሸኪብ ቱኬ ሀሰን፣ 69ኛ ሀሰን መሀመድ፣ እሺ ይሄ ክስ አሁን እጅ ያወጣችሁትን እና ፍ/ቤቱ በልዩ ሁኔታ የተጠራችሁትን ሰዎች ይመለከታል እጃችሁን ማውረድ ትችላላችሁ ክሱን አዳምጡ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 321ሀ እና 25ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበው ከ2000 ዓ/ም እስከ 2001 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ቡርቃ ከተማ ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ብሎ በሚጠራው አሸባሪና ፀረ-ሰላም ቡድን ውስጥ በአባል በመሆን የዚሁ ቡድን እኩይ አላማ እንዲሳካ ገንዘብ በመስጠት በመዘዋወር ለሽፍቶች መንገድ በማሳየትና በመምራት ሞባይል በመግዛት የወዛደር ልብስ በመግዛት እና በማቅረብ እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማቅረባቸው በፈጸሙት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት የማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው። ግልጽ ነው

2ሰ/ዓ

ገብቷችኋል እሺ 4ኛ ክስ በ3ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ የቀረበ ነው 3ኛ ተከሳሽ አህመድ ኑር ኡርጌ እጅህን አውጣ እስቲ ወደዚህ ወጣ በል እሺ ይሄኛው ክስ አንተን የሚመለከት ነው ------ ታዳምጣለህ እጅህን ማውረድ ትችላለህ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 37/1 እና 256ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ሆን ብሎ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ለማፍረስ እና አደጋ ላይ ለመጣል አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ታህሳስ ወር 2001 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 2:00 ሰዓት ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ በዲዲምቱ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውል ሶስት ሳጥን ጥይት እና ብዛት ያለው የወታደር የእስፖርት ልብስ 7ኛ ተከሳሽ ለሆነው ሲራጅ አህመድ በማቅረቡ በመፈጸሙ በአባሪነት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው። 7ኛ ተከሳሽ ሲራጅ አህመድ በማቅረብ ግልጽ ነው ገብቶሃል

አንተ አትናገርም እንዴ

አዎ

እሺ ከገባህ ወደ ኋላ ተመለስ 5ኛ ክስ በ5ኛ እና በ19ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ክስ ነው 5ኛ ተከሳሽ ማለት ከማል አሊዬ አህመድ እና ኢብራሂም ሁሴን ጉራቾ ይሄ ክስ እናንተን ይመለከታል ይሄን ክስ በጥሞና ታዳምጣላችሁ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 321ሀ 27/1 እና 238ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና አደጋ ላይ ለመጣል አስበው ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ/ም ከጠዋቱ በግምት 12:30 ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ጫካ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ብሎ የሚጠራውን አሸባሪና ፀረ-ሰላም ቡድን በመደገፍ ከ70 እስከ 120 የሚደርሱ የኦነግ ወታደሮችን በማስተባበር በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ላይ ተኩስ ከፍተው ተኩስ መክፈታቸው አንደኛው ኡስማን መሀመድ ሁለተኛ ያቆብ አብዱልዋል ሶስተኛ መሀመድ አሊዬ አራተኛ አሊዬ መሀመድ የተባሉትን ግለሰቦችን በመግደላቸው በተጨማሪ ቁጥራቸው የማይታወቅ ሰዎችን በማቁሰላቸው በፈጸሙት በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው። እና በአጭሩ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ተብሎ የሚጠራውን አሸባሪ ፀረ-ሰላም ቡድን በመደገፍ ከ70 እስከ 120 የሚደርሱ የኦነግ ወታደሮችን በማስተባበር በኢትዮጵያ

250

መከላከያ ሰራዊት ላይ ተኩስ ከፍተው ተኩስ መክፈታቸው 1ኛ ኡስማን መሀመድ 2ኛ ያቆብ አብዱልዋል 3ኛ መሀመድ አሊዩ 4ኛ አሊዩ መሀመድ የተባሉትን ግለሰቦች በመግደላቸው በተጨማሪም ቁጥራቸው የማይታወቅ ሰዎችን በማቁሰላቸው በፈጸሙት በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው ክሱ ገብቷችኋል ወይ ግልጽ ነው ወይ

አዎ ግልጽ ነው

ተረዳችሁ

እሺ 6ኛ ክስ በ7ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ ነው 7ኛ ተከሳሽ ሲራጅ አህመድ ሙሳ እስቲ ወደዚህ ውጣ ሲራጅ አህመድ በደንብ ተከታተል ክሱን እናነብልሃለን እሺ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 256ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ የህገ መንግስቱን እና የህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው ቀኑ እና ሰዓቱን በትክክል በማይታወቅ ጥር ወር 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቦሎ አዳ ወረዳ ጋውጋው ቀበሌ ዲምቱ አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ራሱን አነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውሉ አንደኛ ቁጥሩ 243865 የሆነ ባለሰደፍ ክላሺን ቦንብ መሳሪያ ከ34 ጥይት ጋር ሁለተና 1292 የቆዩ ጥይቶች ሶስተኛ ለሰልጣኝ ወታደሮች የሚሆኑ 20 የእስፖርት ልብሶች አዘጋጅቶ በማስቀመጡ በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት የማሰናዳት ወንጀል ተከሷል ይላል። ምንድን ነው ጥፋቱ 1ኛ 243865 የሆነ ባለሰደፍ ክላሺንግ ቦንብ መሳሪያ ከ34 ጥይት ጋር ለኦነግ በመስጠቱ 2ኛ 1292 የቆዩ ጥይቶችን 3ኛ ለሰልጣኝ ወታደሮች የሚሆኑ 20 የእስፖርት ልብሶችን አዘጋጅቶ ለዚሁ ድርጅት መስጠቱን በዚህ ድርጊቱ ተከሷል።

ሁሴን ሀሰን፣ መሀመድ ጉዳ፣ መሀመድ አሊ ሁሴን ነው መሀመድ ሀሰን ነው

መሀመድ አሊ ሀሰን

ሁሴን ነው የሚለው እዚህ ላይ

መሀመድ አሊ ሁሴን ይላል አኛ ጋ

ገብቶሃል

ገባኝ

የፌዴራሉ ጠቅላይ ዓ/ሬፐብሊክ

251

መቀመጥ ትችላለህ 2ኛ ክስ በ7ኛ ተከሳሽ በ59ኛ እና በ61ኛ ተከሳሾች ላይ ነው 7ኛ ተከሳሽ ሲራጅ አህመድ ሙሳ

ሲራጅ አህመድ ሙሳ

ተነስ

ሲራጅ

59ኛ ተከሳሽ

59ኛ አታውቁትም በዝርዝር አሁንም

አብዱላሂ ሙሳ ሀሰን ቁጥራችሁን በዛው እዩ እስቲ አብዱላሂ ሙሳ ሀሰን ወደዚህ ውጣ 61ኛ ተከሳሽ መሀመድ አሊ ሀሰን ተነስ

እሺ 7ኛው ክስ በእናንተ ሶስታችሁ ላይ ነው የቀረበው ወንጀሉን አነብላችኋለሁ አዳምጡ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 321ሀ እና 256ሐ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበው ቀኑ እና ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅ ታህሳስ ወር 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በ------ ኦዳ ወረዳ ከርከፉ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና ፀረ-ህዝብ ቡድን በመቀላቀል ለዚሁ ቡድን ወታደሮች ምግብና ውሃ በማቀበልና በመሸሸግ በአጠቃላይ ቡድኑን እኩኝ አላማ እውን ለማድረግ በመተባበራቸው በፈጸሙት መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰዋል ይላል።

እሺ

ገብቷችኋል

ጠይቃቸዋ ገብቷችኋል በላቸው

ሰምተናል

እና ገብቷችኋል

252

ገብቶኛል

እሺ ቁጭ በሉ 8ኛ ክስ በ7ኛ ተከሳሽ ላይ 7ኛ ተከሳሽ ሲራጅ አህመድ ሙሳ ይህ በሲራጅ ላይ ብቻ የቀረበ ነው በደንብ አዳምጥ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 256ሀ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና በሀገር እና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስቦ ከላይ በ7ኛ ክስ ላይ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ፀረ-ሰላም እና ፀረ-ህዝብ ለሆነ ራሱን አነግ ብሎ ለሚጠራው ቡድን የሚታገሉት 70 ---------- ወታደሮችን መልሶ በማደራጀት ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በማስረከቡ በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት የማሰናዳት ወንጀል ተከሷል ይላል።

ገብቶሃል

ገባኝ

እሺ ቁጭ በል 9ኛ ክስ በ9ኛ ተከሳሽ 9ኛ ተከሳሽ ማን ነው አይታችኋል ጀማል ሀምዛ እሺ 15ኛ ኪሚያ አሚን

ኪሚያ አሚን ተነሽ

22ኛ ተከሳሽ ጀታ መሀመድ የለም 25ኛ ተከሳሽ

22ኛ ተከሳሽ የለም

ቅድም ያልናት ነች

ሻም ኢብራሂም 29ኛ እና 30ኛ ተከሳሽ ጀማል ከዲር እና ረህማ መሀመድ

ጀማል ከዲር

ጀማል

ሁለት ናቸው

ጀማል ከድር ሳኒ እሺ 33ኛ አብዲ ሃጂ 34ኛ፣ 37ኛ ሀጂ ጣሃ፣ 34ኛ ጀማል ከድር ነው ጀማል ከድር ማን ነው ሀጂ ጣሃ ቁጭ በል

253

ሀጂ ጣሃ ቁጭ በል

አብዲ በሽር፣ መሀመድ ነጃሽ እሺ ይሄኛው 9ኛው ክስ በእናንተ ላይ ነው የተመሰረተው እና አዳምጡ እና እሺ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 321ሀ እና 257ሐ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱ እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና ሀገሪቱን ሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀኑ እና ውሉ በትክክል በማይታወቅ በ1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን አወዳይ ከተማ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ህዝብ በሆነው ራሱን ኦነግ ብሎ በሚጠራው አሸባሪ ቡድን ስር ተደራጅተው የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች መኖሪያ ቤታቸው ድረስ በማምጣትና በመደበቅ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማቅረብ እንዲሁም ህዝቡ ለመንግስት እንዳይታዘዝ በመቀስቀሳቸው በፈጸሙት የመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ወንጀል ተከሷል ይላል። አብዲ በሽር

አቤት

እስቲ ማን ነው እዛ ውስጥ

ሳጥኑ ውስጥ እስቲ ማን ነው አሁን ማን ነው ስምህ

መሀመድ ነጃሽ 54ኛ እሺ ሰምተሃል በደንብ

አዎ

ግልጽ ነው ገባችሁ ምን አሉ

ምንድን ነው ያሉት

ገብቶናል

እሺ 10ኛ ክስ 11ኛ ተከሳሽ ላይ ነው 11ኛ ተከሳሽ ዙቤድ ሁሴን መሀመድ አዳምጥ በአንተ ብቻ ላይ ነው የቀረበው ወንጀሉን በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስና አደጋ ላይ ለመጣል አስቦ ቀኑን እና ወሩን በትክክል በማይታወቅ

254

በ1997 ዓ/ም እስከ 2001 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን በለኦዳ ወረዳ ቡርቃ ከተማ የሚኖሩትን የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ራሱን ኦነግ ብሎ በሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ እንዲደራጁ እና እንዲቋቋሙ በመቀስቀስ በፈጸመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል ይላል፡፡

ግልጽ ነው 12ኛ ተከሳሽ 11ኛው ክስ በ12ኛ ተከሳሽ በአብዱረህማን ሁሴን በ17ኛ ተከሳሽ አብዲ ሽቁር ኡመር፣ 18ኛ ተከሳሽ ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል፣ 19ኛ ተከሳሽ ሸሪፍ ኡመር፣ 20ኛ ተከሳሽ አብዲ ኡስማን፣ 21ኛ ተከሳሽ መሀመድ አሊ በእናንተ ላይ ነው የቀረበው አዳምጡ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 321ሀ እና 257ሐ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና ሀገሪቱን በመንግስት ላይ በሀገሪቱ እና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር በማሰብ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሚደጋ ጮላ ወረዳ ነገያ ውስጥ በሚገኘው የተለያዩ ቦታዎች ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ብሎ በሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ደንበል ወቤ በተባለው ከፍተኛ የኦነግ አመራር አማካይነት ተደራጅተው የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ ሽፍቶችን ከጫካው ወደ ከተማ እንዲሁም ከከተማ ወደ ጫካ መንገድ እያሳዩ በመውሰዳቸው በፈጸሙት የመገፋፋት እና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ወንጀል ተከሷል ይላል፡፡ በላ ምንድን ነው ያለው እሱ

ግልጽ ነው ያለው

እነሱ የሚሉትን ስለሚቀረጽ ተናገር እሺ 12ኛ ክስ በ13ኛ ተከሳሽ እና በ16ኛ ተከሳሾች ላይ 13ኛ እና 16ኛ ረምላ ሸሪፍ፣ ዘይነባ መካን፣

ዘይነባ

13ኛ እና 16ኛ ናቸው በእናንተ ላይ ነው የቀረበው አዳምጡ እሺ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 321ሀ እና 256ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና አደጋ ላይ ለመጣል አስበው ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ 1999 ዓ/ም እስከ 2000 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሚደጋ ቶላ ወረዳ ነገያ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን የኦነግ ነፃ አውጪ ግንባር ብሎ

255

የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ደንበል ዋቢ በተባለው ከፍተኛ የኦነግ አመራር አማካይነት ተደራጅተው የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ ለምግብነት የሚውሉ እህሎችን በማስፈጨት እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለቡድኑ ሽፍቶች በማቅረባቸው በፈጸሙት የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል ይላል።

ገባችሁ ግልጽ ነው አደለም

አዎ ገብቶናል

እሺ ቁጥ በሉ 13ኛ ክስ በ23ኛ ተከሳሽ ላይ አብዱልሃሚድ መሀመድ እሺ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ሀ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሹ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና አደጋ ላይ ለመጣል አስቦ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1997 ዓ/ም እስከ 2001 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐረማያ ከተማ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ኦነግ የኦነግ ፖሊሲ ትክክለኛ ነው በማለት ህብረተሰቡ ለሽብር ተግባር እንዲነሳሳ በመቀስቀሱ በፈጸመው መገፋፋት ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል ይላል። ገብቶሃል ግልጽ ነው

አዎ

ስለሚያውቅ ግልጽ ነው አዎ

ተነሳ እስቲ

ማለት ስለሚያውቅ ብዬ ነው

እሱ ብሏል ተናገር አንተ

እሺ

14ኛ ክስ በ24ኛ ተከሳሽ ሼክ መሀመድ ኡስማኤል አዳምጥ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257መ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አደጋ ለመጣል አስቦ ቀኑ እና ወሩ ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅ በ1997 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን

256

ሚደጋ ቶላ ወረዳ ሚደጋ ከተማ አካባቢ በሚገኝ ጫካ ድረስ በመሄድ ራሱን አነግ ብሎ የሚጠራውን የፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ ከግብ ለማድረስ ሲዋጉ የደረሰባቸውን ሽንፈት ---------በማድረግ በመተባበሩ በፈጸመው ---------- ግዙፍ ያልሆነ የመሰናዳት ወንጀል ተከሷል ይላል።

ኢብራሂም መሀመድ ሼክ መሀመድ ኡስማኤል አሁን ተነበበልህ

አዎ

ገብቶሃል የተባለው

ገብቶኛል

ቁጭ በል እሺ ምንድን ነው ያለው

ገብቶኛል

15ኛ ክስ ነው የሚነበበው 27ኛ ተከሳሽ እና 28ኛ ተከሳሽ ኢብራሂም መሀመድ አንተ ነህ የተከሰስከው በ15ኛው ክስ ኢብራሂም አህመድ አብዶ ነው አይደለም እሺ ተከሳሹ በወንጀል ህግ ቁጥር 271 እና 238/1ለን ተላልፏል ተብሎ ነው የተከሰሰው ተከሳሽ ማንነታቸው ካልታወቁ ግብረአበሮቹ ጋር በመተባበር ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለ--------- አስቦ በተለያየ ቀንና ወር በ1998 በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሜታ ወረዳ ጨለንቆ ከተማ ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ብሎ የሚጠራው የፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ለሶስት ጊዜ የተነሳውን አድማ በመምራቱ እና በማደራጀቱ በፈጸመው በህገ መንግስት እና በህገ መንግስቱ ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው በአጭሩ ምንድን ነው የምትለው አንተ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ተብሎ የሚጠራውን ቡድን ንገረው ይህን አሸባሪ ቡድን ለመደገፍ ሶስት ጊዜ የተነሳውን አድማ መርተሃል ተብለህ ነው የተከሰስከው ግልጽ ነው አደለ ይሄኛው 16ኛም ክስ በ27ኛ ተከሳሽ ላይ ነው የቀረበው የወንጀል ህግ ቁጥር 244 ንኡስ ቁጥር 2 የተመለከተውን ተላልፈሃል ተብለህ ነው ይሄም ክስ አንተን ነው የሚመለከተው ይሄ ክስ ደግሞ የሚለው ይነበባል ተከሳሽ ማንነታቸው ካልታወቁ ግብረአበሮቹ ጋር በመተባበር ከላይ በ15ኛ ክስ በተከሰሰው ጊዜ እና ቦታ ራሱን አነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ በጨለንቆ 1ኛ ትምህርት ቤት በየራሪ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሰቅለው የነበሩትን የፌዴራላዊ ኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ የኦሮሚያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

257

ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ አላማን አውርደው በአደባባይ በማቃጠሉ በፈጸመው የሀገሪቱን መንግስት እንዲሁም የሀገሪቱን ምልክቶችና በመንግስት የታወቁ ሌሎች ምልክቶችን በመድፈር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው በአጭሩ አንተ በተመሳሳይ ይሄ ኦነግ የተባለውን የፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ለመደገፍ ስትል በጨለንቆ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በየራሪ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይውለበለቡ የነበሩትን የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ እና እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል መንግስት ባንዲራ በማውረድ በአደባባይ እንዲቃጠል አድርገሃል ተብለህ ነው የተከሰስከው ግልጽ ነው ይሄ ክስ ተቀበል 17ኛ ክስ በ35ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 35ኛ ተከሳሽ አዱኛ መሀመድ 35ኛ ተከሳሽ 17ኛ ክስ ነው የሚነበበው የወንጀል ህግ ቁጥር 371/271 እና 238/1 ደንብ በመተላለፍ ነው የሚለው ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓት በሃይል ለ-------- አስባ ከላይ በ15ኛ ክስ ላይ በተከሰሰው ጊዜ እና ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን የፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ 15ኛ ተከሳሽ እና ማንነታቸውን ያልታወቁ ሌሎች ግለሰቦችን በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር እንዲመቻቸው በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ መጠለያ በመስጠት እንዲወያዩ እና እንዲደራጁ በማድረጓ በፈጸመችው በአባሪነት በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ እንዲደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው አንቺ የተከሰስሽው በመኖሪያ ቤትሽ ውስጥ 15ኛ ተከሳሽ ኪሚያ አሚንን እና ሌሎች ያልታወቁ ግለሰቦችን በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር እንዲያመቻቸው መጠለያ በመስጠት እንዲወያዩ እና እንዲደራጁ አድርገሻል በማለት ነው በአባሪነት ነው የተከሰስሽው ግልጽ ነው የተባለው ገብቶሻል

አዎ ገብቶኛል

ቁጭ በይ 18ኛ ክስ በ31ኛ ተከሳሽ ላይ ነው 31ኛ ተከሳሽ ሰሚራ ሙሜ አብዱላሂ 18ኛ ክስ በ31ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው የወንጀል ህግ ቁጥር 257ሐን በመጥቀስ የቀረበ ክስ ነው 1996 የወጣውን የወንጀል ህግ ዝርዝሩን ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስባ ቀን እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1998 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን የሐሮማያ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ በሚገኘው መኖሪያ ቤቷ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራ የፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የሚታገሉ ሽፍቶችን በማደራጀት መጠለያ በመስጠት እንዲሁም ኦነግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በመሆን መረጃዎችን በማቀባበሏ በፈጸመችው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የመሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው አንቺ የተከሰስሽው በአጭሩ በቤትሽ ውስጥ ኦነግ ተብሎ የሚጠራው የፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን

የሐረሪ ክልል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

278

በመደገፍ የሚታገሉ ሽፍቶችን በማደራጀት መጠለያ ሰጥተሻል እንዲሁም የኦነግ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በመሆን መረጃዎችን አቀብለሻል ተብለሽ ነው የተከሰስሽው ግልጽ ነው ገብቶሻል 19ኛ ክስ በ32ኛ እና በ36ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው 32ኛ ተከሳሽ ጫልቱ ኢብራሂም ድርሲቱ አብደላ ሁለታችሁም 19ኛ ክስ በ32ኛ እና 36ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው የወንጀል ህግ ቁጥር 321ሀ እና 256ለን በመጥቀስ የተፃፈ ነው ዝርዝሩ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበው ቀኑ ወሩ በትክክል በማይታወቅ ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ/ም ድረስ በድሬዳዋ ከተማ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ 32ኛ ተከሳሽ በማዳበሪያ የተጠቀለለ ፈንጂ በማቀበሏ 36ኛ ተከሳሽ ደግሞ 500 ብር በመስጠቷ እንዚህን የመሳሰሉ ቁሳቁሶች በመስጠታቸው በፈጸሙት የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው የእናንተ ክስ በአጭሩ ጫልቱ ኦነግ የሚባለውን የፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ጫልቱ በማዳበሪያ የተጠቀለለ ፈንጂ አቀብለሻል ድርሲቱ ደግሞ 500 ብር ሰጥተሻል እንዲሁም እነዚህን የመሳሰሉ ቁሳቁሶች በመስጠታችሁ ተከሳችኋል የሚል ነው ገብቷችኋል ተቀመጡ 20ኛው ክስ በ32ኛ እና 36ኛ ተከሳሽ ላይ ነው የቀረበው 32ኛ ተከሳሽ ጫልቱ 36ኛ ሁለታችሁም ብድግ በሉ ይሄም ክስ እናንተን የሚመለከት ነው 20ኛ ክስ የወንጀል ህግ ቁጥር 321ሀ እና 257ሐ በመጥቀስ የተፃፈ ነው ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱ እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በህገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ አስበው ከላይ በ19ኛ ክስ ላይ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና ፀረ-ህዝብ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮችና ሽፍቶች መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በማሳደራቸው እና መጠለያ በመስጠታቸው በፈጸሙት መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ተከሰዋል የሚል ነው 20ኛ ክስ በአጭሩ እናንተ ግብረአበር ሆኖ ኦነግ የተባለውን ፀረ-ሰላም እና ፀረ-ህዝብ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮችን እና ሽፍቶች እንዲጠለሉ መኖሪያ ቤታችሁን ሰጥታችኋል አሳድራችኋል በዚሁ ተግባር ነው የተከሰሳችሁት ግልጽ ነው 21ኛ ክስ በ38ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 38ኛ ተከሳሽ ኮኮብ መሀመድ ኮኮብ አንተ ነህ አንተን ነው የሚመለከተው በወንጀል ህግ ቁጥር 256ለን ተላልፈሃል ተብለህ ነው ዝርዝሩ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ቀን እና ወሩ በትክክል ባይታወቅ 1997 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐሮማያ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ኢብሳ ሌንጮ ወይም አሊ አህመድ በተባለው ከፍተኛ የኦነግ አመራር አማካይነት

259

001 በሚል ምልክት ስም ተደራጅቶ ለ3 ጊዜ 480 ብር የወባ በሽታ መከላከያ የሚሆን 30 አጎበር እና የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች ለቡድኑ እኩይ አላማ እንዲውል በመስጠቱ በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት የማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አማርኛ ይገባሃል አደለ አንተ የተነበበው ግልጽ ነው አደለ ገብቶሃል

አዎ

ቁጭ በል አማርኛ ስለምትችል የተነበበው ገብቶታል እሺ 22ኛ ክስ በ39ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 39ኛ ተከሳሽ ሚካኤል አብዱላሂ አማርኛ ትችላለህ እንዴ እሺ 22ኛ ክስ በ39ኛ ተከሳሽ ላይ ነው እንደሚከተለው ይነበባል የወንጀል ህግ ቁጥር 257ሐን በመጥቀስ የተጻፈ ነው ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ቀን እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1996 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ/ም መጨረሻ ድረስ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ በድሬዳዋ እና በሐረር ከተሞች በሚገኙት መኖሪያ ቤቶቹ አሸባሪዎቹን በማሳደሩ በማስጠለሉ የታመሙ የኦነግ ወታደሮች ቤቱ ተቀምጠው እንዲታከሙ በማድረጉ እንዲሁም በእርሻ ውስጥ የጦር መሳሪያዎችን እንዲያስቀምጡ በመፍቀዱ በፈጸመው መገፋፋት እና ግዙፍ ያልሆነ መሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው 22ኛ ክስ የተከሰሰክበት በአጭሩ እንንገርህ አዳምጥ አንተ ከ1996 እስከ 2000 ዓ/ም ባለው ጊዜ

ይገባኛል

ምንድን ነው

ውሸት ነው ምናምን ነው የሚለው

አማርኛ በደንብ ይገባሃል አሀን አዳምጠሃል

አዎ

ገብቶሃል

አዎ

አደረግህ የተባለው

760

አም

ተቀመጥ ገብቶኛል ብሎ አረጋግጧል ተቀምጧል 23ኛ ክስ በ40ኛ እና 70ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው 40ኛ ተከሳሽ አህመድ ሼክ ዩሱፍ 70ኛ ተከሳሽ መሀመድ አብዶ አህመድ አንተ ነህ በሁለታችሁ ላይ የቀረበ ነው 23ኛ ክስ ይነበባል የወንጀል ህግ ቁጥር 321ሀ እና 257ሀን በመጥቀስ የተጻፈ ነው ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው ቀኑ እና ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅበት ሐምሌ 1997 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ጭሮ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ቦታው ቻይና ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ህዝቡን ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ በመንግስት ላይ እንዲነሳሳ በመቀስቀሳቸው በፈጸሙት በመገፋፋት ግዙፍ ያልሆነ የመሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው ክሱ በአጭሩ ይነገራችኋል እናንተ አማርኛ ትችላላችሁ ገብቷችኋል ከገባችሁ ጥሩ ነው ቁጭ በሉ 24ኛ ክስ በ41ኛ እና 42ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው ሳሲዬ አብደላ ሳሚ አብደላ መሀመድ ሀጂ በእናንተ ላይ የቀረበ ነው ይሄኛው 24ኛ ክስ ይነበባል የወንጀል ህግ ቁጥር 321ሀ እና 256ሀን በመተላለፍ የሚል ነው ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው ቀኑን በትክክል በማይታወቅ ነሐሴ ወር 1997 ዓ/ም ከምሽቱ በ2:00 ሰዓት ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ደሩ ወረዳ ሚጨታ ከተማ 42ኛ ተከሳሽ በሆነው መሀመድ ሀጂ ኢብራሂም መኖሪያ ቤት ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ መንግስትን በሃይል ከስልጣን ለማውረድ አንደኛ አዩብ አብደሌ ሁለተኛ ገመቹ ወይም ብሩስ አረዳን ሶስተኛ ጉተማ መሀመድን እና ስማቸውን የማይታወቁ ሌሎች ሁለት ሰዎችን ጆዎ ደራራ በሚል መጠሪያ ስም በማደራጀታቸው በፈጸሙት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት የማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው ይገባችኋል አማርኛ ነው ይተርጎምላችሁ አይገባህም እሺ አንተ ማን ነው 41ኛ ተከሳሽ ሳሲዬ የተከሰስክበት ክስ የሚለው ነሐሴ ወር 1997 ዓ/ም ከምሽቱ 2:00 ሰዓት ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ሐረርጌ ዞን 42ኛ ተከሳሽ የሆነው መሀመድ ሀጂ ኢብራሂም ቤት የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ተብሎ የሚጠራውን የፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ መንግስትን በሃይል ከስልጣን ለማውረድ በሚል 1ኛ አዩብ አብደሌ 2ኛ ገመቹ ወይም ብሩስ አረዳን 3ኛ ጉተማ መሀመድ እና ስማቸው የማይታወቁ ሌሎች ሰዎች ጂዎ ደራራ በሚል ስም

261

መጠሪያ ስም አደራጅተሃል በሚል ነው ----------ከ41ኛ ተከሳሽ ጋር በግብረአበር በመሆን ነው የተከሰሰከው ገብቶሃል ይሄ የተነበበው

ገብቶኛል

ቁጭ በል 25 ክስ ይነበባል በ43ኛ ተከሳሽ ላይ ነው 43ኛ ተከሳሽ አህመድ ኡስማኤል እሱ ነው

አዎ

አንተ ነህ አህመድ ኡስማኤል መተኮ

አዎ እሱ ነው

እሺ ይነበባል 25ኛ ክስ በ43ኛ ተከሳሽ ላይ ነው የወንጀል ህግ ቁጥር 257ለን በመተላለፍ የሚል ነው ዝርዝሩ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ በተለያዩ ቀናት ቀን እና ወር በ2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎል አልፎዳ ወረዳ ቡርቃ ነገያ ቀበሌ ገ/ማህበር ራሱን አነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን ከፍተኛ አመራር የሆነውን ቢራሳ ዶዮ ስንቅ በማቀበል በገንዘብ በመርዳት እና የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች መሰረታዊ ቁሳቁሶችን በመስጠት በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው በአጭሩ ክሱ ይነገርሃል አንተ በ2000 ዓ/ም በተለያዩ ቀን እና ወራቶች በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ነገያ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን አነግ ብሎ የሚጠራው የፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ ከፍተኛ አመራር ለሆነው ቢረሳ ዶዮ ስንቅ በማቀበል በገንዘብ በመርዳትና የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ቁሳቁሶችን በመስጠት ተከሰሃል የሚል ነው ገብቶሃል

ገብቶኛል

ተነስ ምንድን ነው ያልከው

ገብቶኛል ነው ያልኩት

ስነስርዓት ያለበት ቦታ ነው በለው እሺ 26ኛ ክስ በ45ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 45ኛ ተከሳሽ ዩሱፍ ጨሎ ላይ የቀረበ ነው 26ኛ ክስ በ45ኛ ተከሳሽ ላይ የወንጀል ህግ ቁጥር 256ለን

262

በመተላለፍ በሚል የተጻፈ ነው ተከሳሽ ለጊዜው ካልተያዘ ግብረአበሩ ጋር በመተባበር ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ በተለያዩ 4 ቀናቶች ህዳር ወር በ2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቁኒ ወረዳ በዶርዜ ከተማ በሚገኘው አዋሽ ባንክ በኩል የተላከለትን በአጠቃላይ (90200.00) ዘጠና ሺ ሁለት መቶ ብር አውጥቶ ራሱን አነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ አመራር ለሆነው መሀመድ ደራሳ በማስረከቡ በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አማርኛ ትሰማለህ

በደንብ

ገብቶሃል የተባለው

ገብቶኛል

ተቀመጥ 27ኛ ክስ በ46ኛ እና 56ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው 46ኛ ተከሳሽ ሙክታር አብዱጀሪፍ 56ኛ ተከሳሽ ከድር አደም በሁለቱ ላይ የቀረበ ነው በሁለታችሁ ላይ የቀረበ ነው ይነበባል ወንጀሉ የሚለው የወንጀል ህግ ቁጥር 321ሀ እና 256ለን በመተላለፍ ነው የሚለው ዝርዝሩ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ጥቅምት ወር 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ዲንቱ ወረዳ ኩርፉ ሮቃ ቀበሌ ገ/ማህበር ራሱን አነግ ተብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ከላይ በ26ኛ ክስ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ መሀመድ ድራስ ከተባለው ግለሰብ ተቀብለው የአነግ ከፍተኛ አመራር ለሆነው ቢራሳ ዶዮ በማስረከባቸው በፈጸሙት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው አማርኛ አትችሉም አደለ እሺ ይተረጎምላችኋል በአጭሩ እናንተ አደረጋችሁት የተባለው አነግ የተባለውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ለመደገፍ ብላችሁ በጥቅምት ወር 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ሐረርጌ ዞን ቡርቃ አዲቱ ወረዳ ኩርፉ ሮቃ ቀበሌ ገ/ማህበር ከላይ በ26ኛ ክስ የተጠቀሰውን ገንዘብ ብር 90200.00 መሀመድ ድራሳ ከተባለው ግለሰብ ተቀብላችሁ ከፍተኛ የአነግ አመራር ለሆነው ቢራሳ ዶዮ አስረክባችኋላ በሚል ነው የተከሰሳችሁት ግልጽ ነው እሺ ተቀመጥ 28ኛ ክስ በ47ኛ እና በ48ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው 48ኛ ተከሳሽ አልቀረበም 47ኛ ተከሳሽ ቀርቧል አሊዱ አብደሌ ኡስማን አሊዱ

263

በአንተ ላይ የቀረበ ነው በ1996 የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 257ሐ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በሚል የቀረበ ነው ዐ/ህግ ይሄ ----------

አዎ እቺ አሁን እዚህ ጋ ነው የምትገባው 20ኛው ፔጅ እዚህ ያለው

ቆይ 28ኛ ላይ ነኝ ቆይ እሱ አይደለም ሌላው ግብረአበሩ የለም ይሄ ክስ አይደለም

አዎ

ይሰማ

ይሰማልን አዎ

እሺ 257ሐ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1998 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐረማያ ከተማ ውስጥ የቀበሌ 01 የፀጥታና ፍትህ ዘርፍ ሃላፊ ሆኖ ሲያገለግል ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ አባላት ወንጀል ለመፈጸም የሚያደርጉትን የማሰናዳት ተግባር እያወቀ እርምጃ ሳይወስድ በመቅረቱ በፈጸመው በተዘዋዋሪ መንገድ መርዳት እና ማበረታታት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አማርኛ አትችልም አደለ በአጭሩ ይተረጎምልሃል አንተ በ1998 ዓ/ም በትክክል ወሩ እና ጊዜው በማይታወቅበት ጊዜ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ በማሰብ በሐረርጌ ዞን ሐረማያ ከተማ ቀበሌ 01 የፀጥታ እና ፍትህ ዘርፍ ሃላፊ ሆነህ ስታገለግል በአስተዳደር ውስጥ ስትሰራ ኦነግ ተብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ አባላት ወንጀል ለመፈጸም የሚያደርጉትን ተግባር እያወቅህ በአስተዳደር ሃላፊ ሆነህ እርምጃ ሳትወስድ ቀርተሃል በዚህም በተዘዋዋሪ መንገድ እረድተሃል ተብለህ ነው የተከሰስከው ገብቶሃል 30ኛ ክስ በ51ኛ እና 52ኛ

29ኛ ክስ እዚህ ጋ ነው የሚገባው

29ኛ ክስ ይነበባል 29ኛ ክስ በ49ኛ ተከሳሽ የቀረበ ነው መሀመድ ኡመሬ 29ኛ ክስ ደርሶሃል ለብቻው ያለው ወረቀት ይሄ ለብቻው አለ አደለም 29ኛ ክስ በ49ኛ ተከሳሽ ላይ ነው አማርኛ ትሰማለህ አደለም ትሰማለህ አማርኛ

አዎ እሰማለሁ

764

እሺ በ1996 የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 254 ንኡስ ቁጥር 1 በመተላለፍ የሚል ነው ዝርዝሩ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ቀን እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1998 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐሮማያ ከተማ ውስጥ የቀበሌ 01 የፀጥታ እና ፍትህ ዘርፍ ሃላፊ ሆኖ ሲያገለግል ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን አባላት ወንጀል ለመፈጸም የሚያደርጉትን የመሰናዳት ተግባር እያወቀ እርምጃ ሳይወስድ በመቅረት በተዘዋዋሪ መንገድ መርዳትና ማበረታታት ወንጀል በመፈጸም ተከሷል የሚል ነው ግልጽ ነው 30ኛ ክስ ይነበባል 30ኛ ክስ በ50ኛ፣ 51ኛ፣ 52ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው 50ኛ ተከሳሽ ጃፈር ኡመር ጃፈር ወደዚህ ውጣ ዩሱፍ ዳዎድ ውጣ 52ኛ ተከሳሽ ጀማል አደም ኡስማን በእናንተ ላይ የቀረበ ክስ ነው ስለዚህ በአጭሩ የወንጀል ህግ ቁጥር 321ሀ እና 257ሐን በመተላለፍ የሚል ነው ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ እና በአገር እና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀን እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1998 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐሮማያ ከተማ ራሱን ኦነግ ብሎ በሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ አመራር በሆነው መሀመድ አባድር አማካይነት ተደራጅተው የቡድኑን ታጣቂዎች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በማሳደራቸው እና በመሸሸጋቸው በፈጸሙት መግባባትና ግዙፍ ያልሆነ የመሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው አማርኛ ትሰማላችሁ እንዴ በአማርኛ ይነገራችኋል ተርጉምላቸው እናንተ አደረጋችሁ የተባለው ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስባችሁ በ1998 ዓ/ም ቀኑ እና ወሩ ባልተለየ ጊዜ ኦነግ ተብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ አመራር በሆነው መሀመድ አባድር አማካይነት ተደራጅታችሁ የቡድኑ ታጣቂዎችን በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ አሳድራችኋል ሸሽጋችኋል በሚል ነው የተከሰሳችሁት ግልጽ ነው ተመለሱ 31ኛ ክስ በ53ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው በከር ቃሲም በአንተ ላይ የቀረበ ክስ ነው ይሄ ይነበብልሃል በ1996 የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 256ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ ይላል ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ እና በሀገር ላይ እና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስቦ ቀን እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ1997 ዓ/ም ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን አወዳይ ከተማ ውስጥ በክሪ አብዱላሂ የተባለውን ግለሰብ እና ሌሎች አመራሮቻቸው የማይታወቁ ሰዎችን ራሱን ኦነግ ብሎ በሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን ስር በማደራጀቱ በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ

265

በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው በክሪ አማርኛ አይሰማም አደለ ትሰማለህ አሁን ገብቶሃል የተነበበው

አዎ ገብቶኛል

ግልጽ ነው

ግልጽ ነው

እሺ 32ኛ ክስ ይነበባል በ55ኛው ተከሳሽ ላይ ነው 55ኛ ተከሳሽ ጀማል ሁሴን ሙሳ ጀማል በአንተ ላይ የቀረበ ክስ ነው የወንጀል ህግ ቁጥር 27 ንኡስ ቁጥር 1 እና 238/1/ለን በመተላለፍ የሚል ነው ዝርዝሩ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ጥቅምት 23/2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ዲንቱ ወረዳ በዲምቱ ቡራዳ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ማንነታቸው ካልታወቁ ታጣቂዎች ጋር በመሆን የቀበሌ ሚሊሻዎች ላይ ተኩስ በመክፈቱ በፈጸመው ህገ መንግስት እና ህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሰሃል የሚል ነው አማርኛ ትሰማለህ ወይ አንተ ያደረከው ህገ መንግስት እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበህ ጥቅምት 23/2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ሐረርጌ ዞን በዲምቱ ቡረኔ ቀበሌ ገ/ማህበር ኦነግ ተብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምን አሸባሪ ቡድንን በመደገፍ ማንነታቸው ላልታወቁ ታጣቂዎች በመሆን የቀበሌዎች ሚሊሻዎች ላይ ተኩስ በመክፈት ተከሰሃል ተብለህ ነው ግልጽ ነው

ገብቶኛል

39ኛ ክስ በ58ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 58ኛ ተከሳሽ ኡመር መሀመድ ኡመር አንተን ይመለከታል ይሄኛው ክስ 39ኛው ክስ የወንጀል ህግ ቁጥር 257ሐን የተመለከተ በመተላለፍ የሚል ነው ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ሰኔ ወር 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ዲንቱ ወረዳ ቡረዳ ራምሲ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምን አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የኦነግ ከፍተኛ አመራር በሆነው ቢረሳ ዶዮ አማካይነት ቡርቃ ዶዮ በሚል መጠሪያ ስም ተደራጅተው ለምግብነት የሚያገለግል የተለያዩ ቁሳቁሶችን ጫማዎችና የመሳሰሉትን ነገሮች ለቡድኑ ታጣቂዎች በመስጠቱ በፈጸመው የተንኮል

266

ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አንተ ያደረከው በአጭሩ ህገ መንግስት ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበህ ሰኔ 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ራምሲ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ኦነግ ተብሎ የሚጠራውን አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ ከፍተኛ አመራር የሆነው በቢረሳ ዶዮ አማካይነት ቡርቃ ዶዮ በሚል መጠሪያ ስም በመደራጀት ለምግብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁስ ጫማዎች የመሳሰሉ ነገሮችን ለቡድኑ ታጣቂዎች ሰጥተሃል በሚል ነው የተከሰስከው ገብቶሃል 34ኛ ክስ በ61ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 61ኛ ተከሳሽ መሀመድ አሊ ሀሰን ወይም መሀመድ ጉዳ የወንጀል ህግ ቁጥር 271 እና 238/1ለን በመተላለፍ የተጻፈ ክስ ነው ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅ ታህሳስ 23/2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ አዱ ወረዳ ራምስ ወንዝ አካባቢ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ላይ ተኩስ ከፍቶ አንድ ሰው በመግደሉ እና 7 ሰዎችን በማቁሰሉ በፈጸመው ህገ መንግስታዊ እና ለህገ መንግስት ሃይል ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አንተ የፈጸምከው በአጭሩ ታህሳስ 23/2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ አዳ ወረዳ ራምሳ ወንዝ አካባቢ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ተብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን ለመደገፍ እና የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ላይ ተኩስ ከፍተህ አንድ ሰው ገድለሃል 7 ሰዎችንም እንዲቆስሉ አድርገሃል በዚህ ህገ መንግስት እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ የሙከራ ወንጀል ፈጽመሃል ተብለህ ነው የተከሰስከው ገብቶሃል

አንተ ያልከውን ሰማሁ

እሺ ተቀመጥ 39ኛ ክስ በ62ኛ፣ 63ኛ፣ 65ኛ፣ 66ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው 62ኛ ተከሳሽ መሀመድ አንጀባ አብዱላ ወይም ---------- አንተ ወደፊት 63ኛ ተከሳሽ አድናድ ጉሼ አህመድ ተነስ 65ኛ ተከሳሽ ሰኢድ አደም አሊ ተነስ 66ኛ ተከሳሽ ከሊፍ መሀመድ ሼክ ይሄ ክስ እናንተን ነው የሚመለከተው ወንጀሉ የሚለው የወንጀል ህግ ቁጥር 321ሀ እና 256ለ በመተላለፍ የሚል ነው ዝርዝሩ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው ቀኑ በትክክል በማይታወቅ ህዳር ወር 2000 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 2:00 ሰዓት ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ አዱ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ልዩ ቦታው ቦረን ተብሎ የሚጠራው አካባቢ የተለያዩ ቀበሌዎች

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

267

ውስጥ በሃላፊነት ሲሰሩ ለህብረተሰቡ እንዲያከፋፍሉ ከተሰጣቸው የእርዳታ እህል ላይ 10 ሉቃ ስንዴ እና 8 ሉቃ በቆሎ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በመስጠታቸው በፈጸሙት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው ይተረጎምላችኋል እናንተ የተከሰሳችሁት እናንተም ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ በማሰብ ህዳር ወር 2000 ዓ/ም ቀን እና ወሩ በትክክል ባልተለየበት በበኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ ኦዳ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ልዩ ቦታው ቦረን ተብሎ በሚጠራው በሃላፊነት ስትሰሩ በሃላፊነት ስታገለግሉ ለህብረተሰቡ እንዲከፋፈል ከተሰጣችሁ የእርዳታ እህል ውስጥ 10 ሉቃ ስንዴ 8 ሉቃ በቆሎ ፀ/ህግ ሉቃ ምንድን ነው

የመስፈሪያ አይነት ነው የተከበረው ፍ/ቤት

ሉቃ ገብቷችኋል ሉቃ ማለት

አዎ

እሺ 8 ሉቃ በቆሎ ኦነግ ተብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ሰጥታችኋል ተብሎ ነው የተከሰሳችሁት ገብቶሃል ተቀመጡ 36ኛ ክስ በ62ኛ እና በ68ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ነው 62ኛ ተከሳሽ መሀመድ አንጀባ አብደላ ወደዚህ ና 68ኛ ተከሳሽ አብደላ መሀመድ ሰኢድ ወይም ሃማ በእናንተ ላይ የቀረበ ክስ ነው 36ኛ ክስ የሚለው የወንጀል ህግ ቁጥር 27/1፣ 321ሀ እና 238/1ለን በመተላለፍ የሚል ነው ዝርዝሩ ተከሳሾች ማንነታቸው ከማይታወቅ ግብረአበሮቻቸው ጋር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ እና በሀገርና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀን እና ወሩ በትክክል በማይታወቅ በ2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎላ ኦዳ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ ከኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ጋር ተዋግተው በአጠቃላይ 11 ሰዎችን በመግደላቸው እና 1 የመንግስት ንብረት የሆነ መኪና በማቃጠላቸው በፈጸሙት በህገ መንግስት እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ [illegible] ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው እናንተ የተከሰሳችሁት በአጭሩ የህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስባችሁ በተጨማሪ በሀገር እና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር በማሰብ በ2000 ዓ/ም ቀን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

እና ወሩ ባልተለየበት ጊዜ በኦሮሚያ ክልል ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ኦነግ ተብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድንን በመደገፍ እንዲሁም የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ ከመከላከያ ሰራዊት ጋር ተዋግታችሁ 11 ሰው ገድላችኋል 1 የመንግስት ንብረት የሆነ መኪና አቃጥላችኋል ተብላችሁ ነው የተከሰሳችሁት ገብታችኋል ተመለሱ

እሺ 37ኛ ክስ በ64ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 64ኛ ተከሳሽ መሀመድ ኑር አህመድ መሀመድ ኑር ቀርበሃል ክሱ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ ለምግብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ሲጋራ ባትሪ ድንጋይና የመሳሰሉትን እቃዎች ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በመስጠት በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ የሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ በማሰብ ወሩ እና ቀኑ በትክክል በማይታወቅበት 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ሚኖ ቀበሌ ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ለመርዳት ለምግብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ሲጋራ ባትሪ ድንጋይ የመሳሰሉ እቃዎችን ለቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በመስጠት በፈጸመው የተንኮል ድርጊት ተከሷል ግልጽ ነው። 38ኛ ክስ በ67ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 67ኛ ተከሳሽ

እሺ 38ኛ ክስ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ሐ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስበው ቀኑ በትክክል በማይታወቅበት ታህሳስ ወር 2000 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ ከፍተኛ አመራር የሆነው መሀመድ ሀጂ ዳዲ ወይም አሪያ ዳዲን ከምስራቅ ሐረርጌ ወደ ምዕራብ ሐረርጌ መንገድ እያሳየ በመውሰዱ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ በመተባበር በፈጸመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው። እሺ ታህሳስ ወር 2000 ዓ/ም ውስጥ መሀመድ ሀጂ ዳዲ ወይ አሪያ ዳዲ የቡድኑ ከፍተኛ አመራርን ከምስራቅ ሐረርጌ ወደ ምዕራብ ሐረርጌ መንገድ እያሳየ ወስደሃል በመሆኑ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ በመተባበር በፈጸምከው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ወንጀል ተከሰሃል የሚል ነው ግልጽ ነው ገብቶሃል ወይ እሺ 39ኛ ክስም በ67ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው አንተኑ ነው የሚመለከተው

269

ይህም በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 256ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅበት ጥር 23 ቀን 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ቡርቃ ነገያ ቀበሌ ልዩ ቦታው አህመድ ኢብራሂም የተባለ ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውል ሁለት የጦር መሳሪያዎችን ከ34 ጥይቶች ጋር አዘጋጅቶ በማስቀመጡ በፈጸመው የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው። ጥር 23/2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጎሎ ኦዶ ወረዳ ቡርቃ ነገያ ቀበሌ ልዩ ቦታው አህመድ ኢብራሂም የተባለ ቦታ ላይ ራሱን ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውል ሁለት የጦር መሳሪያዎች ከ34 ጥይቶች ጋር አዘጋጅቶ አስቀምጠሃል በፈጠርከው የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰሃል ግልጽ ነው ወይ እሺ ቁጭ በል 40ኛ ክስ በ12ኛ፣ 16ኛ፣ 18ኛ፣ እና 19ኛ ተከሳሾችን የሚመለከት ነው 12ኛ ተከሳሽ አብዱረህማን ሁሴን ጅብሪል ዘይነባ መታን ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል ሸሪፍ ኡመር ኤለን ይሄ ክስ እናንተን ይመለከታል በጥሞና ተከታተሉ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን ህግ አንቀጽ 321ሀ እና 256ለ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው በተለያዩ ቀኖችና ወሮች በ2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሚደጋ ቶላ ወረዳ ነገያ ቀበሌ ውስጥ በሚገኝ መኖሪያ ቤቶች ራሱን ኦነግ ብሎ ለሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን አላማ የሚውል የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን እና ጥይቶችን አዘጋጅቶ በማስቀመጣቸው በፈጸሙት የተንኮል ድርጊቶች ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው። የተለያዩ ጥያቶችን ለፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን ለሆነው ኦነግ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን እና ጥይቶችን አዘጋጅታችሁ አስቀምጣችኋል ነው ግልጽ ነው ወይ ከገባችሁ መቀመጥ ትችላላችሁ 41ኛ ክስ በ71ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 71ኛ ተከሳሽ ኑሬ ኡስማን ይህ ክስ አንተን ይመለከታል ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ሀ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበው ሰዓቱ በትክክል በማይታወቅ ህዳር 5 ቀን 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሀሚ ጉዳና ወረዳ ድሬ ገዳዳ በተባለው ቦታ ራሱን ኦነግ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ እንዲደርስ በማቀድ የኦነግ ወዛደሮች ድሮ ቲ ነበሩ በማለት ህብረተሰቡ በመንግስት ላይ እንዲነሳሳ በመቀስቀሱ በፈጸመው መገፋፋት እና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል

270

ተከሷል የሚል ነው በአጭሩ የኦነግ ወታደሮች ድሮ 10 ነበሩ ብለህ ህብረተሰቡ በመንግስት ላይ እንዲነሳሱ አድርገሃል ነው ግልጽ ነው ገብቶሃል እሺ ቁጭ በል 42ኛ ክስ 72ኛ ተከሳሽን የሚመለከት ነው 72ኛ ተከሳሽ ጫላ ሙክታር ሙሜ እሺ አንተ የተከሰስክበት የህግ አንቀጽ የወንጀል ህግ ቁጥር 27/1 እና 238ለን በላልፈሃል በሚል ነው ይህም ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስቦ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት ሀዳር ወር 2001 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ሐረማያ ከተማ ውስጥ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራው ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ በማቀድ ኤፍ ዋን ቦንብ ለማፈንዳት በከተማው መስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ወርውሮ ሳይፈነዳ ቢከሽፍም በፈጸመው በህገ መንግስት እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አንተ አማርኛ አይገባህም የተነበበው ገብቶሃል እሺ መቀመጥ ትችላለህ። 43ኛ ክስ በ73ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ነው 73ኛ እና የመጨረሻው ተከሳሽ አብዶሽ ሙሜ ጁሞ ወይም ሸፎ ይህ ክስ አንተን ይመለከታል በጥሞና ተከታተል ወንጀሉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 37/1 እና 238ለን ተላልፈህ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ አስበህ ከላይ በ42ኛ ክስ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ እና ቦታ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ቡድን በመደገፍ የቡድኑ እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ 72ኛ ተከሳሽ የወረወረው ኤፍ ዋን ቦንብ ገዝቶ በመስጠቱ እና ወንጀሉ የሚፈጸምበትን ሁኔታ በማመቻቸቱ በፈጸመው ተባባሪነት መሆን በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው አማርኛ ይገባሃል የተነበበው ገብቶሃል ግልጽ ነው።

ተከሳሾቹ እና እንደዚህ አይነት ተመሳሳይ ጉዳዮች በተመሳሳይ ጊዜ ይቀርባሉ እሱ እንትን ማድረጉ አያስፈልግም ስለዚህ ክሱ ተነቧል ክሱ ከተነበበ በኋላ የምታመለክቱት ነገር ካለ አመልክቱ እና ፍ/ቤቱ አስፈላጊ የሆኑትን ትዕዛዞች ይሰጣል። በአጠቃላይ ለማቅረብ ማለት ነው እንግዲህ አስቀርጹ ይቀረጽ አሁን የተባለው

ተከሳሾቹ አንደኛ በርካታ ናቸው በአንድ ጊዜ ለከሌ ዋስ መብት ይጠበቅ ለከሌ አይጠበቅ ለማለት አስቸጋሪ ስለሚሆን አንዳንድ አንቀጾች ሲታዩ የዋስ መብት የሚያስጠብቁ ሆነው አይተናቸዋል ስለዚህ እነዚህን ለይቶ ተደጋጋሚ ክስ የሌለባቸው ከሆነ ወይም ደግሞ ተደጋጋሚ --- ያው የዋስ መብት የሚያስጠብቁ ሆኖ የሚገኙ ከሆነ እነሱን ለይቶ እምነት ክህደቱን ለመስጠት እንዲቻ አንድ ረዘም ያለ ቀጠሮ ይሰጠንና ከተከሳሾቹ ጋር ተነጋግረን

መቃወሚያ በተመለከተ

271

አዎ መቃወሚያውንም በሚመለከት በዛው ጋር አጠቃለን እናቀርባለን

አብራችሁ ታነሳላችሁ

አዎ አብረን አንድ ጋር በጽሁፍ አጠቃለን

ስለዚህ ቀጠሮ ይሰጠን ነው

አዎ

ሌላ ተከሳሾቹን በተመለከተ ግን አስተርጓሚው የት አለ አስተርጓሚ እዛ ጎናቸው ሁንና አስተርጉም ንገራቸው እናንተ የተከሰሳችሁት አሁን የክስ ማመልከቻው ሁሉም ደርሷችኋል የተጠየቃችሁበት ነገር በዝርዝር እዛ ላይ ሰፍሯል እያንዳንዳችሁ የተጠየቃችሁበት በዝርዝር ወረቀቱ ላይ ሰፍሯል የደረሳችሁን ወረቀት ሳይሆን ደግሞ የክስ ማመልከቻ ነው እዚህ ፍ/ቤት ተከሳሾች ናችሁ ማለት ነው ጠበቃ ፍ/ቤቱ አቁሞላችኋል ስለዚህ አሁን ወደፊት የሚቀጥለው ክርክር በሚቀጥልበት መልክ ከጠበቃችሁ ጋር እየተማከራችሁ የሚቀጥል ሙግት ነው የሚሆነው በግልም ሆነ በሌላ የምትጠይቁት ጥያቄ በጠበቃችሁ እየታገዘ ነው የሞያ ስራ ነው የሚሰራው ጠበቃ ማቆም የሚችል አለ እንዴ ፈልግ በግሉ ቁሙ በግላችን ደግሞ ማቆም እንችላለን የምትሉ በግላችን ጠበቃ እናቆማለን በገንዘብ ገዝተን የምትሉ ብቻ ተከላካይ ጠበቃ ይይዛሉ ስም ዝርዝራቸውን እነዚህን ሌላ በቃ ሌሎቻችሁ አትይዙም ሌሎቻችሁ አትችሉም አደለ

አንችልም

እሺ ሌሎቻችሁ ከቆማችሁት ውጪ አዳምጡ ከቆማችሁት ውጪ አሁን የሚባለውን እንትን ትላላችሁ ለፍ/ቤቱ እኛ ከቆማችሁት ውጪ ሌሎች የተቀመጣችሁት አሁን የሚባለውን ደግማችሁ በሉ መሀላ ነው እኛ ጠበቃ ለማቆም ሀብትና ገንዘብ የሌለን መሆኑን ለፍ/ቤቱ እናረጋግጣለን የቆሙት ማን ማን ነው አንተ ስምህ ማን ነው 3ኛ ተከሳሽ ዐ/ህግ እስቲ እያያችሁ

45ኛ

እስቲ አንብቡት 5ኛ ማን ነው

272

45ኛ ---------- አህመድ

ጨሎ አህመድ ሌላ ማን ነው አንተ ከኋላ ያለከው

ኑሬ ኡስማን ጭሮ

ኑሬ ኡስማን ጭሮ ስንተኛ ነው

71ኛ

እስኪ አንብቡት

ኑሬ ኡስማን ጅሎ አዎ እሱ ነው

አንተ ነህ

አዎ እኔ ነኝ

እሺ አንተም ጠበቃ ማቆም ትፈልጋለህ በራስህ እሺ ሌላ ሶስተኛው ማን ነው ማን ነው ስምህ

37ኛ ተከሳሽ

አንተ ስምህ ማን ነው

አብዲ --------- ኡስማኤል

37ኛ ነው ዐ/ህግ

አዎ አረጋግጠናል

አንተ ጠበቃ ታቆማለህ በራስህ ትገዛለህ በገንዘብ እሺ 37ኛ ተከሳሽ እገዛለሁ ብሏል ኑሬ ኡስማን ጭሮ እየተባለ ያለው ገብቶሃል ወይ

አዎ ጠበቃ መግዛት የምትፈልጉ ነው የተባለው

በገንዘብህ ትገዛለህ ጠበቃ

አዎ እገዛለሁ

ጠበቃ ገንዘብ ይፈልጋል

ስለተቸገርኩኝ የደም ብዛት በሽታ ስላለብኝ እሱን ጠበቃን ማቆም ፈለኩኝ

ፍ/ቤቱ ገንዘብ አቅም ከሌለህ ፍ/ቤቱ ያቆማል አይ ገንዘብ አለኝ እገዛለሁ ካልክ ጠበቃ መግዛት ትችላለህ ይሄን ለይ ጊዜ አትግደል አንተ አልተጠየክም ዩሱፍ ጨሎ አንተ ቁጭ በል አንተ እገዛለሁ ብለሃል አንተ ቁጭ በል

ብዙ ገንዘብ የለኝም

ገንዘብ የለህም

ብዙ ገንዘብ የለኝም

ስለዚህ ጠበቃ ፍ/ቤቱ ያቁምልህ ወይ በነፃ ኑሬ

ፍ/ቤቱ እንዳለው

ገንዘብ አለህ እንዴ አንተ ምንድን ነው የምታወራው

በስንት ነው የሚገዛው

ቆይ አዳምጥ በለው ባክህ አንተ አዳምጥ እዚህ ስራ ነው እየተሰራ ያለው የማይገባህ ከሆነ ሌላ ጉዳይ ነው አዳምጥ አንተ በገንዘብህ ከውጪ አሁን ፍ/ቤቱ የሚለውን ትላለህ እኔ 71ኛ ተከሳሽ ኑሪ ኡስማን ጀሎ በግሌ ጠበቃ ለማቆም ገንዘብና ሀብት የሌለኝ መሆኑን ለፍ/ቤቱ በመሀላ አረጋግጣለሁ ተቀመጥ አሁን ተከላካይ ጠበቃ ለ7ኛም ኖት አብዲ በሽር አንተ እገዛለሁ ብለሃል ሌላስ ጠበቃ በራሱ ሊያቆም እሺ ማን ነው ስምህ ሚካኤል አብዱላሂ ስንተኛ ተከሳሽ ነው ዐ/ህግ

39ኛ

እስኪ አንብቡት

ሚካኤል አብዱላሂ መሀመድ

39ኛ ትገዛለህ በራስህ ጥሩን ተወው ባክህ ሀተታውን ተወው ገንዘብ አለህ ትገዛለህ ጠበቃ ከውጭ

274

ከዚህም ካገኘሁ ይበቃኛል

ባክህን አዳምጥ ሚካኤል አዳምጥ የሚባለው ግልጽ እኮ ነው ሌላ ነገር አታምጣ ይሄ ቀላል አማርኛ ነው 45ኛ እንደዚሁም 37ኛ ተከሳሾች በግላችን ጠበቃ እናቆማለን ስላሉ የፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ እነዚህን ተከሳሾች በተመለከተ የሙያ ግልጋሎት አይሰጡም ቀሪ ሌሎቹ ተከሳሾች ግን የቀረቡትን በተመለከተ የሞያ እገዛ ያደርጋሉ ማለት ነው ተከላካይ ጠበቃ በግልጽ መዝግቧቸው 45ኛ፣ 37ኛ እና 39ኛን በተመለከተ አይመለከቶትም ሌሎቹን ግን እኚህ ጠበቃ እናንተን ባላችሁበት ያማክራሉ ለፍ/ቤቱ የሚቀርበውን ክርክር ያቀርባሉ እሺ ይቀመጡ ተከላካይ ጠበቃ ዐ/ህግ ይሄን ጉዳይ በተመለከተ ከዐ/ህግ አቀራረብ ከተመለከተ በአንድ ዐ/ህግ ብቻ ሳይሆን ከአንድ በላይ በሆነ በቲም በጉሩፕ መሰራት አለበት

አዎ ለዛ ብለን ነው

ስለዚህ ከዚህም በላይ መሆን አለበት ብሎ ፍ/ቤቱ ስለሚያምን በዚህ መልክ እንድታስተካክሉ ነው

እሺ እናስተካክላለን

22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ ምንድን ነው የምታመለክቱት ነው አልያዛችሁም 22 እና 48

ቅድም ባመለከትነው የወለድ ጊዜአቸውን

ማን ማን ናቸው 22ኛ ነው 48ኛ በፖሊስ ተለቀቁ ስትሉ አልነበር እንዴ

አዎ

ታዲያ ምንድን ነው

ጀና መሀመድ

22ኛ ጀና መሀመድ እና 48ኛ

ዘሀራ አብዶሽ እነዚህ ናቸው

ምንድን ነው የምታመለክቱት

2175

እነሱ ያው አራስ ጊዜአቸውን እንደጨረሱ

እየተቀረፀ ነው

ነፍሰ ጡር በመሆናቸውና በመውለዳቸው ምክንያት በፖሊስ በዋስ ተለቀዋል ያንን እንደጨረሱ ወዲያውኑ እናቀርባቸዋለን

በወሊድ ምክንያት ነው

አዎ

በቀጣዩ ቀጠሮ ታቀርቧቸዋላችሁ

እናቀርባለን

የተመለከተ ወይስ ያመለክታል

የምናመለክተው ይሄንኑ ነው የማረሚያ ቤት

ይበቃል በቃ ይቀመጡ ዐ/ህግ እነዚህን በሙሉ ተከሳሾች በሃላፊነት ይዘህ የመጣከው አንተ ነህ የቀረቡትን በሙሉ ዛሬ የቀረቡትን ችሎት

አዎ አጠቃላይ የቀረቡትን እኔ ይገፍ ቀረብኩኝ ያው የጉዳዩ ባለቤት ማለት መርማሪም ስለነበርኩ አጠቃላይ በጊዜ ቀጠሮ ስለነበሩ በመደበኛ ዛሬ እንዲቀርቡ ይገፍ የቀረብኩ እኔ ነኝ

71ንም ይዘህ የቀረብክ አንተ ነህ

ትክክል

እሺ ስምህ ማን ነው

ዋና ኢንስፔክተር ብርሃኑ ታጀበ

ከየት ነው ይዘሃቸው የቀረብከው

ከድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን

አጅበህ ነው ይዘህ የመጣከው

276

አዎ አጅቤ ነው

---------- ምንድን ነው የምታመለክቱት

ያው ተከሳሾቹ በቂ ምግብና ህክምና በሌለበት በጣቢያ የሚገኝ ስለሆነ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩልን

መከላከያ ጠበቃ መቼ ነው ትቆያላችሁ አደለ እዚህ

አዎ

--------- አይታችሁ ---------

እናደርጋለን

አሁን ስለታዘዘ ይሄንኑ አድርጉ ሌሎች መብቶችም ስለሚኖሩ በሚሰጡት አጀንዳዎች መጠቀም አለባችሁ

እሺ

የሚሰራ ነገር ካለ በዚህ ቀጠሮ መጠቀም አለባችሁ ፍ/ቤቱ ከእንግዲህ የራሱን ስራ ብቻ ነው የሚሰራው ይሄን ታሳቢ ሁሌ ማድረግ አለባችሁ

እሺ

በራካታ ተከሳሾች ናችሁ ስለ አቀራረባችሁ ክርክር ሂደቱን አመራሩን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ሲመረምር የሚሰጣቸው ነው የሚሆነው የሚመለከታቸው ነገሮች ስለዚህ እናንተ ግራ ቀኞችሁን ይሄንን እያሰባችሁ መሆን መቀጠል አለበት በዚሁ የረጅም ቀጠሮ እያሰባችሁ ቆዩ የማስረጃ ሌላው የመሳሰሰ ማለት ነው

እሺ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል

277

ት ዕ ዛ ዝ

ተከሳካይ ጠበቃው ባመለከቱት መሰረት በክሱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በቀጣዩ ቀጠሮ እንዲያቀርቡ ታዟል ተከሳሾች ከጠበቆቻቸው ጋር በመተባበር እና በመመካከር የእምነት ክህደት ቃላቸውን ለመስጠት ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ አዘናል ዐ/ህግ ባመለከተው መሰረት ቀሪ ተከሳሾቹን እንዲያቀርብ ብለናል ተከሳሾች እስከዚያው በድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ቆይተው ይቅረቡ ብለን ለግንቦት 6 ቀን 2001 ዓ/ም አጀንዳ ይዘናል።

ንገራቸው ማን ነው ስምህ

ኮንስታብል ፉአድ አሊዬ

በዛሬው እለት በማስተርጎም ሰርዶት ኮንስታብል ፉአድ አሊዬ ከፍ/ቤቱ ሂሳብ ክፍል 50 ብር እንዲከፈለው አዘናል በሂሳብ ክፍል በኩል 50 ብር ከጠይቀህ ትወስዳለህ እናመሰግናለን።

ማ/ተ

278

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 11/9/2001

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ በዚህ መዝገብ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌዴራል ዐ/ህግ አቶ ፈይሰል አብዲ፣ ረድኤት ይልማ እና አንተነህ ጌታቸው ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ 73 ተከሳሾች ቀርበዋል

ማረሚያ ቤት እናንተ ጋር ያሉት 7 ተከሳሾች ቀርበዋል በዋስ ያሉት 3 ተከሳሾች ቀርበዋል 21ኛ ተከሳሽ ሰሚራ መሀመድ አሊ፣ አለህ የት አለ ሰሚራ ሙሜ፣ መጥተሻል ጀና መሀመድ፣ የት አለች

አልቀረበችም መሰለኝ

ጀና መሀመድ፣ ዘሀራ አብዶሽ፣

አለች ይችውና

እሺ በዋስ ያሉት ተከሳሾች 22ኛ፣ 48ኛ፣ ተከሳሾች አሉ 31ኛ ተከሳሽ ግን የለችም 31ኛ ተከሳሽ በዋስ እንድትቆይ የተደረገ ቢሆንም ዛሬ አልቀረበችም ሌሎቹ በማረሚያ ቤት ያሉት 71 ተከሳሾች መቅረባቸው ተረጋግጧል እሺ በጠበቃ በኩል እራሳችሁን አስመዝግቡ

የ23ኛ፣ 37ኛ፣ እና 38ኛ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ

እሺ

በጠበቃ ከተወከሉት ውጪ ያሉት ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ አድማሱ መለሰ ቀርቤአለሁ

እሺ ጠበቆችም ራሳቸውን አስመዝግበዋል አንድ ጠበቃ ቀርቷል አደለ

279

አመ

አቶ ፀጋዬ

አቶ ፀጋዬ

እሺ ዐ/ህግ በዛሬ እለት አመጣችሁ የታዘዘውን

አመ የተከበረው ፍ/ቤት መከላከያ እንዲሁም በ26ኛው በ28ኛው ተከሳሾች ላይ ያቀረብነውን ክስ ይዘን ቀርበናል

እሺ በ26ኛ

እና በ28ኛ ተከሳሾች ላይ ያቀረብነው ክስ ይዘን ቀርበናል እና መቃወሚያ ባለፈው ላቀረበው በአቶ አድማሱ ብቻ ላይ ላቀረቡት መቃወሚያ ምላሽ ይዘን ቀርበናል ሁለት ነው እሱኛውን በተመለከተ ሌሎቹንም መቃወሚያ ከተመለከተ ነው

ለጠበቆቹም ስጡ እንጂ ዐ/ህግ

ዐ/ህግ ስለ ዋስትናውስ የጽሁፍ

አመ አቅርበናል

የት አለ

አንድ ላይ ነው

እየለያችሁ አልጻፋችሁትም እንዴ

ለይተናል የዋስትናውን ለብቻ ጽፈናል ሌሎቹንም ለብቻ ነው የጻፍነው

በእኛ በኩል የተከበረው ፍ/ቤት

አሁን ለአቶ አድማሱ መቃወሚያ ብቻ ነው የሌሎቹንም እያየን እንጨምራለን ብለን እኮ ነው

ምንድን ነው እያያችሁ የምትጨምሩት ባለፈው ታዟል እኮ

280

አሁን ለምሳሌ የአቶ አብራሂምም ሊኖር ይችላል የአቶ ፀጋዬም ሊኖር ይችላል አሁን ለየብቻ እያደረግን ነው ያለው ስለዚህ ---------- ችግራችንን ክቡር ፍ/ቤት ይረዳዋል መብራት የለም ምን የለም

እሺ በእናንተ በኩልስ

በእኛ በኩል የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው በታዘዘው መሰረት ለሶስቱ ተከሳሾች የጽሁፍ መቃወሚያችንን እና የዋስትና ጥያቄ መብቶችን አያይዘናል ብለናል

አቅርቡ እሺ

የ23ኛው ተከሳሽ

ቅድም ያልነበረችው ተከሳሽም ቀርባለች

ሰሚራ ሙሜ

አቤት

የት አለች አሁን ነው የመጣሽው

---------- ከዚሁ ነው የቀረበችው ጀና መሀመድ

ጀና መሀመድ የት ነው ያረፈድሽው እስቲ አስተርጓሚ ኦሮምኛ

ልጄን ሀኪም ቤት አድርሼ ነው

ሀኪም ቤት ሄጄ ነው

አዎ ልጄን ሀኪም ቤት አድርሼ ነው የመጣሁት

እና ፍ/ቤት አንቺን መጠበቅ አለበት ዋስ የጠበቀለሽ ፍ/ቤት ነው

የተከበረው ፍ/ቤት ከሐረር መጥቼ ከዛ ሆስፒታል ጎራ ብየየ እንትን ስል መኪናም ችግር ነበረብኝ

ከየትም ነይ ይሄ ፍ/ቤት ግን ዋስትና ጠብቆልሻል ስለዚህ ዋስትና በዋስትና መብትሽ አልተጠቀምሽም ንገሪት በቋንቋ ሼቡ ንገራት ያላከበረ ሰው ደግሞ ዋስትና ይወርዳል ይታሰራል

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

281

ቁጭ በይ ዐ/ህግ 28ኛ ተከሳሽ ከዚህ በፊት ክስ አልቀረበበትም ተከላካይ ጠበቃ 28ኛ ላይ ተቃውሞ ነበራችሁ እንዴ 26 ብቻ ነው የሚለው ጽሁፉ ላይ

አዎ

አልቀረበበትም መቃወሚያ

አብዲ አሊ አህመድ ወደዚህ ኑ ሁለታችሁም እዛ ላይ ቁሙ በላቸው እሺ በእነዚህ ሁለት ተከሳሾች ላይ ዛሬ ክስ ስለቀረበ ክሱ በንባብ ይሰማል አብዲ አህመድ ኑር አስተርጓሚ አብዲ አህመድ የት ነው የምትኖረው እድሜ ስንት ነው

ሥም - አብዲ አህመድ

እድሜ - 20

ሥራ - ገበሬ

አድራሻ- ወተር

ሥም - አብዲ አሊ አህመድ

እድሜ - 27

ሥራ - አስተማሪ

አድራሻ- ሀረማያ

እሺ ተከሳሾች 26ኛ እና 28ኛ በክሱ በተመለከተው መልክ ማንነታቸውን ለፍ/ቤቱ አረጋግጠዋል ክሱን ፍ/ቤቱ ያሰማል።

እሺ 44ኛ ክስ በ26ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ክስ ነው ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 27/1 እና 238/1 ላይ የተመለከቱትን በመተላለፍ ተከሳሹ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስቦ ቀኑ እና ወሩ በትክክል ከማይታወቅ 1999 ዓ/ም ጀምሮ ቀን እና ወሩ በትክክል እስከማይታወቅ 2000 ዓ/ም ድረስ ከሚኖርበት ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቀርሳ ወረዳ ወተር ቀበሌ ገ/ማህበር በመሄድ ራሱን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ብሎ የሚጠራውን ፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድን በመቀላቀል የዚህን ቡድን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጠሮ

292

አላማ ከግብ ለማድረስ በወታደርነት ሲያገለግል በመቆየቱ በፈጸመው በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስት ስርዓት ላይ የሚደረግ የሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው።

45ኛ ክስ በ28ኛ ተከሳሽ ላይ ወንጀሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 257ሀ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሹ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስቦ ቀኑ በትክክል በማይታወቅበት ህዳር ወር 1998 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 4:00 ሰዓት እስከ 6:00 ሰዓት ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ኮምቦልቻ ወረዳ እሬሳ ቦቶ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ልዩ ቦታው ዩሱፍ መንደር አካባቢ አንደኛ አብዲ አዩ ሁለተኛ አብዱላሂ አህመድ እና ሌሎች ሁለት ሰዎችን ሰብስቦ ራሱን ኦነግ ብሎ የሚጠራውን የፀረ-ሰላም እና አሸባሪ ቡድንን አርማ በማሳየት ይህንኑ ቡድን በገንዘብና በጉልበት እንዲደግፍ በመቀስቀስ በፈጸመው መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው። ይሄን ስሟቸው እያየህ አስተርጉምላቸው አንዱ ለአብዱ ስጡትና እያየ አስተርጉሙላቸው

አንደኛው አስተማሪ ነው ያውቃል ይሰማል

ማን ነው 26ኛ ተከሳሽ

አብዲ አሊ ይሰማል

28ኛ ኦኬ ለ26ኛ ተከሳሽ ይተርጎም

እሱን

አዎ ወይ አጠር ባለ መልኩ ሲገለጽ ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሀይል ለመናድ አስበህ ቀኑ እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት 1999 ዓ/ም ጀምሮ ቀኑ ወይም ወሩ በትክክል እስከማይታወቅበት 2000 ድረስ ከምትኖርበት የኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ቀርሳ ወረዳ ወተር ቀበሌ ገ/ማህበር በመሄድ የኦነግ ብሎ ራሱን የጠራው አሸባሪ ቡድን በቀላቅለሃል የዚህ ቡድን አላማ ከግብ ለማድረስ በወታደርነት ስታገለግል በመቆየትህ በፈጸምከው በህገ መንግስቱ እና ህገ መንግስት ስርዓቱ ላይ የሚደረግ ሙከራ ወንጀል ተከሰሃል።

ክሱን ተረድታችኋል ወይ የተነበበው ገባችሁ

አዎ ገብቶኛል

283

ግልጽ ነው

ግልጽ ነው

እሺ ተከላካይ ጠበቃ ተቃውሞውንና የእምነት ክህደት ቃሉን በተመለከተ ተመሳሳይ ነው ወይስ የተለየ የምታስመዘግቡት ነገር አለ

ባለፈው ያቀረብነው ተመሳሳይ ነው በዛው መሰረት እንትን ይባልልን የዋስትናውም በዛው ይታይልን

እሺ ቁጭ በል

አብዲ በሸር ስለ 37ኛ ተከሳሽስ ግንቦት 11 የሚለውን በተጨማሪ ነው የያዛችሁት ግንቦት 11/2001 የሚለውን

ከዋስትናው ጋር የተያያዘ ነው

አንድ ላይ ስላደረጋችሁት ነው

አዎ አንድ ላይ ስላደረግነው ነው ዋስትናውንና መቃወሚያውን አንድ ላይ አድርገነዋል

እሺ ተከሳሾች ባለፈው በታዘዘው መሰረት ነው ያቀረባችሁት

ዋስትናውን እና መቃወሚያውን

ክርክሩን በአጠቃላይ

አዎ

እሺ የ33ኛ እና የ36ኛ ተከሳሾች እና 4ኛ ጠበቃ አልቀረቡም 4ኛ ተከሳሽ አመዲን ኢብራሂም አማርኛ ትሰማለህ እስቲ አስተርጓሚ አቡ ጠበቃ የሉም ዛሬ በለው አላገኘሃቸውም ወይ አሃ አንተ ማረሚያ ቤት ነው ያለከው ጠበቃ ዛሬ የሉም በለው አብዲ ያዲ የአንተም ጠበቃ ዛሬ የሉም በለው ድርሲቱ አብደላ አንቺም ጠበቃሽ ዛሬ የሉም እሺ ቁጭ በሉ ድርሲቱ እስቲ ተነሽ የሰጠሽ ነገር አለ እንዴ ጠበቃው

የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ወንጀል ዲቪዥን

አሃ የሰጠሽው ነው

አዎ

እሺ ማን ነው አመዲን አንተስ ጠበቃ የሰጡህ ነገር አለ ወይ

ለሳቸው ሰጠሁ

ለማን አቶ አድማሱ የተቀበሉት ነገር አለ አብዲ ያዲን አንተስ ሰጥተሃል እስቲ ለዐ/ህግ ስጧቸው ይሄን አመዲን ኢብራሂም

እሺ ቆይ አንዴ እስቲ አመዲን አንተ ያንተ የለም ነው የምልህ እሺ የሌሎቹ የሁለቱ ደርሷችኋል

አንድ ነው

ደርሷችኋል ከዛ በፊት የሁለቱንም የያዛችሁትን ነገር እዩ

አዎ ---------- ቀደም ሲል ከቢሮ የተቀበልነው ነው

ዐ/ህግ አብዲ ሀጂ አሁን የደረሳችሁ ነው ድርሲቱ ቀደም ብሎ ተሰጥቷችኋል እዩት እስቲ የያዛችሁት ወረቀት ላይ

አለን እሺ አዎ ደርሶናል

ስለ 33ኛ ተከሳሽ አብዲ ሀጂ በዚህ ፍ/ቤት ሌላ መዝገብ አላችሁ እንዴ

አዎ አለን

አለን እኮ ምንድን ነው የተከበረው ፍ/ቤት የምናስመዘግበው ለፍርድ የቀረበ ሌላ መዝገብ አለን እርግጥ በዚህ ላይ ያው የፍ/ቤቱንም እማንክደው ነው ክስ አንስተናል ብለን ተናግረናል ግን በዛኛው መዝገብ ላይ ለዛሬ እንደውም ለነገ ለፍርድ የተቀጠረ መዝገብ አለን በ1999 ለተፈጸመ ወንጀል እና የጽ/ቤታችን አቋም ምንድን ነው እሱስ ዛሬም ሊቆይ የቻለው በዚህ መዝገብ ዋስትና በመከልከሉ ነው እርግጥ በዛኛው ተፈቅዶ ነበር ለፍርድ በቀረበው ላይ ስለዚህ ፍርዱን ነገ

285

ለፍርድ የተቀጠረ ስለሆነ በዛው መሰረት ቆይቶልን ፍርዱን እንዲሰጥልን ነው የምናመለክተው ለነገ የተቀጠረ ነው በዚህ ላይ ያቀረብንበትን ክስ አንስተናል ጽፈናል በጽሁፍም

ዐ/ህግ ስለ ሌሎቹስ የጻፋችሁትን ነገር የምትሉት ነገር አለ በቃል ወደ ምርመራ ከማምራታችን በፊት የምትሉት ነገር አለ

ምናልባት የአሁን አቶ አባይን መቃወሚያም አይተን አሁን የአቶ ፀጋዬንም አይተን ጨምቀን ሁለቱንም እናቀርባለን

እሺ በእናንተ በኩልስ

የተከበረው ፍ/ቤት

አስመዝግቡ

መቃወሚያውን በተመለከተ የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያውን በተመለከተ ስለ ክሱ በአጠቃላይ ክሱን በተመለከተ መቃወሚያችን በዝርዝር በጽሁፍ ሰጥተናል ነገር ግን ከዛ በፊት መቃወሚያው ወደፊት ተመርምሮ ብይን የሚሰጠው ቢሆንም በዋስትናም ጥያቄ ላይ የዋስትናውን ጥያቄ በተመለከተ ክቡር ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶት ዋስትናው ጥያቄ ላይ ብይን ቢሰጥልን ይሄንኑ ነው የምናመለክተው፡፡

በእናንተ በኩልስ

በእኛም ይኸው ነው የተከበረው ፍ/ቤት በዋስትናው ጥያቄ ላይ ባለፈው ዐ/ህግ መልስ ሰጥቷል እኛም አቤቱታችንን አቅርበናል ፍ/ቤቱም ይሄን ተቀብሎናል የሱ ብይን ይታይልን ነው መቃወሚያውን በሚመለከት መልስ ተሰጥቷል የነሱ መልስ ቀረን ካሉ አቀባብሎ እንዲታይ ነው ግን የዋስትናው ጥያቄ ክርክሩ የተጠናቀቀ ስለሆነ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄን በሚመለከት አንድ ውሳኔ እንዲሰጥልን ነው የምንጠይቀው በአክብሮት፡፡

ባለፈው በታዘዘው ትእዛዝ መሰረት የቀረበው የጽሁፍ መልሶች አሉ ያልቀረቡም አሉ በሌላ በኩል ዛሬ ቀርበው ክሳቸው የተሰማ ተከሳሾችን በተመሳሳይ በተከላካይ ጠበቃ በኩል መቃወሚያው እንዲመዘገብ ስለተደረገ በተመሳሳይ ይኸው የቀረበው መከላከያ እና በዐ/ህግ በኩል የቀረበው አስተያየት ወይም መልስ በተመሳሳይ ለእነዚህ ሁለት ተከሳሾች ክስ የተሰማላቸው ሁለት ተከሳሾችን ፍ/ቤቱ የሚመረምረው ይሆናል ከዚህ ውጪ የሚቀረው ነገር

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

286

በዚህ መዝገብ ላይ በዋስትና የተነሳው ክርክር ላይ ብይን መስጠት ነው በቅድሚያ የሚሆነው እና ቀጣይ የክርክሩ አመራር ሂደት በተመለከተ ሁኔታዎችን ማመልከት ነው በዚሁ መዝገቡ ሰፊ ስለሆነ ትንሽ ጊዜ ወስደን ፍ/ቤቱ ምርመራ ያደርጋል አጀንዳ ትይዛላችሁ ማለት ነው ለዚሁ ለዚሁ ብይን ለመስጠት የምንይዘው አጀንዳ በተመሳሳይ የዛሬ ሳምንት ግንቦት 18 ጠዋት ላይ

ግንቦት 18 --------- አንድ ላይ ቢሆንልኝ

ፍ/ቤቱ ከግንቦት 18 ውጪ ትንሽ ድምጽ

አንደኛ እንዲታዘዝልን ሁለተኛ

አስመዝግቡ

አንደኛ አበል ያለፈው ሳምንት ነው የተጠናቀቀው የክሱም ብዛት የተከሳሾቹም ብዛትና የክሱን ሁኔታ አይቼ ነው ተቸግሬ ነው ያለሁት ስለዚህ ይሄ የሚሰጠው ቀጠሮ እኔ አዲስ አበባ ደርሼ የምመለስበትን ያገናዘበ መሆን አለበት እዛ ሄጄ አበል አሳዝገሬ ምናምን ብዬ ተመልሼ መምጣትን ይጠይቃል

የእንግዲህ በኋላ ያለውን የቆይታ ጊዜውን ፍ/ቤቱ ለሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ያሳውቃል በዚህ መልክ ያለውን ነገር ተነጋግሮ መጨረስ ነው ስለዚህ በሌላ በኩል እነዚህ ተከሳሾች ቁጥራቸው ብዙ ነው በእስር ላይ ነው ያሉት ስለዚህ በአስተዳደር መፈታት ያለበት ነገር በአስተዳደር መፈታት አለበት ፍ/ቤቱ ለዚህ ትዕዛዝ ይሰጣል ስለዚህ ያለውን ቆይታ ጊዜ ለሚባለው የአስተዳደር ክፍል እንዲደርስ እና በሚያዘው አጀንዳ ድረስ እንዲቆዩ ነው የሚሆነው ማለት ነው ስለዚህ የአጀንዳው ምን አሉ የሚቸግር ነገር አለው ይሄ

አይ የሚቸግር የለውም

ስለዚህ በአጀንዳ በኩል ቅድም በተነሳው ምክንያት ዋናው ምክንያት ግንቦት 18 ነው መሆን ያለበት ምክንያቱም ብዙ ናቸው በጠበቃ በኩል የተነሳውን ጥያቄ በተመለከተ እርሶ የሚወክሏቸው ተከሳሾች ሶስት ናቸው በቁጥር ሌሎች በርካታዎቹ ደግሞ በተከላካይ ጠበቃ የተወከሉ እንደዚሁም --------- ትንሽ ቁጥራቸው ሶስት በተመሳሳይ የተወከሉ ናቸው እና በአብዛኛው መንግስት ባቆመው ጠበቃ የሚወከሉ እና ቁጥራቸውም ሰፊ ስለሆነ አጀንዳን

287

በተመለከተ መቀየሩ ብዙም አስፈላጊ አይሆንም ሌላ የሚሰጠው ብይን ነው በብይን ጊዜ መገኘት የቻለ ይገኛል ያልተገኘም የፍ/ቤት ስራ ስለሆነ የፍ/ቤቱ ስራ በአደባባይ በችሎት ማሳወቅ ነው የሚሆነው እና ይሄንኑ ፍ/ቤቱ ያሰማል ግንቦት 18 ላይ ስለዚህ አጀንዳን በተመለከተ የተነሳውን ክርክር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ለግንቦት 18 ፍ/ቤቱ አጀንዳ ይሟል ብይን ይሰጣል ግንቦት 18 ማረሚያ ቤት ታቀርቧቸዋላችሁ በዋስ ያሉትም ተከሳሾች በዚሁ መሰረት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ በጥብቅ ያሳስባል ምንድን ነው አቡ አስተርጉም ስምሽ ማን ነው መጀመሪያ ስምሽን ስሟት ድምጽ እንትኑን ስሟት ስምሽ ማን ነው በላት

ኪሚያ አሚን

ምን ፈለግሽ

ሰባት ልጆች አባት የሌላቸውን እያሳደኩ ነው ያለሁት አሁን ልጆቼ ተበትነዋል እኔ ነኝ ልጆቼን የማሳድገው አሁን እኔ በመታሰሬ ልጆቼ ተበትነዋል 4 ወር ሙሉ ያው እስር ቤት ነው ያለሁት

በቃ ይሄን ለማለት ነው ሌላ አለሽ

ይሄው ነው ችግሬ

እሺ ሌላ እጁን ያወጣ ማን ነው ማን ነው ስምህ

ጫላ ሙክታር እባላለሁ

ስንተኛ ጫላ

42ኛ

ጫላ መቀጠል ትችላለህ

ሐረር በዚሁ ጉዳይ ተከስሼ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቤ ማለት ነው የዋስ መብት ተጠብቆልኝ እያለሁ እስከ ዛሬ ይኸው እዚህ ቆየሁ

ጽፈከዋል አደለ እሱን

እዚህ ላይ ጽፌዋለሁ ወረቀቱ ላይ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

288

ጽፈከዋል አደለ እሱኑ ነው የደገምከው

አዎ

አይተነዋል እኛ ስለዚህ ተቀመጥ ጫላ

እሺ

ሌላ እንግዲህ ጊዜ አታባክኑ አቡ ንገራቸው ጊዜ አታባክኑ ይሄ በስርዓት የሚመራ ፍ/ቤት ነው እያንዳንዳችሁ የምትሰሙበት ጊዜ አስፈላጊ ሲሆን ይኖራል አሁን ግን ለብይን ነው የተቀጠረው አሁን ባላችሁበት በቆይታችሁ የተቸገራችሁት ነገር ብቻ ካለ አንድ ሁለት ሰው እንሰማለን ሌላ ግን የዋስትና ጥያቄ ገና ብይን አልተሰጠበትም ማስረጃ የሚሰማበትም ሂደትም ገና ስለሱ የተያዘ ቀጠሮም የለም ከወዲሁ ማንሳት የምትችሉት የመብት ጥያቄ በማረሚያ ቤት አሁን ባላችሁበት ቆይታ ጋር በተያያዘ የሚያያዝ ጥያቄ ነው ሌላ ለፍ/ቤት የሚቀርብ የህግ ጥያቄ እና ክርክር ግን በጠበቃ በኩል ቀርቧል በጽሁፍም ቀርቧል ፍ/ቤቱ እሱን መርምሮ ብይን ይሰጣል ይሄን ለማድረግ ለግንቦት 18 ነው የተቀጠረው የዛሬ ሳምንት ማለት ነው ገባችሁ ወይ አሁን እጅ ያወጣችሁት ለምንድን ነው እስቲ አንድ ሰው ማን ነው ስምህ

መሀመድ ኡመር

የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ ግንቦት 17 ነው ፈተናው የሚሰጠው የ10ኛ ክፍል ማትሪክ የሚሰጠው ስለዚህ ትዕዛዙን ወደ ሚመለከተው ቢያሳውቁልኝ

እሱን በጽሁፍ አመልክት ማረሚያ ቤት እንደዚህ አይነት ነገር እርዳታ ያደርጋሉ ስላልጠየክ ነው ጠይቅ እነሱ እንዴት እንደሚቀርብ ይረዱሃል ሌላ ሌላ የሚናገር ሰው እስቲ ስጣቸው ማን ነው ስምህ

ያለኝ ችግር

ስምህ ማን ነው ስምህ

ሀጂ ጣሀ

ሀጂ ጣሀ እሺ ምንድን ነው ችግርህ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

289

ከልጆቼ ላይ ገንዘብም ወስዷል እኔም እንደዚህ እጄ ሽባ ሆኗል እጄ ምንም አይሰራም ብልቴም አይሰራም

ቆይ ቆይ ይበቃል ይበቃል ይሄን ወደፊት አሁን እሱን እያጣራን አይደለንም ሌላ ጥያቄ ሌላ አንድ ሰው ብቻ ነው ከአሁን በኋላ የሚፈቀድለት

45ኛ ተከሳሽ ነበርኩ

ስምህ ማን ነው

ዩሱፍ ጨሎ

አው ዩሱፍ ጨሎ እሺ

አልተጠራሁም ቅድም ሶስት ነው የጠራችሁት አራት ነበር እኔ ከአህመድ አብራሂም ጋር

እነሱ በጠበቃ ስለተወከሉ ነው

እኮ እኔም ጠበቃ ከእነሱ ጋር ነኝ

ጠበቃ አላስመዘገቡም ባለፈው

አስመዝግበዋል 45 ብለው

45

አዎ

አልመጡማ ያንተ ጠበቃ

አልመጣም አዎ ጠበቃው አልመጣም ግን አስመዝግቦ ነበር

ቆይ አንተ 45ኛ ነህ አይደለም

አዎ

45ኛ ተከላካይ ጠበቃ ይሄን ድስታውሳላችሁ አደለም 45ኛ ተከሳሽ

290

አዎ ግን እናንተ የጻፋችሁት ላይ ስለ 45ኛ ተከሳሽ

45ኛ ተከሳሽ ----------

ስላላችሁ ነው

አዎ

አንተ ጠበቃ አመጣለሁ ያልከው ነው

ዛሬ አልቀረበም እንጂ እኮ አስመዝግቧል

አዎ ባለፈው አላስመዘገቡም

አስመዝግቧል 45 ብሎ

አላስመዘገቡም

አስመዝግቦ ነበር እዚሁ

አላስመዘገቡም እኛ እናስታውሳለን እዚህ ተመዝግቧል አቶ ፀጋዬ ፈቲህ ያስመዘገቡት 4ኛን፣ 33ኛ እና 36ኛ ተከሳሾችን ብቻ ነው ዞሮ ዞሮ ጠበቃ ይወክሉሃል አደለም

ወክዬዋለሁ እሱን

ወክለከዋል

አዎ

በቃ አሁን ጠበቃ አልቀረቡም መቅረብ ነበረባቸው በተመሳሳይ የሚታይ ይሆናል የአንተን ልዩነት አያመጣም

እሺ

በቃል ክርክሩ ስለተሰማ የዋስትናው አዎ እኛ ግን መዝግበናል አላስመዘገቡም 45ኛን በተመለከተ በጽ/ቤት ተከላካይ ጠበቃውን ጠይቀናል ምክንያቱም ይሄ ተከሳሽ መጀመሪያ ላይ ጠበቃ አመጣለሁ ያለ መሆኑን ስለምናስታውስ ነው ጠበቃው ግን ይሄን አላስመዘገቡም ጥፋቱ የጠበቃው ሊሆን ይችላል እሱን ወደማጣራት አንሄድም ዞሮ ዞሮ ግን የዋስትና ክርክር ግን

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት
የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ለወከሏቸው ጠበቆች ለተከሳሾች በቃል አሰምተዋል ይሄን ሰው እወክላለሁ ካለ የሚወክሉት ከሆነ ልዩነት አያመጣም የወንጀል ጉዳይ ስለሆነ ያው ይመዘገባል ሌላ እስቲ ይኼኛው ማን ነው ማን ነው ስምህ ሁሴን እስቲ ስጠው ማን ነው ስምህ

ዙቤድ ሁሴን

ተቀበለው አቶ አቡ እሺ ምንድን ነው የምትፈልገው

ተመሳሳይ ቅድም እዚህ ጋ ከቀረበው ጋር ከአሁን ቀደም በሌላ በከፍተኛ ፍ/ቤት እንትን ብዬ ወጥቻለሁ ነው የሚለው

እሱ በብይን ጊዜ የሚታይ ነው በጽሁፍም አድርገከዋል አይተነዋል ስለዚህ እዚሁ ይመረመራል አትድገሙ እንደዚህ አይነት ነገር አትድገሙ ቁጭ በል ሌላ በዚሁ ይበቃናል ማን ነው እሺ እርሶ ስሞት ማን ነው

ሚካኤል አብዱላሂ

እሺ ምንድን ነው የሚፈልጉት

እኔ 90 አመቴ ነው እጄ አይሰራም ያመኛል ስለዚህ አሁን እኔ በ90 አመቴ በማላውቀው ነገር ነው እዚህ ውስጥ ያው በ90 አመቴ

እሱ ወደፊት በማስረጃ ይጣራል አሁን ግን ተጠርጥረው ቀርበዋል ፍ/ቤቱ ደግሞ ህግ በሚያዘው መሰረት ይመለከታል የእርሶን ጉዳይ በላቸው አበቃችሁ በላቸው ሁሉንም ማረሚያ ቤት በዚሁ ሌላ ነገር ዐ/ህግ የምታሳስቡት ሌላ አለ

ምንም የለንም

ከሌለ በእናንተም በኩል የለም ከሌለ በዚህ ሰነድ ላይ ፈርማችሁ ቀጠሮ 18 ጠዋት 2:00 ሰዓት ላይ አጀንዳ በመያዝ ችሎቱ ስራውን አብቅቶ ተነስቷል።

ማ/ተ

292

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 18/9/2001

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ስኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ

73 ተከሳሾች መካከል ያለውን ክርክር ፍ/ቤቱ ማየት ይቀጥላል። እሺ መዝገቡ የተቀጠረው በቀረቡ መቃወሚያዎች ላይ የዋስትና ጥያቄ ላይ ብይን ለመስጠት ነው በሌላ በኩል ደግሞ በመዝገቡ ምርመራ የ22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾች ክስ በንባብ አለመሰማቱ በመረጋገጡ በቅድሚያ የ22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾች ክሱ ችሎቱ ያሰማል ዐ/ህግ የ22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾች ያቀረባችሁትን የክስ ማመልከቻ ስሟቸው ጀና መሀመድ፣ ዘሀራ አብዶሽ፣

ባለፈው በሰጠነው 9ኛ ክስ ውስጥ 22ኛው ተከሳሽ አለች በ28ኛው ክስ ውስጥ 18ኛ

የክስ ማመልከቻ ስጡ ነው የተባላችሁት ከሌላችሁ የለንም በሉ ፍ/ቤቱ እሱን ይመዘግባል

እሺ

የፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠቀባ ለ22ኛም ለ48ኛም ተከሳሾች ተመድበዋል 48ኛ ተከሳሽ ማስረጃ ቀርቧል በወሊድ ላይ መሆኗን የሚገልጽ ነው በ18/9/2001 ዓ/ም የተፃፈ ነው ከቀበሌ 01 ከሐረር ከተማ አስተዳደር 9ኛ ክስ ብቻ ነው የሚመለከተው

አዎ

ለ22ኛ ተከሳሽ ክሱን እንደሚከተለው ይሰማል ክሱ በ9ኛ፣ 15ኛ፣ በ22ኛ፣ በ25ኛ፣ በ29ኛ፣ 30ኛ፣ 33ኛ፣ 34ኛ፣ 37ኛ፣ 54ኛ ተከሳሾች ላይ ተጽፎ የቀረበ ነው ዝርዝሩ በ1996 የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 321ሀ እና 257ሐን በመተላለፍ የሚል ነው ዝርዝሩ ተከሳሾች በዋና

293

ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በህገ መንግስቱ እና በህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ እና በሀገር እና በመንግስት ላይ ሽብር ለመፍጠር አስበው ቀን እና ወሩ በትክክል በማይታወቅበት በ1999 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን አወዳይ ከተማ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ህዝብ በሆነው ራሱን ኦነግ ብሎ በሚጠራው አሸባሪ ቡድን ስር ተደራጅተው የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮች መኖሪያ ቤታቸው ድረስ በማምጣትና በመደበቅ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማቅረብ እንዲሁም ህዝቡ ለመንግስት እንዳይታዘዝ በመቀስቀሳቸው የመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የመሰናዳት ተግባር ወንጀል በመፈጸም ተከሰዋል የሚል ነው ሌላ ክስ የለባትም አደለ ዐ/ህግ

አዎ

አስተርጓሚ አለም ኦሮምኛ የሚያስተረጉም ሰው የለም እንዴ እስቲ ጥሩ አስተርጓሚ ኦሮምኛ ይችላሉ እስቲ ያስተርጉሙ የምንነግሮትን ለሷ አንቺ የተከሰሽው በወንጀል ህግ ውስጥ በቁጥር 257ሐ ስር የተመለከተው ተላልፈሻል ተብሎ ነው አደረግሽ የተባለው ነገር ደግሞ በዝርዝር ከ1999 ዓ/ም እስከ 2001 ዓ/ም ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ዞን ሐረርጌ አወዳይ ከተማ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ህዝብ በሆነው ኦነግ ተብሎ በሚጠራ አሸባሪ ቡድን ስር ተደራጅተው የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮች መኖሪያ ቤትሽ ድረስ በመምጣት በመደበቅ የቡድኑን እኩይ አላማ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ቁሳቁሶች በማቅረብ ህዝቡ ለመንግስት እንዳይታዘዝ በመቀስቀስ በህገ መንግስቱና በመንግስት ላይ የመገፋፋትና የማሰናዳት ወንጀል ተከሰሻል ተብሎ ነው አዳመጥሽ ወይ

እሺ

በአስተርጓሚ እየተረዳች ክሱን እንድትረዳው በችሎት ተደርጓል መስማቷንም ለችሎቱ አረጋግጣለች በዚህ ጉዳይ ተከሳሽ ለሌሎች ተከሳሾች ፍ/ቤቱ ያቆማቸው ተከላካይ ጠበቃ ስለተመደቡ ተከላካይ ጠበቃ የምታሳስቡት ነገር ካለ

የክስ መቃወሚያውን በሚመለከት ባለፈው ግንቦት 6/2001 ባቀረብነው መሰረት በተራ ቁጥር 3 መሰረት መቃወሚያው ለዓቃ የተመዘገበው ሰሚ እንዲመዘገብላት የዋስትና ጉዳይ አስቀድሞ የተወሰነ ስለሆነ በዚሁ እናልፈዋለን

294

እሺ ተቀመጪ በሏት ማረሚያ ቤት 70 ተከሳሾች ቀርበዋል

አዎ

ማረሚያ ቤት በዚህ መዝገብ ከዋስ ውጪ በስር የሚገኙት 70 ተከሳሾች መቅረባቸውን ለችሎቱ አረጋግጦ ተመዝግቧል በሌላ በኩል 48ኛ ተከሳሽ በወሊድ ምክንያት አለመቅረቧ ተመዝግቧል ዐ/ህግ ፍ/ቤቱ በቅድሚያ በ11/9/2001 ዓ/ም ለፍ/ቤቱ በፃፋችሁት መልስ ላይ ተራ ቁጥር 1 ላይ 31ኛ ተከሳሽ በተመለከተ በድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ያለው የአየር ሁኔታ ለህይወቷ አስጊ በመሆኑ የተከሰሰችበትን የህግ አንቀጽ ዋስትና ስለማይከለክል በመጥቀስ መቃወሚያ ማቅረቢን ከመዘገባችሁ በኋላ በዚሁ ላይ በፃፋችሁት አስተያየት ተከሳሽ የተከሰሰችበት የህግ አንቀጽ የዋስ መብት የማይከለክል መሆኑን ካሰፈራችሁ በኋላ ሆኖም የ7 ወር ነፍሰ ጡር በመሆኗ ምክንያት ብቻ ግንቦት 6/2001 በዋለው ችሎት የዋስ መብት መከበሩን በማረጋገጥ ጽፋችኋል በዚህ እለት ለችሎቱ ባቀረባችሁት ክርክር እና በፍ/ቤቱ ማህደር የተመዘገበው እንደሚያሳየው 31ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ህመም ብቻ ሳይሆን የዋስትና ጥያቄውን እንደማትቃወሙ በግልጽ ለችሎቱ አስመዝግባችኋል በጽሁፍ ተመልሶ የመጣው ግን ለችሎት ያስመዘገባችሁት እና ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠበትን በግልጽ ትዕዛዝ የሰጠበትን የሚነካ ትርጉም ያለው ነገር በማህደሩ ውስጥ እንዲያያዝ አድርጋችኋል ይሄ የተደረገበት ምክንያት ምን እንደሆነ ፍ/ቤቱ ማወቅ ይፈልጋል ስለዚህ በዚህ ላይ የምትሰጡት ማብራሪያ ካለ ማብራሪያ ስጡ ፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት

አንዴ ቢደገምልን የተከበረው ፍ/ቤት

በቃል የጻፋችሁት የዚህ ችሎት አስመዝግባችሁ የዋስትና መብት የተፈቀደበት እና ግንቦት 11/2001 ዓ/ም በዛው ችሎት በዚህ ፍ/ቤት ግራ ቀኛችሁ በቃል ያደረጋችሁት ክርክር እንደወረደ ሳይጨመር ሳይቀነስ ምክንያቱም ፍ/ቤቱ ክርክሩን በተፋጠነ ሁኔታ ለመምራት ያመነበትን ትዕዛዝ በሰጠበት ሁኔታ በጽሁፍም እንድታቀርቡ ታዞ ግራ ቀኛችሁ በጽሁፍ አቅርባችኋል በጽሁፍ በዐ/ህግ በኩል የቀረበው ግንቦት 11/2001 ዓ/ም የተጻፈው በተለይ ስለ 31ኛ ተከሳሽ የዋስትና ጉዳይ በተነሳው ላይ በችሎት ያስመዘገባችሁት እና በጽሁፍ የጻፋችሁት የጎላ ልዩነት ይታይበታል በጽሁፍ የጻፋችሁት ላይ በነፍሰ ጡር በመሆኗ ምክንያት የተከሰሰችበት ህግ የዋስ መብት የማይከለክል ሳይሆን ነፍሰ ጡር በመሆኗ ባለባት የጤና ችግር ምክንያት ችሎቱ ግንቦት 6/2001 ዓ/ም በአስቸኳይ ጊዜ በዋስ መብቷን ስላከበረላት አሁን የተነሳው መቃወሚያ ላይ በጽሁፍ መልስ መስጠቱ አስፈላጊ አይደለም በሚል በጽሁፍ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 2

አስፍራችሁ ለፍ/ቤቱ ማህደር ውስጥ እንዲያያዝ አድርጋችኋል ሆኖም በዛን እለት በዋለው ችሎት 31ኛ ተከሳሽ እንደዚሁም ደግሞ በተመሳሳይ 22ኛ እና 48ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ በተነሱት ጥያቄዎች 22ኛ እና 48ኛን በተመለከተ ቀድሞ በፖሊስ በዋስ መቆየታቸውን አሁንም ደግሞ በችሎት ሲታዩ ጤናቸው የታወከ መሆኑን በቀረበው የዋስትና ጥያቄ በግልጽ የማትቃወሙ መሆኑን አስመዝግባችኋል 31ኛ ተከሳሽንም በተመሳሳይ የ7ወር ነፍሰ ጡር ነች በሚል በተከላካይ ጠበቃ በተነሳው አቤቱታ በዋስትና ጥያቄው ላይ ተቃውሞ እንደሌላችሁ በግልጽ አስመዝግባችኋል

እኛም አስመዝግበናል

በጽሁፍ በተጻፈው ላይ ግን ይሄ አይነት ልዩነት ለምን ተደረገ ነው ይሄ ፍ/ቤት የሚፈልገው እያንዳንዱ በመዝገብ ውስጥ የሚያያዝ ማህደር ትርጉምና ከሚሰጥ የዳኝነት ስራ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት በመሸሽ የሚሰጡ የክርክር እና የሚመዘገቡ ክርክሮች መኖር የለባቸውም ይህ ታስቦ ከሆነ ወይም በሌላ ምክንያት ይሄ ማብራሪያ ይፈልጋል ከእናንተ ነው ይህ ማብራሪያ መቅረብ ያለበት ስለዚህ የምትሰጡትን ማብራሪያ ፍ/ቤቱ ይፈልጋል በአጭሩ

የተከበረው ፍ/ቤት ኢንቴንሽናችንን ያውቃል በመሸሽም ያደረግንበት ምናልባትም የታይፕ ስህተት ሊሆን ይችላል እኛ ኢንቴንሽናችን መጀመሪያውኑ እዚህ እንደሰጠነው ሶስቱም ተከሳሾች ከፍተኛ የጤና ችግር ነበረባቸው እርጉዞች ነበሩ እንደውም አሁን የተወለደ ልጅ ይዘው ነው የቀረቡት ያንንም በማየት ነው የዋስትናውንም አንቃወምም ያልነው በጽሁፍም በዛ ---------- ይሆናል የተጻፈው ምናልባት በስራ ጫና ኢንቴንሽኑ ሊቀያየር ስለሚችል እንጂ ---------- ----- በዛ አንቃወምም

እያስመዘገባችሁ

መጀመሪያውኑም እዚህ የተናገርነው ሶስቱም ተከሳሾች በከፍተኛ ሁኔታ የጤና እንትን ነበረባቸው ምንም እንኳን ይህ ባይኖር የዋስትናውንም ጥያቄ የምንቃወም ቢሆንም በነበረባቸው በግልጽ ችሎቱም በሚያየው ሁኔታ ለዚህ ሲባል የዋስትና መብታቸው ላይ ተቃውሞ እንደሌለን ሶስቱን በተመለከተ ነው ያልነው ምናልባት ጽሁፉም በዛኑ አይነት አንደርስታንዲንግ ነው የተጻፈው እና በዛን አይነት ኢንቴንሽን ቢያይልን ፍ/ቤቱ

እዚህ ጽሁፍ ላይ

296

የሥራ ጫናዎች እየተደራረቡብን መጥቷል ክቡር ፍ/ቤት እንደውም አሁንም በሚቀጥለውም ጠቅላላችን ልንሄድ ስለሆነ በጣም ሩጫ ላይ ነን

ዐ/ህግ ተከሳሿ የተከሰሰችበት የህግ አንቀጽ የዋስ መብት የማይከለክል ስለሆነ ብላችሁ ስጻችኋል

እንደዛ ይሄ እንግዲህ በታይፕ ስህተት የገባ ይመስለኛል የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው ያስመዘገብነው እዚህ ላይ የዋስትናውን መብት ተቃውመን ግን እነዚህን በተመለከተ ኤክሰብሸናሊ ባለባቸው የጤና ችግር የተከበረው ችሎት በሚያየው ሁኔታ ነው ያልነው

ስለዚህ በጽሁፍ የጻፋችሁት ነገር በዚህ በቃል ካስመዘገባችሁት ውጪ ነው ማለት ነው

ነው አዎ

ስህተት ነው የተፈጸመው እያላችሁ ነው

አዎ

ሌላ ዐ/ህግ በተጻፉት ክስ ዙሪያ በዝርዝሩ ላይ እነዚህ ወንጀሎች ከህገ መንግስታዊ ስርዓት ጋር ወይም ህገ መንግስቱን ---------- የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተብሎ በወንጀል ህግ ውስጥ የተመለከተውን በዚህ መልክ የተጻፈውን ወይም እነዚህ ወንጀሎች የሚሸፈኑበት የወንጀሉን ክፍል በመጽሀፍ ውስጥ ያለውን በማመልከት ክስ መጻፋችሁ ዝርዝሩ ላይ መረዳት ይቻላል ሆኖም ግን የጠቀሳችሁት ህግ ላይ ግን በዝርዝር የተጻፉትን የሚጠቁም ወይም የሚለይ የህግ ድንጋጌ አላመለከታችሁም ከመገፋፋት በዋና አድርገዋል የተባለው ወንጀል የሚያመለክት የህግ አንቀጽ አለ አስቀምጣችኋል እነዚህ የተፈጸሙት ግን የተባለው በዝርዝሩ ላይ ያመለከታችሁትን ወንጀል አንቀጽ የሚያመለክት ነገር ግን የለም ስለዚህ ይሄ ለምን ሆነ የሚለውን ነገርም ማብራሪያ ብትሰጡበት ችሎቱ ይሰማል

የተከበረው ፍ/ቤት ወደፊት ምናልባት ምስክሮቻችንን አቅርበን በምናሰማበት ጊዜ ግልጽ ይወጣል ብለን ነው እርግጥ እነዚህ ከ248 338 የሚቀጥሉትን ያመለክታሉ በሚል ነው እኛ ያላስገባናቸው ነገር ግን ምስክር በሂደት ውስጥ በሚሰማበት ጊዜ እነኛን ድርጊቶች ቁልጭ አድርገው ያወጣሉ በሚል ነው ፤ ፍ/ቤቱ በሚሳሳም ተቃውሞ ክሳችንን እያየን ፍ/ቤቱ አድርጉ በሚለን አካሄድ እያሻሻልን እንሄዳለን በሚል እሳቤ ይዘን ነው የተነሳነው

ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 4

በሌላ በኩል ከተጠቀሱት ፍ/ቤቱ ለማጣራት ካነሳቸው እና በመጨረሻ ላይ ትዕዛዝ ከሚሰጥባቸው ፍሬ ነገሮች ባሻገር መዝገቡ በዋናነት የተቀጠረው የተነሱ መቃወሚያዎች እንዲሁም የዋስትና ጥያቄ ለያይቶ ተገቢ ነው የሚለውን ብይን በመዝገቡ ላይ ማስፈር ነው በዚሁ ፍ/ቤቱ መዝገቡን አይቶ የሚከተለውን ብይን ሰጥቷል፡፡

ማለት የተከበረው ፍ/ቤት

አስተርጓሚው የታል

የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው ለቀረበው መቃወሚያዎች ምላሽ አምጥተናል

ቁጭ ትላለህ በደንብ አትችልም ሌላ ሰው ፈልጉ እሺ እናመሰግናለን ተመለስ ሌላ ሰው ባለፈው አልታዘዝም ግን የጽሁፍ ስለሆነ እስቲ ተቀበሏቸው ያስተረጉማሉ

አዎ

እሺ ማን ነው ስሞት

አብደላ አሊዬ

በአቶ አብደላ አሊዬ አስተርጓሚነት ፍ/ቤቱ የሰራውን ብይን በንባብ ያሰማል ያስተረጉማሉ ብይን ተሰጥቷል ከሳሽ የፌደራል ዐ/ህግ

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ አቶ ፌይሰል አብዲ ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ 73 ተከሳሾች መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ብይን ሰጥቷል፡፡

ብይን

1ኛ. በ39ኛ ተከሳሽ ክስ ቀርቦ ተከራክሯል በሀሰት ተቀርቧል ነው በሚል የተነሳው መቃወሚያ በህጉ የተፈቀደ መቃወሚያ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም

298

2ኛ. 33ኛ ተከሳሽ ዐ/ህግ ክሱን በማንሳቱ በዚህ መዝገብ ከቀረበበት ክስ እንዲሰናበት ፍ/ቤቱ አሏል

3ኛ. 26ኛ ተከሳሽ ክስ አልቀረበብኝም በሚል የተነሳው ጥያቄ ዐ/ህግ ክሱን አቅርቦ በማሰማቱ ታልፏል

4ኛ. ዐ/ህግ በፃፋቸው ክሶች ወንጀሎቹ ተሰሩ ያለባቸውን ጊዜ በማመልከቱ ወርና ቀን አልተመለከተም በሚል ክሱ እንዲሰረዝ የቀረበው መቃወሚያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም

5ኛ. የዐ/ህግ ሶስተኛ ክስ የቃላት ግድፈት አለበት በሚል የተነሳው መቃወሚያ ግድፈቱ የተጻፈውን ክስ ለመረዳት የማያዳግት እና መሰረታዊ ስህተትም ባለመሆኑ በቀላሉ ሊስተካከል የሚችል በመሆኑ ክሱ እንዲሻሻል ከማዘዝ ዐ/ህግ የቁጥርና የቃላት ግድፈቱን በችሎት እንዲያስተካክል ፍ/ቤቱ አሏል።

6ኛ. 5ኛ ተከሳሽ ክስ በቀረበበት ወንጀል ተከሶ ለመቀጣቱ ማስረጃ ባለማቅረቡ በዚህ ረገድ የቀረበው መቃወሚያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በእስር ላይ ነበርኩ የሚለውም ክርክርም ቢሆን ወደፊት በማስረጃ የሚጣራ እንጂ ከወዲሁ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም

7ኛ. ተከሳሾች ኮኮብ መሀመድ እና ጫላ ሙክታር በሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዋስ መለቀቃቸውን በመግለጽ ያነሱት ክርክር ይህ ፍ/ቤት በቀረበለት ክስ በህግ ባገኘው ስልጣን የሚሰጠውን የዳኝነት ስራ ቀሪ ሊያደርግ ስለማይችል ተቀባይነት የለውም በተጨማሪም በህጉ የሚሸፈን መቃወሚያ አይደለም

8ኛ. ክሱ ግልጽነት ይጎድለዋል ከህጉ አነጋገር ጋር አይጣጣምም የመከላከል መብት ያጣብባል ተብሎ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ ፍ/ቤቱ ክሶቹን በወንጀለኛ ስነ-ስርዓት ቁጥር 111 እና 112 ላይ የተመለከተውን ክስ ማመልከቻ መሟላት ያለበትን መያዙን በመረዳቱ በተመሳሳይ አልተቀበለውም

9ኛ. ክሶቹ ተነጥለው ሊታዩ ይገባል በሚል የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ ተከሳሾች በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ እና የተለያዩ ድርጊቶች በመፈጸም ወንጀል ሰርተዋል በሚል ተጠርጥረው የተከሰሱ በመሆናቸው ክርክሩን በፍጥነትና በሚመች ሁኔታ ለመስማት ክሶቹ

በአንድነት በቀረበበት ሁኔታ እንዲታዩ የተሻለ ሆኖ ፍ/ቤቱ በማግኘቱ በዚህ ረገድ የተነሳውን መቃወሚያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም

10ኛ. ዋስትናን በተመለከተ

10.1. ተከሳሾች ወንጀሉን ተፈጸ በተባለበት አካባቢዎች ቋሚ ነዋሪ መሆናቸው እና ፍ/ቤትም ቀርበው ይሄንኑ በአድራሻነት በማስመዝገባቸው

10.2. ክሶቹን ለማስረዳት ማስረጃዎቹን ተከሳሾች ከሚኖሩባቸው አካባቢዎች የሚቀርቡ በመሆናቸው

10.3. ክሱ በመንግስት እና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ ወንጀል ተፈጽሟል በሚል እንደመቅረቡ የክሱ ስፋትና ክብደት በክሱ አሰማምና በተከሳሾች አቀራረብ ላይ በግምት የሚያዝ ምክንያት ሆኖ በመገኘቱ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከሳሾች በዋስ ቢቆዩ ዋስትና ግዴታቸውን በማክበርና እንዲሁም በቀላሉ እየቀረቡ ይከራከራሉ ተብሎ ባለመታመኑ እንዲሁም ምስክሮቹን ሊያባብሉ እና ማስረጃም ጥፋት ሊያደርጉ ይችላሉ ተብሎ በመታመኑ ፍ/ቤቱ የዋስትና ጥያቄውን አልተቀበለውም በአጭሩ ትነግራቸዋለህ፡፡

በአብዛኛው ያነሳችሁት መቃወሚያ ስጡት እስቲ እንትኑን በአብዛኛው የተነሱ መቃወሚያዎች ከክሱ አቀራረብ እና አጻጻፍ እንዲሁም አንዳንዶቻችሁ ክሱ ወርና ጊዜ አልተጻፈበትም ክሱ በሀሰት የተጻፈ ነው እኛን ለማጉላላት የተደረገ ነው በማለት የተነሱት በአብዛኛው ለክስ መቃወሚያ የሚበቁ አደሉም ከማስረጃ መስማት ጋር በአብዛኛው የሚያያዙ ስለሆነ ወደፊት የእናንተ ክርክር ሲሰማ የሚታወቅና እርግጠኛ መሆን የሚቻል ከወዲሁ ግን ክሱን ሊያስቆም አይችልም በሌላ በኩል በክስ አጻጻፍ ላይ የቁጥር የቃላት ስህተትን በተመለከተ ጥያቄዎች በተመለከተ ክሱን ለማሻሻል መሰረታዊ ባለመሆናቸው እንዲሁም በዚህ ፍ/ቤት የተሰማውን ክስ ለመረዳት እንቅፋት ሆነዋል ተብሎ መውሰድ ስለማይቻል በዚህ ዙሪያ የተነሳውም እንደዚሁ በተመሳሳይ ተቀባይነት አላገኘም በሌላ በኩል የተወሰናችሁት በሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የዋስ መብት ተጠብቆልናል በማለት ያነሳችሁት አለ እናንተ ተጠርጥራችሁ የተከሰሳችሁበት ጉዳይ በዚህ ፍ/ቤት ቀርቧል ይሄ ፍ/ቤት ደግሞ በስልጣኑ የዳኝነት ስራ ይሰራል ስለዚህ በዞን ፍ/ቤቱ በዋስ ተለቀቅን የሚለው ክርክር የዚህን ፍ/ቤት ስራ አያስቆምም ህጋዊ መቃወሚያም አይሆንም ሌላ 5ኛ ተከሳሽ የተከሰሰበት ጉዳይ ተፈርዶብኝ ተቀጥቻለሁ የሚል ክርክር ለማንሳት በጽሁፉ ተሞክሯል ሆኖም ግን ማስረጃ አልተያዘበትም ስለዚህ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም

300

በማስረጃ ስለሚሰራ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ እስር ላይ ነበርኩ የሚለው ወደፊት በማስረጃ የሚጣራ ነው በሌላ በኩል ጉዳዮቹ እየተነጣጠሉ ይታይ የሚል የተነሳ ክርክር አለ እናንተ ሁላችሁም ዐ/ህግ የከሰሳችሁ በመንግስት ላይ የሚሰራ ወንጀል አድርጋችኋል ተብሎ ነው እያንዳንዳችሁ የተጠየቃችሁበት ድርጊት የክስ ማመልከቻው እንደሚያሳየው ይለያያል ወንጀሉ ግን እንደተባለው በመንግስት ላይ የተሰራ ነው ስለተባለ በዚሁ መዝገብ በአንድነት ቢታይ ክርክሩን ያፋጥነዋል አመቺም ነው ብሎ ይህ ፍ/ቤት ያምናል በዚህ ምክንያት በአንድነት ነው ከዚህ በኋላ ክርክሩ የሚቀጥለው ለሁላችሁም በጋራ በተደጋጋሚ የቀረበው በዚህ መዝገብ ላይ የዋስትና ጥያቄ ነው በዚህ ላይ ሰፊ ክርክር በግራ ቀኞችሁ በኩል ቀርቧል ይሄ ፍ/ቤት እንዳመነው ግን እናንተ ድርጊቱን የተጠረጠራችሁበትን ድርጊት ፈጸማችሁ የተባለው በሌላ አካባቢ ነው በዛ አካባቢ ደግሞ ቋሚ ነዋሪ መሆናችሁን ለፍ/ቤቱም አስመዝግባችኋል በዚህ ችሎት ይቀርባል የተባለው ማስረጃም ከዚህ አካባቢ ይመጣል የተባለ ነው የቀረበው ክስም ሰፊ ነው ወንጀሉም በመንግስት ላይ የተሰራ ስለተባለ ክብደት አለው ይኸው ግን በክስ አሰማም እና በእናንተ አቀራረብ ላይ ግምት የተያዘበት ሌላ ምክንየት ሆኖ ተገኝቷል ይኸውም ምክንያት እናንተ እንዴት ትቀርባላችሁ ወደፊት በሚለው ላይ ግምት እንዲያዝ አድርጎታል በእናንተ መቅረብ ላይ ግምት ውስጥ እንዲገባ ማለት በሌላ አነጋገር አሁን በተባሉት ምክንያቶች እናንተ በዋስ ብትቆዩም አሁን እየቀረባችሁ በምትከራከሩበት መንገድ አክብራችሁ ትቀርባላችሁ ተብሎ ለመገመት ፍ/ቤቱ አልቻለም በቀላሉ ትቀርባላችሁ ብሎ እንደዚሁም አልተገመተም ማስረጃው ደግሞ እናንተ ከምትኖሩበት አካባቢ ይመጣል ስለተባለ ለማስረጃው ካላችሁ ቅርበት በተለይ ምስክሮች ስለሆኑ ወደውጪ ብትወጡ ላይመሰክሩ ይችላሉ ስለሆነም በእነዚህ ምክንያቶች የዋስትና ጥያቄውን ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ቀጣይ የሚሆነው ፍ/ቤቱ በሚይዘው የማስረጃ አሰማም ክርክሩ የሚሰማበትን ቀጠሮ ማሳጠር ብቻ ነው።

ተከላካይ ጠበቃ የምትሉት ነገር አለ እምነት ክህደት ቃል መስጠት ይችላሉ ዐ/ህግ የእምነት ክህደት ቃላቸውን የቀረቡትን ተከሳሾች ይጠይቃል ከዚህ በኋላ ማስረጃ የሚሰማበትን አጀንዳ ይይዛል።

አብዱረህማን ባሌ አስተርጓሚ ና ወደዚህ አብዱረህማን አንተ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በቀረበብህ ክስ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ነው የምለው

301

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ሸሪፍ አሊ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በልና ጠይቀው

አልፈጸምኩም

ሁለተኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

አህመድ ኑር አርጌ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው

አልፈጸምኩም

አመዲን ኢብራሂም 4ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው

አላምንም ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል 4ኛ ተከሳሽ

ከማል አሊዩ አህመድ 5ኛ ተከሳሽ ጠይቀው

እስር ቤት ነበርኩኝ እና ይሄንን ጉዳይ አልፈጸምኩም

ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተመዝግቧል

መሀመድ ኢብራሂም አደም ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም

6ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ሲራጅ አህመድ ሙሳ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

7ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ፋጤ አሚን ሳዲቅ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

302

8ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏለች

ጀማል ሃምዛ ቂልቱ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም

ጣሃ አህመድ አብዱሮ

ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ዙቤድ ሁሴን መሀመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

አብዱረህማን ሁሴን ጅብሪል ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ረምላ ሸሪፍ ኡመር ጥፋተኛ ነሽ አይሰለሽም

ጥፋተኛ አይደለሁም አላምንም

13ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብላለች

ኢብራሂም ሁሴን ጉራቾ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ሰርቼም አላውቅም አላጠፋሁም

14ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

15ኛ ተከሳሽ ኪሚያ አሚን ዩሱፍ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብላ [illegible]

ዘይነባ መታ መሀመድ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

303

ጥፋተኛ አይደለሁም አልፈጸምኩም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብላለች 16ኛ ተከሳሽ

አብዲ ሹኩር ኡመር ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም

ኢብራሂም መሀመድ ጅብሪል ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም

ሸሪፍ ኡመር አሌም ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ምንም ጥፋት የለብኝም አላምንም

አብዲ ኡስማን አደም ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ ተመዝግቦለታል ቃሉ

መሀመድ አሊዬ ሰግዳ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ በደንብ ትችላለህ አሁን ያልኩትን ሰምተሃል ገብቶሃል ጥፋተኛ ነህ አይደለም ሲባል እሺ 21ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ጀና መሀመድ ሃዳስ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

ፈጽሜ አላውቅም

እሺ ጥፋተኛ አይደለሁም ብላለች

አብዱልሃሚድ መሀመድ አሊ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ ትችላለህ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ሼክ መሀመድ ኡስማኤል ኪኖ

ጥፋተኛ አይደለሁም እኔ የባህል ህክምና ባለሙያ ነኝ

እሺ ጥሩ ይበቃል ጥፋተኛ አይደለም በሚል ቃሉ ተመዝግቦለታል

304

ሻም ኢብራሂም አብደላ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ፈጽሜ አላውቅም

እሺ 25ኛ ተከሳሽም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

26ኛ አብዲ አህመድ ኑር ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ ትችላለህ በደንብ ትሰማለህ

አዎ

እሺ 26ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ኢብራሂም መሀመድ አብዶ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ጥፋተኛ ነህ አደለህም አማርኛ በደንብ ትሰማለህ እሺ ተቀመጥ

አብዲ አሊ አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አጥፍቼ አላውቅም

ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት አስመዝግቧል 28ኛ ተከሳሽ

ጀማል ከድር ሳኒ አማርኛ ትሰማለህ ጥፋተኛ ነህ

አደለሁም

አደለህም 29ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

ራህማ መሀመድ አብዱረህማን ጥፋተኛ ነሽ ራህማ አማርኛ ትሰሚያለሽ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት አስመዝግባለች

ሰሚራ ሙሜ አብዱላሂ ሰሚራ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም ትሰሚያለሽ አማርኛ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት አስመዝግባለች

ጫልቱ ኢብራሂም አብዱልቀድር ጥፋተኛ ነሽ ጫልቱ አይደለሁም በማለት አስመዝግባለች 32ኛ ተከሳሽ

አብዲ ሀጂ ሙሳ መሀመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ተቀመጥ

305

ጀማል ከዲር አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ ትሰማለህ በደንብ ጠይቀው

አላጠፋሁም

እሺ 34ኛ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

አዱኛ መሀመድ ጅብሮ ወይም ዱንኛ ጠይቃት ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም

አላጠፋሁም

ዱርሲቱ አብደላ አህመድ ጥፋተኛ ነሽ አይደለሽም ጥፋተኛ አይደለሁም ብላለች

አብዲ በሽር ኡስማኤል ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ በደንብ ትሰማለህ አይደል

እሺ ኮከብ መሀመድ ዩሱፍ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ሚካኤል አብዱላሂ መሀመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ሚካኤል ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

አህመድ ሼክ ዩሱፍ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ በደንብ ትሰማለህ ተቀመጥ

ሳላይ አብደላ ሙመድ አማርኛ ትሰማለህ እስቲ ጠይቀው ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አላጠፋሁም

መሀመድ ሀጂ ኢብራሂም አብዱላ አማርኛ ትሰማለህ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም እሺ አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተመዝግቦለታል

አህመድ ኡስማኤል መተኩ አማርኛ ይሰማሉ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው

አጥፍቼ አላውቅም አላምንም

እሺ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተመዝግቧል

ሀጂ ጣሃ ሀሰን ጉሌድ ጥፋተኛ ነህ አስቼ በሶሮምኛ ጠይቀው

ጥፋተኛ አይደለሁም

በማለት ተመዝግቧል ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል

306

ዩሱፍ ጨሎ አህመድ አማርኛ ትችላለህ

አዎ

ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አይደለሁም

እሺ ተቀመጥ

ሙክታር አብዱልጀሊል አህመድ ጠይቀው ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም

አሊ አብደሌ ኡስማን ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም

እሺ 48ኛ ተከሳሽ ዛሬ ስላልቀረበች የእምነት ክህደት ቃል አልተመዘገበም

መሀመድ ኡመሬ ሙመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም

አማርኛ ትችላለህ በደንብ አሁን የተባለው ገብቶሃል እሺ ተቀመጥ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተመዝግቧል

ጃፈር ኡመር አብዱሌ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ጠይቀው በኦሮምኛ

አላጠፋሁም አፈጸምኩም ድርጊቱን

አላጠፋሁም በሚል ተመዝግቧል

ዩሱፍ ዳኦድ ዩሱፍ ጠይቀው ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

አደለሁም ብሏል

307

ጀማል አደም ኡስማን 52ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም ጀማል

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል 52ኛ ተከሳሽ

53ኛ ተከሳሽ በከር ቃዚም ካዬ በከር ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው አማርኛ ትችላለህ በደንብ እሺ ተቀመጥ ጥፋተኛ አይደለሁም በሚል ተመዝግቧል

አህመድ ነጃሽ ሼክ አብዱልሃሚድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ጀማል ሁሴን ሙሳ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ጥፋተኛ አይደለሁም ድርጊቱን አልፈጸምኩም

ከድር አደም ጠደቻ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አልፈጸምኩም ድርጊቱን ጥፋተኛ አይደለሁም

ሼክ ከድር ቱራ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም በለው

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ጥፋተኛ አይደለሁም በሚል ተመዝግቧል

ኡመር መሀመድ ማሙድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ሸኪብ ቱኬ ሀሰን ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ምንም የማምነው የለም ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

መሀመድ አሊ ሁሴን ወይም መሀመድ ኡዳ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

እዚሁ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

308

መሀመድ አንጀባ አብዱላ ወይም ፋልመታ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

አድናን ጉሼ አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

እዚሁ ነው የሰማሁት

አህመድ ኑር አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

እዚሁ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

ሰኢድ አደም አሊ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም

ከሊፍ መሀመድ ሼክ ሰኢድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

እዚሁ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

ኢብራሂም አብዱላ ዋሪዬ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

አላውቀውም ጥፋተኛ አይደለሁም

አብደላ መሀመድ ሰኢድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

ወደ ዞን ተጠርተሃል ተብዬ ነው የመጣሁት እንጂ ጥፋቱን እዚህ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

ሀሰን መሀመድ አህመድ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

እዚህ ነው የሰማሁት ጥፋተኛ አይደለሁም

መሀመድ አብዶ አህመድ 70ኛ ተሸኸ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ በደንብ ትሰማለህ እሺ ቁጭ በል

ኑሬ ኡስማን ጃሎ ወይም ቢቲ ጅሎ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

309

በቂም ነው የታሰርኩት ጉዳዩንም አላውቀውም ጥፋተኛም አይደለሁም

ጫላ ሙክታር ሙሜ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም አማርኛ ትሰማለህ በደንብ እሺ ቁጭ በል

አብዶሽ ሙሜ ጁሞ ወይም ሻሞ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም

በሀሰን ነው የቀመጠብኝ ጥፋተኛ አይደለሁም

48ኛ ተከሳሽ ባለመቅረቧ 33ኛ ተከሳሽ ደግሞ በብይን ከክሱ በመሰናበቱ ከነዚህ ውጪ ያሉ ተከሳሾች በሙሉ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ተጠይቀው ጥፋተኞች አይደለንም ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ለፍ/ቤቱ አረጋግጠዋል ዐ/ህግ

እንደ ክስ አቀራረባችን የሚያስረዱልን ማስረጃዎች እናቀርባለን ግን ለፍ/ቤቱ አጀንዳ አያያዝ እንዲያመችልን ከግንቦት 24 ለአንድ ወር በአጠቃላይ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች እኔ እና አቶ ዝማም ብቻ ስንቀር ሁላችንም ወደ አዲስ አበባ ነው የመጀመሪያ ደረጃም የከፍተኛ ዐ/ህጎችም ይዜዳሉ ለቢፒአር ሲባል በአገር ሁሉ ደረጃ ነው የተደረገው ስለዚህ እኔ ብቻዬን ነኝ ይዜንን ግምት ውስጥ አስገብቶ በምናቀርበው የምስክሮች አቀራረብ ግምት ወስዶ ከአንድ ወር በኋላ እንዲያቀርብልኝ ብቻዬን ነኝ ጠቅላላውንም ችሎቶች የከሰዓቱንም የጠዋቱንም የምሸፍነው እኔ ብቻ ነኝ ማንም የለም ለዚህ ሁሉ ተከሳሽም ብቻዬን መቆም ያዳግተኛል እና ክቡር ፍ/ቤቱ እንዲያቅልኝ ከግንቦት 24 ጀምሮ ይዜዳሉ

ተከላካይ ጠበቃ የምትሉት አለ አስመዝግቡ

እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እነዚህ ሰዎች አንደኛ የዋስ መብት ተከልክለዋል

አንዱ ይቅርታ እስከዛ አስተርጓሚ ቁጭ በሉ እሺ ቀጥሉ

የዋስ መብት ተከልክለው በእስር ቤት ያሉ ናቸው ግማሾቹ አዛውንት ናቸው ግማሾቹ ሴቶች ናቸው ይዜንን ከግምት ውስጥ አስገብቶ የተከበረው ፍ/ቤት የምስክሩን መስማት ሁኔታ በአፋጣኝ ይይልን እና ዐ/ህጉ ከሌሎች ክሶች ላይ የተለየ ስለሆነ እንደምንም አጣርቶ ምስክሮቻቸውን አቅርቦ ማሰማት ስለሚችሉ ምስክሮቹ የሚሰሙበትን ጊዜ ቀጠሮ እሳቸው እንደሚሉት ሳይሆን አጠር ባለ በ15 እና በ10 ቀን ውስጥ እየተቀጠርን ይሰማላቸው ነው እኔ የማመለክተው::

3/0

በሌላ በኩል ማረሚያ ቤት ይሄ ፍ/ቤት ፈተና እንዲፈተኑ የፈቀደላቸው ሁለት ተከሳሾች አሉ 22ኛ እና መሀመድ ኡመር መሀመድ፣ ፋጤ አሚን፣ መሀመድ ኡመር ሙመድ አንተ ነህ ስንተኛ ተከሳሽ ነህ 29ኛ ስምህ ሌላ ነው እንዴ 29ኛ መሀመድ ኡመሬ ሙመድ ማመልከቻህን የጻፍከው መሀመድ ኡመር ሙመድ ብለህ ነው ዐ/ህግ ማረሚያ ቤት ፈተና እንዲፈተኑ አልተደረገም አይደለ ለምንድን ነው ያልተደረገው

የፋጤስ

የሷ ደግሞ ጋራሙለታ ----------

ፋጤ አማርኛ ትችያለሽ

ክፍያም እኔ እፈጽማለሁ ብዬ ጋራሙለታ አና ጉልላ ጉልላ የሚባል ቦታ ነው ጎሎኦዳ የሚባል ወረዳ ነው እዛ ክፍያም እኔ እከፍላለሁ ብዬ ጠይቄ ነበር

መቼ ነው ፈተናው

ማትሪክ ነበረ ዛሬ ተጀምሯል ትናንት ተጀምሯል ሁለት አጃቢ አቅም የለኝም ብዬ ብጠይቃቸውና አንድ አጃቢ ይበቃኛል ብዬ ብል ማረሚያ ቤቱ ስላልተመቸው ይሆናል አልተቀበሉኝም

ለምን አንተ እነሱ ሁለት ሲሉ አንተ አንድ አልክ

---------- ለመክፈል አልችልም የልጆች አባት ነኝ

ቀጣዩ የማስረጃ የሚሰማበትን አጀንዳ መያዝ ነው ይሄን በተመለከተ በዐ/ህግ በኩል ስራ ሰራተኞቹ በሙሉ ወደ አዲስ አበባ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ፍ/ቤቱ በተጠቀሰው በአንድ ወር እና ወይም ከዛም በላይ በሆነ ጊዜ ዐ/ህጎች ሊገኙ ስለማይችሉ አጀንዳው ከዚህ አንጻር ታይቶ ይያዝልን የሚል ጥያቄ ቀርቧል በሌላ በኩል በተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ በኩል ተከሳሾች ዋስትና መብታቸው ተነፍጎ በማረሚያ ቤት ያሉ በመሆናቸው ማስረጃ መስማቱ ሂደት በአጭር ቀጠሮ እየተሰማ እንዲቀጥል ለፍ/ቤቱ አሳስበዋል ፍ/ቤቱ እነዚህን የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ትዕዛዝ ሰጥቷል።

311

ት ዕ ዛ ዝ

ዐ/ህግ ተከሳሾች የዋስትና መብታቸው ዛሬ ተነፍጎ ከአሁን በኋላ ይህ ፍ/ቤት ጉዳዩን ሰምቶ ሌላ ተለዋጭ እስክልተሰጠ ድረስ በማረሚያ ቤት የሚቆዩ መሆናቸው እየታወቀ በሌላ በኩል የክሱ ባለቤትና የጉዳዩ ባለቤት መሆኑ እርግጥ በሆነበት ሁኔታ በቀጣይ ማስረጃ አሰማም ሂደት መስሪያ ቤቱ ይንቀሳቀሳል የለም በሚል የቀረበው ምክንያት ለዚህ ችሎት ተቀባይነት ያለው ሆኖም አልተገኘም አግባብነትም ያለው ሆኖ አልተገኘም ስለዚህ ዐ/ህግ ያቀረበውን ክስ የማስረዳት ግዴታ ሸክሙ በሱ ላይ መሆኑን ተረድቶ ፍ/ቤቱ በሚሰጠው አጀንዳ በዚህ ጉዳይ ላይ አሉኝ የሚለውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ በድጋሚ ያዛል በዚህ መሰረት አጀንዳው የሚያዝ ነው የሚሆነው በሌላ በኩል ማረሚያ ቤት ባለፈው ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ሁለት ተከሳሾችን በተመለከተ መሀመድ ኡመር ሙመድ እና ፋጤ አሚን በተመለከተ ይህ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል ትዕዛዙ አለመፈጸሙን በማረሚያ ቤት የተወከሉት አብራርተዋል ሆኖም ፍ/ቤቱ ይህ ትዕዛዝ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ያልተከበረበትን ምክንያት በተመለከተ ማረሚያ ቤቱ በግልጽ ማብራሪያ በጽሁፍ እንዲያቀርብ ማዘዝ እንዳለበት ገልጸናል ይኸው እንዲፈጸም በጥብቅ ታዟል ቀጣይ ትዕዛዝ የሚቀጥል ነው የሚሆነው በሌላ በኩል በአስተርጓሚ በኩል ተከሳሾች ዛሬ የዋስትና መብታችሁ ተነፍጓል በዚህ ላይ ቅሬታ ካላችሁ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ አንድ መብት አላችሁ በማለት ለሁሉም ንገሯቸው ከዚህ በኋላ የሚቀጥለው የሚሆነው የአጀንዳ ሁኔታ ነው ፍ/ቤቱ ከፍ ሲል እንደተመለከተው በትዕዛዝ ወቅት ይዜ መዝገብ ሰፊ ተከሳሾች ያሉበት ነው በሌላ በኩል ደግሞ የዋስ መብት መነፈጉ ከግምት መግባት አለበት ስለዚህ የሚቀጥለውን የክርክር አመራር ከዚሁ አንጻር ፍ/ቤቱ ለሌሎች መዛግብቶች በርካታ መዛግብቶች ያሉትን አጀንዳዎች በመሰረዝና በማጣበብ ይህን ጉዳይ መስማት እንዳለበት ያምናል ስለሆነም አጀንዳው በዚህ መልክ የሚያዝ ነው የሚሆነው ስለዚህ የፍ/ቤቱ የመጀመሪያ አጀንዳ በሌሎች መደበኛ ችሎቶች የተያዙትን አጀንዳ በመፋቅ ሰኔ 15 እና 16 በሁለቱም ቀን በተከታታይ በዚህ መዝገብ ላይ የሚቀርቡትን የዐ/ህግ ማስረጃዎች ከቀረቡ ችሎቱ ይሰማል በቀጣይ የሚያዙት አጀንዳዎችም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ በአጭር ቀጠሮዎች የሚያዙ መሆኑን ዐ/ህግ ከዚሁ እንዲያስተወሉ ፍ/ቤቱ ያሳስባል በዚህ ምክንያት በዚሁ ምንክያት ሰኔ 15 እና 16 የዐ/ህግ ---------- ሰ/መስማት ሂደት ፍ/ቤቱ ---------- ይዜንኑ ለተከሳሾቹ ንገሯቸው በአጭሩ የእናንተ ማስረጃ የሚሰማው ሰኔ 15 እና 16 በዐ/ህግ በኩል የቀረበውን የሰው ሃይል ያንሳል ቀጠሮ እንዲረዝም በሚል

3/2

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 11/7/2001

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ ተሰይመናል

ከሳሽ - ዐ/ህግ አቶ ፌይሰል አብዲ ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ

ማረሚያ ቤት ሁሉም ቀርበዋል

አዎ

ስንት ናቸው የቀረቡት ከእናንተ ጋ 70 የታመመው አልቀረበም 69 ሰው ቀርቧል በእናንተ በኩል ማን ነው የቀረበው ጠበቆች አስመዝግቡ መቅረጫውን ተጠቀሙ እንጂ

ከተከላካይ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ ቀርቤአለሁ የ37ኛ፣ 38ኛ እና 23ኛ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ

መንግስት ተከላካይ ጠበቃ የመደበላቸው ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ አድማሱ መለሰ ቀርቤአለሁ

ፋጤ ባለፈው ታመሽ ነበር ተቀመጡ ዘሀራ አብዶሽ አልመጣችም ሰሚራ ሙሜ ምን ሆና ነው እስቲ አስተርጓሚ የለም እስቲ ወደ ውጪ አውጧት እስቲ ወደ ውጪ ስነስርዓት ያዙ በላቸው አስወጣት እሷን ብቻ አስወጣት ስነስርዓት አስከብሩ ፖሊስ ማን ነው እስረኞችን ያቀርብ የነበረው ከማረሚያ ቤት ውጪ እስረኞችን የሚያቀርበው ፖሊስ ኮሚሽን እስቲ ማን ነው ስለ ሰሚራ ሙሜ የምታውቁት ነገር አለ

የምናውቀው ነገር የለም

ምንም ነገር የለም

313

ማስረጃውን በሚቀጥለው ይዛችሁ ቅረቡ ጥሩ እሺ ይቀመጡ ጀና መሀመድ አዳስ፣ አሁን የወጣችው ነች እስቲ እዩአት አሁን የወጣችዋ ነች እሺ መዝገቡ የተቀጠረው የዐ/ህግ ምስክሮች በቁጥር 40 የሚሆኑ መቅረባቸውን በመነገሩ እና በሰኔ 29 የተያዘው አጀንዳ በስብሰባ ምክንያት ችሎቱ መሰየም ስላልቻለ ሆኖም ምስክሮች መቅረባቸውን ዐ/ህግ በመግለጹ እና ከርቀት የመጡ የተሰበሰቡ ምስክሮች በመሆናቸው ምክንያት እነዚሁ ምስክሮች ማቅረብ የሚችሉትን ያህል ለመስማት ከተቻለ አጭር ቀጠሮ አድርጎ መስማት በማስፈለጉ ነው የዛሬ ቀጠሮ የተሰየመው እና የተሰጠው እና ችሎቱ የተሰየመው ስለዚህ ከዚህ መጥተዋል ከተባሉት 40 ምስክሮች ከተለያዩ አካባቢዎች ከተሰበሰቡት ውስጥ መስማት የሚቻለውን ያህል ተለይተው እንዲቀርቡ ለዛሬ አጀንዳ ተይዟል በዚሁ ምክንያት ዐ/ህግ ምስክሮች ቀርበዋል

የተከበረው ፍ/ቤት ----------

ተጠቀሙ መቅረጫውን

አሁን ጠዋት ነው የሚነገረን እዚህ እንደመጣን እኛ እንዲፋጠንላቸው በአስቸኳይ መርጠን ዘጠኞቹን ትናንትም እዚህ ነበሩ እዚህ አካባቢ ነበሩ ምስክሮቹ በእኛው ገንዘብ አዋጥተን እዚህ አስቀምጠናቸው ነበር እንዲፋጠን አሁን ጠዋት ስንገባ ይኸው እናንተ እንደመጣችሁ የሉም ተባለ ይሄንን ነው የማውቀው አሁን ጠዋት የት አለ አበበ ያው እስቲ አስረዳልን አንተም ለፍ/ቤቱ ያዘው አስቀርቡና ተናገሩ

ምንድን ነው ምስክሮች የሉም ነው የምትሉት

አዎ

ለምንድን ነው የሌሉት

እኔም አላወኩም እኔም ትናንት እዚህ ነበሩ የተከበረው ፍ/ቤት ትናንትም እዚህ ነበሩ

40 ምስክሮች አለ ብላችሁ

ነበር 40ዎቹ መጥተው ከእኛ መካከል ከፍ/ቤትም ጋር ተነጋግረን ከርቀት የመጡትን 9ዎቹን አስቀርተን የዐ/ህግ ሰራተኞችም ገንዘብ አዋጥተንላቸው ቶሎ እንዲፋጠን ገንዘብም ሰጥተናቸው

314

ዛሬ ስንመጣ የሉም እኔ ራሴ አሁን ነው እዚህ ስገባ የሰማሁት አሁን አሁን አዎ አሁን ነው እንግዲህ እኛ ፖሊስ ጋ ይቀመጣሉ ብለን ነበር ያሰብነው ገንዘብም እያንዳንዱ ሰራተኛ ከየኦፊስ አዋጥቶ ሰጥተናቸው አሁን ስንመጣ የሉም

እስቲ ፖሊስ ኮሚሽን በኩል

ክቡር ፍ/ቤት

ማነህ አስመዝግብ ስምህን

ረዳት ሳጅን ፉአድ መሀመድ እባላለሁ

ከየት ነው

ከፖሊስ ኮሚሽን

ምንድን ነው ስራው

ኮፕሬሽናል ክትትል ሃላፊ ነኝ

ስለምስክሮቹ ታውቃለህ

አዎ ስለምስክሮቹ

ስንት ምስክር ነበር የመጣው

ቀደም ሲል ፍ/ቤት እና ዐ/ህግ በሰጠን ትዕዛዝ የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመቀናጀት ፋክስ አድርገንላቸው ከዚህ 48 ሰዎችን ይዞልን መጥቷል እዚህ ድረስ በቀጠሮው ቀን ማለት ነው ከዛ የዐ/ህጎችን አነጋገርናቸው እና እነዚሁልህ ሰዎቹ መጥተዋል ስለዚህ አበል ክፈሏቸው ከእንደገና የሚቆዩበትን ሁኔታ ፍጠሩላቸው ብለን ገልጸንላቸዋል እስከ ሃላፊው ድረስ የዛን ቀን ምንም የተመቻቸ ነገር የለም ሲባል እኛ ፖሊስ ኮሚሽኑ ወስዶ ማረፊያ ሁሉ ሰጥቷቸው የአንድ ቀን ሙሉ ምግባቸውን ችሎ አሳደራቸው በነጋታው እንሰማለን ብሎ በነጋታውም ያንኑ ያህል ይዘን እዚህ ቀርበናል ከዛ በኋላ ዐ/ህግ ምንም አለ ብሎ የለንም ለጊዜው ከአዲስ አበባዎች ጋር ተነጋግረን ነው የምንከፍለው ብሎ ባልሆነ ምክንያት ሰዎቹ ደግሞ ከአገራቸው ከወጡ 9ነኛ ቀናቸው ነበር የዛን ቀን ከባሌ ወንዝ አካባቢ ነው የመጡት ኦሮሚያ ባሌ ወንዝ አካባቢ ነው የመጡት ስለዚህ

315

እዚህ ልንቆይ አንችልም ባሉት መሰረት እኛም ለዐ/ህጎቹ አስረክበናል ከዛ በኋላ ወደ አገራቸው ሄደዋል እንሄዳለን ብለው ለእነሱም ተናግረው ነው የሄዱት ከዛ ውስጥ 9 ሰው አስቀርተዋል ከ9ኙም ውስጥ ከእንደገና በ3 ተብለናል እኛ እስከዛ ድረስ የምንቀመጥበት በረሃብ የምንሞትበት ነገር የለም ብለው ሄደዋል ወደ ሀገራቸው ቀጠሮውንም ሳያውቁ ማለት ነው

መቼ ነው የሄዱት

ግማሹ በ30 ነው የሄደው ግማሹ ደግሞ በ1 ነው የሄደው ከዚህ 9ኞቹ በ1 ነው የሄዱት እነኛ በ30 ነው የሄዱት አብዛኛዎቹ በ30 ነው በ30ዎቹ ለዐ/ህጎች ላይ እንደውም ቀጠሮ ይነገረን በቃ በራሳችን ጊዜ እንመጣለን ሲባሉ ቀጠሮ አልታወቀም ገና ተብሎ ነው የተሸኙት እነሱም ቀጠሮ አያውቁም የሄዱትም

የዛሬ ቀጠሮንስ አያውቁም

አያውቁም

9ኞቹ ያውቃሉ

9ኞቹ ብቻ ነው የሚያውቁት

ያስቀረናቸው 9ኞቹ መርጠን ከነሱ መሀል 9ኞቹ ያውቃሉ

እነሱስ እንዴት ሊሄዱ ቻሉ የ9ኞቹ ጉዳይ እሱ ላይስ የምታውቁት ነገር ስለሱ

የ9ኙ ጉዳይ የዛኑ ቀን እዚህ በተቀጠረ ቀን እኛ አነጋግረናቸዋል ውጪ ምንም 9ኛ ቀናችን ነው ከአገራችን ከወጣን በረሃብ ገሎናል እኛ ምንም የምንበላው እና የምንጠጣው ነገር የለም እዚህ የምናድርበት የለም ስለዚህ አንቀመጥም እኛ ወደ ሀገራችን እንሄዳለን አሉ ማስገደድ ስለማንችል እኛም ዝም አልናቸው ሄደዋል እነሱ

ጥሩ የዚህ መዝገብ ቀጠሮ ለሰኔ 29 ነው ዐ/ህግ 9 ቀን የሚባለው ረጅም ጊዜ ነው 9 ቀን የሚፈጅ ጊዜ ቆይታ ለምን አደረጉ ከርቀት ነው እንዴ የመጡት

የ9 ቀኑ ቆይታ ሰዎቹ እዚህ አይደለም ሀገራቸው እዚህ አካባቢ አይደለም ወደ በጣም ይርቃል የ5 ቀን ነው መንገድ ነው ከዚህ አብዛኛው ደግሞ ተበታትኖ ነው በምስራቅ እና በምዕራብ ውስጥ ነው ያሉት በምስራቅ ኦሮሚያ እና በምዕራብ ኦሮሚያ ነው ያሉት እነዚህ ምስክሮቹ

3/6

በጣም ሩቅ ሀገር ናቸው የኦሮሚያ ፖሊሶች ናቸው ከእኛ ጋር ተባብረው እስከዛ ድረስ ሄደው ለቅመዋቸው እ አንድ ቦታ እያሳረፉአቸው ለቅመው አንድ ቦታ ለቅመው አንድ ቦታ ከየቦታው ሰብስበዋቸው ነው እነዚህን ሰዎች እዚህ ድረስ ያመጧቸው

ጥሩ ዐ/ህግ የምታመለክቱት ነገር አለ

ያው ተመሳሳይ ነው ቅድም ባልነው መሰረት እንደገና ወይ አንድ ቀጠሮ አሁን ይሄ ሁሉ አንዱ ችግር ያን ቀን መብራት አለመኖሩ ነው እና ጠቅላይ ፍ/ቤት እዚህ ችሎቱን በመያዙ ነው እንጂ 40ውንም አቅርበን ነበር ያው የፈረሙበትም አለ ስለዚህ እንደገና ይጠሩልኝ ከማለት ውጪ ምን አደርጋለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ከኪሳችን ነው ገንዘብ አዋጥተንም የሰጠናቸው

እሺ ይበቃል የ48ኛ፣ የ22ኛ እና የ31ኛ የ23ኛ፣ የ37ኛ እና የ38ኛ ተከሳሽ ጠበቃ አቶ ኢብራሂም መሀመድ የምትሉት ካለ

አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ቀደም ሲልም እንደሚታወቀው የለክቡር ፍ/ቤቱ ጉዳዩ ተለያይቶ ተነጣጥሎ እንዲታይልንም አመልክተን ነበር አሁንም የሚታየው ሁኔታ ያለው ዐ/ህግ ምስክሮቹን ለማቅረብ ከተለያየ ርቀት ቦታ የሚሰበስባቸው መሆኑን እና በተለያየ ቦታ እየተንጠባጠቡ የሚመጡ አይነት መሆናቸውን ነው ከችሎቱ ሂደት የምንረዳው ስለዚህ በተቻለ መጠን የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ክስ ተነጣጥሎ እንዲታይ አሁንም ያለው ሂደት አስቸጋሪ ከሆነ ፍ/ቤቱ ያለውን ጉዳይ ተመልሶ ወደ ኋላ የሚያይበት ምክንያት ስለሌለ አሁንም ዐ/ህግ ለራሱ ምስክሮች በሚያመች መልኩ አንደኛ ረዘም ያለ ቀጠሮ ሰጥቶ ላሉት ደግሞ ክሱን ነጣጥሎ ሊያቀርብ በሚችለው መልኩ ምስክሮቹን ቢያቀርም እና ፍ/ቤቱ ደግሞ እስከዛ ላለው ሁኔታ መፍትሄ ቢሰጥልን ወይ በዋስትና የሚቆዩበትን መንገድ ቢፈልግልን የተሻለ ይመስለኛል የተከበረው ፍ/ቤት።

ለሌሎች ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ አቶ አድማሱ

ይኸው ነው ከሳቸው የተለየ ነገር የለንም ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች አሁን ይሄ የምስክሮቹ አቀራረብ ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ ነው ሲታይ አስቸጋሪ ነው እና ስለዚህ ቢያንስ ቢያንስ የተከበረው ፍ/ቤት እኔ አንድ የእኔ ደንበኞች ካሉት ውስጥ የዚህ ከተማ ውስጥ ያሉ ሰዎች አሉ እዚህ ከተማ ተይዘው ምስክሮቻቸውም እዚህ ከተማ ውስጥ ያሉ ቢያንስ የነዛ እንኳን ቀርቦ ሊሰማ ይገባል እና የተቀረው ግን እሳቸው እንዳሉት የክሱ መነጣጠል ነው ወሳኝነቱ እንጂ

317

አለዛ ሌላ መፍትሄ የሚኖረው አይመስልም ሲታይ ምክንያቱም አንዱ አንዱን እየጎተተው ነው አሁን እዚህ ከተማ ውስጥ አሁን ያሉት ቀርበው መሰማት የሚችሉ ናቸው

አበቃችሁ

አዎ

ማረሚያ ቤት በቅድሚያ ጠቅላላ እናንተ ጋ ያሉት 69 ናቸው እንዴ

አንዷ በዋስ የወጣች ነች

በፊት

አዎ

አብረው ሁሉም በዋስ የወጡ ጊዜ ማለት ነው

አዎ

47ኛው እና 48ኛው ተከሳሾች ላይ ማሻሻያ ክስ ለማቅረብ እወዳለሁ

ምንድን ነው

ባለፈው

አስመዝግቡ

በወንጀለኛ መቅጫ ህግ 119 መሰረት በተከሳሾች እና በዐ/ህግ መካከል በነበረው ክርክር በ47ኛው እና በ48ኛው ተከሳሾች ላቀረብነው ክስ ግድፈት ስላለበት ከውሳኔ በፊት አሻሽለን

ምንድን ነው እሱ አመልክቱ ምንድን ነው ግድፈቱ የምታስተካክሉት

በወንድ ስም ነበር ክሱን ያቀረበው በ48ኛዋ ተከሳሽ ላይ ስለዚህ አሻሽለን አቅርበናል ከውሳኔ በፊት

በ48ኛ

እና በ47ኛው ላይ በሁለቱም ላይ እና የተሻሻለውን

318

እና ክሱን ነው የምታሻሽሉት

28ኛ ክስ

28ኛ ክስ

አዎ

እሱን ለማሻሻል ነው የምታመለክቱት

አዎ

እሺ በጠበቃ በኩል የምታነሱት ነገር አለ እዚህ ላይ አቶ አድማሱ የ48ኛ ተከሳሽ እና የ47ኛ ተከሳሽ ጠበቃ

በዚህ በችሎት ክርክር ተካሂዶ ፍ/ቤቱ ለብይን ነው የቀጠረው ጉዳዩን እኛ የክስ መሻሻል ብቻ አይደለም የጠየቅነው የስራን ድርሻ ጭምር ነው አብረን ጠይቀን የነበረ ስለሆነ ብይኑ ከተሰጠ በኋላ እነሱ ክሳቸውን ቢያሻሽሉት ልንፈቅድላቸው ችግር የለውም ግን ይሄ የእኛ ጥያቄ በዛን ጊዜ የነበረው የእኛ ጥያቄ የክሱ እና አንቀጹ አይስማማም ተከሳሿ በወንድ ጾታ ወይም በሴት ጾታ የመነሳት ጉዳይ አይደለም እኛ የስራ ድርሻን በሚመለከት ነው እኛ ክሱ ሊሻሻል ይገባል

ጥሩ እናስታውሳለን እሱን እሱን እናስታውሳለን

እና ለብይን የተቀጠረ ስለሆነ

መቼ ማመልከቻው ----------

አዎ ስለ ጾታው ቢያሻሽሉት ችግር የለብንም

በመዝገቡ ላይ አሁን መዝገቡ ከደረሰበት ደረጃ አንጻር የሚከተለውን ብይን ሰጥቷል በዚህ መዝገብ ላይ ይህ መዝገብ ቀደም ሲል በመግቢያ ላይ እንደተነገረው እንደተገለጸው ከችሎቱ በተቻለ መጠን የሚቀርበው የዐ/ህግ ምስክሮችን ለመስማት ነው በዚሁ ምክንያትም በአካባቢው የተሰበሰቡ ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን እና ከድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን ጋር ከፍተኛ ትብብር ተደርጎ ምስክሮች ከርቀትም ከቅርብም ተሰብስበው መገኘታቸው እና መቅረባቸውን ፍ/ቤቱ ተረድቷል ይህ አይነቱ ሁኔታ በፍ/ቤቱ ዋጋ የሚሰጠው እና መልካም በምስክር አቀራረብ ረገድ

319

ጥሩ ሁኔታ ነው በሌላ በኩል ግን እነዚህ ምስክሮች ዋናው ነገር በፍ/ቤት ቀርበው ተከሳሾች የተከሰሱበት ጉዳይ ስለሆነ መመስከራቸው ማረጋገጥ እና ለዚህ እንዲበቁ ማድረግም ይጠበቃል ይሄ ደግሞ በግልጽ እንደሚታወቀው የዐ/ህግ ግዴታ ነው በግራ ቀኞችሁ በዐ/ህግም ሆነ በድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን ተወካዮች እንደተነገረው እነዚህ ምስክሮች ወደ ድሬዳዋ ከመጡ በኋላ በቀለብ ምክንያት ሳይመቻቸው እንደቀረ ማረጋገጥ ተችሏል ይህ ደግሞ በዋናው የዐ/ህግ መስሪያ ቤት አበላቸውን ችሎ ምስክሮቹ እስኪመሰክሩ ድረስ በተመቻቸ ሁኔታ እንዲቆዩ ማድረግ ያለበትን ሃላፊነት አለመወጣቱን ያሳያል ስለዚህ ፍ/ቤቱ በዚህ መልክ የሚፈጸም የተፈጸመውን ስህተት ወደፊት የማይደገም መሆኑን ማረጋገጥ ስለሚገባ ዐ/ህግ በዚህ በኩል ተገቢውን ጥንቃቄ እና እርምጃ እንድትወስዱ ችሎቱ በጥብቅ ያዛል በሌላ በኩል በ48ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ባላፈው ችሎት የተነሳ መቃወሚያ አለ ክሱ ከተነበበ በኋላ መቃወሚያው 48ኛ ተከሳሽን አንደኛ የጸታን የሚመለከት ነው ሁለተኛ ደግሞ በክሱ የተመለከተው የስራ ድርሻ አይመለከታትም በሃላፊነት አያስጠይቃትም የሚል መቃወሚያ ነው የተነሳው እነዚህ ሁለቱም ነገሮች ቢሆኑ በክርክሩ ሂደት በዋናው የማስረጃ መስማት ሂደት የሚለይ ነጥሮ የሚወጣ ፍሬ ነገር ስለሆነ ከወዲሁ ክስ መቃወሚያ ሆኖ ክሱን ከወዲሁ የሚጎትት የሚያስቀር ሆኖ ፍ/ቤቱ ስላላገኘው መቃወሚያው ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም በሌላ በኩል በ48ኛ እና 47ኛ ተከሳሽን በተመለከተ በዐ/ህግ በኩል ክስ ለማሻሻል የቀረበ አቤቱታ አለ ይህ አቤቱታ በተመለከተም ተቃውሞ አልተነሳበትም ፍ/ቤቱም ለፍትህ አሰጣጥ ቢሻሻል አግባብ ነው ብሎ ስላመነ ክሱ እንዲሻሻል ተፈቅዶላችኋል በነዚህ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ አዟል በሶስተኛ ነጥብ ላይ በማስረጃ በምስክር አቀራረብ በተመለከተ በርካታ ምስክሮች መሆናቸውን ፍ/ቤቱ ተረድቷል ከርቀትም የሚቀርቡ መሆናቸውን እንደዚሁ ማረጋገጥ ተችሏል ስለዚህ ቀጣይ የምስክሮች አቀራረብ አሁንም የተከሳሾችን ቶሎ አለመሰማት መብት የማያጣብብ መሆኑን ማረጋገጥ ስለሚገባ ከእንግዲህ በኋላ የሚቀርቡት ምስክሮች ሁሉ መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እና ፍ/ቤትም መሰማትም የሚችሉ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል ለዚህ ደግሞ ሁለት መሰረታዊ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ያስፈልጋል አንደኛ እየተለዩ የሚቀርቡት ምስክሮች የቅርብም የሩቅም በዐ/ህግ መስሪያ ቤት በኩል በቂው አበል እየተቆረጠላቸው ድሬዳዋ እስኪሰሙ ድረስ በፍ/ቤት መቆየት የሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት ይሄን ከፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመተባበር እንዲፈጸሙ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሌላው ከመብራት ስርጭት ጋር የተያያዘ ነው በተቻለ አቅም ከፍ/ቤቱ ጋር በመነጋገር የመብራት ስርጭት ባለበት ጊዜ እነዚህ ምስክሮች ቶሎ የሚሰሙበት የአጀንዳ መጣበብም ቢኖር በቅድሚያ

320

ለዚሁ አጀንዳ በመስጠት ምስክሮች የሚሰሙበትን ሁኔታ ፍ/ቤቱ የሚያመቻች መሆኑን ግንዛቤ በመውሰድ በዚሁ መልክ የምትለዩአቸው እና የምታቀርቧቸውን ምስክሮች አስቀድማችሁ ለችሎት እንድታሳውቁ እና አቅርባችሁም እንድታሰሙ ፍ/ቤቱ ያዛል በዚህ ረገድ የሚቀርቡት ምስክሮች በርካታ ስለሆኑ በየአጀንዳው መሰማት የሚችለውን ያህል መሰማት ስላለበት እና የመንግስትም በጀት ያለ አግባብ ከዐ/ህግ በኩል መከፈልም ስለሌለበት ተመጣጣኝ መሆን ስለሚገባው በየአጀንዳው በሚሰጠው አጀንዳ አስር አስር ምስክሮቻችሁን እያቀረባችሁ እንድታሰሙ ፍ/ቤቱ አዟል በዚህ ሁኔታ ላይ ምስክሮች በሚቀርቡበት ጊዜ በተለይ በተከሳሾች ጠበቃ በኩል እንደተነሳው በድሬዳዋ አካባቢ የሚገኙ ምስክሮች ወይም በቅርብ የሚገኙ ምስክሮች ካሉ ለአቀራረብ እንደሚመቻችሁ እና ለጉዳያችሁ የሚመች መልክ ማቅረብ ቢቻል የተሻለ ስለሚሆን በዚህ መልክ ምስክሮቻችሁን እያቀረባችሁ እንድታሰሙ ችሎቱ በድጋሚ ያዛል ስለዚህ ምስክሮቹን ለመስማት አሁን በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት የሚቀጥለው አጀንዳ ለሐምሌ 21 ማክሰኞ እለት ይሆናል ሐምሌ 21 አይችሉም ሐምሌ 20

የተከበረው ፍ/ቤት

ሐምሌ 20 አይችሉም

የተከበረው ፍ/ቤት አሁን ከበላይ የመጣልኝ ትዕዛዝ አለ ባጀት በሚለቀቅበት ---------- ለሐምሌ ወር መጨረሻ በጀት የመንግስት ባጀት ሲለቀቅ ለሚኒስቴራችን ለፍትህ ሚንሴቴር በዛ ቀን የመቅረቡ ቀን ይሁንልን ነው ለምን ቢመጡም ገንዘቡ ስላለ እዚህ አመቻችተን እንይዛቸዋለን አሁን ባጀት ስለተዘጋ እኮ ነው ይሄን ሁሉ ችግር የመጣብን ባለፈው ከሚኒስትሩ ጋር ተነጋግረና እንዲህ 40 ሰው ተጉላልቷል ብለን ስነግር ባጀት የለም ተዘግቷል ነው ሰኔ 30 ስለሆነ ስለዚህ አሁን የተከበረው ፍ/ቤት መጨረሻው አካባቢ አድርግልን ሐምሌ መጨረሻ ላይ ያንን ነው አሁን ወረቀት የመጣልን እንደገና ለምን ሌላ ቀጠሮ ይሰጣል ለእነሱ ድሬዳዋና አወዳይ አካባቢ ያሉትን ማቅረብ እንችላለን የእነሱን እነሱ እዚህ አካባቢ ስለሆኑ መቅረብ ይችላሉ::

ቆይ እስቲ ስርዓት

ዐ/ህግ በቅርብ ያሉት የቅርብ ተዘጋጅተዋል አሉ ማለት በከተማ አካባቢ የሚገኙ ክሱ እንዲሁ ከሩቅ አካባቢ የሚመጡ እና ምስክሮቹም ሩቅ የሆኑ አሉ ቢያንስ ዐ/ህግ አሁን ክሱን በቅርብ በከተማ አካባቢ የከሰሳቸውን ተከሳሾች እዚሁ በቅርብ አካባቢ ያለውን ምስክሮች ለይቶ እነዚህን

321

የሚያቀርብበትን ጊዜ ወደ ገጠር ያሉትንም ደግሞ እንደዛው ተከሳሾቹ ራሳቸው ከገጠር አካባቢ የመጡ ናቸው እና እንደዛው ለይቶ ቢያቀርብ እና አሁን አወዳይ አካባቢ ከአለማያ አካባቢ ከዚህ አካባቢ የሚመጡ ተከሳሾችም አሉ ምስክሮችም አሉ እነዚህ የቅርብ የቅርቦቹን አስቀድሞ የሚያሰማበትን መንገድ ቢፈልግና በዛ አይነት ቢያቀርብና ሂደቱም በዛ አይነት መልክ ቢሆን የተከበረው ፍ/ቤት

ጥሩ ይሄን በተመለከተ አሁን እየተያዘ ያለው አጀንዳ አጭር ነው ስለዚህ አጭር አጀንዳ ስለሆነ ከሩቅም ሆነ ከቅርብ የሚቀርቡት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም አጀንዳው አጭር ስለሆነ ማለት ነው ረጅም አጀንዳ ቢሆን በዚህ መልክ ልዩነት አሁን የተባለውን ነገር ከግምት ማስገባት ይጠቅማል ለአሁን ግን አጭር አጀንዳ ፍ/ቤቱ ለመስጠት እየሞከረ ስለሆነ የተባለው ስጋት ብዙ የሚያሳስብ አይሆንም ስለዚህ ወደ አጀንዳ አያያዙ እንሄዳለን በሌላ በኩል ግን ሁለት ነጥቦች ላይ የተነሱትን መድገም ስለማያስፈልግ በሚል እምነት ነው ክሶች እንዲነጣጠሉ የተባለው እና የዋስትና ጥያቄ የተነሳው በብይን የታለፈ ስለሆነ በብይን ታልፎ ያደረ ጉዳይ ስለሆነ በድጋሚ ችሎት የሚመለከተው ስላልሆነ ባለው ሂደት ክርክሩን መቀጠል ነው እስካልተለወጠ ድረስ በበላይ ፍ/ቤት የዚህ ክርክር ሂደት ስለዚህ ይሄንኑ ከግምት በማስገባት አጭር ቀጠሮ ነው ሌላ በዐ/ህግ በኩል የተነሳው የበጀት ጥያቄ ፍ/ቤቱ በትክክለኛው የሚረዳው ነገር ነው የመንግስት ተቋም ነው የበጀት አወጣጥ እና አፈቃቀድ እና የገንዘብ ተፈቅዶ ስራ የሚሰራበት ሁኔታ በአገር አቀፍ የበጀት አጠቃቀማችን ጋር የተያያዘ መሆኑ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው ስለዚህ የቀረበው ማሳሰቢያ እውነትነት አለው ሲፈቀድ ነው አበል የሚጠይቀን ነገር ካለ አበሉን መሸፈን የምንችለው ማመቻቸት የምንችለው የሚለው የአቅም ጥያቄ እውነት ነው ከዚህ በፊትም የተከሰተው ሁኔታ በሌላ መልኩ ማድረግ የሚቻልበት አቅም አይኖርም ከሚል ግምት ፍ/ቤቱ በመነሳት ነው ዞሮ ዞሮ የተጠየቀው ነገር አግባብ ስለሆነ በአንድ ሳምንት ወደፊት አስተላልፈነው ወደ ሐምሌ 27 እናደርገዋለን ምክንያቱም ከ22 በኋላ ይፈቀዳል የሚል በአሰራር የዳበረ ነገር ስላለ ነው ዐ/ህግ ስለዚህ ሐምሌ 27 ይመቻችኋል

ይቻላል

ሐምሌ 27 ምስክሮቻችሁን አቅርቡ እንደተባለው እዚህ አካባቢ ያሉ ከሆነ አበል የማይጠይቃችሁን ለማድረግ ሞክሩ ሌሎችም ካሉ የተሻሻለውንም ክስ አቅርቡ

322

ባለፈው ---------- ከሩቅ ቦታ እዚህ አካባቢ ያሉትን ቶሎ ቶሎ ከፍ/ቤቱ ጋር ከተከላካዮችም ጋር ስነጋገር ነበር

እሺ

አብዲ በሽርን በተመለከተ አሁን ለሐምሌ 4 ይሁን ምረቃ በዓል አለች የምረቃ በዓል ስላለ ያንን በተመለከተ

ሐምሌ 24

ሐምሌ 29 ላይ የምረቃ በዓል ስላለ ምናልባት እንግዲህ ሞት እና ሰርግ በምድር ላይ ለሚኖር ሰው አንድ ቀን ስለሆነ

የምን ምረቃ ነው

የኮሌጅ ምረቃ እሳቸውም የሚመረቁበት ማለት ነው እና ያንን በተመለከተ በአጃቢ ሆኜ እዛች በዓል ላይ እንድገኝ ክቡር ፍ/ቤቱ

ቆይ ቆይ እሺ እናቋርጦት ገብቶናል በ27 ይሄ የፍ/ቤቱ አጀንዳ ነው

አም

ስለዚህ ከዛ በኋላ ይቀርባል በዚሁ ችሎቱ አብቅቷል።

ማ/ተ

323

በመ/ቁ - 4486

ቀን - ሐምሌ 27 ቀን 2001

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰዒድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ

ከሣሽ - ዐ/ሕግ

ተከሣሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ቀርበዋል

69 ተከሣሾች ከማረሚያ ቤት መቅረባቸው ተረጋግጧል ዘሀራ አብዶሽ ባለፈው ለምን አልመጣሽም አስተርጓሚ የታለ ቁጭ በይ ቁጭ በይ ፖሊስ ነው ያቀረብካት ፖሊስ በፖሊስ ነው የመጣሽው በእራስሽ በላት እስቲ እሺ ጥሩ በሌላ በኩል በእናንተ በኩል ሁላችሁም ቀርባቹሀል

አዎ

ስለማን ነው የቀረባችሁት አስመዝግቡ

ለኢብራሂም መሀመድ ለ23ኛ ለ37ኛ እና ለ38 ተከላካይ ጠበቃ

እሺ በእናንተ በኩል

መንግስት ጠበቃ ለወከለላቸው ለ56 ሰዎች ተከላካይ ጠበቃ አድማሱ መለሰ ቀርቤያለሁ

ጥሩ ዐ/ሕግ ምስክሮች ቀርበዋል ዛሬ

አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ቀርበውልናል

ስንት ምስክር ነው ያቀረባችሁት

12 ምስክሮችን ነው ያቀረብነው

12 ምስክሮች

324

ከዛ በፊት ግን የምናሻሽለው ክሶች ስላሉ በቅድሚያ

በየትኛው የትኛውን ክስ ነው የምታሻሽሉት ይሄ ዛሬ የሚሰማውን ነው የምታሻሽሉት

አዎ በ9ኛ ክስ ላይ እ በ7ኛው ክስ ላይ በ41ኛ ክስ ላይ እና በ19ኛ ክስ ላይ ማሻሻያ ----

እስቲ ማመልከቻውን ተቀበሏቸው እሺ በተከላካይ ጠበቆች በኩል በዚህ ላይ መልስ ትሰጣላችሁ የምትሉት ነገር አለ

የተሻሻለውን ክስ ስላላየነው መልስ መስጠት አንችልም

የተባለውን ሰምታቹሀል

የተባለውን ሰምተናል አዎ

7ኛ 9ኛ 19ኛ 41ኛ ክሶችን እንድናሻሽል ይፈቀድልን የሚል አዲስ ጥያቄ ነው ይዘው የመጡት ዐ/ሕግ

እኛ በመሻሻል ባለመሻሻሉ ላይ የምናቀርበው ተቃውሞ የለንም በማሻሻሉ ላይ ግን የተሻሻለው ክስ ደርሶን ነው እንግዲህ ስለ ክሱ ይዘት እንዲህ ነው እንዲህ አይደለም ብለን ማለት የምንችለው

ማለት የምትችሉት

አዎ

ጥሩ በእናንተ በኩል

ለነገሩ ተመሳሳይ ነው ዐ/ሕግ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሻሻለ ስለማናውቅ ሲደርሰን መልሳችንን እንሰጣለን

ክስ ማመልከቻውን እስቲ የተሻሻለውን እስቲ አስረዱ ምክንያታችሁን ይሄ ክስ ከተባለ ቆይቶ የለ እንዴ ምንድነው እ መ/ቤቱ

ከመዝገቡ ውስብስብነት እና ትልቅነት አንፃር ባለው ጊዜ ውስጥ በመሰራጫ አንዳንድ ስህተቶች ነበሩ

325

እኮ ምንድነው ስህተቱ አሁን እዚህ

እዛ ውስጥ የተጠቀሱት አሉ እሱ ላይ ይታያሉ

አታውቅትም ማለት ነው አሁንም እሺ በበቂ ኮፒስ አላችሁ ይሄ ነገር

አዎ ኮፒ

እስቲ ስጧቸው ለተከሣሾች ለተከላካይ ጠበቆች ተቀበሉ እና አረጋግጡ

7 9ኛ 19ኛ እና 41ኛ ክስ

ደርሷቹሀል

ደርሶናል

ዐ/ሕግ መጀመሪያ ክሱ ሲዘጋጅ አልተነበበም እንዴ

የትኛው

ክሱን ስታዘጋጁ መጀመሪያ ለዚህ ፍ/ቤት ይሄ እረጅም ጊዜ ያስቆጠረ መዝገብ ነው

ይሄኛው

ፍ/ቤቱ በርካታ ስራዎች አሉት

አዲስ አበባ ሄደው ነበር እኮ እነሱ

አዲስ አበባ የመሄድ ነገር እኮ አይደለም አሁን ይሄ መዝገብ ሲቀርብ ቆይቷል አንድ ሰው አይደለም ስራ የሚሰራው ሰው ነው የታሰረበት

አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈውም እኮ ተናግረናል ዐ/ሕጐቻችን አብዛኛው አዲስ አበባ ነበሩ እና ነው

አይደለም አዳምጡ ባለፈውም አዲስ የመሻሻል ጥያቄ አመጣችሁ

አዎ

በእያንዳንዱ ፒስ የተቆረረጠ ማሻሻያ ጥያቄ መቅረብ አለበት እንዴ ለፍ/ቤት

326

አይደለም ተሰቶ የነበረ እና ያልተፃፈ ነው ይሄ አሁን መተው ነው ክሱን የሰሩት አሁን ያንን ግምት ውስጥ እንዲገባልን ነው የተከበረው ፍ/ቤት

አያችሁት የምትሉት ነገር አለ በጠበቆች በኩል

በእኔ በኩል በ37ኛው 9ኛ ክስ የተባለው ነው የሚመለከተን --- ተከላካይ ጠበቃ

ስንተኛው ክስ 9ኛው ክስ

9ኛው ክስ የ37ኛውን ተከሣሽ ተመልክቶ የተመለከተው ነው የተሻሻለው በዚህ ላይ ምንም የምንሰጠው እንትን የለንም

ተቃውሞ የላችሁም

አዎ

እሺ በእናንተ በኩል

በእኛ በኩልም ክሱ ይቀጥል እኛ ችግር የለም

ይቀጥል

ማስረጃ --- ስለሆነ አዎ

እሺ

ትርሲት ጠበቃሽ አልመጣም ዛሬ ቁሚ እስቲ ጠበቃሽ የሉም ዛሬ

የሉም

ለምንድነው የማይመጡት ዐ/ሕግ አሁን ለምሳሌ በ36ኛ ተከሣሽ ላይ ክስ አሻሽላቹሀል የ36ኛ ተከሣሽ ጠበቃ የሉም አላችሁ እንዲያውም ምስክር በ36ኛ ተከሣሽ ላይ

አሁን ዛሬ አልመጡም

የ36ኛ ምስክር የለም

አዎ አዎ

327

ስለዚህ በሚቀጥለው

ምናልባት አሁን መንገድ ላይ መኪና ተሰብሮ 15 ምስክሮቻችን እየመጡ ነው 15 አሁን ደግሞ ግቢ ውስጥ ገብተዋል በሀረማያ እና በድሬዳዋ

ጥያቄው ይግባችሁ ጥያቄው ይግባችሁ

እሺ

እራሳችሁ ያመጣችሁትን ችግር ነው ፍ/ቤቱ እየነገራችሁ ያለው 36ኛ ክስን አሻሽላቹሀል

አዎ

36ኛ ተከሣሽን በተመለከተ ክስ አሻሽላቹሀል

አዎ

ጠበቃቸው የሉም ወይም ተከሣሿ መጠየቅ አለባቸው በሌላ በኩል ደግሞ ምስክር አምጥታቹሀል

አዎ

ይሄኛው የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ሲያገኝ ወደ ሁለተኛው ስነ ስርአት መሄድ አይቻልም ምስክር 36ኛ ላይ የተቆጠረ ምስክር ከሌላቹ አሁን ምስክሩን መስማት እንቀጥላለን 36ኛ ክስ ያሻሻላችሁት በእራሳቹ ጥፋት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ብይን ይሰጣል ማለት ነው ግልፅ ነው የምትሉት ነገር ካለ በሉ

አሁን እኮ በ36ኛ ክስ ላይ ምስክር አላቀረብንም የተከበረው ፍ/ቤት

36ኛ ተከሣሽ ላይ

አዎ

ምስክር የላችሁም

አሁን የለንም አዎ

ችሎቱ ይቀጥላል ምስክሮቹ ጥሯቸው 5 ምስክሮች ጥሩ እና አስምሉ

የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

328

በ1 ላይ ያሉትን ምናልባት ለፍ/ቤቱ እንዲመቸው ባለፈው በተነጋገርነው መሰረት

9 ናቸው

10 ናቸው እነሱ

ጥሯቸው እሺ

እሺ 10ቹን የ--- አካባቢዎቹን አቅርቡልን ወይም በአንድ ላይ ቀርበው መሀላም ይፈፅሙ ከተባለም ---- እንለያለን እንዴት ነው ለፍ/ቤቱ የሚመቸው የተከበረው ፍ/ቤት

መሀላ ከተፈፀመ በኋላ የሚጠራላችሁን ተራ በተራ ታስጠራላቹ ጭብጥ የምታሲዙት

አጠቃላይ የመጡትን መሀላ ይፈፅሙ ፍ/ቤቱ

አይ 10ሩ ብቻ 10ሩ ብቻ

ምንዳ ቃለ መሀላ አስፈፅማቸው አዎ ቃለ መሀላ አስፈፅማቸው

ለየብቻ ይፈፅሙ ወይስ አንድ ላይ

እንደሚቀልህ አድርገህ በአንድ ላይ ይሻላል አንድ አምስቱን አንድ ላይ ምስክሮቹ መሀላ ፈፅመዋል ተከላካይ ጠበቃ ባለፈው ሂወታቸው በዚህ አለም የተለየ አንድ ተከሣሽ አሉ ስለሱ ማረጋገጫ አምጥታቹህል የህክምና ማስረጃ

ዛሬ ያመጣነው የለም ሰዎቹንም አላገኘኋቸውም እስቲ ዛሬ ከሰአት ካገኘኋቸው

አላገኛችሁም

አዎ አንድ ያቀረብነው አቤቱታ ነበር

አልተሰማም

የእስረኞች -----

የእስረኞች

እህ ችግር አለ ----

329

እሱ መጨረሻ ላይ ጀና መሀመድ እሺ ዐ/ሕግ ማን ይጠራላቹ ምስክር

እሺ አብደላ መሀመድ ላይ በ42ኛ መሀመድ ተከሣሽ በመሀመድ ሐጂ ኢብራሂም ላይ የሚመሰክርልን ነው ክሱ በ24ኛው ክስ ነው

በ24ኛ ክስ ላይ ነው አሁን

አዎ

ማን ይጠራላቹ

አብደላ መሀመድ ኡመር

እስቲ 24ኛን ክስ ለማስረዳት ምስክሩን ጥሩ

አህመድ ኡስማን

አህመድ ኡስማን በስንተኛው ክስ

በ46 በ55 እና በ56 ተከሣሾች ላይ የሚመሰክር ነው 27ኛ ክስ ነው

በስንተኛው ክስ አላችሁ ዐ/ሕግ

27ኛ ክስ

በ27ኛ ክስ ነው የተጠራው

46ኛ እና 56ኛ ተከሣሾች ላይ በ27ኛ ክስ የተቆጠረ ምስክር ቀርቧል

ስም - አህመድ ኡስማን ዱላ

ስራ - የመንግስት ሰራተኛ ነኝ

አድራሻ - በሀረር ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ዲሚቱ የሚባል ወረዳ

ዛሬ እዚህ ለምን እዚህ መጣህ

ለምስክርነት ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቅጅ

330

በምስክርነት

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

በማን ጉዳይ

ሙክታር አብዱጀሊል

እሺ ሌላ

ጀማል ሀሴን

ከእነሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ

አንድ ይቀራል

ማነው እሱ

ከዲር አለም

ስለእነሱ ልትመሰክር ነው ወይ የመጣከው

አዎ

ተጣልተካል ወይ

የለኝም

ዝምድና አለህ ወይ

የለንም

አሁን የገለጥከው ስማቸውን የገለፅካቸው ሰዎች እዚህ ውስጥ አሉ ወይ ተነሳ እና ለይ ካሉ መኖራቸውን አሳየሀም ሊኖሩ ይችላሉ

ተነሳ እና እይ ቁም ቁም ቆይ ተነሳ በለው እስቲ ማንን ነው ያሳየከው በለው በመጀመሪያ አሳይ እባክህ

331

ይሄኛው ከዲር ነው ያኛው ሙክታር ነው

ይሄኛው ማን ነው

ሙክታር

ይሄኛውስ

ከዲር

እሺ ሌላ የምታውቀው ሰው ሌላ የለም ወይ ሌላ የምታውቀው

ሶስተኛውን አላየሁትም

ወደ እዚህ እዚህም እይ እዚህ ጉርፕ ውስጥ እይ እዚህ ደግሞ እይ እዚህኛው ውስጥ ማነው የሌለው እዚህ ውስጥ በለው ያጣከው ማንን ነው ማንን ነው ያጣከው

ጀማልን ነው

ዋና ጥያቄ ቀጥል ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

ምናልባት አሁን

ጥያቄ ቀጥል ስነ ስርአት አድርግ እንጂ

እሺ ---

ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

አዲስ አበባ አንድ ስላለን

ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

ምነው ከዚህ በፊት ጣቢያ ቀርበህ ቃል ሰተክል ወይ በለው

አዎ ሰጥቻለሁ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ... የፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ...

እሺ በዛን ቀን ለጣቢያ ቀርበህ የሰጠከው ቃል ምንድነው

ቆይ ቆይ እስቲ አንዴ ቆዩ መቅረጫውን ስጧቸው ተቃውሞ ይመዝገብ አስመዝግቡ ተቃውሞውን

እሺ ተከሣሹ ጥያቄ ሊቀርብለት የሚገባው ጣቢያ የሰጠውን ቃል እንዲደግም ሳይሆን የሚያውቀውን ሊመሰክር ነው ጣቢያ እንዴት ሰተካል ማለት የጣቢያውን ቃል ተፅእኖ ተደርጐ ያንን ቃል እያስታወሰ እንዲሰጥ ሳይሆን የሚያውቀውን ነው ጣቢያ የሰጠው ቃል ያንንም መልሶ መስጠት ይችላል ወይም ሌላ ስለተከሣሹ ምን ታውቃለህ ተብሎ ሊጠየቅ ነው እንጂ ጣቢያ ሰቶት የነበረውን ቃል እንዲደግም አይደለም ህጉም አይፈቅድም

እሺ ምላሽ

አዎ ምላሽ አለኝ ይህም ምንድነው በጣቢያ ቀርበው ፈርመው የሰጡትን ቃል አሁንም በተከበረው ችሎት ፊት አረጋግጠው እንዲመሰክሩልን ነው የምንፈልገው ብዙ ነገር ሊያውቁ ይችላሉ ብዙ ነገር ግን ጣቢያ ቀርበው የመሰከሩት እና እኛም ያንን ግልፅ ፍሬም ያደረግነው በጣቢያ በሰጡት ቃል መሰረት ነው የተከበረው ፍ/ቤት እስከዛሬም የሚሰራበት --- ይሄ ነው

እሺ ዐ/ሕግ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮ ብይን ሰቷል ጥያቄውን በሌላ መልክ አድርጉት እና ወደ ዋናው ምስክሩ ሊናገር ወደ ሚችለው ነገር እንዲያተኩር አድርጉ እና ዋናውን ጥያቄ ይቀጥሉ ስነ ስርአቱ በሚያዘው መሰረት ጥያቄ ይቀጥሉ

እሺ ዛሬ ምን ልትመሰክርልን መጣህ እስቲ ንገርልን

እኔ በእነዚህ ሶስት ሰዎች ላይ ምስክርነት ለመሆን ነው የመጣሁት ምስክር ለመሆን ነው የመጣሁት

እነማን እነማን ናቸው

ጀማል ሁሴን

አንድ

ሙክታር ሷበዱጀሊል

የኦሮሚያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፡ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፡

333

እሺ

ከዲር አደም የሚባሉት ላይ

እሺ እነኚህ ሰዎች ላይ ነው --- ምን ሲያደርጉ አየህ ወይም ሰማህ በጆሮህም ---

ተቃውሞ አላችሁ እሺ ተቃውሞ ይመዝገብ

የተከበረው ፍ/ቤት ክስ ጭብጣቸውን ሲያሲዙ በሁለት ሰው ላይ ብቻ በሁለት ሰው ላይ ነው ክሱም የሚለው ሁለት ሰው ነው ስለዚህ ሶስተኛ የሚል ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም ሁለተኛ ደግሞ ዐ/ሕጉ በስርአቱ እዛው ቦታው ላይ ቆሞ ነው እንጂ በምስክሩ ላይ ተፅእኖ በሚያደርግ አቋቋም ሁኔታ ቆመው እንዲጠይቁብንም አንፈልግም በቃ መቆሚያ ቦታ አላቸው እዛ ጠረቤዛቸው ላይ ሆነው ይጠይቁት ምስክሩን ተፅእኖ በሚያደርግ መልኩ ነው እየጠየቁት ያለው

እሺ ጥሩ እዚህ ላይ አስተያየት መልስ

አስተያየት አለኝ ምስክሩ ምናልባት እዚህ ውስጥ ሶስተኛውን ምስክር ቅድም ላያየው ይችላል በእስር ቤት ተለውጦም ምን ብሎም ሊሆን ይችላል በሶስተኛውም ላይ ነው የሚመሰክርልን በ27ኛው ክስ በተገለፀውም እና በ32ኛው ክስ ላይ ነው የሚመሰክሩልን ቅድም አስመዝግበናል የተከበረው ፍ/ቤት 32ኛው ክስ አለ እና እዚህ ስለማይመቸን ነው እዚህ ላይ ተጣበን ነው ያለነው ለመቀመጥም አልተመቸንም እና ነው የተነሳነው እንደነሱ ሰፋ ያለ ቦታ አልተሰጠንም ለእዛም ነው ሰፋ ቢለን ምንም ችግር የለም

በመጀመሪያ ሁለተኛው ጥያቄ ላይ ሁለተኛው ነጥብ ላይ ተንቀሳቅሶ የማስመስከሩ ሁኔታን በተመለከተ ይሄ አይነቱ የ ምስክርን የመጠየቅ ሂደት ብዙ የሚነቀፍ አይደለም የቀረበውን ምስክር ክብር እና በነፃ የመመስከር መብት እስከማያጣብብ ድረስ ይሄ ፍ/ቤቱ የሚቆጣጠረው ነው በሌላ በኩል ግን ለማስመስከር የሚደረጉ እጅን በማንቀሳቀስ በሌላ መልክ በእንቅስቃሴ የሚደረገው ነገር የሚበረታታ ጥሩም ነገር ነው ተደርጐ ነው የሚወሰደው ከዛ ውጪ ግን የሚፈፀም ነገር ካለ ፍ/ቤቱ ዝም አይልም እርምጃ እንዲወስድበት ነገር ነው የሚሆነው ይሄ መስመር አፍፎ ወደ ምስክሩ ነፃነት ላይ የሚመጣ ከሆነ ጥንቃቄ ይደረጋል በእዛ ላይ በእዚህ በኩል ጥንቃቄ እንዲደረግም አሻራመንገድ እንዲታወቅ ሌላው ግን 32ኛን ክስ በተመለከተ ዐ/ሕግ ያስመዘገባቸው ጭብጥ አልነበረም ሆኖም ግን ጭብጥ ሊሰፋ ስለሚችል ምስክሩ ይሚያውቀውን የሚያስታውሰውን አድማስ እየሰፋም እየጠበበም ስለሚሄድ እሱን ከግንዛቤ

334

በማስገባት የሚመሰክረነው ነገር እንዲቀጥል በማለት ብይን ተሰቷል ግን አለማስመዝገባችሁን እንድታውቁ ፍ/ቤቱ እየተከታተለ መሆኑን እንድታውቁ ቀጥል

እሺ በእነኚህ ሶስት ተከሣሾች ላይ የምታውቀው ምን አለ ምን የሰማከው

ሙክታር አብዱጀሊል የሚባለው ከበዴሳ የመጣ ገንዘብ ለኪዳር እንደሰጠው ከዲር ደግሞ ለቢራ ሳዶዬ እንዳስተላለፈ

እሺ

እሱ እንደዚህ ሲል ሰማሁ ነው ፖሊስ ምርመራ ሲያደርግ

እሺ ከበዴሳ ይላል ከበዴሳ ምን ጫት መሀበር ነው ወይስ ገበሬ መሀበር ከበዴሳ --- ይላል

መሀመድ ደረሳ የሚባለው መጀመሪያ ላይ 20.000 (ሀያ ሺ) ሁለተኛው ዙር ላይ ደግሞ 29.900 ብር (ሀያ ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር) ሶስተኛው ዙር ላይ ደግሞ 40.000 (አርባ ሺ ብር) እሱ ደርሶት እንዳስተላለፈ ያንን ገንዘብ ከዲር ሲናገር ከዲር እና ሙክታር ሲናገሩ ሰማሁ በምርመራ ላይ

የት ምርመራ ነው የሰማከው

የአና ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ

እነኚህ ምስክሮች ምንድነው ተከሣሹ በዛ ጊዜ ቃላቸውን ስሰጡ በሙሉ ፍቃደኝነታቸው ነው ወይስ እንዴት ነው

እኛ ለታዛቢነት እዛ ቁጭ ብላቹ ተመልከቱ ተብለን ዐ/ሕግ ባለበት ፖሊስ መርማሪዎችም ባሉበት ቁጭ ብለው እያለ ተመርምረው ቃላቸውን ሰተው ነው የሄዱት

ገንዘቡን ለማን ነው የላኩለት

ለአባዎ ወይም ለቢራ ሳዶዬ መጀመሪያ ላይ እንደደረሰ ሁተኛው ደግሞ ሁተኛው ዙር ለሌላ ሰው ነው የተሰጠው ስሙን ግን ጠፋኝ አሁን ከስሬ

አባዎ ማለት ምንድነው

ሸፍታ ማለት ነው

335

እሺ መቼ ነው ---- የተባለው

ጥቅምት ወሩ ውስጥ ነው ቀኑን ግን አላውቀውም

ዓ/ም መቼ ነው በለው

ቆይ ቆይ

ጥቅምት ወር ውስጥ ነው 2001 ዓ/ም በዚህ ዓ/ም ይላል

ቦታው የት አካባቢ ነው

ምእራብ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ታይፊ ከተማ ውስጥ ነው

ይሄንን ገንዘብ የተላኩት ለምንድነው ግንባታ ነው ወይስ ለምንድነው የተላከው

ተቃውሞ አለ

አዎ

እስቲ ቆይ ቆይ

ለምን ተላከ ማን ላከው አዎ ወይም ነው የሚያስገኝ መልስ በመጀመሪያ ጥያቄ ላይ ሊጠየቅ አይገባም መሪ ጥያቄ ነው

እሺ ጥሩ

የተከበረው ፍ/ቤት እነኚህ ወርቃማ ጥያቄዎችን ናቸው ማን ላከው እንዴት ተላከ ሲባል መልስ ነው እንጂ ነው ወይም አይደለም እኮ ለምንድነው የተላከው ገንዘቡ ሲባል ለዚህ ነው ተብሎ ዝርዝር ነገር ነው አዎ ወይንም አያስከትልም አምስት ስድስቱ ወርቃማ ጥያቄዎች ናቸው እነኚህ እኮ

እሺ ይበቃል

አዎ

እሺ ፍ/ቤቱ ጥያቄው ይቀጥል ተብሏል

336

እሺ ለምንድነው ለንግድ ነው ለግንባታ ገንዘቡ የተላከው

አባዎ ማለት ሽፍታ ነው ያው ለሽፍታ ሰዎችን ሰላም ለመንሳት ለማድረግ የሚንቀሳቀስበት ነው እና እሱ የሚጠቀምበት ነው እንግዲህ እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለም

የማውቀው ነገር የለም እሺ አበቃቹ

አላበቃንም አሁን ቅድም ሶሶት ሰዎች ላይ ነው ምስክርነቴን እሰጣለሁ ያልከን በሁለቱ ላይ ነው የሰጠከን በጀማል ሁሴን ላይስ ምንድነው ምስክርነትህ

የጦር መሳሪያ ይዞ ከአባዎቹ ጋር ሆኖ ከሽፍቶቹ ጋር ማለት ነው ከእነሱ ጋር ሆኖ የጥይት ተኩስ ከፈተብኝ ነው ጥይት ተኮሰብኝ ነው

መቼ

በዚህ አመተ ምህረት ውስጥ ይመስለኛል

እሺ የት አካባቢ ነው ተኩስ የተከፈተባችሁ

በምእራብ ሐረርጌ ዞን ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ቡርቃ ዋቤ ቀበሌ ገበሬ መሀበር

እናንተ እነማን ናችሁ ተኩስ የከፈተባችሁ --- ወይስ በግሩፕ እያላችሁ ነው ተኩስ የተከፈተባችሁ

ከሰው ጋር ነበርኩኝ

እነማን ናቸው

አብዱለቂ መሀመድ፣ አብዱለሊ መሀመዶ፣ 9 ሚኒሾች እንሆናለን

አዎ በሚኒሻዎች ላይ ነው የተኮሱት

አዎ

በቃ የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል

አብቅታቹሀል መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ይቀጥል

337

ለተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አቶ መሀመድ አቶ አህመድ አቶ አህመድ አንተ ፖሊስ ጣቢያ እንዴት ሄድክ

ኮ እና እንደታዛቢ እዩ ተመልከቱ ተብለን ነው ማነው ና ታዛቢ ሆነህ ተመልከት ብሎ የጠራህ

ፖሊሱ ነው ፖሊስ ጣቢያ ነው የተጠራሁት የወረዳ ፖሊስ

ስትሄድ ማንን አገኘህ

ሙክታር እና ከዲርን አይቻለሁ ጀማል ደግሞ የለም

እሺ ሌላ ማን አለ

አብዱለኪም የሚባል

ምንድነው አብዱለኪም

ገበሬ ነው

አብዱለሚምስ

አብዱለሚምም ገበሬ ነው

እሺ ይሄ ሁላ የት ነው ያገኻቸው መርማሪውስ የለም እንዴ ፖሊሱ

መርማሪም አለ ዐ/ሕግም አለ ነው

እሺ ከእዛ ገባቹ ምን ተባለ መጀመሪያ እንዴት ተጀመረ ጥያቄውስ

እነሱ ናቸው ጥያቄ የጀማመሩት ምን ስትሰራ ነበርክ ምን ስትሰሩ ነበረ ብለው ነው የጠየቋቸው

ምን ስትሰሩ ነበር ብለው ነው ጥያቄው የጀመረው

አዎ

እሺ ከዛ በኋላ ምን አሉ አነሱ

ይሄንን ቅድም ስናገር የነበርኩትን ነገር ነው ያሉት የመለሱት

339

አሁን ይሄንን ከማለታቸው በፊት ለተከሣሾች ተከሣሾቹን ብትፈልጉ ቃላችሁን መስጠት ትችላላቹ ብትፈልጉ ቃላችሁን መስጠት አትችሉም ብሎ አልነገራቸውማ ዐ/ሕጉ ጠበቃው ይሄ መርማሪው ፖሊስ

አዎ የሚመታቹ የለም የሚነካቹ የለም ብሎ ተናግሯቸዋል

አላቸው እንጂ መናገር ወይም አለመናገር ብትፈልጉ ማመን ብትፈልጉ አለማመን አትችሉም አላላቸውማ

አዎ ማመንም መካድም ትችላላችሁ የሚነካቹ የለም ይኸው ዐ/ሕግም አለ ብሎ ነው የነገራቸው

እሺ ይሄ ተወሰደ የሚለው ብር አንተ ሲነገር ሰማህ እንጂ በአይንህ አላየህም

ቅድም እንደተናገርኩት በአይኔ አላየሁም ያየሁት ነገር የለም ግን እንደዚህ እንደዚህ አድርገን ወሰድን እንዲህ ላክን ሲሉ ከእነሱ ነው የሰማሁት

እሺ ማን መጀመሪያ ተናገረ ማን መጀመሪያ ተጠየቀ

ከዲር ነው የተጠየቀው

እሺ ከእዛ በኋላ

ሙክታር

ከአንተ ጋር ማን ነበረ እንደ አንተ የሚሰማ

አብዱለቲም አብዱለሚም የሚባል እና ዐ/ሕግ አለ

አሁን ለምስክርነት መተዋል

አዎ ዛሬ መተዋል ለምስክርነት

አበቃችሁ

ይሄ ሰጡት የምትለው ቃል ተመዘገበ

አዎ እዛው የዛኑ ሰአት ነው የተፃፈው

339

ይበቃናል

አበቃችሁ

አዎ

አላችሁ

አዎ አለን አለን

ቆይ ቆይ ቆይ እስቲ ዐ/ሕግ ስነ ስርአት አድርጉ እንጂ ወይ የማትከታተሉ ከሆነ በእናንተ በኩል የለም 33ኛ 37ኛ 38ኛ ነው በአንድ ይበቃሉ በዚሁ ይበቃል እሺ ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ ቀጥሉ

የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

አህመድ ኡስማን ያኔ እነኚህ ምነው ሁለቱ ተከሳሾችም በጣቢያ እንደዛ ሲጠየቁ የተደበደቡበት የተጐሳቆሉበት በግዴታ ቃል እንዲሰጡ የተደረገበት ሁኔታ ነበር ወይ

ምንም ከመጡት የተናገሯቸውም የለም ማንም ሰው

አበቃቹ

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አንተ ለምን እዛ ቦታ ላይ ተገኘህ ምንድነህ አንተ ስራህ --- እዛ የሄድከው

እኔ ኮሮዬ እዛው ነው ፖሊስ ጣቢያው አካባቢ ነው ኮሮዬ እዛ አካባቢ ነው ፖሊስ ጣቢያው አካባቢ ነው

አንተ ተለይተህ ለምን እዛ ቀረብክ እዛ ቆየህ

ስራ አለኝ ስራ መኖሩ ሳይሆን ኑ ታዛቢ ትሆናለህ ተብዬ ነው የመጣሁት የተጠራሁት

ሌሎች ለምን አልተጠሩም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

340

እኔ በጥሪ ጠሩኝ ና ብለው ጠሩኝ ሄድኩኝ ሌሎች ሰዎች መጥራት ያልቻሉበት ምክንያት አላውቅም

ሙክታር እና ከዲር ገንዘብ ለማን ሰጠን ነው ያሉህ

ሙክታር ለከዲር ሰጠ ሶስት ዙር ነው የሰጠው ከዲር ደግሞ ሙክታር ለከዲር ሰጠ ከዲር ደግሞ ሶስት ዙር ነው ያንን ገንዘብ ያስተላለፈው መጀመሪያ ብሩን ቢራ ሳዶዬ ሰጠ

ማነው ለቢራ ሳዶዬ የሰጠው

ከዲር ነው የሰጠው

ሲሰጥ አይተካል ወይ

አላየሁም እነሱ ተናገሩ እንጂ እኔ አላየሁም

የተናገሩትን ነው የሰማከው ማለት ነው

አዎ

ቢራ ሳዶዬ ምንድነው

የአባዎ ወታደር አዛዥ ነው

እንዴት አወቅህ ይሄንን

ከዚህ በፊት ያ ቢራ ሳዶዬ የሚባል ሰውዬ በመንግስት ወታደሮች ተይዞ አደባባይ ላይ ቆሞ ፊት ለፊታችን የስራውን ድርሻ እና ሲያደርግ የነበረውን ነገር ገልጾልናል ነው

አባዎ ምንድነው

ሽፍታ ማለት ነው

ቢራ ሳዶዬ ሽፍታ ነው ወይ

አዎ ሽፍታ ነው

በማን ላይ ነው የሸፈተው

የፌዴራል ዲ/ሪ ፐብሊክ ፖሊስ ኮሚሽን የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

3411

መንግስትን ለመናድ ነው የሸፈተው በመንግስት ላይ ነው

ከማን ጋር ሆኖ

ብዙ ናቸው የአባሞ ሰራዊቶች ጋር ከአባሞ ሰራዊት ጋር ሆኖ ነው የሸፈተው

ማነው የሚመራቸው

ዋና አዛዡ ፋርጋስ ይባላል ቢራ ሳዶዬም አዛዥ ነው

ድርጅት አላቸው ወይ

የላቸውም

አታውቅም

አላውቅም

እና በግል ነግሮካል ወይ ሙክታር ለአንተ ነግሮካል ወይ ለቢራሳ ብር ሰጠሁ

አልነገረኝም

አልነገሩክም

አልነገረኝም

እዛ ጣቢያ የሰማከውን ነው የነገርከን

አሞ እዛ ነው የሰማሁት

ታስረው ነበረ እንዴ ይሄንን ስናገሩ

እንዲሁ እኛ እንደተቀመጥነው ቁጭ ብለን ነው የተናገሩት

ጣቢያ ውስጥ

አሞ አልታሰሩም ነው

እሺ እናመሰግንሀለን ከኋላ ቁጭ በል ማን ይጠራላችሁ

የፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ክልሎች ጠቅላይ ፍ/ቤት ከጥቅምት

3412

አብዱለኪም መሀመድ

አብዱለኪም መሀመድ ጥሩ

32ኛ ክስ ላይ ነው የሚመሰክሩልን

ድምፅ እንዲሰማ እሺ አስተርጓሚውም ምስክሩም ድምፃቸው እንዲሰማ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል ድምፃችሁን ከፍ አድርጉ ትላቸዋለህ በስንተኛው ክስ ላይ ነው ዐ/ሕግ የተጠራው በ32ኛ ክስ ለማስረዳት ነው

2ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ቀርቧል

በ32ኛ ክስ ላይ ነው ተብሏል

ስም - አብዱለኪም መሀመድ

አድራሻ - ቦኬ ተፈ የሚባል ቦታ ተፍኪ የሚባል ቦታ ጪራ የሚባል አካባቢ ነው ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ውስጥ ነው ምስራቅ ሐረርጌ

ዛሬ ለምን መጣህ እዚህ

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

በማን ላይ ልትመሰክር ነው የመጣከው

መኳታር አብዱጀሊል

እሺ ሌላ

ከዲር አደም ጠንደቻ

ጀማል ሁሴን መሳ ላይ ነው ምስክርነት

ተጣልተካል ወይ ከእነዚህ ሰዎች ጋር

የለኝም

ዝምድና አለህ

3ኛ/3

የለኝም

በታያቸው ትለያቸዋለህ ወይ እነዚህን ሰዎች

አዎ

እስቲ ተነሳ እና እዚህ ውስጥ ፊልግ እና እያቸው መሄድ ትችላለህ ወደ እዛ በለው እስቲ አሳይ በለው እባክህ እስቲ ብድግ በሉ ብድግ በሉ እነሱ ናቸው ወይ በለው

ሙክታር አብዱጀሊል ይባላል ያ ጥቁሩ

እሺ ይሄኛውስ

ይሄ ከዲር አደም ይባላል ነው የሚለው

እሺ ሁለቱንም በችሎት ለይቶ አሳይቷል ና ቁጭ በል

አንዱ ይቀራል

ተነሳ ማነው እሱ ጀማል ማን

ጀማል ሁሴን ሙሳ

--ኛን ተከሣሽ ጀማል ሁሴን ሙሳን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

አብዱረሂም መሀመድ እኚህ ሶስት አሁን ለይተህ በችሎት በግልፅ ባሳየካቸው ተከሣሾች ላይ የምታውቀው ነገር ምን አለ

ሙክታር አብዱል ጀሊል ከመሀመድ ደረሳ ላይ ገንዘብ እንደተቀበለ ፖሊስ ላይ ሲሰጠው ቃል አውቃለሁ ሶስት ጊዜ ሰጠኝ ብሎ ሲል ሶስቱንም ዙር ለከዲር አደም ነው ያሸጋገርኩት የሰጠሁት ብሎ የምስክርነት ቃሉን ለፖሊስ ሲሰጥ ሰምቻለሁ

ስንት ስንት ገንዘብ ነው ሶስት ጊዜ የተሰጠው

በመጀመሪያው ዙር 20.000 ብር ሁለተኛው ዙር 29.000 ብር ብሎ ተናግሯል ሶስተኛው ደግሞ 40.000 ብር ብሎ ነው የተናገረው

3414

እነኚህ ገንዘብ እሺ ቀጥል እንዴት ተላከለት ይሄ ገንዘብ

እሱ እሱኑ ነው የሰማሁት እኔ የሰማሁት ሌላ ነገር አልሰማሁም ምንድነው መሀመድ ደረሳ አስልኬ ሶስት ዙር ለከዲር አሸጋገርኩለት ሰጠሁለት

መሀመድ ደረሳ ማነው በለው

እኔ መሀመድ ደረሳ የሚባለውን ሰው አላውቀውም ግን ከመሀመድ ደረሳ ተቀብሎ ሶስት ዙር አንዱ 20.000 ብር መጀመሪያ ሁለተኛ 29.000 ሶስተኛ ላይ ደግሞ 40.000 ሺ ብር ለከዲር ሰጠሁ ብሎ በፖሊስ ቃሉን ሲሰጥ ሰምቻለሁ

ከዲርስ ለማን እንደሰጠስ ተናግሯል

እሱ ከድር ደግሞ ቃሉን ሲሰጥ የመጀመሪያውን 20.000 ብር ለቢራሳ ሰጠሁ ሁለተኛውን ደግሞ 29.000 ብሩን ለገመቺስ ሰጠሁ ሶስተኛውን ደግሞ 40.000 ብር እሱንም ለገመቺስ ሰጠሁ ብሎ ቃሉን ሲሰጥ ሰምቻለሁ ይሄ ሁለት ቃላቸውን የሰጡትን ቃል ይሄንን አውቃለሁ ነው

አሁን እነኚህ ገንዘብ የተቀበሉት ገመቺስ እና ማነው ያልከኝ

ቢራሳ

ቢራሳ የተባሉት ምንድን ናቸው ለምንድነው ገንዘቡን የሰጧቸው ጫት ሊገዙበት ነው ቤት ሊገዙበት ነው

እኔ አላውቅም ግን እንደዛ

አልጠየክም

ቆይ ዐ/ሕግ ይመለስ ጥያቄው

እሺ እሺ

እኔ አላውቅም ግን ለእነሱ ሰጠን ብለው ሲሉ ነው የማውቀው ነው

ለምን አላማ ነው የተሰጠው

345

ገንዘቡ ለአባዎ ነው የተላከው ብሎ ይመስለኛል ነው ይመስለኛል ነው ለአባዎ ነው የተላከው ማነው ይሄን ያለው

ወንዝ ሄጀ ነው የሰጠሁት ለአዲር አደም ሙክታር ብሎ ነው ያለው

አባዎ ያለው ማነው ብሩ ለአባዎ ነው የሚሰጠው ያለው ማነው ከአድር እና ከሙክታር በቃ

ከዲር ነው ያለው

እሺ ቀጥሉ ጥያቄ አበቃቹ

እሺ

እንደዛ ብሎ ያለው ከዲር

እነማን ናቸው ቅድም በተናገረው ገንዘቡን የተቀበሉት የት ቦታ ነው የተቀበሉት

እኔ ይሄንን ነው የሰማሁትኝ ሌላ የማውቀው ነገር የለም

የት ጋ ነው እንደህ ብለው ቃላቸውን የሰጡት በለው

---- የሚባል ቦታ ፖሊስ ላይ ነው ቃላቸውን የሰጡት

እሺ መርማሪው ያለበት

ሌላስ ማን ነበር

አህመድ ኡስማን፣ ዱላ፣

መቼ ነበር እንዲህ ብለው ቃላቸውን የሰጡት

በ2001 ዓ/ም አላውቀውም ወሩን ነው

በዛ ጊዜ

ጥቅምት ነው ጥቅምት ነው ይላል

ጥቅምት አዎ እሺ

346

ጥቅምት 2001 ዓ/ም

እሺ አሁን ቅድም አባዎ ስትል ነበር አባዎ ምንድነው የልማት ድርጅት ነው ወይስ የምንድነው

የመንግስት ተቃዋሚ እንትኖች ናቸው ሰራዊቶች ናቸው

እሺ

የመንግስት ተቃዋሚዎች ናቸው

እሺ የመንግስት

አበቃቹ

ቆይ አላበቃንም አሁን ሁለት ሰው ላይ ነው ሙክታር እና ከዲር ላይ ነው የመሰከርከው ቅድም ለይተህ ያወጣከው ጀማልስ ምን አደረገ

ከዚህ በፊትም አንድ አካባቢ ነው ያለነው እንተዋወቃለን እዛ እኛ የሆነ ቦታ ለስራ ሄደን ነው አብረን እያለ ከ አባዎ ሰራዊት ጋር ተገናኘን እና ተኩስ ከፍተን እያለን የተኩስ ልውውጥ ስናደርግ ከእዛው ውስጥ ከእዛ ሰራዊት ከነበሩት ተኩስ ከከፈቱት ውስጥ ጀማል ሁሴንም አለ እየሄድን እያለ ተኩስም የከፈተብን እሱ ነው ነው

መቼ ነው ይሄንን ያደረገው

በ2001 ዓ/ም ቀኑ 13 ነው 6:00 ሰአት ላይ

አንተ ከእነማን ጋር ነበርክ ያኔ ተኩስ ሲከፈት በእናንተስ እነማን ነበሩ ዛሬ ከመጡት መሀከል

አህመድ ኡስማን እና አብዱላሊ

እሺ ቦታው የት ጋ ነው ተኩስ የተከፈተው

ቀሬ ሀሮ ዲምቱ የሚባል ቦታ ነው መሀል ላይ

እናንተ ተኩስ የተከፈተባቹ ምንድን ናችሁ

እኛ ሚኒሻ ነን

317

የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄዬን አብቅቻለሁ

አበቃችሁ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ይቀጥል

የተከሣሾች ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

መቼ ነው ---------- የተባለው

ጥቅምት ወር ውስጥ ቀኑን ግን አላውቀውም

ቆይ ቆይ የተከሳሾች ጠበቃ እንዲሁም ሌሎች መንግስት ጥብቅና ያቆመላቸው ተከሳሾች

ፖሊስ ጣቢያ ለምን ሄዱ

እዛ ወጥተን እዛ አካባቢ ነበርኩኝ እኔ እዛው ቁጭ ባልንበት ቦታ ነው ቃላችንን የተቀበሉን ነው

አንተ ሚኒሻ ነህ

አዎ ሚኒሻ ነኝ

አንተ አሁን አንተ ስትገባ ማንን አገኘህ ---------- ማን ጠራህ መጀመሪያ

ዘኮ የሚባል ፖሊስ አለ

መርማሪው ማን ነው

ስማቸውን አልጠየኳቸውም ቄሮ ከሚባለው አካባቢ ነው የመጡት

ምርመራውን የሚያጣሩት የእዛ አካባቢ ፖሊሶች አይደሉም እንዴ

ከዞን ነው የመጡት መሰለኝ

አበቃችሁ

እሺ እዛ ስትገባ ከአንተ በፊት ማን ገብቷል

እኔ እንግዲህ እዛ ስገባ የነበሩት ሰዎች ስማቸውን የማላውቃቸው ሰዎች ናቸው ቃላቸውን የተቀበሏቸው ፖሊሶች ናቸው

በኦሮሚያ ክልላዊ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 2

348

እነዚህን ሰዎች እዛ አገኝካቸው እንዴ እዛው ቁጭ ብለው

የትኞቹን

እነዚህ ተከሳሾችን አሁን ሁለቱን

አሁን ፊት ለፊቴ ቁጭ ብለው ነበር እኔ --------- ቁጭ ብለው ነበር

ከየት መጥተው ነው

እነሱ ተይዘው ያመጧቸው ይሁን እኔ አላውቅም እኔ እዛው ነው ያገኘኋቸው ነው

ፖሊስ እነሱን ጥያቄ ሲያቀርብ ምን ብሎ ጀመረ

እንግዲህ በዛን ሰዓት ከመርማሪዎቹ ውጪ ሌላ ፖሊስ የለም ነበር እዛ ክፍል ውስጥ እና እስቲ ከዚህ በፊት የነበርክበትን ሁኔታ አስረዳ ስራህ ምን ነበር የምትሰራው ብሎ ሲሉት ሲባሉ ሲጠየቁ እንደዛ ተብለው ይዜን ነው ስንሰራ የነበረው በማለት ይዜንን የተናገሩትን ቃል ሰጥተዋል ነው

እንጂ ከዛ ውጪ ጥያቄ አላቀረበላቸውም

ከዛ ሌላ ነገር ደግሞ የተናገሩት ሳይገደዱ እና ሳይገደዱ ቃላቸውን እንደሰጡ እናንተም ምስክር ሁኑልን ብለው ተናግረዋል

ማን ነው ይዜን ያለው ---------- መሆኑን ምስክር ሁንልን ያለው ማን ነው

መርማሪዎቹ ናቸው

እንጂ ሰዎቹ በገዛ ፈቃዳችን እኛ ሳንገደድ ነው የምንሰጠው ደስተኛ ነን ቃላችንን ለመስጠት ብለዋል አላሉም

አዎ ብለዋል ነው

አበቃችሁ ጥያቄ

ከአንተ ሌላ ማን ነበር ምስክር ሆኖ የመጣ ዛሬ ማለት ነው

ምስክር ሆኖ ዛሬ የመጣ

349

አህመድ ኡስማን ሉላ

ምስክር ሆኖ የመጣ

አዎ አህመድ ኡስማን ሉላ

ሌላስ ዛሬ የመጣ

እኔ እና እሱ እንጂ ሌላ የመጣ የለም ዛሬ በእነዚህ ሰዎች ላይ

ማን መጀመሪያ ተናገረ መጀመሪያ የተናገረው ማን ነው

ሙክታር ነው

ሙክታር ነው መጀመሪያ የተናገረው

አዎ ሙክታር ነው

ፈረሙበት እንዴ ያንን ተጻፈ የምትለውን

ያድርጉ አያድርጉ አላውቅም ይፈርሙ ግን እኔ ወጥቻለሁ

ወጥተህ ሄደሃል

አዎ ወጥቼ ሄጃለሁ

አንተስ ፈረምክ እንዴ

አዎ ፈርሜአለሁ

እነሱ በሰጡት ቃል ላይ ነው በራስህ ቃል ላይ

አልፈረምኩም ነው

ይበቃናል

አበቃችሁ በእናንተ በኩልም እሺ አላችሁ ድጋሚ ጥያቄ ዐ/ህግ አላችሁ ድጋሚ ጥያቄ

የለንም የተከበረው ፍ/ቤት

350

እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ድጋሚ ጥያቄ ስለሌለ የምስ መልስ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ድሪሳ ገመቺስ መሀመድ ምንድን ናቸው

ማን

ድሪሳ፣ ገመቺስ መሀመድ ድሪሳ ምንድን ናቸው

እነሱ ሲሉ እንጂ ድሪሳ የሚባለው አባጆ ነው ተብሎ ሲባል ነው የሰማሁት እሱ እንደዛ ተይዞ ነው ቢራሳ ይሄ ነው ቢራሳ እንደዚህ ነው ብሎ ሲናገር ነው እንጂ የሰማሁት

እኮ ምንድን ነው አለ ሲናገር ምን አለ ቢራሳ ምንድን ነው አለ

ለእሱ ነው የሰጠሁት ብሎ ሲል ነው

ምንድን ነው አለህ ቢራሳ የሚባለው ምንድን ነው የሚሰራው ተማሪ ነው

አባጆ ነው

ምን ማለት ነው አባጆ

አባጆ ማለት

የመንግስት ተቃዋሚ ላይ ነው መንግስት ላይ ጥቃት የሚሰነዝር ማለት ነው

ማለት ነው

አጆ

ስም የለውም መጠሪያ መንግስትን የሚቃወመው

እኔ ይሄንን ሲባል እንጂ ሌላ

ማን ተብሎ ነው የሚወራው መንግስትን የሚቃወመው

አባጆ ይባላል የመንግስት ተቋም

የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፓብሊክ ኢትዮጵያ

አባዎና አነግ ልዩነት አላቸው የላቸውም

አባዎም አነግም ማለት ይባላል ግን አንድ ናቸው ያው መንግስትን ነው የሚቃወሙት መንግስትን ነው የሚያጠቁት

አንድ ናቸው

አዎ ይባላል ነው የተከበረው ፍ/ቤት

አንተ ሙክታር ከድር ጀማል የሚኖርበት አካባቢ አብረህ ነዋሪ ነህ ወይ

ከድር አደም የሚባለውን የዛን ቀን እንጂ ያየሁት ከዛ በፊት አይቼውም አላውቅም

ሙክታርንስ

ሙክታርን ግን በአንድ እንተዋወቃለን ነው

አንድ አካባቢ ናችሁ

አንድ መንደር አይደለንም ያው እንቀራረባለን

ጀማልስ

ከጀማል ትንሽ እንቀራረባለን እንጂ የተለያየ ቀበሌ ነን

አንተ ምንድን ነው የምትሰራው ቀበሌ ውስጥ ታጣቂ ነኝ ብለሃል

ሚኒሻ ነኝ

ሚኒሻ ጀማልስ

ከዚህ በፊት አባዎ ውስጥ ገብቼ እንቀሳቀስ ነበር

በዛ ነው የምታውቀው

አዎ አውቃለሁ ፡

ሙክታርስ

352

ሙክታርን አላውቅም አባዎ ውስጥ እንደሚንቀሳቀስ የዛኑ ቀን ነው የሰማሁት

እሺ ከድርን አታውቀውም

የዛን ቃሉን ሲሰጥ ብቻ እንጂ ያየሁት ከዛ በፊት አይቼውም አላውቅም

እሺ እዛ ታዛቢ ሆነህ ስትቀርብ በሚኒሻነትህ ነው ወይስ ሌላ የስራ ድርሻ ነበረህ

ከስራ ስመጣ ነው ሌላ ስራ የለኝም ከስራ ስመጣ ነው በዛ ነው የተጠራሁት

ከእነማን ጋር ነው የተጠራከው

እኔ እና አህመድ ኡስማን

መስክሯል ይሄ አህመድ ኡስማን

መቼ እዛ ነው እዚህ

ዛሬ እዚህ መስክሯል ወይ

አዎ

ጀማል ሲተኩስ አይተከዋል ወይ በአይንህ

አዎ አይቻለሁ

አንተ ተኮስክ ወይ ምላሽ

አዎ ተኩሻለሁ መልስ ሰጥቻለሁ

ጀማል ስንቴ ተኮሰ

በዛን ሰዓት ስንት እንደሆነ ጥይቱን አላውቅም እዛም ተኩስ ተከፍቷል እኛም ምላሽ እየሰጠን ነበር ከዛ በኋላ ትንሽ ቆይቶ ከቆየው ጊዜ በኋላ እጁን ሰጠ ጀማል

እንዴት አወቅህ እሱ መሳሪያውን

ሰራዊቱ እዛ ድረስ አምጥቶ እዛ እኛ ጋር ይዞ አመጣ

ይሄን ታውቃለህ

አዎ እጁን ስለመስጠቱ ሳይሆን እዛ ስለመምጣቱ ነው የማውቀው ከዛ በፊት ተይዞ እጁን እንደሰጠ አላውቅም ግን ሰራዊቱ እዛ ሲያመጣው አውቃለሁ::

እሺ እናመሰግናለን ከኋላ ቁጭ በል ዐ/ህግ ቀሪ ምስክሮች በተመለከተ እስቲ ጥሯቸው ሰዓቱም ስለገፋ ሙቀቱም ስለጨመረ ተከሳሾቹም በርካታ ስለሆኑ ልጅም የያዘ ተከሳሽ መኖሩ ስለታየ በዚህ ሂደት ማቆየት ትንሽ አስቸጋሪ ነው ስለዚህ ምስክርነቱን ከቀትር በኋላም እንቀጥላለን በዚሁ የተሰማው ይበቃናል ጥሯቸው ሌሎቹን ምስክሮች

አጠቃላይ ይምጡ የተከበረው ፍ/ቤት ወይስ

ቆይ እስቲ አንዱ ምስክሮቹን ዐ/ህግ ራሳችሁ ከሰዓት በኋላ እንዲመጡ አድርጉ እዛው ይቆዩ ውጪ ቆዩ

27ቱንም እናቅርባቸው ወይስ እንዴት ነው

የቀሩትን ምስክሮች ከሰዓት በኋላ አቅርቡ ችሎቱ ሳያልቅ ስለ ሌላ ነገር አትጠይቁ ይቅርታ በላቸው የቻልነውን ያህል እንሰማለን ያልተቻለውን ደግሞ እናስተላልፋለን ዐ/ህግ በጽህፈት ቤት ባሳሰባችሁት መሰረት ከርቀት የመጡ ምስክሮች አሉ ስላላችሁ መስማት የምንችለውን ያህል አንድ ሁለት ምስክሮች እነዚህ ግን ከጠረፍ ከርቀት የመጡት እንዲሆኑ እንድታደርጉ እንጠይቃለን የተቻለውን እንሰማለን ማለት ነው ስለዚህ ማን ይጠራላችሁ

አብዱላሂሊም አህመድ

አብዱላሂሊም አህመድን ጥሩ

እሺ በ55ኛ ተከሳሽ ጀማል ሀሰን ላይ የሚመሰክር ነው ክስ 32 ነው

አሁንም ክስ 32 ነው

አዎ በአንድ ላይ ነው በአጭሩ ነው እያስረዳን እንሄዳለን

ጥሩት ይቅረብ እስቲ ጥሩት

የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

3ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ሥም - አብዱላሂሊም አህመድ

እድሜ -

ሥራ - ገበሬ ነኝ

አድራሻ- ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ኦጋ ቀላ ቀ/ገ/ማህበር ነው

ዛሬ ለምን መጣህ

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ጀማል ሁሴን ሙሳ ላይ

ሌላስ

የለም

ጀማል ብታየው ትለየዋለህ ወይ

አዎ እችላለሁ

እስቲ ተነሳና ወደዚህ ዐ/ህግ በሚቀጥለው እንለያለን አሁን በዚሁ ይቀጥል ወደዛ ሂድና ለይ ከፊት ጀምር በለው ከዚህ ጀምር ምንዳ ንገረው እንጂ ተራ በተራ እያየህ ቀጥል ቀና ቀና በሉ በላቸው ቀና በል ቀና በሉ በላቸው እዛ ጋ ማን ነው ስምህ

አብዱላሂ ሙሳ ነኝ

አብዱላሂ ሙሳ እሱ ነው ወይ ጀማል በለው ሽ ስርዓት አድርጉ በላቸው ንገራቸው በስነ ስርዓት ተቀመጡ እየተሂሂርክ ረጋ ብለህ እይ በለው ንገረው ድጋሚም ማየት ትችላለህ ቆይ የትኛው ተነሳ ማን ነው ስምህ

ጀማል ሁሴን

355

ከእንግዲህ በኋላ የሚያቀረቅር ከታየ አሁን ቀደም ሲል እንደታየው እርምጃ ይወሰዳል በላቸው ጀማል መጀመሪያ ለምንድን ነው ያቀረቀርከው በለው ፍ/ቤቱ እኮ አይቶሃል ያውቅሃል ተነሳ እስቲ ለምንድን ነው መጀመሪያ እንደዛ ያደረከው ፍ/ቤቱ እኮ ያያል ዝም ብሎ አይደለም እዚህ የተቀመጥነው በለው ቁጭ በል እሺ ተጣልተሃል ወይ ከጀማል ጋር

የለኝም

ዝምድና አለህ

የለኝም

ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

አብዱልሃሚድ ዛሬ ከጀማል ጋር የሚያገናኝህ እና ልትመሰክርልን የመጣከው በምን ጉዳይ ነው

ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ቡርቃ ዋቢ የሚባል ቀበሌ ገ/ማህበር አሮ ዲምቱ የሚባል አካባቢ ቦታ በአባዎ ምክንያት አንድ ላይ ከእኛ ጋር አብረን መጥተን በዛ መሀል ተኩስ ተለዋውጠን አባዎ ውስጥ ነኝ እኔ

አባዎ የሚለውን እየተረጎማችሁ ምንዳ እየተረጎምክ ተርጉም

አባዎ ማለት ሸፍታ ማለት ነው

እየተረጎምክ

ሸፍታ ማለት ነው እያለ ነው ሸፍታ ልበል አባዎ ማለት እኔ አላውቀውም የተከበረው ፍ/ቤት አነግ ማለት ነው አነግ ውስጥ ነው የሚገኘው አነግ ውስጥ ነኝ ብሎ እሱ አነግ ውስጥ ነው ያለው እኔ ከሚኒሻዎች ጋር ነኝ እኛ ሚኒሻዎች ዘጠኝ ሰዎች ነበርን እነሱ አምስት ነበሩ 6:00 ሰዓት ይሆናል እዛ አንድ ቦታ መጥተን 2001 ዓ/ም ነው 6:00 ሰዓት ይሆናል 2001 ዓ/ም ሁለተኛው ወር ጥቅምት በዛን ሰዓት ተኩስ ከፈተብን እኛም መልስ ተኩስ ተኩሰንባቸው እና በዛ ምክንያት ነው እዛ ውስጥ እና ከዛ በፊትም በዚህ ጉዳይ እዚህ አካባቢ አውቀው ነበር

በኋላ ተይዟል ወይስ አልተያዘም

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

356

አልተያዘም

ካዛ በኋላስ

ካዛ በኋላ ተያዘ

በዛ ጊዜ ከእናንተ ሚኒሻዎች ጋር የነበሩ እና ዛሬ የመጡ ሰዎች አሉ ወይ

አዎ ሁለት ሰው አለ

እነማን ናቸው

አብዱለኪም መሀመድ እና አህመድ ኡስማን

የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሻለሁ

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ይቅረብ እንደዚሁ

የተከሳሾች ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ካዛ በፊት ታውቀው ነበር ወይ ተከሳሹን

አዎ አውቀዋለሁ

የት ነበር የምታውቀው

ቀበሌአችን ይለያያል እንጂ አንድ አካባቢ ነን ርቀትም የለንም ነው አንራራቅም

በምን ያህል ርቀት ነበር ተኩስ ተለዋወጥን የምትለው

በግምት አላውቀውም እኔ አንድ ሄክታር ላይ ነበርን

እስቲ ወደ ውጪ እይና ከዚህ እስከዛ ብለህ እስቲ ብድግ ብለህ ነዋ ፊት ለፊት እይ በለው እዚሁ ሁንና ገምት እስከየት ይሆናል

እዛ ሰዎቹ የተቀመጡበት

ስንት ይሆናል ፖሊስ እስቲ ግምት ሰዎቹ ያሉበት እዚህ ሰዎቹ የተቀመጡበት ርቀቱ ስንት ገመታችሁ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፬ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ

357

በእርምጃ ይለካልን የተከበረው ፍ/ቤት

ከ70 እስከላይኛው ድረስ ሰዎቹ እስካሉበት

ኮንቴነሩ የተቀመጡት

አዎ ኮንቴነሩ ጋር ከ70 እስከ 80 ተገምቷል ሌላ ጥያቄ ካለ

በዚህ ርቀት ነው ተኩስ ልውውጥ የምታደርጉት

አዎ በዚህ ርቀት ነው

በዚህ ርቀት የተኩስ ልውውጥ በምታደርጉበት ጊዜ ይሄን ያህል እንደዚህ የሰው መልክ ለይተህ የምታውቅ ከሆነ የሚተኩሰው ጥይት አይመታህም ወይ አነጣጥረህ የምታይ ከሆነ

እነሱ አድፍጠው ተይተው እኛ ድንገት ነው የተገናኘነው እዛ ቦታ ስንሄድ ነው ነው የደረስነው እዛ ቦታ መልሱን ብቻ እንትን ሌላ ነገር መልሱን በቻ ልናገር የጠየቁኝን ጥያቄውን ብቻ መልስ የጥያቄውን መልስ ብቻ ልናገር

አዎ መልስ ስጥ

አዎ እነሱ ተኝተው እያለ እኛ እዛ ቦታ ድንገት ነው የደረስነው እና በእዛ መሀል ነው ጥይት የተኮሱብን

ጥያቄ

ስንት ነበሩ እነሱ

5 ናቸው

እናንተስ

እኛ 9 ነን

እነሱ ተኙበት የምለው እምን ጋር ነው የተኙት እምን ላይ ነው የተኙት

ዛፍ ስር ነው ጥላ ነበረ በእዛን ሰአት እዛ ስር ተኝተው ነበር

358

እነሱ ዛፍ ስር ተኝተዋል እናንተስ

እኛ እየሄድን ነበር

እናንተ እየዜዳችሁ ነበረ

አዎ

የሚከልል ነገር የለውም መሀል ዛፍ ስር ካልክ ከዛፉ በስተጀርባ ከሆኑ ማየት ትችላለህ ወይ ምንም የሚከለክለን ነገር የለም እነሱ ቁጭ ብለው ነበር እዛ ስር

ተኝተው ነው ቁጭ ብለው

ተኝተው ነበር አለ አሁን ቁጭ ብለው ነበር አለ አሁን ደግሞ

የትኛው ነው ትክክሉ ተኝተው ነው ቁጭ ብለው

---- አልክ የትኛው ነው ትክክሉ

እሱም እኛ በዛን ሰአት ቁጭ ብለው ነበር እሱ መጀመሪያ ነው የተቀመጠው እሱ እንደውም መጀመሪያ ቁጭ ብለው ነው ታዲያ ተኝተው ያልከው መቼ ነው የተኙት

መሬት ተኝተዋል ማለቴ አይደለም የቋንቋ ነገር ነው እና ተሰብስበው እዛ ቦታ ነበሩ ማለቴ ነው አበቃችሁ

እሺ አዎ ይበቃናል

በእናንተ በኩል አለ ይላችሁም እሺ አማክሩት

አሁን እናንተ ደረሳችሁ ሰውዬውን ስታየው ልክ ሰውዬው ምን መሳሪያ ነበር ይዞ የነበረው

ክላሽ ይዞ ነበር

የለበሰውስ ልብስ ታስታውሳለህ

አዎ አስታውሳለሁ ጃኬት ነው የለበሰው

የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ቢሮ ክፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

359

ምን አይነት ከለሩ ትዝ ይልካል

ጥቁር ነገር ሆኖ ዳለቻ ነው እንትን

ኤው አሁን ተኩሱ ልውውጥ እነሱ ቁጭ እንዳሉ እናንተ ደረሳችሁ ከእዛ በኋላ ተኩሱ ልውውጡ ቆሞ ነው ተኝተው ነው

ምን አሉኝ

ኤው እነሱ ቁጭ እንዳሉ ደረሱ አሁን በ80 ሜትር እርቀት ላይ እነሱ ደረሱባቸው ወደ እነሱ ጋር ሄዱ ሲሄዱ ምን ሆነ መጀመሪያ

ስትደርሱ ምን ሆነ የተቀመጡበት ቦታ ስትደርሱ ምን ሆነ

እንደደረስን ተኩስ ነው የተለዋወጥነው

ተኩሱ ልውውጡ በምን መልክ ነው ኤው አሁን ተኩስ አንድ ጊዜ ቆሞም መታኮስ ይሆናል ተኝቶም ይሆናል ወይ ደግሞ ቁጭ እንዳሉ ተኩሰው ይሆናል እንዴት ነው የተኩስ ልውውጡ

ድንገት ነው እዛ ቦታ የደረስነው እና እዛ እነሱ ባሉበት ቦታ ወደ እኛ ተኩስ የጀመሩት ነው

እየተኮሱ ምን አደረጉ እናንተ ሸሻቹ እነሱ ሸሹ

እነሱ እሮጠው ሄዱ

እነሱ እሮጠው ሄዱ

አዎ

ከአንተ ጋር ማን ነበር አሁን ለምስክርነት የመጣ

ሁለት ሰው አለ

ቆይ ቆይ ቆይ ምንድነው ተቃውሞ አስመዝግቡ አስመዝግቡ

ከዚህ በፊት በዋና ጥያቄ ተናግሯል ከእሱ ጋር ማን ማን እንደነበረ እና እየደጋገሙ ጊዜ ከመፍጀት ውጪ ሰዎቹን ደግሞ እንዲናገር ማድረግ አግባብ አይደለም የሚል ነው ተቃውሟችን

360

ይሄ ነው ተቃውሞ

አዎ

መልስ አላችሁ የምትሉት

አዎ የመስቀለኛ ጥያቄ ጥቅሙም አንዱ ይሄ ነው እኮ ያን መስክሮ የነበረውን እንደገና ጠርቶ መጠየቅ ነው በቃ ጥቅሙም አላማውም ይሄው ነው እና ስለዚህ ተቃውሞው ተቀባይነት የለውም የተከበረው ፍ/ቤት

እሺ ጥያቄው ይቀጥል ተቃውሞው አግባብ አይደለም ተብሏል ይመልስ መልሱን

እሺ መልሷል እኮ

መልሷል

ሁለት ሰዎች ነበሩ

ሌላ ጥያቄ

ሁለት ሰዎች ነበሩ ብሏል

አዎ እነሱ ሲሸሹ ከአንተ ጋር ማን ነበረ ነው ጥያቄው አሁን ከአንተ ጋር ምስክርነት የመጣ ማን አለ አብሮ ሲታኮስ የነበረ

ሁለት ሰው ነበረ

ስም ስም

አብዱለኪም መሀመድ እና አህመድ ኡስማን ነበሩ

አሁን ለምስክርነት መቅረብ ወይ

አዎ መተዋል ለምስክርነት

እሺ

አበቃችሁ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ ፍ/ቤት ቁጥር 4

አዎ ይበቃናል

እሺ አላችሁ ድጋሜ ጥያቄ ዐ/ሕግ

የለንም የተከበረው ፍ/ቤት

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ

የሞተ ሰው ነበረ ወይ በለው እስቲ

የለም

እሺ እነዚህ ተቀምጠው ነበረ ያልካቸው ሰዎች ጀማልን ጨምሮ የአባዎ አባል መሆናቸውን አንተ ታውቃለህ ወይ

አዎ አውቃለሁ ስማቸውን አላውቅም እንጂ

ምናለ

አዎ አውቃለሁ ስማቸውን ግን አላውቅም እንጂ

ጀማል አባል መሆኑን ታውቃለህ ወይ ለምሳሌ

አዎ አውቃለሁ

በምን አወቅህ እስቲ ንገረን

አባዎ ማለት አነግ ---------- ገብቶ ሲወጣ ለአት መሆኑን አውቃለሁ ከእዛም በኋላ ከእንደገና በ2000 ዓ/ም በእዛን ሰአትም ደጋፊ መሆኑን አውቃለሁ

እሺ እናመሰግናለን ከኋላ ቁጭ በል ማን ይጠራላችሁ ዐ/ህግ

አብዱመሊክ አብዱሉሀ

አብዲመሊክ በማን ላይ ነው የሚመሰክረው

በ58ኛው ተከሣሽ ላይ ነው

58ኛ

በኦሮሚያ ክልል ፌዴራላዊ ዲ/ሪ/ፐ/ብሔ/ክ
የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

382

አዎ በክስ 33 ላይ ባለው ነው

በስንተኛ ተከሣሽ ዐ/ሕግ በስንተኛ ተከሣሽ ዐ/ሕግ በስንተኛ ተከሣሽ

በ58

ማነው 58ኛ ተከሣሻችሁ

ኡመር መሀመድ አህመድ

ኡመር ኡመር መሀመድ

አዎ

ኡመር መሀመድ ኡመር መሀመድ ኡመር መሀመድ ኡመር ውጣ እዛ ላይ እዛ እዛ ላይ ውጣ ስንተኛ ተከሣሽ ነው ያላችሁት ዐ/ሕግ

58ኛ

4ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ቀርቧል በ58ኛ ተከሣሽ በስንተኛ ክስ ላይ ነው

በ33ኛ ክስ ላይ

ስም - መብዱመሊክ አብዱልወሀብ

ስራ - ገበሬ ነኝ

አድራሻ - ከምእራብ ሀረርጌ ሐረር ወረዳ - ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ዞን - ተርፌ የሚባል ቦታ ነው

ዛሬ ለምን መጣህ እዚህ

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ኡመር መሀመድ መሀሙድ

የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 2 ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ያን ተከሣሽ እስቲ እየው በለው ታውቀዋለህ ወይ

አዎ አውቀዋለሁ

ማነው ስሙ

ኡመር መሀመድ መሀሙድ

ተጣልተካል ወይ ከእሱ ጋር

የለኝም

ዝምድናስ አለህ ወይ

የለኝም

ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ ዛሬ ተከሣሹን ታውቀዋለህ ወይ በለው

አውቀዋለሁ አለ ዐ/ሕግ ሌላ ጥያቄ

እሺ እሺ እሺ ምን አድርጉ ነው የተከሰሰው

ምንድነው በአባዎ አነግ መደራጀቱን እና ዲሲሳ የሚባል እንዳደራጀም የሚለውን ሰምቻለሁ ነው

ስም ጠቅሷል ማን ማን አልክ አለው የኦነግ ስም ቢሲሳ ነው

ዲሲሳ አለ እኮ ይሰማል እኮ ሌላ ጥያቄ

አይ -------

ጠይቁ

------ አካባቢውን ነው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

364

እሺ እሺ አደራጇቸው ምን አደረጉ

7 ሰዎች ሆነን በእዛ በቡርቃ ዶዬ አካባቢ እንደተደራጀን ሲናገር ነው የሰማሁት ነው

እሺ ከእዛስ ተደራጅተው ምን አደረጉ

አላውቅም እኔ እንግዲህ ያደረጉትን ነገር

የት ነው እንዲህ ሲል የሰማከው

ቁጭ ብዬ እኔ አጠገብ ፖሊሶች ምርመራ እያደረጉለት ለፖሊሶች ሲናገር ነው የሰማሁት

መቼ ነው ይሄ ነገር -------

2000 ዓ/ም ሰኔ ወር ነው

እሺ የት አካባቢ ነው

ተይፌ ይባላል

የት ነው ተይፌ በለው

ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ውስጥ ነው

እሺ ቡርቀ ዲምቱ እሺ

ቡርቃ ዲምቱ ወረዳ ውስጥ ተይፌ የሚባል ቦታ ነው

እሺ በእዛ ጊዜ በእዛ ቦታ ላይ በእዛ ጊዜ ውስጥ ጣቢያ ስንት ሰው ነበራችሁ

እና የወረዳው ፖሊሶች አሉ ነው

እዛ ቦታ ላይ ምን ምን አደረግን ብለው ቃል ሲሰጥ ሰማህ

ቡርቃ ዶዬ በሚባል ስም ተደራጅተን ተደራጅን ያደራጀንም ዲሲሳ ነው የሚባል ዲሲሳ የሚባል ሰውዬ ነው ብሎ ሲል ሰማው ነው

እሺ ተደራጅተውስ ምን ምን አደረጉ

365

ምንም የፈፀምኩት ነገር የለም ግን ተደራጀን ብሎ ሲናገር ነው የሰማሁት

አበቃችሁ

ምንድነው የሚሰራው በለው

ማን

ድሬሳ ዶዬ የሚባለው

ትቃወማላችሁ መቃወሚያ ምንድነው ቆይ ቆይ

ሰውዬው በምስክርነት የተጠራው በዚህ ተከሣሽ ላይ ለመመሰከር ነው ይሄ ተከሣሽ እገሌ አደራጀን ብሎ ሲናገር ሰማሁ ነው የዛኛው ስራ በክስ ላይ የለ በጭብጥ ላይ የለ ይሄ ጥያቄ ሊቀርብብን አይገባም የተከበረው ፍ/ቤት

እሺ እዚህ ላይ አስተያየት ካላችሁ

ምላሽ አለን

አከሌ አከሌ አደራጀን አለ ያደራጀው ለልማት ለግንባታ ለምን እንደሆነ ሰውዬውም ያስፈልጋል ክሱም ላይ እኮ አከሌ አከሌ የተባለ እንዲህ እንዲህ የሆነ ቡድን ብለን እኮ ነው የጠቀስነው ያንን ነገር እንዲመሰክርልን ነው የፈለግነው

የተከበረው ፍ/ቤት ሲናገር ነው እኮ የተሰማው

ቆይ ቆይ

ክሱ ላይ በግልፅ አለ እኮ አከሌ በሚባል ድርጅት ተደራጅተው እንዲህ ሆነ ቡድን ብለናል ያ ያደራጃቸው ቡድን ስለመሆኑ ምንድነው ስራው ብሎ መታወቅ አለበት

ቆይ የተከበረው ፍ/ቤት

አበቃችሁ

አይ

በቃ

366

አንዴ

ምንድነው የምትሉት

ምስክሩ እኮ ደምድሞ ከእዛ በኋላ የሆነውን ነገር አላውቅም እኔ ሲናገር የሰማሁት እገሌ የተባለ አደራጀን ሲል ነው እንጂ ለምን ይደራጅ ለምን ይደራጅ አላውቅም ብሎ ደምድሞ እኮ ዘግቷል

እሱ አሁን የተከራከራችሁበት ነጥብ እሱ አይደለም እኮ አሁን እሺ ቆይ ተነጋግረን ብይን እንሰጣለን እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል ጥያቄው አግባብነት አለው ይቀጥል ተብሏል በአጭሩ መልስ መልስ ስጥ ቶሎ በል

ዲሊሳ ዶዬ ምንድነው

የኦነግ ሰራዊት ነው

ጨርሰናል

መስቀለኛ ጥያቄ ካለ

የተከሣሽ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ኤው የት ነው ይሄ ይሄን ቃሉን ሲሰጥ የሰማከው የት ነው ፖሊስ ጣቢያ ነው ፍ/ቤት ነው

ፖሊስ ጣቢያ ነው

ምርመራውን ያጣራ የነበረው ማን ነበር

አድማሱ ይባላል አንዱ አንደኛውን አላውቀውም

አድማሱ ምንድነው ስራው

የፖሊስ መርማሪ ነው

የት ፖሊስ ጣቢያ ነው ይሄ የተደረገው

ተፈ የሚባል ቦታ ነው ተፈ ፖሊስ ጣቢያ ነው

አንተ እንዴት ተጠርተህ መጣህ እንዴት መጣህ

367

ፖሊስ ነው የጠራኝ

ማን የተባለ ፖሊስ ጠራህ

ዘኩ ይባላል

አንተን ለምን መረጠህ

እንግዲህ የመረጠኝ እና የጠራኝ ሁኔታ አላውቅም እሱ ነው የሚያውቀው

ስንት ሰው ነበረ ከአንተ ሌላ ከአንተ እና ---- ከፖሊሱ ሌላ ስንት ሰው ነበረ

2 ሰዎች ነበሩ

ታውቃቸዋለህ ወይ

አደም መሀመድ አሊ የሚባል

አሁን መቷል ወይ ለምስክርነት

አዎ መቷል

እሺ አሁን ይሄ አለ የምትለው ከአለሙ እና ከአንተ ማን ቀደሞ ገባ አንድ ቦታ ተጠርተን አንድ ላይ ነው የገባነው አንድ ቦታ ነው የተጠራነው

አንድ ቦታ ነው ነበራችሁ አንድ ጋ ገባችሁ

አዎ

ስትገቡ ማን ማንን አገኛችሁ

ፖሊሶች ነበሩ ሶስት ፖሊሶች ነበሩ ከጠራን ጋራ አራተኛ ነበር

እሺ ገባችሁ

አንዴ እናቋርጣችሁ አንዴ ይቅርታ ፖሊስ እቺ ልጅ የያዘችዋን እዛ በር ላይ አስቀምጧት ከነ ወንበሯ ወንበሯን ውሰዱላት እሺ ቀጥሉ እናንተ

እሺ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፩

ሶስት ፖሊሶች ከጠራን ጋር አራት ፖሊሶች ነበሩ ስንገባ

ገባችሁ ተከሣሹ የት ነበር ይሄ ሰውዬ የት ነበር የዛኔ

እዛው ነው ያለው

እዛው ውስጥ ፖሊሶቹ ጋር ነበር

አዎ እዛው ነበር

እሺ ፖሊስ ምን ብሎ ጥያቄ ጀመረ

ምን ትሰራ ነበረ ብለው ጠየቁት

እሺ

እኔ ምንም የሰራሁት ነገር የለም ግን አዎ ብሎ ሲመልስ ኦነግ ውስጥ ምን ትሰራ ነበር ብለው ሲሉ በቡድን ተደራጅተን ነበረ በቡድን ተደራጅተን ነበረ ያም ቡድን ስሙ ማነው ሲሉት ቡርቃ ዶዬ ይባላል ስንት ሰዎች ናችሁ 7 ሰዎች ነን ብሎ መለሰ ይሄ ነው ይሄንን ነው የሰማሁት

አበቃችሁ ጥያቄ

ቆይ አላበቃንም ይሄን ብሎ ከመናገሩ በፊት ቃሉን መስጠት ወይም አለመስጠት ዝም ማለት እንደሚችል መብቱን ነገረው ወይ ፖሊስ

ከዛ በኋላ ነው ያመጡት እና አላውቅም ነው

እሺ ይሄ እሱ የሚመሰክረው ቃል ይሄ እሱ ቃሉን ከሰጠ በኋላ ምን ሆነ ያ ሰውዬው ሲናገር ይፃፍ ነበር

አዎ ይፅፉ ነበር

ምን ሆነ ያ የተፃፈው

መፃፉን እና መፈረሙን እንጂ ምንነቱ እንደሆነ አላውቅም

አልተነበበማ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 2

367

አልተነበበልንም እዛም የሄድነው ኑ እና ይሄንን ምርመራ ስናደርገው እንድትሰሙ ብለን ነው የጠራናችሁ ብለው ነው ያሉን

---- እንጂ አልተነበበለትም

አስፈረሙት እንጂ አላነበቡለትም ነው

ይበቃናል

አበቃችሁ

እናመሰግናለን

አላችሁ ድጋሜ ጥያቄ ዐ/ሕግ እሺ ድጋሜ ጥያቄ ይቀጥል

የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ የድብደባ ምልክት የስቃይ ምልክት ምን ይታይበት ነበር ወይ በለው

የለም

እንዴት ነው ታስሮ ነበር ወይስ ምን ተደርጐ ነበር ወይ

እኔ ቁጭ እንዳልኩኝ እንዲሁ በንፁህ ነው ቁጭ ብሎ ያለው ነው

ከእዛስ ቃል ሲቀበል የሚሉትን የእሱ እንዲሰማ እየተደረገ ይፃፍ ነበር ወይ

አጠገቡ ስለሆነ ስላልራቀ አዎ

በኦሮምኛ ቋንቋ ነው ወይስ በሌላ ቋንቋ ነው

በኦሮምኛ ቋንቋ ነው ሁሉም የሚናገሩት

ጨርሻለሁ

አበቃችሁ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ካለ የምስክሩ መልስ

የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፩ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ

370

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አንተ በታዛቢነት ለምን ተገኘህ

አላውቅም እንግዲህ እነሰ ናቸው ኑ እና ብለው የጠሩን ኑ ብለው የጠሩን

ሚኒሻ ነህ እንዴ የአካባቢ ታጣቂ

አዎ የቀበሌ አስተዳደር

የቀበሌ አስተዳደር

አዎ የቀበሌው አስተዳደር ነኝ

ከተከሣሹ ጋር ትተዋወቃለህ ወይ በፊት

አዎ እንተዋወቃለን

በምን ነበር የምትተዋወቁት ከእሱ ጋር ከኡመር ጋር

ያው እዛው መሀበረሰቡ ውስጥ ሲኖር ነው የማውቀው

አሁንም አብሮ ነበረ የሚኖረው

አሁንማ የለም እስር ቤት ነው ያለው

ከእዛ በፊትስ

አዎ እዛው ህብረተሰቡ ውስጥ ነበር

አብራቹ ነው የምትኖሩት

ቀበሌ ውስጥ ነው ያለው በአንዲ መንደር ውስጥም ባንሆን ቀበሌ ውስጥ ነው ያለው ያው

የኦነግ አባል መሆኑን ታውቃለህ ወይ

እሱ ከገለፀ በኋላ ነው ያወኩትኝ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

371

እስቲ እሱ ኡመር ተደራጅተን ተደራጀን ካለ በሷላ ተደራጅተን ምን አደረግን አለ ኡመር ኡመር ምን ተናገረ

ምንም አልፈፀሙም ነው ያለው

ለኡነግ እርዳታ ሰጠን አላለም ያኔ

ምንም ነገር ገና ሳልፈፅም ነው ሰራዊቱ የያዘኝ የተያዝኩትኝ

ሳይፈፅም የተያዘው ምን ላይ ነው የተያዝኩት አለ ምን አድርጌ ነው የተያዝኩት አለ ምን እንዳደረገ ነው የተያዘው

እንቅስቃሴ ላይ እያለ ነው የተያዘው

እ

በእንቅስቃሴ ላይ እያለ ነው የተያዘው

ምን አይነት እንቅስቃሴ ነው

ከተማ ውስጥ ሲሄዱር ነው የተያዘው

ካተማ ውስጥ

አዎ ሲሄዱር ነው

ምን አይነት እንቅስቃሴ አደረኩ አለ ያኔ ሲናገር የሰማከው ኡመር ይሄን አደረኩ ይሄን አደረኩ ያለው ነገር አንተ የሰማከው አለ ወይ

አልሰማሁም እንደዚህ እንደዚህ አደረኩ ብሎ ሲል አልሰማሁም

በኡነግ ውስጥ ተደራጀሁ ሲል ሰመተከዋል ወይ የዛን እለት

አዎ

እሱን ብቻ ነው የሰማሁው

በስም ነበረ ---- እና 7ሰዎች መሆናቸውን ሲገልፅ ነው የሰማሁት

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

372

ከእዛ በእዛ ተደራጅተን ይዤንን አደረግን ሲሉ ሲል አልሰማከውም

ምንም አልሰራሁም ነው ያለው

እሺ እናመሰግንሀለን ከኋላ ቁጭ በል ዐ/ሕግ በዚሁ ዛሬ የምንሰማውን ማስረጃ በህመም ውስጥ ሆነን እየሰማን ስለሆነ ትንሽ ያስቸግራል የፍትህ ስራ ስለሆነ ደግሞ በንፁህ አምሮ መሰራት አለበት ስለዚህ በእዚሁ ምክንያት ቀሪ ምስክሮቻችሁን ከእዛ በፊት ግን ዐ/ሕግ ማሳሰቢያ አለ ከእንግዲህ በኋላ የሚቀጥለው የችሎት ሂደት ባለፈው እንደተሰጠው በየ አጀንዳው 7 ምስክሮችን ነው የምንሰማው 9 የተባለው ወደ 7 አሻሽለነዋል በዚሁ መሰረት እየመረጣችሁ ማምጣት እና ማሰማት ነው በዛሬ የተያዘው 9 ነው ከ9ኞቹ 4 ተሰምቷል 5ቶቹ ይመለሳሉ 5ቶቹን ብቻ ለይታችሁ ጥሩ በፍ/ቤት ተመዝግበው እንዲመለሱ ለአበል አከፋፈል 5 ምስክሮቹን ጥሩ የተሰሙት ደምራችሁ ነው የምታመጡት ሂሳቡን

ያልተሰሙት ይናገሩልን እንዲቀርቡ

እስቲ ጠዋት የተሰሙት ስማቸውን ንገረን

አብዱለኪ ማን መሀመድ ሌላ ሁለተኛ የተሰሙ

አህመድ ኡስማን

አህመድ ማን ኡስማን

አብዱለዚዝ ማን አህመድ አህመድ ኡስማን ሶስተኛው ማነው

አህመድ ኡስማን

ሶስተኛው አህመድ ኡስማን

አዎ

4ኛው ማን ነው አብዱራህኪም መሀመድማ ተብሏል

አብዱመሊክ አብዱልወሀብ

ሌላ ነው

በኦሮሚያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

አዎ

ማነው አብዱል

አብዱመልኪ አብዱልወሀብ

5ኛው ማነው

4 ናቸው የተሰሙት

5ተኛ የመጣውስ ዛሬ ያልተሰማው ስምህ ማነው

አደም መሀመድ

አደም መሀመድ ማነው እስቲ እጅህን አውጣ አደም እጅህን አውጣ እሺ ሌላ

ኢብራሂም መሀመድ

ማን

ኢብራሂም መሀመድ

ኢብራሂም መሀመድ

20ኛ ምስክር ----

ሌላ 7ኛ

ከሊፋ ሼክኡመር

ከሊፋ ከሊፋ ሼክኡመር አንተ ነህ እሺ 8ኛ

አብዱልዋሂድ መሀመድ

ማነው እስቲ እሺ 9ኛው ማነው

አብደላ መሀመድ

ሬድዋን መሀመድ

374

ማነው ስምህ

ሬድዋን

ሬድዋን መሀመድ እሺ ዐ/ሕግ ዝም ዝርዝሩን አታውቁትም ማለት ነው

እሺ

እሺ አንተ ምንዳ የታለ ሬድዋን አብዱልዋሂድ መሀመድ ከሊፋ ሼክኡመር ኢብራሂም መሀመድ አደም መሀመድ እናንተ በሚቀጥለው ቀጠሮ ነው የምትቀርቡት በላቸው አሁን የተጠራችሁት በሚቀጥለው ቀጠሮ በእራሳችሁ ነው የምትመጡት ይሄ የፍ/ቤት ትእዛዝ ነው ስትመጡ ከመሰከራችሁ በኋላ የአበል ክፍያ ይከፈላችኋል የዛሬ እና የሚቀጥለውን ይሄ የፍ/ቤት ትእዛዝ ነው አክብራቹ እንድትገኙ ትእዛዝ ያላከበረ ፍ/ቤቱ እርምጃ ይወስዳል ዛሬ የመሰከራችሁት በላቸው እናመሰግናለን ጨርሳቹሀል ከዐ/ሕግ ጋር የአበል ክፍያችሁን ውሰዱ ፍ/ቤቱ አሏል ዐ/ሕግ በቀጣዩ 7 ምስክሮቻችሁን በቁጥር እየለያችሁ ከተራፊው መጨመር ያለበትን እየጨመራችሁ አምጥታችሁ አሰሙ በሌላ በኩል በተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ በኩል የቀረበ ማመልከቻ አለ በቃል ምንድነው የምታመለክቱት ስለ የተፃፈ ማመልከቻ ነው ወይስ ሌላ ነገር ጠኂት ያሳሰባችሁት ምንድነው በእስር ላይ ችግር አለ አስመዝግቡ አስመዝግቡ ቆይ እስቲ አንዴ አንዴ ቆይ አንዴ እስቲ አስመዝግቡ መጀመሪያ እናንተ

8ኛ ተከሣሽ እና 39ኛ ተከሣሽ ሚካኤል አብዱላሂ እና እቺ ልጅ ታመዋል ህመማቸውም ከዚህ ከሚታከሙበት ከድል ጮራ በላይ የሆነ ነው በአቶ ሚካኤል የሚሉት

8ኛ እና 30ኛ

8ኛ እና 39ኛ

ባለፈው ታክማ የለ እንዴ 8ኛዋ

አዎ ባለፈው

ማረሚያ ቤት ቆይ እስቲ

ተነሽ ተነሽ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፡ ጋሞ ቁጫ ዞን የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

375

8ኛ ባለፈው ታክመዋል አይደል

ተነሽ እቺ ነች

----- ድነው መተዋል

ድነው መተዋል

አዎ

እሷስ

አሁን

አዲስ ነው ባለፈውም አልቀረበም እሺ ምንድነው አሁን ጥያቄው

አሁን እሷ ህመም አለብኝ እየተሰቃየሁኝ ነው ያለሁት እና ወደ ሌሊት ሁላ እያመመኝ ሌሊት ሳልተኛ ነው የማድረው ስለዚህ ወደ ተሻለ ሀኪም ሄጀ ልታከም ያሳክመኝ ነው እሳቸውን አቶ ሚካኤልን በሚመለከት እኔ ህመሜ በጣም እየጠና ነው በእራሴ ገንዘብ በግል ሆስፒታል አጃቢ ብቻ ተፈቅዶልኝ በዚሁ ከተማም ቢሆን በግል ሆስፒታል ልታከም በጣም በከፍተኛ ደረጃ እጢ ነው እየተበታተነ በከፍተኛ ደረጃ ታምሜያለሁ ይላሉ እድሜያቸው 80 አመት አካባቢ ናቸው ይኸው በግልፅ የሚታዩ ናቸው ቁመ እስቲ

ማረሚያ ቤት የምትሉት ነገር አለ

አዎ

አስመዝግቡ አስመዝግቡ

የተከበረው ፍ/ቤት

ለ8ኛው መጀመሪያ ባለፈው --

ባለፈው የታመመው ድኖ ገብቷል እሳቸው አሁን በግል የሚሉት እኛ ውል ያለን ከመንግስት ከድል ጮራ ጋር ነው በግል ሆስፒታል ደግሞ ያው አይቻልም በማረሚያ ቤትም ደረጃ ማለት ነው ይሄንን ያው ከግምት ውስጥ እንዲገባልኝ እሷን በተመለከተ ደግሞ ያው ህክምና ከዚህ በላይ የሚል ነገር የለም ሁሉንም የተሟላ ነው ያለው ይህ ነው ያለኝ

376

የተከበረው ፍ/ቤት እሳቸው በግፅ ፍ/ቤቱም ሊያይ ይችላል እጪዉ ሰውነታቸውን እየተቆጣጠራቸው ነው ይሄ ሰውነታቸውን የመያዝ አይነት ነገር ስራቸውን የመጨባበጥ እሳቸው እኮ ማረሚያ ቤቱ አጃቢ ይመድብልኝ ነው በግል ገንዘቤ እታከማለሁ እኔ የማረሚያ ቤቱን ወጪ አልፈልግም የማረሚያ ቤቱን ወጪ አላስደርግም እና መሞቴ ነው እዚህ ደረጃ ላይ ነኝ ነው

እሺ ይኸው ነው ሌላ ጥያቄ የለም

አዎ ይኸው ነው ጥያቄ ተናገሪ አንቺ

ቆይ ቆይ ምንድነው እናንተ አላችሁ የምታመለክቱት ነገር እስቲ አስመዝግቡ ቢመዘገብ ይሻላል

እሺ 1ኛ ጥያቄያችን ባለፈውም ጥያቄውን ማመልከቻውን በቃል ለፍ/ቤቱ አስመዝግበን በሚቀጥለው ይታያል ተብሎ ነው አንደኛው 37ኛው ተከሣሽ አቶ አብዲ በሺር የምርቃት ስላላቸው በሐረር ቴክኒክ በሐረር ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በ29 ምረቃ አላቸው ያንኑ በተመለከተ ክቡር ፍ/ቤቱ ለወህኒ ቤቱ አስተዳደር ትእዛዝ ሰቶላቸው በአጃቢ ሄደው ያን እንዲካፈሉ ነው ሌላው ተመሳሳይ

ማነው የሚመረቀው አሁን የቤተሰብ ምረቃ ላይ ለመካፈል ነው ጥያቄው

አይደለም

እህ

የትምህርት ነው

እራሳቸው ናቸው የሚመረቁት

ተመራቂ ናቸው

ተመራቂ ናቸው እሺ እሺ ጥሩ ባለፈው አሁን ይቅረብ የተባለው ነው ዛሬ ይቅረብ የተባለው ጥያቄ ነው አይደል

አዎ

ጥሩ እሺ ሌላ

377

ሌላው ደግሞ እንደዚሁ የተያያዘ ከእሳቸው ጋር ከጤናቸው ጋር የተያያዘ ነው ከአሁን በፊት በመኪና አደጋ ተገልብጠው እጃቸው ውስጥ ብረት አለ ይሄንን አዲስ አበባ እየተመላለሱ ነበር እየታከሙ የነበረው ቀደም ሲል እና አሁንም ያንን የብረት ቀጠሮ እንትን የሚታዩበት ጊዜ ቀጠሮም አልፎባቸዋል ፍ/ቤቱ ቢፈቅድላቸው የሄንኑ አንዱ ሄደው መታየት ይፈልጋሉ ብረቱ የሚወጣበትም ሰአት ስለሆነ ማለት ነው ተመሳሳይ 23ኛውም እንዲሁ የመኪና አደጋ መገልበጥ ያለባቸው እና ይሄ መኋሂታቸውን ብዙ ጊዜ አሁን በመኝታም በምንም እየተሰቃዩ ነው እሳቸውም ህክምና ይፈልጋሉ ይኸው ነው የተከበረው ፍ/ቤት

23ኛ እና 37ኛ ተከሣሽ 23ኛ ህክምና 37ም ህክምና እና ምረቃ

አዎ

እሺ አበቃችሁ

አዎ

እሺ አንቺ ደግሞ ምንድነው እስቲ ና አስተርጓሚው የታለ ምንድነው የአንቺ ጥያቄ

ድልጮራም ወስደውኝ ነበረ እና ልቤን ያመኛል እኔ የልብ በሽተኛ ነኝ ድልጮራ ሆስፒታልም ወስደውኝ እኛ ማከም አንችልም ከአቅም በላይ ነው እና ከእኛ በላይ ነው ብለውኛል ነው የምትለው የተከበረው ፍ/ቤት ማረሚያ ቤት ከማድርበት የበለጠ ሆስፒታል የምተኛበት ነው የሚበዛው

እሺ ጥሩ የእሷ ጥያቄ ቆይ ገብቶናል ቁጭ በይ ቁጭ በይ እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል ዐ/ሕግ ቀደም ሲል የተሰጠውን ትእዛዝ እንድታከብሩ በድጋሜ ችሎቱ ተነጋግሮበት ማሳሰቢያውን በጥብቅ እንድትወስዱት በአበል አከፋፈል ላይም በተመሳሳይ ያለውን በጀት አጠቃቀምም ያለ አግባብ እንዳይወጣ በዚሁ የተመጠኑ ከርቀት ያሉ እንዲሁም ደግሞ ከቅርብ ያሉ ምስክሮች ድሬዳዋ አካባቢ የሚገኙ ምስክሮችን በቅድሚያ እያቀረባችሁ እንድታሰሙ ባለፈው በተሰጠው ትእዛዝ እያስታወሳችሁ እንዲሰሙ እንድታደርጉ ነው ይሄ 7 ኮታ የሚለውን ነገር አሁንም እንድታስቡበት በማሳሰቢያ ፍ/ቤቱ ያስተላልፋል በትእዛዝ መልክ ሌላ በተከሣሾች በኩል የቀረበ ተከሣሾች በተከሣሾች ጠበቆች በኩል የቀረበ የህክምና እና አንድ ተከሣሽ ደግሞ በተለየ ሁኔታ የምረቃ ሁኔታ ጥያቄ ቀርቧል የምረቃውም ሆነ የጤናውን በተመለከተ ሁለቱም በማረሚያ ቤት ባለው አስተዳደር ደንብ መሰረት ፍ/ቤቱ እስከሚረዳው ማረሚያ ቤቱ ይሄ ግዴታ አለበት

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

378

የማንኛውንም ተከሣሽ የጤና ሁኔታ የመንከባከብ እና ይሄን የማድረግ መሟላቱም ጭምር ማረጋገጥ አለበት ከአቅም በላይ ሲሆን ከአቅም በላይ ሲሆን ከቅም በላይ መሆኑን ደግሞ እንደዚሁ በአካባቢ በሚገኙ የህክምና ባለሞያዎች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች ሲረጋገጥ ፍ/ቤቱ ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል በማንኛውም መልክ ህክምና በሚደረግበት ሁኔታ ላይ ማዘዝ ይችላል ከዚህ መለስ ግን ይሄ መሆኑ ሳይረጋገጥ ከወዲሁ በተነሱ ጥያቄዎች ላይ የማረሚያ ቤቱን አስተዳደር እና ደንብ ተላልፎ በዚህ መልክ ይሁን ማለት ፍ/ቤቱ የተለየ ትእዛዝ አይሰጥበትም ይሄ ግን የማረሚያ ቤት ግዴታ ግን በማንኛውም መልክ ተከሣሾችን መብት በሚነካ የጤና ሁኔታ በሚያስተጓጉል ሁኔታ ለበለጠ አደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ የሚፈፀም ከሆነ ወደ ፊት እነሱ የሚያስጠይቅ ስለሆነ በዚህ መልክ ጥንቃቄ ይደረጋል ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ፍ/ቤቱ በጥብቅ ያዛል ማረጋገጫው ግን በሚቀርብበት ጊዜ በማንኛውም ሰአት ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል በጤናም ሆነ በምረቃ የተባለው በዚህ መልክ ነው የሚታየው የማረሚያ ቤቱ ተከሣሾችን ወይም እስረኞቹን ሲያመላልስ የተለያዩ ኮንስትሬት አሉበት የሚወስድበትም የሚያወጣበትም ሁኔታ እንደዚሁ የተጠበቁ ስርአት በየትም ሀገር የሚሰራ አሰራር ስላለ ከዛ ውጪ የሆነ አይሆንም በሚል በመውሰድ በእዛው የሚፈፀም ነው የሚሆነው ሌላ በተመሳሳይ በ8ኛም በ39ኛም ተከሣሾች የቀረበው የህክምና ጥያቄም በ37ኛም በ23ኛም ተመሳሳይ ስለሆነ ከፍ አሁን ቀደም ሲል በተነገረው ትእዛዝ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን በማለት አዘናል በሌላ የሚቀረው ነገር በዚህ መዝገብ ላይ የሚቀሩትን ምስክሮች ለመስማት ቀጣይ አጀንዳ መያዝ ነው ይሄ አመት ተጠናቋል ሌሎች አጣዳፊ ስራዎች ካልሆነ በስተቀረ ስለዚህ ችሎቱ መሰብሰብ በሚችልበት ጊዜ የሚቀጥለው አጀንዳ መስከረም 28 ይሆናል መስከረም 28 ላይ ዐ/ሕግ ቀጣይ ምስክሮቻችሁን እንድታቀርቡ ፍ/ቤቱ አሏል። ሀሙስ ላይ ነው የሚሆነው አስተርጓሚ ምንዳ የታለ አሁን የተባለውን በጠቅላላ ንገራቸው በቅድሚያ እናንተ እዚህ የቆማችሁት ምስክሮች ያልተሰማችሁት መስከረም 28 ትመጣላችሁ መጥሪያ የለም እራሳችሁ አውቃችሁ ትመጣላችሁ የዛሬን እና የሚቀጥለውን የምትመጡበት አበል ይከፈላቹሀል በሚቀጥለው ዛሬ ምስክርነት የሰጣችሁት 4 ምስክሮች በላቸው ምስክርነት የሰጣችሁ አራቶቻችሁ ግን በተመለከተ ዛሬ የመጣችሁበት እና መመለሻችሁን አበል በተመለከተ ከዐ/ሕግ ፅ/ቤት እንድትወስዱ ፍ/ቤቱ አሏል ስለመጣችሁ እናመሰግናለን አሁን መሄድ ትችላላችሁ አሁን ፍ/ቤቱ አሰናብቷቹሀል በላቸው ሌሎች ተከሣሾች በተመለከተ ንገራቸው አስተርጓሚ ሌሎቻችሁን በተመለከተ የምስክርነት መስማት ሂደቱ ይቀጥላል የዚህ አመት የፍ/ቤት ስራ ተጠናቋል ተጠናቋል ፍ/ቤቱ ስራ የሚጀምረው መስከረም 28 ነው በእናንተ ጉዳይ መስከረም 28 ላይ ቀሪ የዐ/ሕግ ምስክሮች

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

379

መስማት ይቀጥላል ስለዚህ ጠበቆቻችሁም ያውቃሉ እናንተም ታውቃላችሁ ማረሚያ ቤትም ስለሚያውቅ መስከረም 28 ትቀርባላችሁ በሌላ በዋስ ያላችሁ 22ኛ እና 48ኛ ተከሣሾች የታለች 22ኛ ተከሣሽ በዋስ ያላችሁ 2 ተከሣሾች ብድግ በሉ የታለች ጥራት 48ኛ ተከሣሽ ዘሀራ እናንተ በቀጣይም መስከረም 28 ነው የምትመጡት በላት ቀጠሮሽን እያከበርሽ ደግሞ ተገኚ ባለፈው የቀረሽው በማስጠንቀቂያ ታልፏል ጥንቃቄ አድርጉ ስለዚህ መስከረም 28 ነው የምትመጡት ማረሚያ ቤት በዚሁ ዐ/ሕግ ሌላ ጥያቄ የለም በዚሁ ችሎቱ ስራውን አብቅቷል።

መ/ወ

390

የመ/ቁ - 4486

ቀን - 12/4/2002

ዳኛ - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን

- ዩሱፍ መሀመድ በዚህ መዝገብ ተሰይመናል

ከሣሽ - ዐ/ሕግ አቶ እያሱ ቀርበዋል

ተከሣሽ - እነ አብዱራህማን ባሌ 73 ሰዎች ከማረሚያ ቤት 69 ተከሣሾች ቀርበዋል

መዝገቡ የተቀጠረው የዐ/ሕግ ምስክሮች ካሉ ለመስማት ነው በዚህ መሰረት የቀረቡ ምስክሮች ካለ ፍ/ቤቱ መስማት ይቀጥላል ከእዛ በፊት ግን አስተርጓሚ የለም እንዴ ዛሬ እስቲ ኦሮምኛ የሚችል ሰው በዋስ የነበራችሁ ሰዎች ቀርባቹሀል ቁጭ በሉ ምስክሮች የሉም

ከኦሮምያ ክልል ምእራብ ሐረርጌ ዞን ፖሊስ መምሪያ እና

እየተቀረፀ ስለሆነ

እሺ ምስክሮች አልቀረቡም ከኦሮምያ ክልል ምእራብ ሀረርጌ ዞን ፖሊስ መምሪያ እና ከድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር ፖሊስ ካምሺን ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የመጣልን ደብዳቤ አለ ምስክሮችን በተመለከተ የምእራብ ሐረርጌ ዞን የፃፈው ምንድነው 1ኛ አጭር ቀጠሮ ነው የተሰጠን 2ኛ ምስክሮቻችን ያሉበት አካባቢ ሀይለኛ ዝናብ እየዘነበ ገበሬውም ምርት ስብሰባ ላይ አዝመራ ስብሰባ ላይ ስለሚገኝ ወይ ወረዳዎቹም ተሽከርካሪዎች እንደ ልብ ስለማይገቡ ጭቃውም ሀይለኛ ስለሆነ ምስክሮችን ለማቀረብ አልቻልንም ስለዚህ አንድ እረዘም ያለ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጠን የሚል የምእራብ ሀረርጌ ዞን ፖሊስ መምሪያ ፅፏል ይሄንኑ ደብዳቤ የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮምሽን እንድንገነዘበው ፅፎልናል ስለዚህ የምእራብ ሀረርጌ ፖሊስ መምሪያ በነገረን መሰረት አንድ እረዘም ያለ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶን እንድናቀርባቸው እንዲታዘዝልን ነው የምንጠይቀው

381

በእናንተ በኩል የምታመለክቱት ነገር ካለ አስመዝግቡ

ይሄ መዝገብ

ስም አስመዝግቡ ስለማን

ተከላካይ ጠበቃ እንግዲህ ከ73 የ37 የ38 እና የ23 አይዳለሁም ሌሎቹን ነኝ ማለት ነው በፍቃዱ ስዩም እባላለሁ ይሄ መዝገብ ለእረጅም ጊዜ ቆይቷል እስረኞቹም ወደ 1 አመት አካባቢ የሆናቸው ይመስለኛል አሁንም ምስክር አቀራረብ ላይ ነው ምስክር የማይቀርብ ከሆነ አንድ ወደ ጎላ ተመልሶ ዋስትናው የሚታይበት ነገር ይመቻች ወይም ደግሞ ተከሣሾቹ እስር ቤት እየተጉላሉ ነው የቤተሰብ አስተዳዳሪ ናቸው መዝገቡ ተዘግቶ ምስክሮች በቀረቡ ጊዜ ጉዳይ የሚታይበት ነገር ቢመቻች ተከሣሾች ቢሰናበቱ እንጂ አሁን ባለበት ሁኔታ ምስክሮች ባለመቅረብ ምስክሮች ባለመቅረብ 80 ምስክሮች ናቸው መሰለኝ የቀረቡት እንግዲህ የተሰማው ወደ 4 መሰለኝ ከተሰማ ግን እያየን ያለነው ወደ አመታት አካበቢ ነው እስረኛ እስር ቤት ያሉት ፍ/ቤቱ ይሄንን ዳኝነት ቢሰጠን መልካም ይመስለናል

እሺ በእናንተ በኩል አስመዝግቡ እና

ኢብራሂም መሀመድ እ የ23 የ37 እና የ38ኛ ተከሣሾች ጠበቃ ክቡር ፍ/ቤቱ እንደሚያውቀው በእነዚህ ተከሣሾች ላይ ምስክር እስኪቀርብ ከአንድ አመት በላይ ነው እየተቆጠረ ያለው ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ ይሄንኑ ጉዳይ ስናመለክት ነበረ ለተከበረው ፍ/ቤት ፍ/ቤቱ አሁንም ደጋግመን የምንጠይቀው ነገር ቢኖር የፍትህ ጉዳይ ነው እና ስለ ቤተሰቡ ስላላቸው ችግር ሁሉ ከአሁን በፊት ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል ሁሉ ነገር እና የሚያውቀው ነው የተከበረው ፍ/ቤት ተከሣሹን ዐ/ሕግ እነዚህን ምስክሮች ማቅረብ ካልቻለ መዝገቡ ለጊዜው ተዘግቶ ተከሣሾቹ እንዲሰናበቱ እናመለክታለን ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ተከሣሾቹ የዋስትና መብታቸው ተጠብቆ የተከበረው ፍ/ቤት ዐ/ሕግ እስከ እዛ ድረስ ምስክሩን ለእረጅም ጊዜ እያለ እነግዲህ ክረምቱም ጭቃውም ምኑም እስኪደርቅለት ድረስ ተከሣሾቹ ወህኒ ቤት ቁጭ ብለው አይደለም መጠበቅ ያለባቸው የእነዚህ የምስክሮች መምጣት ስለዚህ ለተከበረው ፍ/ቤት የምናሳስበው አንድ ተከሣሾቹ የዋስትና መብታቸው ተጠብቆ ዐ/ሕግ ምስሩን ማቅረብ በቻለበት ጊዜ ያቅርብ አለበለዚያ ደግሞ ዐ/ሕግ የተከሣሽ ምስክሮቹን ፈልጐ እስኪያቀርብ ድረስ መዝገቡ ተዘግቶ ተከሣሾቹ እንዲሰናበቱ እናሳስባለን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

382

እሺ አሁን ዘይግይተው የቀረቡ የመጡት ጠበቃ

ከእሳቸው የተለየ ሀሳብ የለኝም በእርግጥ በአጭሩ ምስክሮች ካልቀረቡ ተከሣሾች ወህኒ ቤት ተቀምጠው መቆየት የለባቸውም በዐ/ሕግ በኩል በቂ ምክንያት ካልቀረበ ደግሞ በህጉ ቀጠሮ መሰጠትም የለበትም ከአሁን በፊትም ያለ በቂ ምክንያተ ቀጠሮ ተሰጥቷል እና አሁን ድጋሜ ቀጠሮ መሰጠት የለበትም

ስለ ማን ነው

ስለ ወ/ሮ ዱርሲቱ እና 2 ሰዎች

ማን እና ማን ናቸው

የሱፍ ጨሎ እና ዱርሲቱ አብደላ

ጠበቃ

ፀጋዬ ፊጤ

የምትሉት ነገር አለ በእናንተ በኩል ዐ/ሕግ

ምስክሮችን በተመለከተ ክቡር ፍ/ቤቱም እንደሚያውቀው የነበሩትም ጠበቆች እንደሚያውቁት ከአሁን በፊት አቅርበን በእኛ ምክንያት ሳይሆን በሰአት መጣበብ ምክንያት ብዙ ጊዜ እየቀረቡ መመለሳቸው ይታወቃል ስለዚህ ዐ/ሕግ አንድም ጊዜ እንዳላቀረበ ተብሎ የታሰበው ነገር አግባብ አይመስለኝም ሌላው ነገር ዋስትና እያሉ የሚሉት ነገር የዋስትናው ነገር እልባት ያገኘ ጉዳይ ነው ይህ ፍ/ቤት ውሳኔ ሰጥቶታል ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሰራበት የህግ ማእቀፍም ያለን አይመስለኝም 3ኛ ምክንያተ የተባለው ነገር የቀረብነው ምክንያት በቂ ምክንያት ነው በቂ ምክንያት ነው የኦሮሚያ ፖሊስ የምእራብ ሐረርጌ ፖሊስን የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮምሽን የሰጠውን ደብዳቤ ማቅረብ እንችላለን አዝመራ መሰብሰቢያ ወቅት ነው በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ ጭቃ አለ ተሽከርካሪዎች መግባት አይችሉም ለምስክሮቹ መንገር አልተቻለም እየተባለ ነው ያለው ይህ ደግሞ በቂ ምክንያት ነው ምስክሮቹ አድሬስ ካልተደረጉ ቦታው የተፈጥሯዊ በሆነ ዝናብ እና ጭቃ ምክንያት እየተጓዙ ነው ለምስክርነት ብለው አዝመራቸውን ሳይሰበሰቡ እዚህ ቢመጡ አዝመራቸው ላይ የሚደርስባቸው ኪሳራ ስላለ ከዚህ አንፃር ነው ይሄ ደግሞ ካለው

383

ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር በቂ ምክንያት ስለሆነ ለምስክርነቱ እረጅም ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶን እንድናቀርብ እንዲታዘዝ ብለን ነው የምንጠይቀው አመሰግናለሁ

ቆይ እስቲ እጃችሁን አውጡ

የድሬዳዋ አካባቢ ነዋሪዎች የሆኑ ምስክሮች አሉ

እነሱን ለማግኘት ችግር ነው

ትክክል ነው ድሬዳዋ አካባቢ የሚል ምስክር አለ ከአሁን በፊት በታዘዝነው መሰረት

ስንት ናቸው

7 7 ምስክሮች እያደረግን እንድናቀርብ ታዘን ነበረ

አዎ

በእዛ መሰረት 7 መርጠን የምእራብ ሐረርጌ ዞን ፖሊስ መምሪያ እንዲያቀርብልን ለምእራብ ሐረርጌ ዞን በድሬዳዋ ፖሊስ ኮምሽን አማካኝነት ፃፍን እየጠበቅን የነበረው እሪዛን ነው ምክንያቱም ያንን ያደረግንበት ምክንያት 1ኛ አነዛ ምስክሮች በበርካታ ተከሣሾች ላይ የሚመሰክሩ ናቸው አንዱ ምስክር በብዙዎቹ ላይ ስለሚመሰክር 2ኛ ከአሁን በፊት መጥተው የተመለሱ ናቸው በዚህ ምክንያት ለእነሱ ነው የፃፍነው ስንፅፍ መጀመሪያ ደብዳቤውን ማለት ነው 7 አድርገን ለፖሊስ ኮምሽን የፃፍነውም ይሄው አለ ለ7 እና ለ13 ብለን ፖሊስ ኮምሽን የምእራብ ሐረርጌ ዞን ፖሊስ መምሪያ የፃፈልንም የምእራብ ፖሊስ ኮምሽንም የፃፈልን ይሄ ነገር አለ በዚሁ መሰረት ፅፈን እነሱን ነበር እየተጠባበቅን የነበረው ከዛም አሁን ዛሬ ከዛ ፋክስ ተደርጐ ደብዳቤው እዚህ ለፖሊስ ኮምሽን ደርሶ የደረሰን ግን መልክት ይህ ነው ምስክር ስንጠራ 7 7 አድርገን በመጥራታችን ምክንያት የምእራብ ሐረርጌን አዘን ስለነበረ የምእራብ ሐረርጌ ጥምር ስለሆነ ነው ሁሉንም ምስክሮች በአንድ ቀን አልጠራናቸውም እና ማለት ነው

በትእዛዙ መሰረት ነው ያደረግነው ነው

በትእዛዙ መሰረት ነው ያደረግነው

----- አልፈለጋችሁም በዚህ ምክንያት ነው ነው

384

በዚህ ምክንያት መርጠንም የጠራና---

እና አላችሁ ምስክር ከድሬዳዋ

አሉን ከዚህም

ስንት ይሆናሉ

ከሐረማያም አለን በእርግጠኝነት መናገር አሁን አልችልም

በግምት ስንት ይናሉ

አይቼ መናገር ካለብኝ እንጂ አሁን አልችልም

ቢሮ ያሉ አንድ 7

ድሬዳዋ ስፔሲካል ድሬዳዎች ይኖራሉ ግን በጣም በጣት የሚቆጠሩ እና አናሳ ናቸው የሚሆኑት ግን ከዚሁ ምስራቅ ሐረርጌም አካባቢም የሚኖሩ ምስክሮች አሉን

ምን ያልህ ጊዜ ነው አሁን እነዚህን ሰዎች ለማቅረብ እንትን ቢፈቀድ እንኳን የምትጠይቁት በምን ያህል ጊዜ ታቀርባላችሁ እነዚህን ሰዎች በምእራብ ሐረርጌ የመጡትን ምስክሮች ብዙ ያውቃሉ ብዙ ይመሰክራሉ የምትሏቸው

አዎ ከአንድ ወር ያላነሰ ጊዜ እንዲሰጠን እንጠይቃለን

እሺ በእናንተ በኩል ምን አላችሁ

እጅ ማን ነው ያወጣው

እኔም አውጥቻለሁ እሳቸው

እሺ ተራ በተራ እያስመዘገባችሁ

አዎ ይሄ

እያስመዘገባችሁ

385

ምንም አይነት ከዚህ በፊትም ፍ/ቤቱ ነው አስተያየት አድርጐ ቀጠሮ የሰጣቸው እኛ እንደውም ከፍ/ቤት ጋር ነበር መነጋገር ያለብን ዐ/ሕግ ከዚያ ቀጠሮ በኋላ የእሳቸው ቀጠሮ አይደለም ማምጣት አልቻሉም በቂ ምክንያት የላቸውም ቀጠሮ አይሰጣቸውም ተብኋል ከዚህ በፊት እና ፍ/ቤቱ በራሱ ነው የሰጠው ስለዚህ አሁንም የእሳቸውን እንትን ሳይቀበል በእራሱ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ እና ይሄ ጭቃ ነው ክረምት ነው ምእራብ ሐረርጌ ምስራቅ ሐረርጌ ጤፍ የሚሰበሰብ የለም ማሽላ ነው የሀገሩ እንትን ሰብል ሲሰበስቡ ገበሬዎች የሚልም ነገር አይሰራም እና ቀጠሮ አይሰጥ ዛሬውኑ ውሳኔ ይደረግ እና አንድ እልባት እናግኝ ነው እኔ ጨርሻለሁ

አበቁ

ጨርሻለሁ

አበቃችሁ

በመሰረቱ

እያስመዘገባችሁ እያስመዘገባችሁ

ተከላካይ ጠበቃ በፍቃዱ ስዩም መሰረቱ ያው ፍ/ቤቱ መጀመሪያ ሲያዝ ላሉት የዐ/ሕግ ምስክሮች እንዲቀርብ ነበር ትእዛዝ የተላለፈው ከእዛ 087 ምስክሮች እንዲቀርቡ ነበር ትእዛዝ የተላለፈው የተመረጡ 7 ምስክሮች አሉ ተብለው እነዛ ምእራብ ሐረርጌ እንደሆኑ ተገልጿል

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ሐረሪ ክልል የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

386

እነሱ ይቅረቡ በጅምላ ሊያስረዱ ስለሚችሉ ተብሏል ይሁን እንጂ እነዚህ ምስክሮች አለመቅረባቸውን ዐ/ሕግ ከወዲሁ ካወቀ እነዚህ ድሬዳዋ አካባቢ ያሉት ምስክሮች ቀርበው ቢሰሙ ምክንያቱም መጉላላት ለማጉላላት ካልሆነ በስተቀረ እዚህ ያለው የቅርብ ያሉት የዐ/ሕግ ምስክሮች ቀርበው ቢሰሙ ኖሮ ዛሬ ችሎቱ ያለ መስክር ባሰናበተ ነበር ስለዚህ ይሄ ምክንያታዊ ነገሮችን ለማጉላላት የተደረጉ ነገሮች ግለሰቦቹ በእስር ቤት ቆይተው ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ ከማድረግ ውጪ ሌላ ነገር ስለሌለው የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ግንዛቤ ውስጥ ከቶ አሁንም ደግሞ ያለው ወራት ፀደይ እንጂ በኢትዬጲያው ፀደይ እንጂ ክረምት አለመሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ከቶ ያለ ቀጠሮ ግለሰቦቹን አዝገቡን ዘግቶ ተለዋጭ ቀጠሮ ሳይሰጥ መዝገቡን ዘግቶ ተከሣሾችን ቢያሰናብትልን

እሺ አጭር አድርጉት

እሺ ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ የተከበረው ፍ/ቤት ቀደም ሲልም እንዳመለከትኩት በተለይ የእኔ ደንበኞች 2ቱ በሽተኞች ናቸው በዚህ ላይ ደግሞ አንደኛው ከፍተኛ ሀላፊነትም ያለበት ሰው እንደሆነ ቀደም ሲልም ስናመለክት የቆየነው ነው ስለዚህ አሁንም ከተከላካይ ጠበቃው እና ከአንደኛው አብሮ ካለው ጠበቃ ጋር በተመለከተ ሁሉ ዛሬ በሚሰጠው ቀጠሮ ላይ ከአሁን በፊት ፍ/ቤቱ የመጨረሻ ቀጠሮ ነው ብሎ ለዐ/ሕግም ኡሳስቦ ቀጠሮውን ወደ ፍ/ቤቱ ተመልሷል እና ይሄ ቀጠሮ ሊሰጠው አይገባም ለዐ/ሕግ ይበቃል ከዚህ በኋላ ያለውን ቀጠሮ ፍ/ቤቱ እራሱ ወስኖ ተከሣሾቹን ሊያሰናብትልን ይገባል እላለሁ የከበረው ፍ/ቤት

እሺ

አስተርጓሚ ኦሮምኛ የሚችል ሰው ፈልጉ ኦሮምኛ የሚችል ከማረሚያ ቤት ሻረው ትሞክራለህ ና ወደዚህ ቆመህ ይሻላል እዛ አካባቢ ቆመህ ለእነሱ ባይቀዳም ባይቀረፅም ችግር የለውም ለእነሱ ትነግራቸዋለህ በእናንተ በእናንተ --- ክርክር ተሰምቶ የሚከተለው ብይን ተሰጥቷል እሺ ብይን ነው የተሰጠው እሺ ጠበቆች ብይን እየተነገረ ነው

ብ ይ ን

እሺ ግራ ቀኞችሁ አንደኛ በቀጠሮ በተመለከተ ሁለተኛ ዋስትናን በተመለከተ ነው በዋናነት አንስታችሁ ክርክር ያደረጋችሁት ዋስትናን በተመለከ ይህ ፍ/ቤት ቀደም ሲል ትእዛዝ የሰጠበት ስለሆነ በድጋሜ የሚታይ ስላልሆነ በዚሁ ይሄንን በተመለከተ ዋስትናን በተመለከተ የተነሳውን

387

ክርክር ፍ/ቤቱ አልፎታል በሌላ በኩል ቀጠሮውን በተመለከተ ግን አሁን ከፍ ሲል ለተከሣሾች በአስተርጓሚ እንደተገልፀው ይህ ጉዳይ እረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑ ይሄንኑ ታሳቢ በማድረግ የዚህ ጉዳይ ክርክር ከእንግዲህ በኋላ በየሳምንቱ የሚሰማ መሆኑን እና በዚህ መልክ አጀንዳ መያዙ እንዲታወቅ በብይን ይሄንኑ ፍ/ቤቱ ያስተላልፋል ስለዚህ ቀጣይ ቀጠሮ የሚሆነው ማለት የዛሬ ሳምንት በ20 ነው ማለት ነው እንዲህ እያለ

እኔ አልችልም አስቀድሞ የያዝኩት 3 ቀጠሮ

ስነ ስርአት አድርጉ ስነ ስርአት አድርጉ በየሳምንቱ አጀንዳ ተይዟል ምስክሮቹ በዚህ መልክ ነው የሚሰሙት በ0/ሕግ በኩል ምስክሮቹን ለማቅረብ ካለው ቦታ አይመችም ምስክሮቹን በተመለከተ በየሳምንቱ አጀንዳ መያዙን ታሳቢ በማድረግ ምስክሮቻችሁን ማሰባሰብ ከወዲሁ እንድታስቡበት እና ማሰባሰብ እንድትቀጥሉ በተገኘ ጊዜ ፍ/ቤቱ ይሰማል በማንኛውም ማክሰኞ ማክሰሀኞ በየሳምንቱ ይሄው ችሎት ለዚህ ጉዳይ ስለሚሰየም የተገኘው ምስክር በዚሁ ችሎት በዚሁ የችሎት ውሎ ይሰማል ማለት ነው ስለዚህ በሚቀጥለው ሳምንት በቅርብ የሚገኙ በተለይ ከድሬዳዋ አካባቢ የሚገኙትን አንድም ሁለትም የተገኘውን ያህል ምስክር አቅርባችሁ እንድታሰሙ ከወዲሁ እያሳሰብን በየሳምንቱ አጀንዳ መያዙን ፍ/ቤቱ ማሳወቅ ይወዳል

አቤቱታ አቤቱታ አቤቱታ

እሺ አቤቱታ ካለ እንሰማለን

እኔ ማለትም የሆነ ሌሎች ባለጉዳዬች የሰጡኝ ጉዳይ በጠቅላይ ፍ/ቤት ላይ 3 ጉዳይ አለኝ እና እኔ በዚያ ቀን አልችልም እና ፍ/ቤቱ ባይሆን

በ20 አልችልም ነው

አዎ በ21 ይደረግ

በ20 አልችልም በ21 ይደረግ ነው ሌላ ሌላ ሌላ አቤቱታ አላችሁ ሌላ አቤቱታ እናንተ አቤቱታ አላችሁ

በ20 ቀደም ሲል በክቡር ፍ/ቤቱ የተነገረ ነገር አሱን ክፍት አድርጌዋለሁ ግን የሚቀጥለው ቀጣዩ ቀጠሮ ላይ እንግዲህ በ21ም በሳምንት በሳምንት የሚቀጥል ከሆነ ምን ቀን እንደሚያ-- ስላላወቅን

388

20 ካልሆነ የሚቀጥለው ሳምንት 27 7 7 እየደመሩ መሄድ ነው

እሺ ፍ/ቤቱ በዚሁ ነጥብ ላይ ተነጋገሯል ይሄ ቀጠሮ መዝገቡ ላይ ከዚህ በፊት ከመዘግየቱ አንፃር የሚለወጥ አይደለም በየሳምንቱ ይሄ ጉዳይ ይሰማል ብይን የተሰጠው በብይኑ ቅሬታ ካላችሁ ይግባኝ ማለት ነው የሚለወጥ ነገር የለውም ሌላ በተከሣሾች እጅ ስለሚያወጡ 1 2 3 እጅ እንሰማ እና በዚሁ ችሎቱ አብቅቶ ይነሳል ማለት ነው ከኋላ ያለውን

መ/ወ

389

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 20/4/2002

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ አቶ እያሱ መኮንን ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ 73 ሰዎች ከነዚህ ውስጥ 69 ተከሳሾች ከማረሚያ ቤት ቀርበዋል 2 በዋስ ያላችሁ 2 በዋስ ያሉ ተከሳሾች ቀርበዋል::

የጠዋት ውሎ ስራውን ጀምሯል ትንሽ ዘግይተናል በስራ ምክንያት ነው ምስክሮች መቅረብ ለመጠባበቅ ነው::

ዐ/ህግ አንድ ተከሳሽ ህይወቱ ያለፈ አለ አደለም ማረጋገጫ ከእናንተ በኩል እናመጣለን ያለ ሰው ነበር አደለም ጠበቆች በአንድ ችሎት ውሎ ላይ እናቀርባለን ብላችሁ ነበር

ቀደም ሲል የነበሩ ተከላካይ ጠበቃ አቶ አድማሱ

ብለው ነበር

አዎ

ስለዚህ የሚያውቁት ነገር አለ የደረሳችሁ ነገር የለም

አዎ

ከ73ቱ ውስጥ የአንዱ ተከሳሽ ክስ የተቋረጠው ነው ሌሎቹ ሁሉም ተሟልተዋል ማለት ነው ይህ መዝገብ ዛሬ የተቀጠረው የዐ/ህግ ምስክሮች ካሉ ለመስማት ነው በዚህ መሰረት የዐ/ህግ ምስክሮች ቀርበዋል

የዐ/ህግ ምስክሮች አልቀረቡም

390

አልቀረቡም

አዎ

ለምን አልቀረቡም

ለ10 ምስክሮች መጥሪያ በቅርብ ላሉት ልከን ነበር ከ10 ውስጥ ሶስቱ ፈርመዋል ለሶስቱ ደግሞ ለቤተሰቦቻቸው ተነግሯል ሌሎቹን ለጊዜው አላገኘናቸውም ስለዚህ ያው ተገቢውን ጥረት ብናደርግም ዛሬ ሊቀርቡልን ስላልቻሉ ፈርመውና ሌሎች ለቤተሰቦቻቸው ተናግረን ያልቀረቡት ታስረው እንዲቀርቡ ሌሎቹን ደግሞ እኛ እንድናቀርብ እንዲታዘዝልን ነው የምንጠይቀው

ስንት ሰወ ነው ፈርሞ ያልመጣው

ሶስት ሰው

ሶስት ሰው

አዎ

ከየት አካባቢ ነው

ከአለማያ አካባቢ

ከአለማያ ሌሎቹስ

እዛው አካባቢ አለማያና አካባቢው ያሉትን ነው

ከሶስቱ ውጪ የፈረመ ሰው የለም

ከሶስቱ ውጪ የፈረመ የለም ሶስቱ ሎሎቹ ሶስቱ ግን ለቤተሰቦቻቸው ፖሊስ በአድራሻው ሄዶ ነግሯቸዋል ለቤተሰቦቻቸው ነግረው እንነግራቸዋለን ብለዋል

ለቤተሰቦቻቸው

አዎ

ከዚህ ውጪ ያሉትስ አሁን 6 ሰው ሆኑ ከዛ ውጪ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 6

391

ማለት መጥሪያው የላክነው ለ10 ሰዎች ነው አለማያ አካባቢ ላሉት በአንድ አካባቢ ላሉት

ለ10 ሰው ብቻ

እነሱ ነበር እየተጠበቁ የነበረው እየከፋፈልን ለማምጣት ነው ቀደም ሲል በ7 ነበር ታዘን የነበረው ከዛ በ2ኛው ትዕዛዝ ደግሞ በቅርብ በቅርብ ያሉትን እያቀረባችሁ አሰሙ የሚል ስለነበር በቅርብ ያሉት ድሬዳዋ አካባቢ ያሉትን ሰዎች አለማያ ያሉትን ለማቅረብ በዚህ መልኩ ነበር የተንቀሳቀስነው።

እሺ የምትሉት አለ በጠበቆች በኩል ከሌለ የለም በሉን

አይ ሃላፊው ከተወው ያው ምስክሮችን ቢያንስ የድሬዳዋዎችን እንኳን ተሰብስበው መጥተው በዚህ ቀጠሮ እንዲታይ ነው የተፈለገው ከዐ/ህግ የምንረዳው አደለም የድሬዳዋዎቹ አለማያዎቹንም ሊመጡ እንዳልቻሉ ነው የአለማያዎቹ የድሬዳዋዎቹ ራሳቸው ሊመጡ እንዳልቻሉ ነው እና የሚገልጸው ስለዚህ የተከሳሾቹ እዚህ መቆየት ምስክሮቹ የማይገኙ ከሆነ የመብታቸውን ጉዳይ ማለት ምስክር የመሰማት መብቱ ራሱ ያጡ የተጣመመባቸው ይመስለኛል እና ነፃ የሆነ የመገመት መብታቸው ምክንያቱም ባለፈው በክረምት ጉዳይ ነው የቀረው አሁን ደግሞ እዚህ ላይ ነው ያሉት ፍ/ቤቱ አሁንም መዝገቡን ይዝጋው ይዝጋና እነሱን ያሰናብትና ምስክሮች ተሰባስበው በመጡ ጊዜ የሁለት ጊዜ የ2 ቀን ችሎት እኮ ነው 80 ሰው ለመስማት 2 ቀን ችሎት ውስጥ ምስክሮች ሊሰሙ ይችላሉ እውነታውን ለማረጋገጥ ግን ምስክሮቹ እዚህ ተቀምጠው ደግሞ ረጅም ጊዜ ቆየ ሁለት አመት ሊሞላቸው ነው ስለዚህ ፍ/ቤቱ በዚህ ዳኝነት ቢሰጥበት ነው የተሻለ የሚሆነው።

ሌሎቻችሁ የምትሉት ካለ በአጭሩ ጠበቃ ማን ነው

ጠበቃ ኢብራሂም መሀመድ 37 እና 38 ተከሳሾች ጠበቃ ቀደም ሲል እንደተሰጠው ማሳሰቢያ መሰረት ፍ/ቤቱም ቀደም ሲልም ይሄንኑ ሁኔታ ስናሳስብ ነበር አሁንም ፍትህን በሁለቱም አቅጣጫ ያለውን የፍትህ ሚዛን አይቶ ይጠበቅልን ነው ዐ/ህግ እንደተባለው ያሉትን ምስክሮች አንድ ላይ በሚመቸው ጊዜ አሰባስቦ ያቅርብና ያሰማ እስከዛ ድረስ ግን ተከሳሾቹ የዐ/ህግን ምስክሮች ለመጠበቅ ወህኒ ቤት ውስጥ መቆየት የለባቸው የተከበረው ፍ/ቤት እና ይሄንን ጉዳይ ቀደም ሲልም ስሰጥ በነበረው ማሳሰቢያ መሰረት ክቡር ፍ/ቤቱ ከግምት ውስጥ አስገብቶ አንድ ውሳኔ ቢሰጠን።

392

እሺ የምትሉት አለ

አዎ የአንድ ቀን የሁለት ቀን ችሎት የሚባለው ምስክሮቹ በአጠቃላይ 87 ምስክር ነው ያለን 87 ምስክር በአንድ ቀን ብናመጣ ወይም በሁለት ቀን ብናመጣ ካለው የሰዓት ማነስ ላይሰሙልን ይችላሉ ስለዚህ በነበረን ነገር ዛሬ እያደረግን ያለነው ምስክሮችን እየከፋፈልን ማምጣት ነው እየከፋፈልን ማምጣት ደግሞ ተገቢውን ጥረት አድርገና ምስክሮችንም በተመለከተ እኛው እዛ ቦታቸው ድረስ ወስደን ያገኘናቸውን አስፈርመን ያላገኘናቸውን ደግሞ ለቤተሰቦቻቸው ነግረን ተመልሰናል ተገቢውን ጥረት አድርገናል ፈርመው ካልቀረቡ የዐ/ህግ ችግር ሳይሆን የሰዎቹ የፍትህን አለማገዝ ባህሪውን ነው የሚያመላክተው በእነሱ ደግሞ ምስክሮቹ ፍትህን አለማገዝ ምክንያት ፍትህ መጓደል የለበትም ስለሆነም እንደውም ምስክሮች አንዳንዶቹ ከአሁን በፊትም ቀርበን ነበር እና አንቀርብም ምናምን የሚል ነገር አዝማሚያ አላቸው ይህንኑም ለፍ/ቤቱ እያሳሰብን ነው ለሚቀጥለው ጊዜ ግን እኛው መኪና ይዘን ከፖሊስ ጋር ተባብረን ይዘናቸው እንቀርባለን አሁን ይሄ ከዐ/ህግ ድክመት ተብሎ መመዝገብ የዐ/ህግ ምንም አይነት ድክመት የለበትም ተገቢውን ጥረት ማድረግ የሚገባውን ነገር ሁሉ አድርጓል ከዚህ ቀሪውን ነገር ደግሞ ተከላካይ ጠበቃዎችም ቢሆኑ ለፍትህ ነው የቆሙት እኛም ለፍትህ ነው የቆምነው ለፍትህ የቆመ አካል ደግሞ ፍትህን ያጓደለውን አካል ነው እንጂ መውቀስ ያለበት እዚህ ፊት ለፊት የሚገኘውን አካል ብቻ የሱ ችግር ነው ፍትህ ይጓደል ነፃ ይውጡ ማለት ተገቢ አይመስለኝም አመሰግናለሁ።

እስቲ መተማመኛ የሰጡት ዝርዝር እስቲ ዐ/ህግ 7 ሰው ነው እንዴ ያስፈረማችሁት

ያስፈረምነው ሶስት ሰው ነው እሱ ላይ የቀረቡት --------- አስፈላጊ ከሆነ መተማመኛው መሸኛውም ይኸው አለ

ብ ይ ን

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል ብይን ተሰጥቷል በዚህ መዝገብ ላይ እርግጥ ነው ምስክሮች ለመስማት ቀጠሮ እየተሰጠ ነው ያለው ካለፈው ሳምንት አንስቶ ግን ቀጠሮው በየሳምንቱ እንዲሆንና የቀረቡትን ያህል እንዲሰሙ የሚል ትዕዛዝ በዚህ ፍ/ቤት ሰጥቷል ይሄ ትዕዛዝ አሁን በዚሁ ትዕዛዝ ነው ፍ/ቤቱ መስማት የሚቀጥለው በተጨማሪ ግን ማሳሰቢያ በትዕዛዝም ሊወሰድ የሚገባው የቀረቡትን ያህል ምስክሮች ይሄ ፍ/ቤት ከቀረቡለት በማንኛውም ሰዓት

393

ያሉትን ሌሎች ፕሮግራሞች ወይም አጀንዳዎች በመሰረዝ የሚሰማ መሆኑን መታወቅ አለበት በዚህ መልኩ ነው የሚሰራው ስለዚህ ይሄንን ማሳሰቢያ በትዕዛዝ መልክ ውሰዱትና ቀደም ሲል በተሰጠው 7 ይቅረብ በሚለውም ትዕዛዝ --------- መቅረብ የሚችሉት ምስክሮች በቁጥር ሳይሆን መቅረብ የሚችሉ ሁሉም ሰው በእኩል ላይመቸው ይችላል መቅረብ የሚችለውን ምስክር ሁሉም እየቀረበ ቁጥራቸው እየታወቀ መስማት የምንችልበትን ሁኔታ እያመቻቸን የምንሰማቸው መሆኑ ታሳቢ በማድረግ ምስክሮቹ በሚቀጥለው ቀጠሮ በተመሳሳይ በተያዘው ትዕዛዝ መሰረት እያቀረባችሁ እንድታሰሙ በጥብቅ ፍ/ቤቱ አሟል በሌላ በኩል ዛሬ ፈርመው ባልቀረቡት ሶስት ምስክሮች ፖሊስ ዐ/ህግ ባሳሰባችሁ መሰረት ምስክሮችን በመኪና ሄደን አሰባስበን እናመጣለን ስላላችሁ እነዚህንም ሶስት ተከሳሾች አስራችሁ እንድታመጧቸው ምስክሮቹ ሶስት ምስክሮች ታስረው እንዲመጡ ፍ/ቤቱ አሟል ስለዚህ ቀጠሮ ለዛሬ ሳምንት ነው በዚህ መዝገብ የተያዘው አጀንዳ ማለት ነው በ27 ማረሚያ ቤት ታቀርቧቸዋላችሁ በዚሁ የዚህ ችሎት ስራ አብቅቷል።

ማ/ተ

394

የመ/ቁ - 04486

ቀን - ጥር 19/2002 ዓ/ም

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰዒድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ

ከሣሽ - የፌደራል ዐ/ሕግ እያሱ መኮንን ቀርበዋል

ተከሣሾች - እነ አብዱራህማን ባሌ 73 ሰዎች 69 ተከሣሾች ከማረሚያ ቤት ቀርበዋል

1 ተከሣሽ በብይን ተሰናብቷል 2 ተከሣሾች በዋስ አሉ በዋስ ያላችሁት ቀርባቹሀል 2 ተከሣሾች በዋስ ቀርበዋል መዝገቡ የተቀጠረው የዐ/ሕግ ምስክሮች ካሉ ለመስማት ነው ምስክሮች ቀርበዋል ዐ/ሕግ

አዎ ቀርበዋል

እሺ ጥሯቸው የዐ/ሕግ ምስክሮችን እሺ ዐ/ሕግ 15 ምስክሮች መቅረባቸውን አስመዝግበዋል ቅደም ተከተል የምትፈልጓቸው አሉ የሚሰማ ወይስ

አዎ አዎ በቅደም ተከተል

ነው እሺ ማን ይጠራላችሁ

6ኛ ምስክር ከድር አህመድ ሙሳ

በቅድሚያ ስንት ምስክሮች እንደመጡ አስመዝግቡ ስላልተቀረፀ

19 ምስክሮች ቀርበዋል

እሺ ማን ይጠራላችሁ

ከድር አህመድ

395

ከድር አህመድ አለም መሀላ አስፈፅማቸው ምስክሮቹ በደንቡ መሰረት ቃለ መሀላ ፈፅመዋል ይችላሉ ኦሮምኛ በደንብ አማርኛስ ለ2 መሆንም ትችላላችሁ -- ሲያስፈልግ እየሰካካችሁ ማድረግ ትችላላችሁ አማርኛ በደንብ ይችላሉ

አዎ እችላለሁ

እስቲ አስፈፅሚቸው መሀላ ይምላሉ አይ እዛ አምጣው እና እንትን በላቸው በእውነት የትርጉም ስራ ለመስራት ለፍ/ቤቱ በመሀላ ስር ሆኜ አረጋግጣለሁ በሉ

ስምህ ማነው በሉት

አሜ ሼካ የሱን እሱን ነው የሚጠይቁት እኮ

አዎ እሱን እየጠየቁት መልሱን ነው እርሶ የሚነግሩን

6ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ከድር አህመድ

ስራ - እርሻ ግብርና

አድራሻ - ምእራብ ሀረርጌ ሂርና ከተማ ነው

እሺ ጥሩ

ለምንድነው የመጣከው ዛሬ ለምስክርነት ነው ወይ

ለምስክርነት ነው የመጣሁ

ጥሩ እዚህ ያሉትን ተከሣሾችን የምታውቃቸው አሉ ወይ መለየት ትችላለህ ወይ

እዚህ ካለ ያ ሰው

ማንን ታወቃለህ እስቲ በስም ግለፀን ቁም እና አሳየን የምታውቀውን ብቻ ቁም እና የምታውቀውን ከዚህ ውስጥ ለይ በሉት ቁም እና ቀስ ብለህ እያየህ አሳየን የምታውቀውን ብቻ በሉት በ2ቱም አቅጣጫ ፖሊሶች እርዱት የምታውቃቸውን ብቻ አሳይ

እሱን ብቻ ነው የማውቀው

396

እሺ ማነው ስምህ

ስንተኛ ነህ ተራ ቁጥርህን አታውቀውም

40ኛ

40

40 አዎ

አህመድ ሼኪ ዩሱፍ አህመድ ነህ እሺ 40ኛ ተከሣሽን ብቻ በችሎቱ ለይቶ አሳይቷል

እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

አህመድ ሼካን አውቅሀላሁ ብለዋል በእሱ ጉዳይ ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለሀል ምንድነው እስቲ ያደረገው እሱ ይሄንን ለፍ/ቤቱ በአጭሩ

ቆይ ለማስተርጉም እንዲረዳዎት አጭር አጭር በሉት

አጭር አጭር በሉት

እሳቸው እንዲተረጉሙ በሉት

እሱ ቤት መጥቼ ኮሌጅ እየተማርኩኝ ነኝ የእሱን ቤት ተከራይቼ እየተማርኩ ነበር

እሺ ከዛ

ለ1 ወር አከራይቼ ተቀምጫለሁ በዚህን ጊዜ በአባዎ ስር እናከራያለን ብለው ይሄንን ቃል አስተላለፉልን

የተከበረው ፍ/ቤት አስተርጓሚ ሌላ ሰው ቢቀየር ምንም እንያቱም አሁን በትክክል እየተረጎሙልንም አይደለም ተከራይቼ ነው የኖርኩት ሲል የነበረውን አከራይቼ ነው ብለው የተናገሩት እና ሌላ አስተርጓሚ ካለ ቢፈለግልን ይሻላል

397

እስቲ ሌላ አስተርጓሚ ካለ ጠይቁ እና ኑ ምንዳ ለምንድነው የቀረው አለም እስከ እዛ አድምጡ እስቲ ስጠው እንትኑን ጥሩ እሺ ጥያቄውን ቀጥል

እሺ አህመድ ሼካ ያደረገውን ነገር ንገረን በድጋሜ በለው የጀመርከውን

ድምፅህን ከፍ አድርግ አንተ እሱ ሲመልስ ብቻ ንገረን አንተ የምታስተረጉምበት ነው እሱ በቃ አንተ በቃል መንገር ብቻ ነው

እሺ

እሺ ቀጥል አስተርጉማ እያስተረጉምክ

በ1997 የእሱ እቤት ተከራይቼ ነበረ ለ1 ወር ለ1 ወር ያህል ተከራይቼ ነበረ በዛ ወር መጨረሻ ላይ በአባዎ ስር እንደራጅ ብሎ ይሄንን ሀሳብ ለእኔ አስተላለፈልኝ በዚህ ተደራጅተን ይሄንን መንገስት እናፈናቅል አሁንም ከእዛ በኋላ በሂርና ከተማ ውስጥ 2 ቀን 50 50 ብር ብር እናዋጣ ተብሎ 50 50 ብር 2 ጊዜ አዋተናል ከእኔ ላይ ለዚህ መዋጮ ተብሎ አዋጥቻለሁ ይሄን ነገር ስንጀምር መሀላ አስገቡን ይሄን ሚስጥ ካወጣን መሀላ ፈፅመናል ይሄን እጭት ካወጣን ብለን

ገንዘቡ ለምን ጉዳይ ነው የወጣው በለው

እነኚህ አነጐችን ለመደገፍ

አባዎ ምንድነው በለው ለምን የተቋቋመ ነው በለው

እነኚህ እንደሚባለው ከሆነ ኦሮሞን ነፃ የሚያወጣ ነው ይባላል

አንተስ በበኩልህ ምንድነው ያደረከው እስቲ ይሄንን ተናገር በለው

መሀላ ፈፅመናል ይሄንን እጭት ካወጣን ብለን

ገንዘቡ ለምን ጉዳይ ነው የወጣው በለው

እነኚህ አነጐችን ለመደገፍ

አባዎ ምንድነው በለው ለምን የተቋቋመ ነው በለው

398

እነኚህ እንደሚባለው ከሆነ ኦሮሞን ነፃ የሚያወጣ ነው ይባላል

አንተስ በበኩልህ ምነድነው ያደረከው ይሄንን ተናገር በለው

እኔ በእራሴ በኩል 2 ጊዜ 50 50 ብር አዋጥቻለሁ

ከእዛስ በኋላ ምን አደረክ

እኔም ከእዛ በኋላ 2 ሰው አደራጀሁት ይሄንን ነገር እንድሰራ ያደረገኝ ደግሞ አህመድ ሼካ ነው እኔ የማውቀው ይሄንን ያህል ነው

የት ቦታ ነው ይሄ ነገር የተፈፀመው በልልን

ሂርና አና ቱሉ ነው

የሚባል ቦታ ነው እሺ ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

አበቃችሁ ለተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ የፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ የምስክሩ መልስ

የፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አቶ ከድር አንተ 50 አወጣሁ ነው ለማን ሰጠከው

ለአህመድ ሼካ ሰጠሁት

ማን ነበረ እንደዚህ ብሎ ሲነግርህ ብሩን ሲቀበልህ ከአንተ እና ከእሱ ሌላ ሰው ነበረ እንዴ

አዎ ሌላ ሰውም ነበረ

ማን

ኢብራሂም ጐፈር የሚባል በዛን ጊዜ በወቅቱ ነበረ

ዛሬ መታል እንዴ ለምስክርነት

አልመጣም

ዛሬ ለምስክርነት አልመጣም ስንት ወር ቆየህ በዚህ ሁኔታ ስንት ወር ቆየህ

399

ከአንድ ወር ይበልጥ አልቆየሁም የአንድ ወር ያህል አብሬ ቆይቻለሁ

ኤው አንድ ወር ሳይሞላህ ነው እንዴ ታዲያ የ2 ወር መዋጮ የከፈልከው በየወሩ 50 ብር ነው የማወጣው ብለህል ስለዚህ

በ1 ወር ውስጥ ነው 50 50 ብር የከፈልኩት እንጂ በየወር አይደለም ይሄን የከፈልኩት መጀመሪያ ሲቋቋም ይሄ ሲነገረኝ ከፈልኩ እንደገና በሚቀጥለው ከፈልኩ እንጂ በየወሩ አይደለም

በገባህ በስንተኛው ቀን ተነጋገርክ እንደዚህ አይነቱን ንግግር ቤቱን በተከራየህ በስንተኛው ቀን እኮ ቤቱ መቼ ገባህ መቼ ተከራየህ ቤቱን

ሀምሌ ብሏል ቅድም ሐምሌ ወር ነው ቤት ተከራይቼ የነበረው ብሏል

አዎ እኮ ከገባ ከስንት ቀን በኋላ ነው ነው

በ1997 እዛ እቤት ሐምሌ ወር ተከራይቼ ገብቻለሁ ቀኑን ግን በውል አላውቀውም

ኤው ጥያቄውን ንገረው

በስንተኛው ቀን ገንዘብ ከፈልክ ቅድም ያልከውን ገንዘብ

አዎ ወይንም በስንተኛው ቀን ጥያቄው ቀረበልህ

እሺ ምንድነው ሐምሌ ወር ውስጥ ያው እዛ እቤት እንደገባሁ አውቀዋለሁ በሐምሌ ወር ውስጥ ደግሞ እዛው እንደገባሁ ይሄ ጥያቄ እንደቀረበልኝ እና የዛን ጊዜም እንደከፈልኩ ይሄንን አስታውሳለሁ ቀኑን ግን በውል ይሄን ቀን ነው ብዬ በውል አላውቀውም

ሌላ ጥያቄ ጨረሳችሁ

ና እስቲ ና በዚህ

አማክሩ ሁሉንም በዚህ መልክ እያንዳንዱን መጠየቅ እድል መስጠት ባይቻልም

ኤው በስንት ብር ተከራየ ቤቱን

30 ብር ነው የተከራየሁት

400

ስንት ክፍል ቤት ነው

1 ክፍል ነው

ግቢው ውስጥ ስንት ክፍል ቤት አለ

ግቢው ስንት ክላስ እንዳለው አላውቅም ግን እኔ 1 ክላስ ነው የተከራየሁት እዛ ተከራይቼ እንደኖርኩ ግን አሁንም እዚህ አለ እኔ እዛ እንደኖርኩ የሚያውቀኝ ሰው አሁንም እዚህ አለ እዛ ግቢ እንደተከራየሁ

እሺ አበቃችሁ አይደለ

ምንድነው እሱ የሚሰራው

አስተማሪ ነው

አንተስ

እኔ የገብርና

ኸረ በእዛን ጊዜ ነው በእዛን ጊዜ

የግብርና ት/ት ማሻሻያ በዛን ሰአት እዛ እየወሰድኩ ነበረ

ቤቱን የተከራየከው አንተ እራስህ ጠይቀህ ነው ወይንስ በደላላ ነው

በእራሴ ጠይቄ ነው የገባሁት

የመጀመሪያ ቤት ሳጣ ቀጥታ ሄጄ እራሴ ስጠይቀው እዛ አገኘሁ እዛ ገባሁ

ግን የክፍሉን ብዛት አታውቀም ስንት ክፍል እንዳለው

ተመልሷል እሱ ሌላ ጥያቄ

እሱን አላውቀውም ብሏል

ይበቃናል

እሺ በዚሁ ይበቃል ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ አለም

ዘዐ(

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

እስቲ ቅድም ሚስጥር ካወጣችሁ በሚል ምለናል ብለሀል ምን ማለት ነው በለው የምን ሚስጥር ነው በለው

እነዚህ በእዚህ በአባዎ ስር መደራጀታችን ይዜንን ነገር እንዳናወጣ ካወጣን ያ መሀላ እንዲይዘን ለማድረግ ነው መሀላ የፈፀምነው

የስፈፀመህ ማን ነው መሀላውን

ይዜ ነው

ማነው ስሙ

አህመድ

አሁን ያሳየከን

አዎ

እዚህ የለየከው ተከሣሽ

አዎ

እሱ ነው ያስማለህ

አዎ

በምንድነው ያስማለህ

እንደዚ እጅ ተያይዘን ነው መሀላ የገባነው

እስቲ ትነግረናለህ እጅ ከተያያዛችሁ በኋላ ያላችሁትን

አሁን የ ኦሮሞ አፅም አሁን ይዜ ማለት የኦሮም በ7 ቤት አመፅ ማለት ነው አሁን እሱ አነጋገሩ ማለት ነው

እሺ አፅም ነው አፀም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፓብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 4 ርክብ

402

አፅም

እሺ አፅም እሺ

የኦሮሞ ጀግኖች አጥንት እንዲወጋን

ተባብላችሁ ነው እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ መሀላው ይዤ ነው በለው

አዎ

እሺ ጥሩ አባዎ የምትለው ማንን ነው ማንን ለመጥቀስ ነው ማንን ለማመልከት ነው አባዎ የምትለው ድርጅት ነው ወይ በለው

በዛን ጊዜ ያው የኦሮሞ ነጫ አውጪ ግንባር ኦሮሞን ነፃ የሚያወጣ ነው

የእዛ አባል ነው አንተ የሆንከው

አዎ በዛን ጊዜ በወቅቱ አዎ

ጥያቄውን ጠይቀው

በዛን ሰአት እንደዛ እንድሆን ነው እኔንም ያደራጀኝ ከእዛ ተነስቼ እኔም እኮ 2 ሰው አደራጅቻለሁ ነው የሚለው

ጥሩ የእዛ አባል ነው የሆንከው አንተ ማለት ነው በለው

አዎ

እሺ አህመድ ሼካን እንዴት አመንከው በለው እስቲ እሱ ሲጠይቅህ ሲመለምልህ እንዴት እሱን ተቀበልከው በለው

ይዤን መጀመሪያ ይዤንን ሀሳብ ከእሱ ጋር የጀመርኩት በሜሶ በኩል ኢሳ መጥቶ በሜሶ በኩል ኢሳዎች መጥተው አንድን ሴት ደፈሩ በመጥፎ አደፋፈር

እሺ ቀጥል

በእዛ ነገር ከእዛ ይዤንን ነገር ተነስቶን ከእኔ ጋር ይዤንን ነገር አወራን ይዤንን ነገር እንዳወራን ከእዛ በኋላ ይዤንን ሀሳብ ደግሞ አመጣ በእዛ ችግር ተነስቼ እኔ ደግሞ ይዤን እሱ ሀሳቡን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ

403

ያመጣውን ልቀበል ቻልኩት እኔ ከእዛ በኋላ የመንግስት ስትራቴጂ አውቄ ከእዛ በኋላም ስልጠናም ከወሰድኩ በኋላ ይሄ ነገር ስህተት እንደሆንኩ ተረድቼ ተመለስኩ ለእራሴ ነው የሚለው

2 መለመልኩ ያልከው ሰዎች እንዴት ነው የመለመልካቸው በለው

እነዚህ መዋጮ እኔ እንዳዋጣሁ እንዳዋጡት ነው እኔም እነዚህን አባል እንዲሆኑ ያደረኩት አልኩት እንጂ ብሩን አልተቀበልኩትም

ጥሩ አህመድ ሼክ መልምል በሎህል እንዴ መህላ ስትገባ

አዎ በእዛ ውስጥ ያሉት 5 ሰዎች ናቸው 5ቱም 5 5 ሰው እንዲያደራጅ እኔ የወንድሜን እና እህቴን ያገባ ነው 2ቱን ያው 2 ሰው ነው ያገኘሁት 5 ሰው አላገኘሁም

ጥሩ አንተ ገንዘብ ለማን ነው የከፈልከው

ለአህመድ ነው የከፈልኩት እኔ እሱ ነው የተቀበለኝ

እሺ

አህመድ ሼካ በኦነግ ስር እንደተደራጁ ሲነግራችሁ ከአንተ ሌላ ማን ነበረ

ከ5 4ቱን አስታውሳቸዋለሁ እነዚህ 5ቱ ከእኔ ጋር እንዳደራጀ እሱ አገኘዋለሁ

እነማን ናቸው 5ቱ

እ

እነማን ናቸው

ደጋን ጉራሬ

ሌላ

መህመድ አብዶ

ሌላ

ዘዐሃ

መሀመድ የሚባል

ሌላ

አባስ የሚባል

ሌላውን አላውቅም ብሏል

ስንቱን ነው የምታውቀው 3ቱን

4 ከእሱ ጋር 4

አሁን አሉ እንዴ እነሱ ዛሬ ለምስክርነት መጥተዋል

አንዱ ከሀገርም የለም

አሁን ከ5ቱ እዚህ ውስጥ ያለ አለ ወይ ዛሬ ለምስክርነት የተጠራ

የሉም

አህመድ ሼክ የሰበሰበውን ገንዘብ ወዴት አደረገ በለው ታውቃለህ ወይ

ይሄንን ገንዘብ ሰብስቧል ለእነዚህ ለአባሞች ተብሎ ተሰብስቧል ይሄ ብር ይላክ አይላክ ወዴት እንዳደረሰው ግን የማውቀው ነገር የለም

እሺ እናመሰግንሀለን ጨርሰህል ከኋላ ቁጭ በል አስቀምጡት ቀጣይ ማን ይጠራላችሁ ዐ/ሕግ

27ኛ ምስክር መሀመድ ሁሴን

27ኛ

አዎ

መሀላ አስፈፅማችሁታል ምስክሩ መሀላ ፈፅሟል

27ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - መሀመድ ሁሴን ሸሪፋ

405

ስራ - ገበሬ

አድራሻ - ምዕራብ ሀረርጌ

ለምስክርነት ነው ወይ የመጣከው

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

አሁን አንዴ ትቆም እና እዚህ ከተከሰሱት መሀላ የምታውቀውን ብቻ ትለይልናለህ ተረጋግተህ በለው ተረጋግተህ ዞር ብለህ የምታውቀውን ለይ አሳዩት በ2ቱም በኩል ስምምት ማን ነው ተነስ 2ቱን ነው ከዚህ መሀል የምታውቃቸው ወይ በለው

አዎ እነዚህ 2ቱን ናቸው የማውቃቸው

ስማቸውን ታውቃለህ ወይ እስቲ ንገረን

ሀጂ ጣሀ ነው አንዱ

ሀጂ ጣሀ የትኛው ነው ሀጂ ጣሀ

አና

እሺ ያኛውስ

ሼክ ከዲር ቱራ

እሺ ሀጂ ጣሀ 44ኛ ተከሣሽን እና 57ኛ ተከሣሽ ሼክ ከዲር ቱራ 57ኛን ለይቷል ጥሩ ከእነሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ ከ2ቱ ጋር

ምንም የለንም አንድ አካባቢ ነን

እሺ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

መሀመድ እስቲ ሀጂ ጣሀ ሀሰን እና ሼክ ከዲር በወቅቱ ያደረጉትን በእነሱ ላይ የምትመሰክረውን ያደረጉትን የምታወቁውን ነገር ለፍ/ቤቱ አስረዳ

ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 1

ሀጂ ጣሀ ላይ የአባዎ አባል መሆን 71000 ብር ለአባዎ መሰጠቱን አባዎች 3 አባሎች ከኩርፋ ላይ መተው በመኪና ሰንበቱ አደረሱት ዋቤ ቀሎ የሚባል አካባቢ ላይ ሀጂ ጣሀ እና ሼክ ከድር ሶዳቶ የሚባል ላይ አደረሱት ከእዛ በኋላ ሀጂ ጠሀን ሞኮረኒ አንድ ኪስ ለእነሱ ሰጠ

እስቲ ከፍ ድምፅህን

ከእዛ በኋላ 6000 እና 1 ማክሮፍ ሽጉጥ የእኛ የመከላከያ ሰራዊት ለእነሱ ሰጠ እስከ እዚህ ነው የማውቀው ነው

መቼ ነው ይሄ ነገር የሆነው

በ2000

ወሩን ታስታውሳለህ ወይ ወሩን ካስታወስከው ቦታውስ

ወሩን አላስታውሰውም

ቦታው ቦታው

አና ቡርቃዲምቱ የሚባል

አሁን ከነገርካቸው ሌላ በ6000 ብር እና እንዲሁ ከማካሮፍ ሽጉጥ ውጪ ለመከላከያ ሰራዊት የተሰጠ ነገር አለ ወይ በለው

ከዚህ ውጪ ምንም የማውቀው ነገር የለም

እነዚህ ከማን ነው የተያዙት በለው

ፋርጋርቱ የሚባል የአባዎ የኦነጉ ማለት ነው እሱ ሲያዝ እሱ ጋር እንዳለ መከላከያዎቹ ሲይዙት አከሌ ጋር አለ ብለው ሲጠቁሙ እሱም ተያዘ በእዛ ምክንያት ነው ይሄ በር ሊወጣ የቻለው

ብሩን ያወጣው ማን ነው ማነው እሱ በለው

ሀጂ ጣሀ ነው ከእራሱ እቤት 6000 እና ሽጉጡንም ያ ፋርጋሶ የሚባል ሰውዬ ስለ ኦነጉ ሲጠቁም መከላከያዎች ይዘው ሲያመጡ ከእራሱ እቤት አውጥቶ ሰጠ ነው

407

እሺ ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

ጥሩ ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ለተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ የምስክሩ መልስ ጥያቄ ካለ ይቀጥል

የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አንተ ምን ልታደርግ ሄደህ ነው ይሄንን ያየከው

ድምፃችሁን ከፍ አድርጉ ድመፃችሁን

አይሰማም እኮ አንተ የምትናገረው አንተ እሱን የምትጠይቀው ድምፅ እኮ ሊሰማ ይገባል

እሺ

ጠይቀዋ

ጠይቀዋ ጥያቄውን

አንተ ምን ልታደርግ ሄደህ ነው ይሄንን ያየከው

ምን ልታደርግ ሄደህ አየህ ይሄንን

ይሄንን ነገር ለማየት ነው እኔ እዛም ቦታ የሄድኩት

ማን ጠራህ

እኔ በዛን ሰአት ቀበሌውስጠ ተመራጭም ታጣቂ ነኝ ይሄንን ነገር ውስጥ ውስጥ የምከታተል ስራ ነበረኝ እና ይሄ ነገር ስራዬም ስለሆነ ነው

ሌላ ጥያቄ

እሺ አሁን አንተ ይሄ ሰውዬ ተያዘ ይሄኛው ሰውዬ መራ የምትለው ሰውዬ በፊት ታውቀው ነበረ ወይ በለው እስቲ

አላውቀውም

ሌላ ጥያቄ

ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

እሺ ይሄ 71000 የምትለው አይተካል ወይ አንተ በአይንህ

ይሄ ይታወቃል በአይኔ አይቻለሁ 71000

የት

ሰንበቲ የምትባል ቦታ ላይ ነው ያየሁት

ማን ይዛት

ሀጂ ጣሀ እጅ

ሀጂ ጣሀ ይሄንን ብር ከየት አመጣው

አንድ አስተማሪ በሮዳ ላይ አምጥቶ ለእሱ አምጥቶ እንደሰጠ ነው የማውቀው

ማን ነገረህ ይሄን እንዴት አወቅህ በለው እስቲ

እነዚህ ነገሮች ውስጡን በምንከታተልበት ደርሰንበት ነው

አይደለም እንዴት አወቅህ አንተ ማን ነገረህ ላንተ

እኛ በዛን ሰአት ምስክር ነበረን በተጨባጭ ከእነሱ ጋር የነበረ ሰው ነበረ

ማን ይባላል

ማሩፍ የሚባል ነበረ

የት ነው አሁን ያለው

አሁን የት እንዳለ አላውቅም

አንተ መርማሪ ፖሊስ ነህ አንተ ፖሊስ ነህ/ሽ ወይ በለው ወይንስ ደህንነት ነህ ወይ

እኔ በእዛን ሰአት ሚኒሻ ታጣቂ ነኝ እንጂ ፖሊስም አይደለሁም ግን --

ሌላ ጥያቄ ተመልሷል እኮ

እሺ

409

ቆይ ቆይ ቆይ

ይሄን ጉዳይ አንተ አሁን እከታተል ነበር ብለሀል እንድትከታተል ማን ነው የሾመህ

ተቃውሞ አላችሁ አስመዝግቡ እየተመዘገበ ነው

1ኛ ስራውን ተናግሯል የቀበሌው ፀጥታ ሰራተኛ ነኝ ይሄ ደግሞ በማንኛችንም የምንገነዘበው እንግዲህ የደህንነትን ስራ የሚሰሩት እነሱ ናቸው የአካባቢውን ፀጥታ የሚያስከብሩት ታጣቂ ነኝ ብሏል በዚህ ስራው አጋጣሚ እንደሆነ እየመሰከረ ነው 2ኛ ተጨማሪ

ይሄ ሰውዬ --

ቆይ ቆይ

ተጨማሪ አለን ይሄንን በህዝብ እና በመንግስት ላይ የተነሳን ነገር ማን ሾመህ አይባልም ማንኛችንም -- ግዴታ ስላለብን ማን ሾመህ መን ላከህ ተብሎ ሊጠየቅም አይገባውም እነሱ ምስክሩን ሀላስ ማድረጊያ አይነት ነገር ስለሆነ ጥያቄውን እንቃወማለን

የተከበረው ፍ/ቤት አንድ ሰው አንድን ነገር አጣራሁ ሲል ወይ ከሰዎች ጋር ሆኖ ነው ወይም ይሄንን ተከታተል ተብሎ ከበላይ ሀለቃ ተነግሮት ነው በተጨባጭ ሄዶ ነው እንጂ ግለሰቡ ዝም ብሎ እንደዚህ አየሁ ማለት ብቃት አለው ወይ ነው ጥያቄው ይሄ ነው

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበታል ሌላ ጥያቄ ካለ ቀጥሉ የላችሁም

ምንድነው ስለ መሳሪያውስ ሽጉጥ አየሁ የምትለው የማን ነው ሽጉጡ የማን እንደሆነ ታውቃለህ

ይሄ ሽጉጥ የሀጂ ጣሀ ይባላል እና ገዛውም ይባላል ግን በትክክለኛ የእሱ ከየት እንዳመጣ ከየት እንደገዛም አይታወቅም ነው የሚለው

ሌላ ጥያቄ

እሺ ፍቃድ ይኑረው አይኑረው አታውቅም/ሪፐብሊክ

ሰማሁ ነው ያለው እንጂ እንዲህ ሲባል ሰማሁኝ የሀጂ ጣሀ ነው ሲባል አበቃችሁ

ያረጋግጥልን

ሀ/0

ጠይቀዋ

ይሄ ሽጉጥ ፍቃድ የኑረው አይኑረው በምን ታውቃለህ

ከየት እንደገዛው አላውቀም ግን ፍቃዱን አውጥቶበታል

ፍቃዱን አውጥቶበታል

አዎ

ይበቃናል

እሺ ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ሕግ የላችሁም

ድጋሜ ጥያቄ የለንም

ድጋሜ ጥያቄ የለም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

71000 ብር አንድ አስተማሪ ለሀጂ ጣሀ እንደሰጠው የሰማህ መሆኑን ወይም ያየህ መሆኑን ነግረከናል ያ አስተማሪ ያንን ብር ለምን እንደሰጠው ታውቃለህ ወይ

አዎ አውቀዋለሁ ለምን እንደሰጠው አውቀዋለሁ

ለምንድነው

ለአባዎች እንዲሰጥ ነው

እንዴት አወቅህ

እኛ ኪሚኒሻዎች እና ከፖሊሶች ጋር ሆነን ይሄንን ነገር በምንከታተልበት ሰአት ይሄ ብር ቀጥታ ወደ አባዎች እንደሚደረስ በምስክሮች ያረጋገጥን ነው

ከማን ጋር ሆነህ ነው ያረጋገጥከው

ከፖሊሶች ጋር ሆነን ነው ነው

እንዴት አድርጋችሁ ነው ያረጋገጣችሁት

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ክፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

በይበልጥ ይሄ የተያዘው ከአባዎ ኢትፋርጋሱ የሚባል በዋናነት በተጨባጭ ዋናዎቹ የተገኙት ከእሱ ነው ግን ከእዛም ደግሞ የሚከታተሉ አብረው ሲሰሩ የነበረው ወደ እኛ የመጡት የነበሩ ከእነዛም አጊኝተናል በይበልጥ ግን በዋናነት ከእነሱ የተያዘ ያ ነው ሁሉ ነገር ያወጣው ነው

ብሩ እንዴት ሆነ 71000 ብሩ እንዴት ሆነ ከእዛ በኋላ

ይሄ 71000 ለእነሱ ተሰጥቷል ለአባዎቹ ተሰጥቷል ሳይሰጥ በፊት ነው ያያችሁት ብሩን አይቻለሁ ስላልክ ነው

ብሩ እንደተሰበሰበ ሀጂ ጣሀ ጋር እንደደረሰ ታወቀ ከእዛ በኋላ እኛ ሳንደርስበት ፋርጋሱ ጋር ደረሰ ከእዛ በኋላ መከላከያዎቹ ፋረጋሱን ያዙት ፋርጋሱ ጋር እንደደረሰ ብሩ ታወቀ

71000 ብሩን አይቻለሁ ብለሀል ቅድም ማን እጅ ሆኖ ነው ያየከው

ሀጂ ጣሀ እጅ ነው ያየሁት

ከእዛ በኋላ ይሄ ብር እንዴት ሆነ

ለአባዎቹ ተሰጥቷል

ማን ሰጠ

ሀጂ ጣሀ ለረሺድ አብዶ የሚባል ሰጠ ረሺድ አብዶ ደግሞ ለ ፋርጋሱ የሚባል የአባዎ ተሰጠ

ይሄን ገንዘብ የኦነግ ከሆነ ለምን አልያዝክም የፀጥታ ሰራተኛም ከነበርክ ገንዘቡ ሳይሄድ

በይዛን ሰአት እነሱ በሀይለኛ ተበትነው ነበረ የእነሱን በጣም ተበትነው ስለነበር እኛም እራሱ በጣም እንፈራ ነበረ እና በዛን ሰአት ሀይል ነበረ ጉዳዩን ብቻ ከመከታተል ያለፈ አቅም የለንም

ገንዘቡን እንዴት ለየህ 71000 ብር ይሁን ይብለጥ ይነስ ሌላ ነገር ይሁን

ይሄ ሀጂ ጣሀ እራሱ እኛ ደህና ሰው አድርጎን እንቆጥረው ነበረ ከእኛ መኪናም ጋር አብሮ ከእኛ ጋርም ይንቀሳቀስ ነበረ ከእዛ በኋላ ግን በምስክር ይሄ ፋርጋሱ የሚባል ከተያዘ በኋላ ነው እሱ ላይ ያረጋገጥነው

71000 ብሩን ቆጥረህ ነበረ ወይ አንተ

412

እኔ በአይኔ አልቆጠርኩትም

እንዴት አወቅህ ታዲያ የገንዘቡን መጠን

ምስክሮቹ ነው ይሄንን የለዩልን እንጂ እኔ በአይኔ አልቆጠርኩም

አንተ ገንዘቡን አይተካል ወይ ወይንስ የተሰማውን ነገር ነው እየነገርከን ያለው

በአይኔም አይቻለሁ ግን አልቆጠርኩትም እንጂ በአይኔ አይቻለሁ ነው የሚለው

ሀጂ አብዲስ ምንድነው ያደረገው ሀጂ ሼክ ከድር

አንድ ሞባይል ከነቻርጁ ማለት ነው ሀጂ ጠሀ ነው የሰጠኝ ብሎ እሱ ጋር ተገኝቷል

ምን አይነት ሞባይል ነው

ቶሪያ የሚባል ሞባይል

ምንድነው ቶሪያ

ቶሪያ የሚባል ሞባይል

ምንድነው ቶሪያ

የሚጠቀምት ግንኙነት አባዎች የሚጠቀሙበት የግንኙት ማስተላለፊያ ነው እንደ መገናኛ ማለት ነው

አሁን ሰው ከሚጠቀመው ሞባይል የተለየ ሞባይል ነው ወይንስ አንድ አይነት ነው

በቃ የዚህ ሞባይል --- አይኮ ይሄ መከላከያዎች የሚይዙት የለም ትንንሾቹ

እህ

ያ ነው ነው የሚለው

ሀጂ አብዲ ለምን ሰጠኝ አለ

እ

ለምንድነው የሰጠኝ አለ ሀጂ አብዲ

ሀጂ ጣሀ ለፋረጋሱ አድርስ ብሎ ሰጠው ፋርጋሱም ይሄን ነገር እቃውን ሳያደርስ ፋርጋሱም ተያዘ ሀጂ ጣሀም ተያዘ እኔ ያንን ነገር አወጣሁ እኔም እዚህ እኔ ጋ ያለውን አውጥቻለሁ ብሎ በመሀከል እቃው ተያዘ ፋርጋሱም ጋር ሳይደርስ እዚህ ጋ መሀከል እነኚህ ተያዙ መከላከያዎች ያዙት ነው የሚለው

አሁን ተያዘ ያልከው ሼክ ከድር ላይ ነው ወይ የተያዘው ይሄ የመገናኛ መሳሪያ የተያዘው ማን እጅ ነው በለው

ሼክ ከድር እጅ ላይ ነው የተያዘው

ጠይቀው ባክህ አንተ

ሼክ ከድር እጅ ላይ ነው የተያዘው

ጥሩ ይሄ ፋርጋሱ ያልከው ማን ማንን ነው መርቶ ያስያዘው በለው እስቲ

ሼክ ከድር ሀጂ ጣሀን አስያዘ

አስያዘ ጥሩ ያኔ እሱ እየመራ ሲያዙ ምን ተያዘ በተጨማሪ በለው

አንድ ፍየልም እንዳረደላቸው

ማን

ሼክ ከድር

እሺ

እ አባዎች በተቀመጡበት መንገዱን እያስቀየሰ መከላከያዎችም እንዳያገኙ ታጣቂዎችም እንዳያጉኙ መንገድ በተለያየ መንገድ ሲመራ እንደነበረ ነው እነዚህን ነው የማውቀው

መርቶ ሲያሲዝ ምን ተደረገ ከእጃቸው ላይ ሌላ

በቃ ይሄ መገናኛ ብቻ ነው የተያዘው በእጁ በእጁን ሰአት ሼክ ከድር እጅ ላይ የተያዘው መገናኛ ነው

ዘዘ

ይሄ 6000 ብር እና ሽጉጥ ያልከው ነገር እስቲ

ይሄንንም ሀጂ ጣሀ ሲያዝ በእራሱ ጊዜ ሄዶ 6000 እና ሽጉጡንም አውጥቶ አመጣ

71000 ብሩስ የዛን እለት ነው ሌላ ጊዜ ነው እሱ ምን ተዋጥቶ ምን መጣ በምስክሮች አረጋገጥን ያልከው

ይሄ የተለያየ ነው

የተለያየ ጊዜ ነው

አዎ

ብዙ እርቀት አለው እንዴ ጊዜ ልዩነት ልዩነት በጣም አላቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው በእረጅም ጊዜ ውስጥ ነው

ይሄ 71000 ቆይቷል ሀጂ ጣሀ ግን ያ ቱራ የሚባል ከተያዘ በኋላ ሀጂ ጠሀም ከተያዘ በኋላ የወጣ ነው እና ልዩነት አለ ጊዜ ነበረ ክፍተት ነበረው

ጥሩ አንተ ምን ያህል ጊዜ በክትትል ሰርተሀል ይሄ እንደዚህ አይነት ነገር ስትከታተሉ

ከ2000 ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ እዛው ነው ያለሁት በዚህ ስራ ነው አሁንም እስከ አሁንም ስቲል እየሰራሁ ያለሁት

በፊት እንፈራ ነበር ሀይል የለም ያልከው ምንድነው በለው

በእዛን ጊዜ የነበረው መንግስት ፖሊስም አላደራጀም ታጣቂም በይበልጥ አላደራጀም መከላከያም አልነበረም በዛን ጊዜ አባዎች በብዛት ነበረ የእነሱ ህዝብ የተደራጀ በሰፊው ስለነበረ እኛ እንፈራ ነበረ ከእዛ በኋላ ግን ይሄ ነገር ከታወቀ በኋላ መከላከያ መጣ ፌደራል ፖሊስ የኦሮሚያም መጣ በይበልጥ ተደራጀ ከእዛ በኋላ ነው ነገሮች እየወጡ የመጡት እና በእዛን ጊዜ ክፍተት ነበረ ነው

ከሼክ ከድር ላይ ከመገናኛ መሳሪያ ውጪ ሌላ ያገኘው ነገር አለ ወይ

ይሄ ነው የተያዘው

ፋርጋሶ ምን ማለት ነው በለው እስቲ ማን ነው በለው

ዘለና

የአባዎች አዛዥ ነው

አዛዥ ነው ጊዜው መቼ ነበረ መገመት ትችላለህ ጊዜውን

በእዛ በ2000 ውስጥ ነው የተያዘው

በ2000 የት ነው ያለው አሁን በለው

ያው መንግስት እጅ እንዳለ ነው የማውቀው የት ግን እንዳለ አላውቀውም

ምን ስልጣን ነበረው እንዴ ወታደራዊ ስልጣን ነበረው በአባዎ ውስጥ በለው

አዎ አለው

ምንድነው እስቲ እሱን ማእረጉን ንገረን

እሱ በምእራብ ሀረርጌ እና ምስራቅ ሀረርጌ እንደ አዛዥ ነው የሚቆጠረው አዛዥ ነው

ጥሩ እነዚህ 2 ያሳየካቸው ተከሣሾች የእዛ አካባቢ ነዋሪዎች ናቸው ወይ

አዎ የእዛ ነዋሪ ናቸው

አባዎ ምን ማለት ነው በለው እስቲ ይሄ መጠሪያ ለምንድነው የሚሰራው

ያው አባዎ ማለት ስንቀይረው በተዘዋዋሪ ሌባ ናቸው

እኮ ምን ማለት ነው መጠሪያውን ተርጉምልን እስቲ

ሽፍታ ማለት ነው

ድርጅት ነው ወይ

ስሙ ድርጅት ነው እና ያው

ታውቀዋለህ ወይ ስሙን የድርጅቱን ስም ታውቃለህ ወይ

በአባዎ ነው የማውቀው

ጥሩ መሪዎቹንስ ታውቃለህ ወይ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፩ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ዘ/6

እኔ በይበልጥ የማውቀው ፋርጋሱን ነው

ጥሩ እናመሰግንሀለን ጨርሰህለ ከኋላ ቁጭ በል ቀጣይ ምስክር ማን ይጠራላችሁ ዐ/ሕግ

30ኛ ሰይፈ አብዲ

30ኛ

አዎ

ሰኢድን ጥሩ 30ኛ

ሰይፈ አብዲ

ሰይፈ

አዎ

ሰይፈ አብዲ ኡመር

3ኛ የዐ/ሕግ ምስክር በዛሬው ችሎት በ3ኛ ተራ ቁጥር ቀርቧል ይሰማል መሀላ አስፈፅሙት ምስክሩ መሀላ ፈፅሟል

30ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ሰይፈ አብዶ ኡመር

ስራ - ታጣቂ ነኝ

አድራሻ - ኢርቆ ዴካ ወረዳ

ለምስክርነት ነው ወይ የመጣከው

አዎ

ጥሩ አንዴ ትነሳ እና እዚህ ውስጥ የምታውቀውን ተከሣሽ ብቻ ትለይልናለህ የምታውቀውን ብቻ ተነስተህ እረጋ ብለህ እየዞርክ እይ በለው ፖሊሶች ያስተናግዱት ፖሊሶች አስተናግዱ ሙሉ ስምህን በድጋሜ ንገረን

417

ስም - ሰይፈ አብዶ ኡመር

ስራ - የአካባቢ ታጣቂ

አድራሻ - ቡርቃፌንቶ

አሁን ካሳየከን ፀብ ዝምድና አለህ ወይ

አዎ አውቃቸዋለሁ

ፀብ ዝምድና አለህ ወይ ተጣልተሀል

የለኝም

ዝምድና አለህ

የለኝም

ጥሩ ለምስክርነት ነው የመጣከው

አዎ

ስማቸውን ታውቃቸዋለህ ወይ

አዎ አውቀዋለሁ

ንገረን

አንዱ ሀጂ ጣሀ ይባላል

እሺ 1ኛውስ

አንድ ሼክ ከዲር ይባላል

እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

አሀ ሌላ የለየከው ሰው አለ 3ኛ

አዎ

ለ19

ጥሩ እሱስ ማን ነው ማነው ስሙ

አካባቢ ሀገሩን ነው የማውቀው እሱ ስሙ ጠፋብኝ

ስሙ ጠፋብህ ግን እሱን ታውቀዋለህ

ስሙ ጠፋብኝ ግን አካባቢውን አውቀዋለሁ

ታውቀዋለህ

አዎ

ማነው ስምህ በለው አማርኛ ትችላለህ አይደል

አዎ

ማነህ ስምህ ዩሱፍ ስንተኛ ተራ ቁጥር ነህ

15

ዩሱፍ ጫሎ አህመድ

አዎ

ጥሩ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

ሰይፈ የመጣሁት ለምስክርነት ነው እነዚህን አውቃቸዋለሁ ምንድነው ያደረጉት እስቲ ለፍ/ቤቱ ዘርዘር አድርገህ አብራራ በእያንዳንዳቸው ላይ

ሀጂ ጣሀ ያደረገው ከ2000 ጀምሮ 71000 ብር ለአባዎች እንዳደረሰ እና መኮሮኒ ሱኳር የአባዎች 3 አባዎች በመኪና ጭኖ ከሰንበቲ እንዳደረሰ እና ወስዶ እንዳደረሰ ነው

እሺ

6000 ሽጉጥ እና እነዚህንም ከእሱ እንዳደረሰው

እሺ የአሁኑን ድገመው ምንድነው ያለው አሁን

ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ ... ዩ/ቤት ቁጥር ...

ዘ/ዓ

6000 እና ሽጉጥም ለመከላከያ እንደሰጠም አውቀዋለሁ

እሺ የማን ናቸው በለው

በወቅቱ የእኔ ነው የምለው

ቦታው የት ነው

አንዴ አንዴ አንዴ

ቦታው የት ነው

ከይሴ የምትባል ቦታ ነው

ዩሱፍ ጨሎን በተመለከተ እና ሼክ ከድርንስ በተ*መለከተ የምታውቀውን ለፍ/ቤት አስረዳ

ሼክ ከድር መከላከያዎች እንዳያገኙ እንደሚያስተላልፍ ይዛንን አውቃለሁ ሼክ ከድር እንደገና ደግሞ ይዛ መገናኛ የተባለውም ለኦነጎች ይሰጥ እንደነበር ነው ይዛንን ነው የማውቀው ዩሱፍ ጨሎ ደግሞ ከሐረማ አካባቢና ብርም ሰብስቦ እህልም ጭምር በበዴይሳ በኩል አድርጎ ለኦነግ እንደሚያደርስ ራሱ ሲናገር ሰምቻለሁ በቆሎም አጠቃላይ አንድ ላይ

መገናኛው ምንድን ነው

ሶላር ቱሪያ የሚባል ነው

ሶላር ቱሪያ ምንድን ነው ለምንድን ነው የሚያገለግለው

ወደ ውጪ ከፀሐይ ላይ ስለሚሞላ የውጭ ግንኙነት ያደርጋል ወደ ውጭ

ቅድም አባዎችን በመኪናው ጭኖ ወስዷቸዋል ሸኝቷቸዋል ከማን ጋር ሆኖ ነው ይዛንን ያደረገው

ከሼክ ከድር ጋር ሆኖ ነው

የት ድረስ ነው የወሰዷቸው

እስከ ዋቤ ድረስ ነው

የፌዴራሊ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፕብሊክ

420

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

አበቃችሁ

አዎ

እሺ ለተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ የምስክሩ መልስ እንደሚከተለው ተመዝግቧል

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

71 ሺህ ብር እማን ጋር ተገኘ ነው የምትለው

ጣሃ እኔ ነኝ ለአባዎች ያደረስኩት ነው የሚለው

ጣሃ እኔ ነኝ ያደረስኩት ብሎ ሲናገር ነው እንጂ የሰማከው አላየህም

እኔ ነኝ ያደረስኩት ብሎ ሲል ነው የሰማሁት እንጂ በአይኔ አላየሁም

ማን ሲጠይቀው

ዐ/ህግ እና ፖሊስ ሲጠይቅ ነው የሰማሁት

መቼ

በ2001

የት

ቡርቃዴንቶ ጤፊ የምትባል ቦታ ውስጥ

ምንድን ነው ቢሮ ነው ሜዳ ነው

ቢሮ ውስጥ ነው

የምን ቢሮ ነው

ህክምና ቢሮ ነው

ማን ይባላሉ ዐ/ህግ እና ፖሊሶቹ ታውቃቸዋለህ

የኢፌዴሪ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ ቡሬ ከፍተኛው ፍ/ቤት

421

አዎ አውቃቸዋለሁ

እነማን ናቸው

ዐ/ህጉ መሀመድ ይባላል ፖሊሱ ደግሞ ሽብሩ ይባላል

እየው አሁን አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ይሄንን ሰውዬ ሲጠይቁት ና ብለው ቃሉን ሲጠይቁት መጀመሪያ ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኝነቱን አረጋገጠላቸው ወይ

በፍላጎቱ ነው የምሰጠው ይሄንን ቃል በምሰጥበት ሰዓት ተገድጄ ሳይሆን ተመትቼም ሳይሆን በፍላጎቱ ነው የምሰጠው ብሎ ነው

ተፃፈ ወይ ያ ቃል እየተፃፈ ነው ወይ

አዎ እየተፃፈ ነው

ማን ነው ይጽፍ የነበረው

ፖሊስና ዐ/ህግ በዛን ሰዓት እየፃፉ ነበር

ሁለቱም ናቸው እንዴ የሚጽፉት

ፖሊሱ ይጠይቃል ዐ/ህጉ ይፅፍ ነበር

አንተ ያንን የሚፃፈውን ወረቀት ፈረመበት ወይ ሰውየው

አዎ ፈርሚል

በዛን ጊዜ ይሄ ሰውዬ የት ነበር የነበረው ከየት ነው ያመጡት አንተ ለመስማት የበቃከው ከየት አመጡት አንተስ ከየት መጣህ

እኔም በዛን ሰዓት ተጠርቼ ነው የሄድኩት ከዛ እነዚህ ሰዎች ደግሞ በፖሊስ ጣቢያ ተጠርተው ነው የመጡት

ማን ቀድሞ ገባ

ጣሃ ነው መጀመሪያ የገባው

4/22

ከአንተ እና ከጣሃ ማን ገባ እዛ ምርመራ ክፍል ውስጥ

እኔ ነኝ መጀመሪያ የገባሁት ከጣሃ በፊት

ከአንተ ሌላ ማን ነበር እንዳንተ የምታውቀው ከአንተ ሌላ ማን ነበር

ከታዛቢዎች አንዱ በዛን ሰዓት የተጠሩት ወደ 5 ናቸው

ማን ማን ናቸው

አንዱ ራሴ ነኝ አንዱ መሀመድ ሁሴን ይባላል አንዱ አብዲ ይባላል አንዱ ማሩፍ ይባላል አንዱን ስሙን አላስታውስም

አሁን ለምስክርነት መጥተዋል ወይ

ሶስት ሰው መጥቷል

ማን ማን

አንዱ እኔ ነኝ አንዱ መሀመድ ሁሴን ነው አንዱ አብዲ ነው

ሌላ ጥያቄ መሀመድ ሁሴን እና አብዲ አሉ ተብሏል ሌላ ጥያቄ

ማን ከአንተ እና ከአብዲ መሀመድ ሁሴን ማን በፊት ገባ እዛ ምርመራ ክፍል

ከነዚህ እኔ እቀድማቸዋለሁ እኔ ቀድሜ ገባሁ

ከመሀመድ ሁሴን እና ከአብዲስ ማን ቀድሞ መጣ

መሀመድ ሁሴን ነው ቀድሞ የገባ

ከዛ በኋላ አብዲ መጣ ሶስተኛ እሺ

አማክሯቸዋ እዚህ ቆመዋል እነሱንም ጠይቋቸዋ

ቅድም የተጠየቅንበት ቦታ የህክምና ቦታ ነው ብለሃል አደለ እንዴ አሁን ደግሞ ፖሊስ ጣቢያ አደረከው የትኛው ነው ትክክለኛው

423

ይሄ ቦታ እኔ የምለው እዛ የህክምና ክላስ ውስጥ ፖሊስ ነው የሚሰራበት እዛ ነው የሚሰሩት ፖሊሶቹ ቦታው አንድ ነው የተለያየ አይደለም

ሌላ ጥያቄ

ይሄ ብር አሁን 70 ሺህ ብር የምትለው በምን አወቅህ አንተ 71 ሺህ ብር የምትለው ይሄንን 71 ሺህ ብር እንዴት አወቅህ አየከው ወይ ቆጠርከው ወይ ተያዘ ወይ ከሰውየው እጅ

እኔ 71 ሺህ ብር ተሰጠኝ አደረስኩ ሲል ነው ራሱ የሰማሁት እንጂ እኔ አላየሁምም

ቆይ ቆይ እያስታወሳችሁ ቅድም መልሷል ደጋግማችሁ አትጠይቁት ሌላ ጥያቄ

6 ሺህ ብር እና ሽጉጥ የምትለው ከየት መጣ

እሱ የሚለው የራሴን የአባዎች ነው ብዬ ራሴን 6 ሺህ እና ሽጉጡንም የራሴን የአባዎ ነው ብዬ ነው የሰጠሁት ለመከላከያዎች ሲናገር ነው የሰማሁት

ነው እንጂ የአባዎች ነው ብዬ ሰጠሁ እንጂ ንብረቱ የራሴ ነው ነው 6 ሺህ ብር እና ሽጉጡ

አዎ

ሀጂ ጣሃ ተደብድቦ አላየካቸውም እጃቸው ቆስሎ ታስረው የፊጥኝ ታስረው እጃቸው ቆስሎ ተደብድበው ይሄ አሁን የምታየው ጠባሳ በገመድ ተሰርስሮ ገብቶ አላየህም የዛን ጊዜ

ተቃውሞ አለ ቆይ መቃወሚያ አለ ቆይ

በዐ/ህግ ዋና ጥያቄአችን ላይ ያላነሳነው እና ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለው ነገር ስለሆነ ጥያቄአቸው ውድቅ ይደረግልን በዋና ጥያቄ ላይ አላነሳንም መስቀለኛ ጥያቄ የሚነሳው ደግሞ በዋና ጥያቄ ላይ ከተነሳው ነገር ላይ ተነስቶ ስለሆነ ነው

የተከበረው ፍ/ቤት እናስረዳ ይሄ ሰውዬ ይሄንን ቃል ሊሰጥ የቻለው ተደብድቤ ነው እጄ በገመድ ታስሮ ነው ቆስዬ ነው መከላከያ ሰራዊቱ ደብድቦኝ ነው ገብቼ ይሄንን ቃል የተናገርኩት ነው እና ከጥያቄው ጋር የተያያዘ ነው ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት እኮ የሚስችል ነው ነፃ ቃል አይደለም የሰጠው

እሺ ጥያቄው ይቀጥል ተብሏል

እኚህ ሰውዬ በመከላከያ ሰራዊቱ ተደብድበው ተገርፈው እጃቸው ቆስሎ ገመድ ሰርስሮ ይዟቸው አላየህም

እኔ አላየሁም

ሌላ ጥያቄ

ምንም ጉዳት በአካላቸው ላይ አላየህም

አላየሁም አለ ሌላ ጥያቄ

እሺ ጥያቄ አበቃችሁ

በእውቀቱ በኩል አብቅተናል

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ህግ እርሶ አያውቁትም እንዴ ለሁሉም ነው ፍ/ቤቱ የሰማው እኮ

አይ የግል ጠበቃ እኮ ገዝተው አምጥተዋል

ማን ነበር ጠበቃህ

ዩሱፍ እሺ ትጠይቃለህ

አዎ

እሺ የ45ኛ ተከሳሽ ዩሱፍ ጨሎ መስቀለኛ ጥያቄ አማርኛ ትችላለህ

የ45ኛ ተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ

እችላለሁ

እሺ እንዲተረጎም ነው

እሺ እንዲተረጎም ያን ጊዜ ይዤ ገንዘብ ከአለማያ በኩል የመጣ የበቆሎ ገንዘብ ነው ብዬ አላልኩም ወይ

ብሏል አላለም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

4/25

ስለ በቆሎም ተናግሯል በቆሎ እዛ እልካለሁ ብሎ ተናግሮ ነበር

ጥያቄ ከጨረስክ በቃኝ በል

መቼ ነው

በ2001 ዓ/ም

ብሎ መልሷል

አዎ

በ2001 ዓ/ም

እሺ የተከሰስኩት ይያዝልኝ በ2000 ነው

ማብራሪያ ተው ተባልክ ባክህ

እሺ

በአቃህ ጥያቄውን መጀመሪያ ለእኛ ተርጉም

የተጠየኩት በአገሬ ነው በሌላ አገር ነው በለው

ምን ማለት ነው ቆይ እስቲ ቆይ ዩሱፍ ጨሎ አማርኛ የምትጠይቅ ከሆነ ጠይቅ ፍ/ቤቱ መስማት አለበት

የተጠየኩበት ቦታ የት ነው በልልኝ

ቡርቃ ዲምቱ የምትባል ቦታ ውስጥ ነው

መልሷል እኮ ቅድምም ተናግሯል

እሺ ስለበቆሎ ይመዝገብልኝ በቃ

እሺ አብቅተዋል ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ ዐ/ህግ

አንድ ጥያቄ አለን

የዐ/ህግ ድጋሚ ጥያቄ

6 ሺህ ብር እና ሽጉጥ ሰጠ ብለሃል ያ 6 ሺህ ብር ለማን የተዘጋጀ ነበር ወይም ደግሞ ------- የተዘጋጀ ነበር

ለምን እንደተዘጋጀ አላውቅም ግን እንደሰጠ ነው ሲናገር ስለሰማሁ ለምን እንደተዘጋጀ እኔ አላውቀውም

እሺ ጨርሰናል።

እሺ ድጋሚ ጥያቄም አብቅቷል የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ ካለ ይቀጥል

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ

መከላከያ ያልከው የምን መከላከያ ነው ለምን መከላከያ ነው የተሰጠው መከላከያ ማለት ምን ማለት ነው

የአገር መከላከያ ነው

የምን አገር

የኢትዮጵያ አገር መከላከያ ነው

እነሱ ለመከላከያ የሰጡት ለማን ነው የሰጡት ለየትኛው መከላከያ ነው የሰጡት ጠይቀው እነሱ ለየትኛው መከላከያ ነው የሰጡት አንተ የሰማከው ለማን ሰጠን ሲሉ ነው የሰማከው

ጣሃ ለአገር መከላከያ ሰጥቻለሁ ሲል ነው እኔ የሰማሁት

እሺ ያኛውስ ከድርስ

ያኛው ደግሞ ብር ለኦነግ እንደተሰጠ ነው የሰማሁት

ይሄንን ሲናገሩ ሰምተሃል

አዎ

ቅድም ያልካቸው 5 ሰዎችም ነበሩ ከአንተ ጋር

ዘገግ

አዎ እነዚህ ታዛቢዎችም ከእኔ ጋር አብረን ነበርን

እሺ ዩሱፍ ጨሎስ

ዩሱፍ ጨሎም እዛው ነበር

እኮ እሱስ ምንድን ነው የተናገረው

በዚሁ ሰበብ ነው እሱም ያው የተያዘው

እኮ ምን ሲናገር ሰማህ የዛን እለት የታዘብከው ምንድን ነው

92 ሺኅ ብር ሙክታር አብዱጀሊል የሚባልና አህመድ ደረሳ የሚባል ከነዚህ አማካይነት ወደ አባዎች እንደሚደርስ ሲናገር ሰምቻለሁ

ሽጉጡ ለመከላከያ ሰራዊት የተሰጠው ለምንድን ነው

እሱ የአባዎች ደጋፊ ስለነበረ በዛ ምክንያት ነው ለመከላከያ ሊሰጥ የቻለው

ሽጉጡ ፍቃድ የነበረው ነው ወይስ ያልነበረው ነው

ፈቃድ አለው

እሺ ዩሱፍ ጨሎ ለኦነግ እርዳታ እንደሚያደርስ ከእሱ ሌላ ከሌላ ሰው ሰምተሃል

እኔ አልሰማሁም ከዚህ ውጪ

ከእሱ ብቻ ነው የሰማከው

አዎ

ቃሉን ሲሰጥ ነበርክ እንዴ እሱ

አዎ እዛ ቃል ሲሰጥ ነበር

ያኔ ነው የሰማከው

እኔ በዛን ጊዜ ነው የሰማሁት

ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

ተገዶ ነበር እንዴ ቃሉን የሰጠው

በፍላጎቱ ነው አላስገደዱትም

መብቱን ነግረውታል እንዴ

መብትና ግዴታው ተነግሮት በፍላጎቱ ነው የተናገረው

ስለ መብቱ እንዴት ነው እስኪ የገለጹለት ንገረን

እኔም ዐ/ህግ ነኝ ይሄም ፖሊስ ነው እና ማንም መብትህን ሳይገፋህ በፍላጎትህ መናገርህን እውነቱን እንድትነግር ብለው ገለጹለት

እሺ ስለ ሃጂ ጠሃ 6 ሺህ ብሩ የራሴ ነው ግን የአነግ ብዬ ነው የሰጠሁት ብሎ ቃሉን ሲሰጥ ሰምተከዋል እንዴ እንደዛ ብሎ ሲሰጥ ሰምተሃል ወይ

የዛን ጊዜ እኔ ይሄንን ገንዘብ የራሴ ገንዘብ ነው ግን የነሱ ነው ብዬ ሰጥቻለሁ ሲል ሰምቻለሁ በዛን ሰዓት ሰምቻለሁ

ስለተገደደ ነው ወይ

እኔ ተገዶ ይሁን በዛን በወቅቱ ሲናገር ግን ምንም በዛን ሰዓት በፍላጎቴ ነው የምናገረው ብሎ ነው የተናገረው ብሎን በዛን ሰዓት አይደለም

ከዛን በፊት እንዳስገደዱት እንደደበደቡት የገለፀው ነገር ነበር ወይ

እኔ ከእሱ ጋር የተለያየ ቦታ ነን የዛን ጊዜ ነው የተገናኘነው ከዛ በፊት ይገደድ ምንም ይሁን የማውቀው ነገር የለም በዛን ሰዓት ግን በወቅቱ ቦታ ቃሉን ሲሰጥ ግን በፍላጎቱ እንደሰጠ ነው የማውቀው

በሰውነቱ የሚታይ ነገር ነበር ወይ እሱ የተናገረው ቃላቶች ነበሩ

እኔ እሱ ላይ ያየሁትም ነገር የለም እሱም የተናገረው ነገር አልነበረም

ዩሱፍ ጨሎን ከየት ነው ያመጡት ከየት መጥቶ ነው ቃል የሰጠው

ዩሱፍ ጨሎን ከበዶ ይሻ ነው ያመጡት

ሀ/ፖ

እንዴት ሲያመጡት አይተሃል ወይ

አላየሁም

እንዴት እንደመጣ ከቤቱ ነው የመጣው ከየት እንደመጣ ታውቃለህ

ጣቢያ አድሮ ነው

ከየት እንዳመጡ አላውቀው እሱን

ቀበሌውንስ ታውቃለህ እንዴ የሱን

አላውቀውም

እሺ እናመሰግንሃለን ጨርሰሃል ከኋላ ቁጭ በል ማን ይጠራ ዐ/ህግ ና ቁም ወደዚህ አቁም ስትባል ማቆም እኮ አለብህ ይሄ ስርዓት ያለበት ቦታ ነው አሁን እኮ ስነ-ስርዓት እያፈረስክ ነው

መሀላ አስፈጽሙት

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ።

81ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ሬድዋን መሀመድ አብዱላሂ

ሥራ - አርሶ አደር

አድራሻ- አሰበ ተፈሪ

ለምስክርነት ነው ወይ የመጣከው

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

ዐ/ህግ ነው የጠራህ

አዎ

ይዜንን ታውቃለህ

130

አዎ አውቀዋለሁ

እዚህ ከተከሰሱት ውስጥ የምታውቀውን ብቻ ለይልን ተነሳና

አዎ አይቻለሁ

ጥሩ የሱን ስም ታውቃለህ ወይ

አዎ አውቀዋለሁ

ማን ነው ስሙ

አህመድ ሼክ ዩሱፍ

40ኛ ተከሳሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ምስክሩ ከእሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ

የለኝም

ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

ሬድዋን የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለሃል ተከሳሹ ---------- ምንድን ነው ያደረገው እስኪ አስረዳ የምታውቀውን በእሱ ጉዳይ

እሱ ያደረገው በ1997 ሐምሌ ወር ውስጥ የአባዎ በሳሳዎች በመሆን ህዝቡ ውስጥ በመንቀሳቀስ በራሱ ቤት በመሰብሰብ ወጣቶችም የመሰብሰብ እየሰበሰበ የአባዎ በሳሳ መሆኑን መታወቂያም እንዳለውና በዚህ ነገር የተነሳ አንዳንዴ ለስልጠና ሌላ ቦታ ሌላ አገርም ሄዶ እንደሚመጣ እስከዚህ ድረስ አውቀዋለሁ።

ከእርሱ ጋር ሌላ ሰው ካለ ለፍ/ቤቱ አስረዳ አብሮት የሚሰራ ማን ነው ከእሱ ጋር በስም የምታውቀውም ካለ ስም ጥራልን

ከእሱ ጋር የነበረው እነ አብዲ አደም የሚባሉ

ሌላስ

431

ከድር አህመድ የሚባል ሌሎቹን አላውቃቸውም እነዚህን ግን መሀመድ አብዶ የሚባልም አለ አብሮ

አባዎ ምንድን ነው

ትንሽ ድምፃችሁን ከፍ እያደረጋችሁ

እሺ

ቀጥሉ

ይሄን መንግስት ለመገልበጥ የሚፈልጉ ናቸው

የተከበረው ፍ/ቤት አባዎ በኦሮምኛ ነው አባዎ የሚለው ቃል አማርኛ አስተርጓሚው በአማርኛ መተርጎም ከቻለ ቢተረጉምልን ለፍ/ቤቱ ቢተረጉመው በአማርኛ አባዎ በኦሮምኛ ነው

እየተረጎመው እኮ ነው ጠይቀው አባዎ ምን ማለት ነው በለው

አባዎ ማለት መንግስትን ለመገልበጥ የሚያስቡ ናቸው

ሌላ ስም አላቸው ወይ

አነግ ይባላል

እሺ አነግ ምንድን ነው

የዚህ መንግስት አሸባሪ ነው እነዚህ በስሙ ነው

ቦታው የት ነበር የቅድሙ

አሰበ ተፈሪ አካባቢ ነው

እሺ ዋና ጥያቄ ጨርሰናል።

መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ለተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ የምስክሩ መልስ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

በሳላ ማለት ምንድን ነው በአማርኛ ምን ማለት ነው

1132

ውስጥ ለውስጥ የሚሰራ ማለት ነው ስለላ ማለት ነው

ስለላ

አዎ

እየው አሁን አንተ ሌላ ቦታ እየሄደ ይሰለጥናል መታወቂያም አለው ብለሃል እንዴት አወቅህ

እሱ ተይዞ መታወቂያ ሲሰጥ በአይኔ አየሁት

መቼ ተይዞ

በ1997

ሲናገር ነዋ የሰማከው እንጂ አታውቅም

በአይኔም አይቻለሁ ሲቀበሉት

ምኑን

የምስክር ወረቀቱን በአይኔ አየሁት

አነበብከው ማን ነው የተቀበለው

በፖሊስ በዛን ሰዓት ተይዞ እሱ አውጥቶ ከቤት አውጥቶ ሲሰጥ በአይኔ አየሁት ለፖሊስ ሲሰጥ

አሃ የደረጃ ምስክር ሆነህ ነው እንዴ ፖሊስ በምስክርነት ወስዶህ ነው ወይ ያየከው

እኔ እዛ ሰፈር ነኝ

እኮ እዛ ሰፈር ነህ ና ጠራህና ና ተመልከትልን አለህ ወይ

እዛ ስለነበርኩ ና እይ ተብዬ ነው

ና እይ ተብለህ መታወቂያውን አየህ

አዎ

አነበብከው

አዎ አንብቤአለሁ አይቻለሁ

አሁን ከፖሊስ ጋር ሆነህ ያንን መታወቂያ ሲሰጥ አየከው ሌላስ ምን አየህ

ይዜንን ነው ያየሁት

ይዜንን ነው ያየከው ቀኑ መቼ ነው

ቀኑን አላስታውስም ወሩ ግን ሐምሌ ወር ውስጥ ነው

ቃሉን ወዲያው ቃሉን ሰጠና ተመዘገበ እንዴ

አዎ ወዲያው ተመዝግቧል

ማን መዘገበው

ፖሊስ ነው

ስንት ናቸው

2 ፖሊሶች ነበሩ

ከአንተ ሌላ ማን ነበር ይዜንን የሚያይ

አዎ አሉ

እኮ ማን ነበር ከአንተ ሌላ ልክ እንዳንተ እያየ ነበር ማለት ነው

ኡስማኤል ኡመር የሚባልም ነበር

እሺ ሌላስ

አብደላ ዩያ የሚባልም ነበር

እሺ ሌላስ

እነዚህ ነበሩ

አሁን ለምስክርነት መጥቶዋል እንዴ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

435

የመጡ የሉም

የመጡ የሉም ሌላ ጥያቄ

ይሄ ቃሉን ሰጠ የምትለው ነገር ፈረመበት እንዴ ተፈረመ ወይ ተከሳሽ ፈረመበት ወይ ፈርሚል

አንተስ ፈረምክበት እንዴ

እኔ አልፈረምኩም

እነዛስ ፈረሙበት ወይ

እነሱም አልፈረሙም

አልፈረሙም

እሺ ማን ፃፈው

ፖሊስ አለ እኮ ቃሉን ፖሊስ ተቀበለ

ፖሊሱ ፃፈ እሺ አነበበለት ወይ መልሶ

አዎ አንብቦለታል

አንተም ሰምተሃል

ሲነበብ ሰማህ ወይ ቀላል ጥያቄ አይደለም

አዎ ሰምቻለሁ

ሰምቻለሁ ሌላ ጥያቄ

በምንድን ነው የተፃፈው በኦሮምኛ ነው በአማርኛ

በኦሮምኛ ነው የተፃፈው

ይበቃናል

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 የፌዴራል ዲ/ሬፐብሊክ

436

እሺ ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ ድጋሚ ጥያቄ ካለ በዐ/ህግ በኩል

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

ድጋሚ ጥያቄ የለም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

አብዲ ያልከው ሰው አለ አብዲ ማን ነው

አብዲ አደም የሚባል ነው

ያስ መሀመድ ያልከው ማን ነው

መሀመድ አብዶ የሚባል

ተይዟል

አዎ ተይዟል መሀመድ አብዶ የሚባል ተይዟል

አለ ወይ እዚህ ውስጥ

እዚህ ግን አላየሁም ግን እንደተያዘ አውቀዋለሁ

መሀመድ ማን

መሀመድ አብዶ

መሀመድ አብዶ ማን

አብዶ ማን እንደሆነ አያቱን አላውቀውም

መሀመድ አብዶ አለ እዚህ ውስጥ መሀመድ አብዶ እስቲ ተነስ መሀመድ አብዶ አህመድ ነህ 70ኛ እስቲ እየው

አዎ እሱ ነው አውቀዋለሁ

ታዲያ ቅድም ፊልገህ ለምንድ አጣከው እዚህ ፊት ሲፈት አላየህም ነበር አስተርጉም እንጂ አንተ ምንድን ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 1 የፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ

437

ፊቱ በደንብ አልታየኝም ነበር

ጥሩ እሱን ማለትህ ነው

አዎ

እሺ እሱ ምን አደረገ ነው የምትለው

እሱም አብሮ በዚህ ጉዳይ ላይ አብሮ ነበር ከዚህኛው ጋር

ከማን ጋር

ከአህመድ ጋር የእሱ ቤት አብሮ ተሰብስቦ ነበር

አብሮ ተሰብስቦ ነበር ስለዚህ ታውቀዋህ እሱን ማለት ነው

አዎ አውቀዋለሁ

እስቲ አሁን ተነሳና ሌላ በድጋሚ እስቲ ዙርና እይ ቀና በሉለት አንዴ ይይ መሀመድ ቃል ሰጥቷል ወይ እሱም መሀመድ አብዶ አህመድ 70ኛ ተከሳሽ

አልሰጠም

የዛን እለት ቃል አልሰጠም

ቃል አልሰጠም

ጥሩ የማን ቤት ነው ተሰብስበው አየሁ ያልከው

የአህመድ ቤት

ተሰብስበው ማን ነው የሰበሰባቸው

አህመድ ነው የሰበሰባቸው

አህመድ ምንድን ነው ሃላፊነቱ ለምንድን ነው የሚሰበስበው

ይሄ አህመድ የአባዎቹ ሰላይ ነው እና ውስጥ ለውስጥ የሚያደራጅ እሱ ነው

ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 2

ይሄንን በምን አወቅህ ወይም በምን ተረዳህ አንተ

እሱ ያደራጃቸው ሰዎች በሙሉ ነው ህዝቡ ላይ ወጥቶ እሱ ነው ያደራጀኝ እሱ ነው ያደራጀኝ ብሎ ህዝቡ ላይ ወጥቶ ራሱ ራሱን ግልጽ ያወጣው

ምንድን ነው ሌላ ስራው በሙያ ምንድን ነው የሚሰራው

አስተማሪ ነው

የት ነው የሚያስተምረው

ማረሚያ ቤት ነው የሚያስተምረው

ማረሚያ ቤት ከዛ በፊትስ

ከዛ በፊት ስራ አልነበረውም

ምንድን ነው የሚሰራው

በቃ ይሄንን ስራ ነው ውስጥ ለውስጥ የሚሰራው እንጂ ሌላ ስራ አልነበረም

ሰዉ ይሄንን ሲል አንተ የት ነው የሰማከው በምን አጋጣሚ ነው እስቲ ንገረን እሱ ነው ያደራጀን እሱ ነው እንደዚህ ያለን የሚለውን ነገር ሰዎቹ አሉ ያልከው የት አካባቢ ነው መቼ ነው

እኔ የዛ አካባቢ የአንድ ሰፈር አካባቢ በዛን ጊዜ ሃላፊ ነበርኩ እዛ ህዝቡ ላይ በዛን ሰዓት ህዝቡ ራሳቸውን ግልፅ አወጡት አከሌ እሱ ነው ያደራጀኝ ብሎ ራሳቸውን ግልፅ አወጡት

ምን ምን አድርጉ ይለናል እንዴት አድርጎ ነው ያደራጀን ምን አምጡ አላቸው

ኦሮሞ ነፃ አውጪ እንደግፋለን አንድ አምስት አምስት ሰው እያደራጀን ወታደርም ውስጥ ለውስጥ እናሰለጥናለን ብሎናል ብለው ሲናገሩ ነው ህዝቡ ራሳቸውን ክስ ያወጡት ሲሉ ነው የሰማሁት ብርም ሰብስበን እንደሰጠን

ይሄንን ሰዉ ያለውነው በስብሰባ

አዎ በስብሰባ ላይ ያሉት ነው

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ጥሩ ይሄ መሀመድ አብዶስ ምንድን ነው ሰብስቦ ምን አደረገ ነው የምትለው

ይሄ መሀመድ አብዶም ከእሱ ጋር አብሮ እንደሆነ ነው እንጂ እሱ በውል ያደረገውን አላውቀውም

ሰዎቹስ እንዲህ አደረገ ብለው ተናግረውበታል ወይ

እኔ አልሰማሁም

ተሰብስቦስ አይተከዋል ወይ ከአህመድ ሼክ ጋር

ተሰብስቦ አይቻለሁ አዎ አይቻለሁ

የት ነው የተሰበሰቡበት ቦታ

የአህመድ ቤት ነው

አህመድ ቤት ውስጥ

አዎ

አንተ ነበርክ እንዴ ሲሰበሰቡ አይተካቸዋል ደርሰህባቸዋል

አዎ የእሱ ቤት ውስጥ ሲሰበሰቡ እኔ አይቻለሁ

በምን ምክንያት ሄድክ

ከእሱ ቤት እና ከእኔ ቤት አንድ ቤት ብቻ ነው ያለው እና አያለሁ

በምን ምክንያት እንደሚሰበሰቡ ታውቃለህ ወይ ሊጠይቀውም ሊገባ ይችላል

አንዳንድ ችግር መፈጠሩ እና የተለያየ ችግር ስለነበረ በዛን ሰዓት በዚህ ነገር ጉዳይ ላይ አውቅ ነበር

እኮ ምንድን ነው የምታውቀው የምታውቀውን ንገረኝ በል

አሁን የተናገርኩት ነገሮችን ነው የማውቀው

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅጥር ግቢ

ዘላዐ

አንተ ስብሰባውን እንዴት አወቅህ እሱን ብቻ ንገረን ስብሰባ መሆኑን ጎረቤት ነኝ አልክ ስብሰባ ላይ መቀመጣቸውን እንዴት አወቅህ

እኔ በዛን ሰዓት የአንድ ሰፈር ተመራጭ ነኝ አንዳንድ ችግር ስለነበረ በዛን ሰዓት ውስጥ ለውስጥ ክትትል አድርጉ ተብለን የተመደብን ሰዎች ነበርን የዛን ጊዜ ስንከታተል ይሄ ነገር እንደተሰበሰቡ ደረስንባቸው

እኮ እንዴት ደረስክባቸው እንደተሰበሰቡ ይዘካቸዋል ለምሳሌ ወይስ እንዲያዙ አድርገሃል

ሰው ተደርጎበት እንዲያዙ ተደርጓል ተይዟልም

ስብሰባ ላይ እያሉ በሰው እንዲያዙ አድርገሃል

አዎ ተይዟል

በዚህ ምክንያት ነው ያወከው

አዎ በዚህ ምክንያት ነው ያወኩት

ሲያዙ ምን ተያዘባቸው

ያው በወቅቱ ይሄ በእጁ የተያዘው ይሄ መታወቂያ ቅድም ያልኩት ነገር ነው የተያዘበት

ጥሩ ------ ተያዘ ከመሀመድ አብዶ ላይስ ምን ተያዘ

እሱ ላይ የተያዘውን ነገር አላየሁም

ግን ስብሰባ ላይ አብሮ ተይዟል

አዎ በዛ በወቅቱ ስብሰባ ላይ አብሮ ተይዟል

ስብሰባው ምን እንደነበረ ለምን እንደተሰበሰቡ ማጣራት ችለህ ነበር ከዛ በኋላ

የተሰበሰቡበት ጉዳዩን አውቀናል ህዝቡም ራሱ ውስጥ ለውስጥ እንደተደራጁ ይሄንን ነገር ራሱ ሲያወጡበት ከዛ ምክንያት ከዛ በኋላ ነው በዚህ ጉዳይ እንደተሰበሰበው ህዝቡ ራሱ ግልፅ አውጥቷል

በህዝቡ ጥቆማ ነው የተያዙት ማለት ነው

ዘዘ

አዎ

ወረቀት ሌላ ነገር ተይዟል እንዴ

እኔ አላወኩም

እሺ እናመሰግንሃለን ከኋላ ቁጭ በል ማን ይጠራላችሁ አብዱረዛቅ

መሀዲ አሚን ስንተኛ ነው

5ኛ የዐ/ህግ ቀጣይ ምስክር ቀርቧል መሀላ አስፈጽሙት በመሀላ ስር ሆኖ የሚከተለውን የምስክርነት ቃል ለፍ/ቤት ይሰጣል

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ

መሀላ ፈጽሟል

ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - መሀዲ አሚን

ሥራ - ተማሪ

አድራሻ- ሐረማያ

ለምስክርነት ነው የመጣከው ዐ/ህግ ጠርቶህ ነው

አዎ

የስንተኛ ክፍል ተማሪ ነህ

3ኛ አመት ተማሪ ነኝ

የት

ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ ክፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ሀዛ

ጥሩ አንዴ ትነሳና የምታውቃቸውን ሰዎች ብቻ ትለይልናለን ከተከሳሾች መሀል ረጋ ብለህ የምታውቃቸውን ዞረህ ምረጥልን እስከመጨረሻ ያለውን በሙሉ እሺ ምስክሩ በችሎት ሁለት ተከሳሾችን ለይቷል እነሱን በስም ትለያቸዋለህ ወይ

አዎ አውቀዋለሁ

ንገረን እስቲ ስማቸውን

ራማና ጀና

ራማ የትኛዋ ነች እሺ ስንተኛ ተራ ቁጥር ላይ ነው ያለሽው 30 እሷስ ማን ነው ስሚ

ጀና

ከእነሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ

የለኝም

ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

የመጣሁት ለምስክርነት ነው በእነሱ ላይ ብለሃል እስቲ ምንድን ነው ስለ እነሱ የምታውቀው ለፍ/ቤቱ አስረዳ

በአንዳንድ ነው ወይስ በአጠቃላይ ነው የምገልፀው

በአንዳንድ እያንዳንዱን

ከማን ልጀምር

ከምትፈልገው

ትንሽ ድምጽኅን ከፍ አድርግ ተረጋግተህ ቀስ ብለህ ድምጽህን ከፍ ለማድረግ ሞክር የቻልከውን ያህል

ከጀና ጋር ከአሁን በፊት እንተዋወቃለን በ1998 እስከ 2000 ድረስ እንተዋወቃለን ሰርዳ ወይም ኢብራሂም የሚባለው ሰውዬ አንተን ይፈልጋል እያለችኝ ትነግረኝ ነበር የሆነ ስልክ በዚህ ስልክ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

ዘዘ3

ይፈልግሃል ብላ ስልኩን ሰጠችኝ ከዛ ጊዜ ጀምሮ እኔ እና እሱ ሰውዬ አልተገናኘንም አብዲ ጢቃ የሚባለው ሰውዬ ጋር እሱ በታሰረበት ጊዜ እሱ በታሰረበት ከእሷ ጋር ሄጄ አብረን እናየው ነበር ይሄ ኢብራሂም እና ይሄ አብዲ ጢቃ የሚባለው የኦነግ ሰላይ እንደነበር ነው ካድሬ እኔ የማውቀው ከዚህ ጋር በተያያዘ ጋር ነው

አብዲ ጢቃ አሁን እዚህ አለ ወይ

እስር ቤት እንዳለ ነው የማውቀው

ከዛ ምን አደረጋችሁ ሄዳችሁ ጠየቃችሁ

በ4 ሺህ ዋስ እሷ ወስዳ እሱን ለማስወጣት እንደሄደችም አውቀዋለሁ ሐረር ታስሮ ነበር

መጀመሪያ ሌላ ሰው ፈልጎህ ብሎ አልነበረም ወይ ምንድን ነው ያ ሰውዬ ለምንድን ነበር የፈለጉህ

ይሄ ሰውዬ ከአሁን በፊት ለኦነጎች ሰውን ያደራጅ ነበር እና በዛ ምክንያት ነው እኔንም በዛ ውስጥ እንዲቀረጽ ብለው ነው

እሷ ምንድን ነበር ተሳትፎዋ በዛ ውስጥ

ተቃውሞ አላችሁ እስቲ መቃወሚያው ምንድን ነው

አዎ ወይም ነው የሚል ነው መልስ ሊያስገኝ የሚችለው ይሄ ጥያቄ ምክንያቱም የእገሌ ተሳትፎ ምንድን ነው እሷ ነገረችኝ አለ ግልጽ እኮ ነው ሰውየው እኮ እገሌ የተባለ ሰው ይፈልግሃል ብላ ስልክ ሰጠችው ነገሩ እዚህ ላይ ቆመ በቃ ሌላ ሰው እስረኛ ሊጠይቁ አሁንም እስር ቤት ጠየቀች ተመለሱ ለአራት ሺኅ ብር ለሰውየው ዋስ እያቀረበችለት ነበር ብለው ደመደመ ይሄ ከተደመደመ በኋላ የእሷ ተሳትፎ ምንድን ነው ተብሎ ምኗ ነው የሚጠየቀው ምን ስለ እሷ ላይ መሰከረባት ምን ተናገረ

እሺ እዚህ ላይ

የተከበረው ፍ/ቤት እኛ መሪ ጥያቄ አልጠየቅንም መሪ ጥያቄ የሚባለው እሷ ኢሃዲግ ነች ወይ ብል አዎ ወይም አደለም ነው የእሷን ድርጊት ምን ነበር ግለጽልን ተሳትፎዋ ምንድን ነው የሚለው ከወንጀል ከምናስረዳው ጭብጥ ጋር የተያያዘ ነገር ነው

ዘዘዛ

ከዚህም በተጨማሪ አብዲ ጢቃ የተባለው ግለሰብ ኦነግን እያስተባበረ የነበረ በመሆኑ ምክንያት እንደታሰረ እና አራት

ጨርስ ጨረስክ

አልጨረስኩም እና ኦነግ ሲያደራጅ እንደነበረ እና እሱ የዛ አባል በመሆኑ ምክንያት ታስሮ አራት ሺህ ብር ዋስትና ልታስወጣ የሄደች መሆኑን ከዛ በፊት ግን ለእሱ ደውላ ይህንን ግለሰብ አግኘው ብላ ስልኩን የሰጠች መሆኑን ነግሮናል ይሄ ሰውዬ ያደራጅ ነበር ካለ የእሷ ሚና ምን ነበር ማለት ይሄ ነች ይሄ ነች የተባለ ነገር የለም የሚመራ ነገር የለም በወቅቱ ተማሪ ነች ይበለን ወይም የሆነችውን ነገር እንዲያስረዳ ነው ለፍ/ቤቱ የሚመራ ሳይሆን በወቅቱ የነበረውን የእሷን ተሳትፎ ምን እንደነበረ ገልጾ እንዲያወጣ የነበረውን ፋክት እንዲገልጽ የሚገፋ ጥያቄ እንጂ እንዲ ነበረች ወይም አልነበረችም ወይ ተብሎ የተጠየቀ ስላልሆነ ፍጹም የሚመራ እንዳልሆነ ፍ/ቤቱ እንዲገነዘብልን እና ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎ ጥያቄውን እንዲያዝልን።

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል ጥያቄው ይቀጥል ተብሏል መሪ ጥያቄ አይደለም እስቲ አስረዳ በለው በምንድን ነው የምታውቃት ለቀረበልህ ጥያቄ ተሳትፎዋ ተብለሃል ምንድን ነው በለው

ከእነሱ ጋር መቆየቷን ነው የማውቀው

የት ነው ከእነሱ ጋር የቆየችው

አወዳይ

ምን እያደረጉ

እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ሐረር 4ኛ ነው ያየሁትኝ ግን ወደ አወዳይ አብረው እንደሚሄዱ ነው የማውቀው

እሺ አብዲ ጢቃ ሲያደራጅ ነበር ብለሃል ለኦነግ አብዲ ጢቃ ካደራጃቸው ሰዎች የምታውቃቸው አሉ ወይ አንተ

ቆይ ቆይ ቆይ አብዲ ጢቃ ያደራጃቸውን ሰዎች ታውቃለህ ወይስ ቀላል ጥያቄ ነው ቀላል ጥያቄ ነው የጠየቀው ታውቃለህ አታውቀም ታውቃለህ አታውቅም መጀመሪያ

አውቃለሁ አውቃለሁ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁ.፻፫ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

1/1/16

በቃ የምታውቃቸውን ንገረን በለው

ለጊዜው አሁን 8 ሰዎች ኬንያ ነው ያሉት 2 ሰዎች ግን አሁን አሉ አንዱ ወደ ሱማሌ ክልል መምህር ነው በቃ እነዚህ 2ቱ ነው ያሉት

እሺ እዚህ ያሉት ስማቸው እነማን ነው

አንዱ ፋሚ ሙሳ ይባላል

እሺ ሌላውስ

ቶፊቅ መሀመድ

እሺ የአብዲ ጢቃን ስልክ የሰጠችህ ጀና ምን ለምንድነው የሰጠችህ ምን እንዲያደረግ ነው የሰጠችህ

---- የሰርዳ ቦሩን ነው

የሰጠችህ ማንን ነው

ሰርዳ ሰርዳ ብሏል እያዳመጣችሁ

የሰርዳ ቦሩን

አዎ

እሺ የሰርዳ ቦሩን ስልክ የሰጠችህ ምን እንድታደርግ ነው ለምንድነው የሚፈልግህ ታዲያ ለምንድነው የሚፈልግህ ብላ ነው የሰጠችህ

እሱ --- ያደራጃል ስለዚህ ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ ነው

አህ እሱ አማርኛ ትችላለህ እንዴ

ቆይ ቆይ እየተተረጐመ ስለሆነ እየተተረፀ ነው 2ቱ ሲቀላቀል ለመቅረፅ ያስቸግራቸዋል በኦሮምኛ በቋንቋህ እንደጀመርክ አየተናገርክ እንደሚ ነው እሺ ግልፅ ነው ቀጥሉ አሁን መልሱን መልስ እና አስተርጓሚው ለእኛ ንገረን

ድምፅህን ከፍ አድርግ እና

ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ቆይ ቆይ እስቲ ተረጋግተህ መልስ እንትን አትበሉት አንተ ምስክር ነህ ተረጋግተህ ተናገር በለው መጀመሪያ እሱን መጨነቅ የለብህም አሁን ንገረን እሺ

ሰርዳ ቦሩ የአባዎ አደራጅ ስለሆነ ነገሩ ከእዛ ጋር የተያያዘ ነው

እሺ ሰርዳ ቦሩ አደራጅ ስለሆነ እንድታገኘው በእዛ በተያያዘ ነው ያገናኘችህ ታዲያ እሷ ምንድነች ማለት ነው

ቆይ ቆይ እስቲ

እንደዚህ አይደለም ትርጉሙ

ቆይ ቆይ ቆይ ቆይ ስነ ስርአት አድርጉ ከአሁን በኋላ እንደዚህ አይነት ነገር ተጨማሪ ነገር ከሰማን እርምት ይወሰድበታል መቃወሚያ በስነ ስርአቱ መሰረት ማንሳት ነው ሌላው ነገር ግን ትክክል አይደለም ጥንቃቄ አድርጉ አሁን ምንድነው መቃወሚያው መቃወሚያውን አስመዝግቡ

መቃወሚያው እሱ እሷ ምስክሩ ይሄን አሁን እሱ እንደሚለው አይነት አይደለም ያለው

ቆይ ያልተባለ ነገር ተነስቷል በጥያቄው ላይ

አዎ ያልተባለ ነገር እንዲህ እንዲህ አይደለም ወይ ያለችው አዎ ካለ አዎ የሚል --- መሪ ጥያቄ ነው አላለም ካሉ አስፈላጊ ከሆነ የተቀረፀው እንደገና ይሰማ

ጥሩ እሺ ፍ/ቤቱ ስለሚያዳምጥ እሺ ዐ/ሕግ

እሺ እኔ የጨመርኩት ነገር ያለ አልመሰለኝም ሰርዳ ቦሩ ኦነግን በሴል ያደራጀ ከእዛ ጋር በተያያዘ ነው የሰጠችኝ ስልኩን የሰጠችኝ ብሏል ምናልባት

--- የተቀረፁት

አዳምጡ እንጂ ምንድነው አላለም አላችሁ እሱ እኛ ደግሞ ብለናል አሉ በቃ የፍ/ቤት ስራ እኮ ነው እየተካችሁ እየሰራችሁ ያላችሁት እሺ ቀጥሉ ጨረሳችሁ አይደለም እዚህ ላይ መልሳችሁን ጨረሳችሁ

አዎ ጨርሰናል

አልጨመርንም ነው

ስለዚህ የጨመርነው ነገር የለም የጠየቅነው የተባለውን ነገር እንዲያብራራልን ብቻ ነው የጠየቅነው

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯ ዐ/ሕግ ጥያቄያችሁን በተመለከረው ፍሬ ነገር ላይ መሰረት አድርጋችሁ አትጠይቁ ሌላ ተጨማሪ ነገር ጠይቁ ምስክርም ሊያደናግር ስለሚችል ጥያቄ ጠይቁ አሁን

እረሀማን በተመለከተ የምታውቀው ነገርስ ምንድነው ንገረን

--- ለመጀመሪያ ጊዜ

ድምፅ ትንሽ

በ1998 እኔ እና ያያ መሀመድ የሚባል የእነሱ እቤት ሄድን ኡመር የሚባል የእነሱ እቤት ተዋወቅሁ ኡመር ማለት የኦነግ አባል ነው ሱፍያን እና አልያ ዳዲ የሚባሉ ነበሩ እነሱ 3ቱም ግን እንደታሰሩ ይመስለኛል ከዚህ ጋር ተያይዞ ከእነዚህ ሰዎች ጋር እንደምትሄድ ነው የማውቀው

ሌላ ጥያቄ

ለምንድነው ነበር ከእነዚ ሰዎች ጋር የምትሄደው

በቃ እንደ አባልነት ነው አብረው የሚሄዱት

የምን አባልነት

እነዚህ ሰዎች የአባዎ አባዎዎች ማነው ሰላዬች ናቸው አደራጆች ማለት ነው ካድሬ ማለት ነው

እ

ደበሌ ማለት ካድሬዎች ማለት ነው የአባዎች ካድሬዎች ማለት ነው ያው ከእነዚህ ሰዎች ጋር እንደምትሄድ ነው የማውቀው

እሺ ከእነዚህ ሰዎች ጋር በአባልነት ትሄዳለች ብለከናል አዛ ሄዳ ምን ታደርግ ነበረ

እነሱ የሚሰሩትን ነዋ የምትሰራው

እነሱ የሚሰሩት ምንድን ነበረ

ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 4

ሰውን ያደራጃሉ

ለምንድነው ነበረ የሚያደራጁት

ትንሽ ድምፅ ድምፅ ለምንድነው የሚያደራጁት

ብር ይሰበስባሉ ከተማሪም ከህብረተሰቡም የሚያደራጁት ብዙ ነው እና ብሩም ይሰበሰባል

ብር የሚሰበስቡት ከተማሪም ከአስተማሪም ከህዝቡም የሚያደራጁት ደግሞ ለምን እያሉ ነበረ ምን እያሉ ነበረ ብር የሚሰበስቡትስ ለምንድን ነው

የህዝቡን ለማነሳሳት እና ለአባዎች ለማድረስ ነው

አሁን ከለየካቸው 2 ሰዎች ውጪ እዚህ ውስጥ በአዳራሽ ውስጥ ካው ሌላ የምታውቃቸው ሰዎች ካሉ ደግመህ እንድትለይልን ነው የተከበረው ፍ/ቤት

በጣም ብዙ ጊዜ ስለቆየብኝ በስም ካልሆነ በስተቀር እንደዚህ በፊት ለመለየት ይቸግረኛል

በስም የምታውቀውን በዚህ ጉዳይ ማነው በለው

አብዱ አሊ የሚባል

ሌላስ

አላስታውስም ዛሬ ማታም አልተኛሁም ቃዲራ ነው ያደርኩት እና

የተከበረው ፍ/ቤት የምናሳስበው ነገር አለ ይሄ ምስክር ጠኋት መጥቶ ሪጀክክ ተደርጓል በሌሎችም ሰዎችላይ ምስክርነቱን ሰጥቷል ከዚህ በፊት እዚህ ባሉ አውቃቸዋለሁ ብሏል አሁን ሀሰተኛ ምስክርነቱን እየሰጠ ነው አላውቅም እያለ ነው ስለዚህ መስቀለኛ ማነው መሪ ጥያቄ እንድንጠይቅ እንዲፈቀድልን ነው

እኮ እየተመዘገበ እኮ ነው ለምንድነው የማትከታተሉት ችሎቱን

እኛ የተከበረው ፍ/ቤት 1ኛ መሪ ጥያቄም ፈፅሞ አይፈቀድም እሱ ይሄንን ብቻ ነው የማውቀው ብሎ ደምድሞ ከዚጋ ቀኋላ እነ እገሌን እወቅ እነ እገሌን አትወቅ እን እገሌን አውጣ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

እየተባለ ፍ/ቤቱ እንደዚህ አይነት የስራ ሂደቱን ስነ ስርአቱም አይፈቅድ ህጉም አይፈቅድ የሰዎቹንም ትክክለኛ ፍትህ የማግኘት መብት የሚጫን ነው ስነ ስርአቱም አይፈቅድም የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ ሊቀበልብን አይገባም

እሺ ለመቃወሚያው መልስ አላችሁ

አም የተከበረው ፍ/ቤት መሪ ጥያቄ ፍ/ቤቱን አስፈቅዶ ዐ/ሕግ ሊጠይቅ እንደሚችል ስነ ስርአት ህጉ ላይ አለ ከዚህም በተጨማሪ ምስክሩ አላውቅም ሳይሆን ያለው ጊዜው ስለረዘመ እና ዛሬ ለሊት ቃዲራ ስላደርኩ ለማስታወስ እጅግ ተስኖኛል አብዲ አሊ የሚባለውን ብቻ ነው እያስታወስኩ ያለሁት ሌሎችም እንዳሉ ነገር ግን እንደረሳው ነው እያሳሰበ ያለው ስለሆነም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ መሪ ጥያቄ ጠይቀነው እስሌ እስሌ እያልን እየመራነው ታውቃለህ ወይንስ አታውቅም ብለን እንዲያስታውስ አቴንድ እንትኑን ሚሞሪውን ጌት ባክ እንዲያደርግ ካፕቸር ለማድረግ ያህል እንድናስታውሰው እንዲፈቀድልን ነው የምናሳስበው ስነ ስርአት ህጉም ይሄንን ይፈቅዳል አይከለክልም

በቃ ተቃወማችሁ መልስ ሰማን እኮ

ተከሣሽን እገሌ እገሌ ብሎ ዐ/ሕግ --

ተቃወማችሁ ሰማን እኮ ቅድም አይደል

እሺ

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል በአብላጫ ድምፅ የሚቀጥለው ብይን ተሰጥቷል ይህ ምስክር በምስክርነት ቃሉ ቀጢራ አድሬ ነው የሚል ቃል ተናግሯል ከግራ ቀኞችሁ መቃወሚያ እና ከዐ/ሕግ መልስ አንፃር በአብላጫ ድምፅ ይሄንን ክርክራችሁ ተመርምሮ ቀጥታ እየተመራ ሊጠየቅ የቀረበው ጥያቄ መቀጠል የለበትም ተብሏል በተጨማሪም በፍ/ቤቱ ይህ ምስክር ቀጢራ በማደሩ አድሮ መጥቶ ይሰማ የሚል ሀሳብም ተነስቷል ይሄንንም በአብላጫ ድምፅ ፍ/ቤቱ ስላልተቀበለው ታልፏል የልዩነት ድምፁ ግን በቀጥታ መጠየቅም አለበት ካስፈለገም ለፍትህ ሲባል ቀጢራ በማደሩ የሚያውቃቸው ሰዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ አድሮ ቢሰማ ለትክክለኛ ፍትህ ይገባ ነበረ በሚል የልዩነት ሀሳብ ቀመዝግቧል ስለዚህ ሌላ ጥያቄ ካለ ዐ/ሕግ ይቀጥል

ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር ፡

ሌላ ጥያቄ የለንም

አበቃችሁ እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጠያቄ ካለ የምስክሩ መልስ

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

እ ራህማ እነ አብዲ ይፈልጉህል ብላ ነግራህለች ከእዛ ባለፈ ለዚህ ለዚህ ጉዳይ ይፈልጉህል ብላ የነገረችሁ ነገር አለ ወይ

ጀና ነው ወይንስ ረህማ ነው

ረህማ ጀና ጀና በለው

ጀና ስልኩን በምትሰጠኝ ወቅት ነው ወይ

አዎ አዎ

ውስጡን እንደዚህ የገለፀችልኝ ነገር የለም

እሺ ሌላ ጥያቄ እነዛ ከእነዛ ጋር በተያያዘ ነጃ የትኛዋ ናት ነጃ የትኛዋ ነሽ ኦኬ ከራህማ ጋር በተያያዘ ከእሷ አብራ ትውል የነበረው ሰዎች ካድሬዎች መሆናቸውን ተናግረህል እሷስ ካድሬ ነች ወይ የኦነግ ካድሬ ነች ወይ ነች ወይንስ አይደለችም አጭር መልስ

እኔ

ነች ወይንስ አይደለችም አጭር መልስ ስጠን የማታውቅ ከሆነም አላውቅም በል

እኔ አባል መሆንዋን ነው የማውቀው እንጂ ካድሬ መሆንዋን አላውቅም

አንተ የኦነግ አባል ነህ ወይ

መቼ ጊዜ ነው

በዛን ጊዜ እሷ አባል በነበረችበት ጊዜ አንተ አባል ነበርክ ወይ

አዎ አብረን ነበርን

ምን ምን ሰራችሁ

451

በዛን ጊዜ እኔ ታስራ ነበረ

እሷስ

ከእዛ በኋላ እኔ ሸሸሁ እና ተለየሁ

እሷ ያደራጀችው ሰው አለ ወይ

እሷ አብራ ትሄድ ነበረ አብረውት የቆዩም ሰዎች አሉ እንጂ እኔ ከእነ ሶፊያም ጋር ነው

አቤት

ከእነ ሶፊያም ጋር አብራ እንደሆነች ነው የማውቀው

እሷ አደራጅታለች ወይ ያደራጀችው ሰው ካለስ ታውቃህ ወይ እነሱን

ያን አላውቀውም

ሰበካ ስታደርግስ በካድሬነት ህዝት ሰብስባ ወይ ሰዎችን ሰብስባ ሰበካ ስታደርግስ አይተካል ወይ ስለ ኦነግ አላማ በተመለከተ

እሷ ብቻዋን ሳይሆን ከእነዚህ ሰዎች ጋር ስትሄድ ነው እንጂ ብቻዋን ሄዳ እንደዚህ ስታደርግ አላውቅም

እሷ ስትሰብክ አይተካል ወይ በግል

ለብቻዋ አላየሁም

ስትሰብክስ አይተካል ወይ ከእነሱ ጋርስ ሆና

አለ

ምን ብላ ተናገረች

በ1998 ጀምሮ

452

ምን ብላ ተናገረች ሰውን ለማደራጀት ብሩን እንደሚለግሱ ናኖ ባቴ የሚባል እና ሐረማያ አካባቢ ባቴ ባቴ አካባቢ ወደ ሐረማያ ገባያ ከእነ ሶፊያ ጋር ሆኖ እነዚህ ነው የማውቀው ከእነዚ ጋራ ተንቀሳቅሳ በእነዚህ ዙሪያ ላይ

እሷ ስትናገር ስትሰብክ አይተካል ወይ

እሷ ስትናገር የተናገረችው ቃል አለ ወይ እሷ አባል ናት አብራ ነው የምትሄደው

እሺ በእናንተ በኩል ጥያቄ ትጠይቃላችሁ የተዘለለ ይመስለናል ነው አትጠይቁም ትጠይቃላችሁ ጥሩ

የተከሣሽ ጠበቃ ጥያቄ

አንተ የኦነግ አባል ናት ብለሀል እንዴት አወቅህ

አብረን ነበርን

አብረን ነበርን ብሏል ቅድም ሌላ ጥያቄ ሌላ ጥያቄ

እነዛ የምትጠራቸው ሰዎች የኦነግ ካድሬ ስለመሆናቸው በምን አወቅህ

እነሱ ሰዎች እራሱ እስር ቤት ነው ያሉት

በመታሰራቸው ነው በልዩ የምታውቀው ነገር አለ

እነሱ ያደራጁት ሰዎች እነሱ ላይ ምስክርነት ወጥቶ አለ

ምንድነው ያለው አሁን መጨረሻ

በተጨባጭ እነሱ ያደራጁት ሰዎች አሉ አሁንም እራሱ አሉ

እሺ ሌላ ጥያቄ ያደራጇቸው ሰዎች አሉ

እነሱ ሲናገሩ የሰማከውን ነው

እኔ እራሴ አውቀዋለሁ

አውቃቸዋለሁ እኔም አውቃለሁ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፩ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

453

ጆናን የት ነው የምታውቃት

መጀመሪያ በሀረር መንገድ ነው የተዋወቅነው እኔ ከትምህርት የተባረርኩ ጊዜ ነው

እሷ ምንድነው ስራዋ

አወዳ አካባቢ ጫት እንደምትነግድ ነው የማውቀው

ይሄንን ነው የምታውቀው

ሀረር ነው የተዋወቅነው አላልኩም ወይ

ከማን ጋር ከማን ጋር በለው

ሶፊያ እና አራራ ዳዲ የሚባሉ አሉ 2ቱም እስር ቤት ነው ያሉት

እሺ ሌላ ጥያቄ

እሺ ራህማንስ የት ነው የምታውቃት

ቅድም ምን አልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ እኔ እና ያያ የሚባል የእነሱ እቤት ሄደን እዛ ነው የእነሱ እቤት ነው የተዋወቅነው

ምንድነው እራህማ የምትሰራው

ተማሪ ናት

ይበቃናል

እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ በመሀል ተጀምሮ ነበረ ወደ እዛ ከመሄዳችን በፊት ድጋሚ ጥያቄ አሁን በተነሳው ላይ ካለ

የዐ/ሕግ ድጋሚ ጥያቄ

ቅድም የጠራናቸው ሰዎች አሉ አሁንም በመስቀለኛ ጥያቄ እና አብዲ አሊ የተከበረው ፍ/ቤት እዚህ ካለ ቢለይልን አብዲ አሊ

አይሰማም አብዲ

2154

አብዲ አሊ የተባለውን ሲጣራ ነበረ ከጠራቸው ስዎቹ ውስጥ አንዱ ነው

አም

እዚህ በችሎት ካለ እንዲጠየቅልን

ንገረዋ አብዲ አሊ አብዲ አሊ እሱን ታውቀዋለህ ወይ

አም አውቀዋለሁ

ታውቀዋለህ ታዲያ ቅድም ዞረህ አይተህ አልነበረ እንዴ

የዛን ጊዜ በደንብ አላየሁም ቃጠራም ስላደርኩት በደንብ አላየሁትም

እስቲ አሁን ተነሳ እና እንደገና ዙር በለው በል ተነስ ነቃ በል ወይ ፊትህን ታጠብ በለው ነቃ ብለህ ንፋስ ወስደህ ና በለው ውጪ አውጡት እና ተመልሶ ይግባ ለየህ በለው በዚህ በኩል ለየህ

ሴቶቹን በደንብ እስቲ ሴቶቹም ጋር በደንብ እይ

በእዛም በኩል እይ በእዛ በኩል አሁን ቅድም ያሳያኸውን አውቃለሁ ያልከውን እንኳን -- እሺ አብዲን ለይቶላቹህል

እሺ

አብዲ ማን ነበረ ስንትኛ ነህ 28ኛ እሺ አብዲ አሊ አህመድ ነህ

አብዲን መቼ ነው የምታውቀው

በ1998 ነው የማውቀው

እስቲ እንዴት ነው የተገናኛችሁት ለፍ/ቤቱ ግለፅልን

ለመጀመሪያ ጊዜ አርያ ከእነ አሪያ ዳዲ ጋር ከእነሱ ጋር ተገናኘን

ማን አገናኛችሁ

ያያ መሀመድ የሚባል

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጋሪቁ ጊዜያዊ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ

456

ተገናኝታችሁ ምን ተባባላችሁ ለፍ/ቤት እስቲ

እኔም በዛን ጊዜ አባል ስለነበርኩ አብረን እንድንሆን ነው

እሱ ምን ነበረ በወቅቱ በለው

ከእነ መሀመደ አባዲር ከሚባለው ጋር አብሮ እንደሚኖር ነው የማውቀው

ምን ብላችሁ ተዋወቃችሁ

በዛን ሰአት አንድ አንድ ሰዎችን ማደራጀት ስለሆነ ስራው ሰውን አደራጅቶ በዛን ሰአት አባዎ አባሎች ጋር ግንኙነት እንዲደረግ ነው

ማነው ይሄንን ያደረገው

ያው አንዱ የዛን ጊዜ እኔም አብሬ ነበርኩ አብዲም ነበረ እኔ ከእዛ በኋላ ግን እኔ አቆምኩ እሱ አብሮ ነበረ

አርአያ ምን ነበረ በለው

የአባዎች ሀላፊ ነበረ

እስቲ አብዲ ያደረግ የነበረውን በዝርዝር ንገረን

ከእነ አርአያ ጋር ሆኖ ጮቢ ፊ ቂሌ ጮባ የሚባል ቦታ አብሮ እንደሚንቀሳቀስ ነው የማውቀው

ለምንድነው የሚንቀሳቀሱት ምን ለማስፈፀም ነው

በተለያየ ነገር እና ሰውን ማደራጀት ስራቸው በእዛን ሰአት ብዙ ነው

መቼ ነበረ ወቅቱ

ከ89 ጀምሮ እስከ 2000 ድረስ እንደነበረ አውቀዋለሁ

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

በመጨረሻ የተለየ ተከሣሽ ስለሆነ መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ ፍ/ቤቱ ይፈቅዳል 28ኛ ተከሣሽን በተመለከተ

1156

ቀደም አድርገን 28 ቀደም አድርገን ተቃውሞ ያቀርብንበት ስለሆነ 28ኛ ተከሣሽን በሚመለከት እራሱ በተቀረበው ጥያቄ ላይ የህግ ቅሬታ ስላለን ጥያቄ አንጠይቅም

እሺ ጥያቄ የለም ተብሏል ድጋሜ ጥያቄም አይኖርም የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ካለ በሁሉም በተመሰከረው ጭብጥ ዙሪያ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

እስቲ በእነ ራህማ እና ጀና አብዲ ላይ በተሰይ ራህማ እና አብዲ አባላት ነበሩ ብለሀል እና እነሱ በአባልነታቸው ምንድነው የሰሩት

በእዛው ወቅት አብረው እንደሚሄዱ ነው የማውቀው

ሄዱ ማለት ምንድነው ለምንድነው ምን ሊሰሩ ነው የሚሄዱት

ያው ሰውን ለመቀስቀስ እና ሰውን ለማደራጀት እና ከተደራጀው ላይ ደግሞ ገቢ ለመሰብሰብ ነው

አንተ በአባልነትህ መዋጮ አድርገሀል ወይ በለው

እኔ በዛን ሰአት ተማሪ ነኝ እና እነሱ ደግሞ በአዋዳይ ዙሪያ ነው

መዋጮ የሚያደርጉትን ገንዘብ ለማን ነው የሚሰጡት በዛን ጊዜ

ኡመር ዳዲ የሚባል አለ ኡመር የሚባል ሰብስቦ ለዳዲ የሚባል ይሰጣል ለአርአያ ዳዲ ይሰጣል አርአያ ዳዲ ማለት የአነግ ሀላፊ ማለት ነው ለእሱ ይሰጣል

አብዲ በተለየ በአባልነቱ የሰራውን ነገር የሰራውን ነገር የምታውቀው ነገር ምንድን ነው

አሁን ቅድም የጠቀስኩት ቦታዎች ከእነዚህ ከእነሱ ጋር ሆኖ አብሮ እንደተንቀሳቀሰ ነው የማውቀው

ተንቀሳቅሰው ምንድነው የሰሩት

ያው ቅድም ገልጫለሁ እና ሰዎችን ማደራጀት እና ገቢን መሰብሰብ ከተደራጁት ላይ

2157

እሺ ራህማ እና አብዲ አባል ከነበሩ ጀና ምን ነበረች ያኔ ጀና ጀና ብቻ ጀና ምንድን ነው ተሳትፎዋ

ያው አበው ከእነሱ ጋር አብራ መሆንዋን ነው የማውቀው እንጂ ጀናን በውስጥ በደንብ አላውቅም

አባል አይደለህ አባል አልነበረችም

ከእነሱ ጋር መሄዷን ነው የማውቀው

መሄድ ማለት ምንድነው በመሄዷ ምንድነው የሰራችው ለድርጅቱ

አብረው መኖሯን ነው እንጂ በግሏ የሰራችው ነገር እኔ የማውቀው ነገር የለም

እና አብራ በመኖሯስ ምንድነው የሰራችው

እነሱ እንደ አጠቃላይ ቅድም የነገርኩት ነው የእነሱ ስራ ሰውን መቀስቀስ ማደራጀት ከተደራጀው ላይ ገቢ መሰብሰብ ነው ስራቸው ይሄ ነው

ራህማ ጀና እና አብዲ የአባሞ አባል ናቸው አይደሉም በለው

አሞ አሞ እስከ እኔ እስከ ከወጣሁ ወዲህ አላወኩም እስከ ከ88 እስከ 2000 ድረስ እስከ 2000 ድረስ የእነሱ አባል መሆናቸውን አውቀዋለሁ

ከ88 እስከ 2000

አሞ

ጥሩ ከ88 እስከ 2000 ዓ/ም ጃና እረሀማ እና አብዲ አባል ነበሩ በአባልነት ተንቀሳቅሰዋል ተንቀሳቅሰዋል አልተንቀሳቀሱም

አብረው መቆየታቸውን አውቀዋለሁ

አባል ነበሩ አልነበሩም ግልፅ አድርገው 3ቱ አባላት ነበሩ አልነበሩም ከ88 እስከ 2000

መቆየታቸውን ነው የማውቀው

በምንነት ነው የቆዩት

1/58

አባልነት

በአባልነት በአባልነት ከቆዩ ቅድም ያልከው የሰው ማደራጀት ገንዘብ መሰብሰብ ሰው መቀስቀስ የሚለውን ስራ ተቀብለው ይሰሩ ነበረ ወይ በለው

ቅድም የጠቀስኩት ስምች ጋር አብረው ይንቀሳቀሱ ነበረ

ጥሩ እነዚህ አሁን 3 ሰምች እራሀማ ጀና እና አብዲ ሰምችን ሲቀሰቅሱ ገንዘብ ሲሰበስቡ ሲያደራጁ አንተ የምታውቀው ነገር አለ ወይ በለው

እኔ ያው ከ88 ጀምሮ እኔ ከእነሱ ተለይቻለሁ አብዲ ጢቃ በታሰረበት ሰአትም ለእሱ ዋስ ተብሎ ይሄ ብሩ መሰብሰቡንም አውቃለሁ እነዚህ ግን እንደሚሰበሰብ አውቀዋለሁ እኔ ግን ከእነሱ ጋር ከ88 ወዲህ ከእነሱ ጋር አልነበርኩም

እንዴት ነው የምታውቀው አሁን እነሱ ያንን ስራ መስራታቸውን እንዴት ነው አንተ የምታውቀው የምታስረዳው እንዴት ነው

በተለያየ መንገድ አገኛለሁ የእዛ አካባቢ ልጆች አሉ

ከእዛ መረጃ ትቀበላለህ

እነዛ ልጆች አሁንም አብረን ነው ያለነው

እነሱስ አባል ናቸው ወይ መረጃ የሚሰጡህ

የተቀየሩም አሉ ያልተቀየሩም አሉ በዚህ ጉዳይ ላይ

ስለዚህ እነዚህ አሁን ያልካቸው መንቀሳቀሳቸውን ከእነሱ ነው የምታውቀው

እኔም እንደ ግሌ የማውቀው ነገር አለ ከእነሱም ደግሞ የማገኘው ነገር አለ

በግልህ ደግሞ የምታውቀውን እስቲ ንገረን ከእነሱ የምታገኘውን ነገርከን በግልህስ የምታውቀው ምንድነው

እንደ አጠቃላቅ ቅድም የጠቀስኩቸው ነገሮች ናቸው

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 4

459

ጥሩ ራህማ ይዜንን ስታደርግ ታውቃለህ አንተ በግልህ ቅድም በአጠቃላይ የጠቀስከውን ጥሩ ጀናስ ጀና ይዜንን ማድረጓን ታውቃለህ

አዎ አውቀዋለሁ

እሺ አብዲስ

አውቀዋለሁ

ይዜንን ነው የምታረጋግጠው ይዜንን ነው የምትለው ወይ ለፍ/ቤት

አዎ

ጥሩ አንተ ከ88 በኋላ ነው የወጣከው ከድርጅቱ በለው ስንት አመተ ምህረት አቆምክ ቀላል እኮ ነው ጥያቄው ከድርጅቱ አባልነት ስንት አመተ ምህረት ወጣህ

98 መጨረሻ

በ1998

አዎ

ከስንት አመተ ምህረት ጀምሮ ነበርክ በአባልነት

የተጀመረው 88 ነው

አመተ ምህረት አትችልም እንዴ የሚተረጉመውን ሰዎቹ እየተቃወሙህ ነው ከስንት እስከ ስንት ተናገር በአማርኛ ተናገር ከመቼ እስከ መቼ ነበርክ እዛ

98 መጀመሪያ ላይ እስከ መጨረሻ ወይንም 99 —

መጀመሪያ ድረስ ስለዚህ ከ98 እስከ 99 መጀመሪያ ነበርክ

አዎ

አንድ አመት ማለት ነው የነበርክው በዚህን ጊዜ እነሱ አብረውህ ነበሩ እንዴ

አዎ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

460

እነሱ ከእዛ በኋላ ቀጠሉ

አዎ

አንተ ወጣህ

2000 እኔ አውቃለሁ

አንተ ወጣህ

እህ

እነሱ እስከ 2000 ቀዩ

አዎ አውቃለሁ

ከ2000 በኋላስ ያቁሙ ይቀጥሉ እሱን እንዴት ታውቃለህ አንተ ማቆማቸውን አሁን እስከ 2000 ከ2000 በኋላ ያለውን ነገር ታውቃለህ እንዴ አንተ

እስከ ታሰሩ ድረስ እንደቀጠሉበት ነው የማውቀው

እሱን ታውቃለህ እሺ

አሁን ራህማ ጃና እና አብዲ ከኦነግ አባሎች ጋር ከመንቀሳቀሳቸው ውጪ እነዚህ ስዎች በግል ሰው ስለማደራጀታቸው ከሰዎች ገቢ ስለመሰብሰባቸው የምታውቀው ነገር አለ ወይ ሰው እንዳደራጁ ወይም ገቢ እንዳሰባሰቡ የምታውቀው ነገር አለ

በግል እኔ የማውቀው ነገር የለም ከእነሱ ጋር እንደሚንቀሳቀሱ ነው እንጂ በግላቸው የማውቀው ነገር የለም

እሺ እናመሰግንህለን ጨርሰህል ከኋላ ቁጭ በል ቀሪ የዐ/ሕግ ምስክሮችን ከቀትር በኋለ ከምሳ በኋላ እንቀጥላለን ማረሚያ ቤት 9 ሰአት ጀምሮ ፍ/ቤቱ የሚሰየም መሆኑን አውቃችሁ ከ9 ሰአት ጀምሮ ልታመጧቸው ሞክሩ 9 ሰአት ላይ ፍ/ቤቱ ከቀትር በኋላ እንደሚሰየም ነው::

ማ/ተ

1911

የመ/ቁ - 04489

ቀን - ጥር 19/2002

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰዒድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ

ከሣሽ - ዐ/ሕግ

ተከሣሾች - እነ አብዱራህማን ባሌ 73 ሲዎች

ባለው ክርክር ከቀትር በኋላ ተሰይመናል ምስክር መስማቱን ችሎቱ ይቀጥላል ሁሉም ተከሣሾች ቀርበዋል ማረሚያ ቤት

አዎ

ቀርበዋል ተከሣሾች መቅረባቸው ተረጋግጧል ምስክርነት መስማቱን እንቀጥላለን ማን ይጠራላችሁ ዐ/ሕግ

59ኛ ምስክር አብዱረዛቅ ረሀብ አብደላ

59ኛው አብዱረዛቅ

አዎ

ምስክር በዛሬው ችሎት ውሎ ቀርቧል በአስተርጓሚ እየተረዳ ሙሉ ስምህ ማን ነው በለው ምስክሩ መሀላ ፈፅሟል

59ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - አብዱረዛቅ ራቢር

አድራሻ - አና ምስራቅ ሀረርጌ አና ግሎዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ ፡ ጋራቁ ፍ/ቤት ፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

162

ስራ - የመንግስት ሰራተኛ ነኝ

የምታውቀውን ተከሣሽ ቆመህ ትለይልናለህ ፖሊሶች እርዱት እሺ ስማቸው ማነው አሁን ያየህ እዚህ የለየካቸው

አዎ አውቀዋለሁ

ስማቸውን ንገረን የእሱ ስም ማነው

አብዱራህማን ባሌ ጂቦት 1ኛው

እሺ የዚህኛውስ

ሌንጂሳ ቦኬ ይባላል አያቱን አላውቀውም

ሌንጂሳ ስንተኛ ተራ ቁጥር ላይ ነበር ዐ/ሕግ ታውቁታላችሁ

ምስክሩ ወይንስ

ማነው ስምህ አንተ

ዙቤር ሁሴን

ዙቤር ወይንም ሌንጂሳ ነው ያለው

ዙቤር

ዙቤር 11ኛ

ዙቤር ሁሴን መሀመድ ነህ ሁለቱን ብቻ ነው ወይ የምታውቀው በለው

ማወቅ ብዙውን ነው የማውቃቸው አሁን ለጊዜው ግን እነዚህ 2ቱን ብቻ ነው ልለይ የቻልኩት

እሺ ሌሎቹን መለየት አልቻልክም

ላይ ላዩን ነው የማውቃቸው እንጂ የውስጥ ስራቸውን በደንብ መግለፅ ስለማልችል ነው

እሺ ጥሩ ከእነሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ

463

የለኝም

እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

ዙቤር እና አብዱራህማን ባሌ አውቃቸዋለሁ ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለሀል ከእነሱ ጋር ከእነሱ ጋር ሌላ የምታውቀው ሰው አለ እነሱን ታውቃቸዋለህ በስም በስም በስም ተርጉምለት

አዎ አውቀዋለሁ

እነማንን ታውቃለህ በስም

እነ ከማል ይባላል አንዱ ከማል አልይ

ሌላስ

ኢብራሂም ደረሳ

እነዚህ ያውቃሉ

በስም ከመናገር --

በመልክስ

የምጠረጥር ሁሉንም በአይንም አውቃቸዋለሁ

እሺ አሁን የጠራካቸውን ባያቸው አውቃቸዋለሁ ነው እስቲ ካሉ በደንብ እያቸው አሁን

ሌላ--

ከማል አልይንና ኢብራሂም ሁሴንን እስቲ ስለእነዚህ እያንዳንዱን የምታውቀውን ነገር ለፍ/ቤቱ አስረዳ

እስቲ ቆይ አንዴ ማነው ስምህ ዙቤር ነህ ስምህ ማነው ዙቤር ሁሴን እሺ 11ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ከማል ስንተኛ ተራ ነው ያለከው 6ኛ

5ኛ

በኦሮሚያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

5ኛ ተከሣሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል እሱ አብዱራህማን ባሌ ነው 1ኛ ተከሣሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል አንተ ማነው ስምህ ስንተኛ ቁጥር ነህ ስምህ ማን ነው ኢብራሂም ሁሴን 14ኛንም ለይቶ አሳይቷል ይቀጥሉ ጥያቄ

እሺ ስለእነዚህ አሁን አውቃቸዋለሁ ስላልካቸው ሰዎች እስቲ ለፍ/ቤቱ የምታውቀውን ነገር አስረዳ ምን ምን እንዳደረጉ

ከአብዱራህማን ባሌ ላይ ነው የምጀምረው አብዱራህማን ባሌ ተማሪ ነበረ በ1999 ከተማሪ ውስጥ ወጥቶ እሱ የአባዎች የሆነ አመት በአል ነበራቸው ያንን አመት በአል ለማክበር ከትምህርት ቤቱ ሄዶ እዛ ጫካ ሊያከብሩ ሄደዋል በእዛን ሰአት ሽማግሌዎች እና ኮሚቴዎች በነበሩበት ቦታ ላይ አንድም ጫና ሳይደርስባቸው በፍላጐቱ እኔ ከሬዲዬ እንደሰማሁ ሻማ እና ሳማዎች በተለያየ አይነት ከለር ገዝቼ አንድ ዋንዛ ዛፍ ስር አክብሬ ዋልኩት የሞቱት የኦሮሞ ጀግኖች ስለምን ዋልኩ ጫትም ስቅም ዋልኩ አንድም ሰው ከእኔ ጋር አልነበረም በእዛ ገባሁ --- ይቅርታ አድርግልኝ ብሎ ግለይሱን አወረደ

ምንድነው ያከበረው በለው

የጀግኖች በአል

የትኞቹ ጀግኖች

የአባዎ ነው

አባዎ ሌላ ስም አለው ወይ በለው

በኦሮምኛ አባዎ ነው የሚባለው

ምን ማለት ነው

ነፃ አውጪ የኦሮሞ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ነው

መቼ ነው ይሄ የሆነው እና ቦታው የት ነው ዶቡርቃ ከተማ ውስጥ ነው እሱ ያከበረበት ኢጀ የምትባል ቦታ ውስጥ ነው ሰብቻ ለብቻው

ወቅቱ መቼ ነበረ

465

የካቲት ወር ውስጥ ነው በፍላጐቱ ይሄንን ነገር እሱ በቃሉ የተናገረ ነው ህዝቡ ላይ ይሄንን ሰምቻለሁ

ስለሌሎቹስ በለው

ሌንጂሳ ቦኬ የሚባል

እስቲ ሌንጂሳ ያልከውን አሳይ በለው አሳይ እንደገና አሳይ እንጂ የትኛው እሱ እሺ ተመለስ 11ኛ ተከሣሽን ጁቤር ሁሴን መሀመድን ሌንጂሳ እያለ እየመሰከረ ያለው በሌላ ስሙ ቀጥል

ቀኑን በውልም ባላውቅም ከአሁን በፊት በብዙ ጊዜ ከአባዎች ጋር እንደነበረ እና ከእዛ በኋላ በ1986 በ1986

1996 ይቀጥሉ ይቀጥሉ

በ1986 ውስጥ እንደነበረ አባዎች ተጠራርገው በሚጠፋበት ሰአት እሱ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ወደ ህዝቡ ተቀላቅሎ ነበረ ከእዛ በኋላ በ1997 በኋላ በሀሳብ ወደ እነሱ መመለሱን በሀሳብ እሱ ላይ የሰማሁት ነገር አለ ይሄም አንድ ሰው የአንድ ከዚህ ተልኮ የመጣ ጀማል ይባላል ጠርቶት እኛ ጋር አነጋገረው ለተማሪዎች እና ለእነዚህ ህዝብ ግልፅ አድርገህ አባዎች ምንም ጥቅም እንደሌላቸው ለህዝብ ኢፋ ታደርጋለህ ከእነሱ ጋር ደግሞ እንዴት መስመር እንደከፈትክ መጀመሪያ ለእኛ ግልፅ አድርገህ አብረን ከተነጋገርን ከተስማማን በኋላ ከእዛ በኋላ ለህዝቡ ግልፅ ታደርጋለህ ከተነጋገርን በኋላ እሱም በእዛን ጊዜ እንደገለፀው ለአባዎች ብዙውን ጊዜ ሳገለግል ቆይቻለሁ ሰውነቴም ለእሱ ስል ተጐድቷል ከእነሱ ምንም ያገኘሁት ጥቅም የለም ከ1997 ምርጫ በኋላ ቆብሳ የሚባል ሰውዬ ከጐለኦዳ ላይ የጠፋ ሰውዬ ጠርቶኝ በሀረር ከተማ ውስጥ አነጋገረኝ ከአሁን በፊትም የእኛ ወታደር ነበርክ ጠንካራም ነበርክ አሁንም የእኛን አላማ ከግብ ለማድረስ ከእኛ ጋር ትንቀሳቀሳለህ እንዴት ነው ብሎ አነጋገረኝ እኔ ደግሞ ምን ብዬ የመለስኩለት አሁን ነው ያገባሁት ለራሴም ችግር ውስጥ ነው ያለሁት እንደዚህ አይነት ነገር ውስጥ መመለስ አልችልም ብዬ መለስኩለት እሱም ከዚህ ነገር ላይ ደስ ስላላለው የእነሱን ሀሳብም በፊትም ስለማውቀው እኔንም ስለማይተውኝ መልሼ ከእናንተ ጋር ትግል ባላደርግም ትግሉ ላይ ግን እንቅፋት አልሆንም ይሄንን ብዬ መለስኩለት በዛን ሰአት ሽጉጥ 2 ሽጉጥ ሰጥቶኝ ቱምሳ ለሚባል ሰውዬ አድርስ ተባልኩ ከእዛ ይዤው ለዚህ ቱምሳ አደረስኩት ከእዛ

2166

በኋላ እኔ ላይ ተደርሶብኝ እሱ ጠፍቶ እኔ ያወጣሁበት በዚህ አይነት ነው ከዚህም ይዤ ነገር ዋጋ የለውም ብዬ ለህዝቡ ግልፅ አደርጋለሁ ብዬ በዚህ አላማ ላይ እኔ አጠገብ በመነጋገራቸው

ቆይ አንዴ አንዴ ቆይ

ቀጥሉ

በዚህ ጉዳይ ላይ ተረዳሁት ይዤንን ነው

ለማን ነው ይዤንን ብሎ የተናገረው

የፀጥታ ጠባቂ ይመስለኛል ከላይ ነው ተልኮ የመጣ በመንግስት መጥቶ እዛ እኛን በምናነጋግርበት ሰዓት ነው ጀማል ይባላል የዛን ጊዜ በእኛ ላይ ነው ይዤንን የተናገረው

እሺ ከማል አሊዩንስ በተመለከተ

ከማል አሊዩ እንግዲህ ኢብራሂም ደሬሳ የሚባል ፋጢሺ የሚባል በተጨባጭ በአይኔ ባላይም በእያንዳንዳቸው ባላይም ከተማሪዎች ጋር ሰላማዊ ሰልፍ ህገወጥ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳወጡ የሚከታተሉ ፖሊሶችና ከተማ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ልጆች እነዚህን ሲያደርጉ አየሁ ከዛ በኋላ ፍ/ቤቱ የወረዳው እርምጃ ወስዶበት የጠቀጣ ተማሪ ነበር ከማል ግን ይቀጣ አይቀጣ አላወኩም እነሱም ሁለቱ መጨረሻ ላይ ወደ አባጆ ተቀላቅለዋል ወደ አንድ አመት ያህል ከእነሱ ጋር ተንቀሳቅሶ ወደ 2000 አካባቢ ከነመሳሪያቸው መጥተው እጅ ሰጡ ከዛ በኋላ የማውቀው ነገር የለም::

ኢብራሂም ደሬሳ የሚባለው የትኛው ነው

ቁጭ በል ማን ነው ስምህ ኢብራሂም እሺ ኢብራሂምን አሳይቷል ቀጥል

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

አበቃችሁ ጥያቄ

ምን መሳሪያ ነው ያስረከቡት

መዩ ወረዳ የሚባል ላይ መሳሪያ እንዳስረከበ ነው እኔ በዛን ሰዓት ይፋ የተደረገው መሳሪያውን በአይኔ ስላላየሁ ይዤ ነው ብዬ መግለጽ አልችልም ከእነሱ ላይ የፈታ ሰውዬም ሺኖ ይባላል

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 4

8167

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

አበቃችሁ ጥያቄ

አዎ

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ለተከላካይ ጠበቃ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

መሳሪያውን ለማን ሰጠ ተባለ ከነመሳሪያው ገባ በምህረት ብለሃል ለማን ሰጠ ተባለ

አንድ ታጣቂ ሽኖ የሚባል ይሄ ታሞ በተኛበት ወባ ይዞት ሄዶ ሽሮ የሚባል ከእሱ ላይ መሳሪያውን ፈቶ

ከዛስ ምን ሆነ

ለመንግስት እጅ ሰጠ

ለመንግስት እጅ ሰጠና ተለቀቀ ወይ

ለተወሰነ ጊዜ ተለቆ በሰላም እየኖረ እንደነበረ ነው የማውቀው

እሺ ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት

እጃቸውን ሊያማክሩ ይፈልጋሉ መሰለኝ ይበቃችኋላ ጥሩ ድጋሚ ጥያቄ አለ ዐ/ህግ

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

እሺ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ከማልና ኢብራሂም ተማሪን ሰላማዊ ሰልፍ ሲያጋቀሳቅሱ መቼ ነው ጊዜው

በ1998

መሳሪያ ያስረከቡትስ መቼ ነው

1169

በ1999 መጨረሻ ወደ 2000 መግቢያ ላይ

ከዛ በኋላ ምን ተደረጉ በመንግስት

ከዛ በኋላ ከገባ በኋላ አንዱ እዛ ከተማ ነው አንዱን ደግሞ እዛ ከተማ አካባቢ ገጠር ነው ከዛ በኋላ በሰላም እየኖሩ ነው የማውቀው እኔ ከዛ በኋላ ግን ምን እንደሆኑ አላውቅም

አሁን የተያዙበት ጉዳይስ

አሁን አዲስ የተያዙበት ጉዳይ አላውቅም

እሺ እናመሰግንሃለን ከኋላ ቁጭ በል ዐ/ህግ ማን ይጠራላችሁ

እነዚህ ምስክሮች በጣም በርካታ ክሱም እጅግ በጣም በርካታ ነው አንድ ክስ ቢሆን በክስ ይመሰረት ይባል ነበር ስለዚህ ዐ/ህግ እያንዳንዱን ምስክር በሚገባበት ጊዜ ያ ምስክር ስለምን እንደሚያስረዳላቸው ጭብጣቸውን እያስያዙ ምስክሩ ይሰማልን የተከበረው ፍ/ቤት ምክንያቱም ክሱ በጣም በርካታ ነው በየትኛው ላይ ምስክር እንዳመጡት አይታወቅም ስለዚህ እያንዳንዱን ጭብጥ እያስያዙ ሊያስመሰክሩ ይገባል ይሄ ደግሞ ህጉ የሚያዘው ነው ስነ-ስርዓቱም የሚፈቅደው ነው

እሺ ዐ/ህግ የምትሉት አለ

ይሄንን በተመለከተ ለፍ/ቤቱ ከዚህ በፊት ክሳችንን ስናቀርብ ማን በማን ላይ እንደሚመሰክር በማስረጃ ዝርዝራችን ላይ በግልጽ አስቀምጠናል ከዛ ተነስቶ ፍ/ቤቱ ጭብጡ ያ መሆኑን ሊገምት ይችላል ብለን ነው የምናስበው

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል በክስ ማመልከቻው ላይ ቀደም ሲል ያለ ነው አሁን ደግሞ እየተመሰከረ ያለው እያንዳንዱ የሚያውቁትን ሰው እየለዩ የተመሰከረ ስለሆነ ለአካሄድም ብዙ ችግር እስከ አሁንም አልፈጠረም ወደኋላ መመለስም የለበትም ባለው መቀጠል ነው ያለብን ስለዚህ ቀጣይ ምስክር ይጠራ ማን ይጠራላችሁ

79ኛ ምስክር ይጠራልን አቶ አብዱረህማን አብዲላዚ

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ::

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ዘ69

79ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አብዱረህማን አብዱላሂ

ሥራ - ስራ የለኝም

አድራሻ- ከአለማያ ወረዳ

ጥሩ ለምስክርነት ነው የመጡት ጥሩ የሚያውቁትን ተከሳሽ ይነሱና ይለዩልናል እሺ ምስክሩ 1ኛ ተከሳሽ አብዱረህማን ባሌን በችሎት ለይቷል ሌላ የሚያውቁትን አማርኛ በደንብ ይችላሉ እንዴ

እችላለሁ በደንብ እችላለሁ

አንተም እዚህ ሁንና በአማርኛ እንቀጥላለን ምስክሩ አማርኛ እችላለሁ ስላሉ በአማርኛ ምስክርነቱን መቀበል ችሎቱ ይቀጥላል ከእሱ ሌላ የሚያውቁት የለም እንዴ እዚህ ውስጥ ከአብዱረህማን ሌላ

በእሱ ጉዳይ ነው የመጣሁት

በእሱ ጉዳይ ነው የመጡት

አዎ በእሱ ጉዳይ ነው የመጣሁት

ፀብ ዝምድና የሎትም ከእሱ ጋር

ምንም ነገር የለኝም

ጥሩ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እሺ አቶ አብዱረህማን እስቲ ስለተከሳሹ የሚያውቁትን ነገር ለፍ/ቤቱ ያቅርቡ ያዩትን የሰሙትን የተገነዘቡትን

እሺ ምንድን ነው በ1997 ዓ/ም ነው እኛ የቀበሌው ሊቀመንበር ነበርኩኝ በዛ ጊዜ ውስጥ በዛ ወቅት ማለት ነው እና የእሱን ጉዳይ እንድሰማ በፖሊስ እጋበዛለሁ በምጋበዝበት ሰዓት ያው

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር

41/70

እኛ ቁጭ ብለን እነሱ እሱን አመጡት እሱን ሲያመጡት ለፖሊሶች በትክክለኛ ያለ ምንም አስገዳጅነት ቃሉን ሲሰጥ ነበር እና በሚሰጥበት ወቅት እንግዲህ የሰማሁት ጉዳይ ቢኖር አንደኛ ነገር እሱ ኦነግ ነኝ ብሎ ሲናገር ሁለተኛ ነገር ደግሞ እንደገና ከጎሎኦዳ ከሚባለው አገር አወዳይ ከተማ መጥቶ ቪዲዮና የኦነግ ሬዲዮ ጣቢያ እንደሚያዳምጥ ቃሉን መስጠቱን በሶስተኛ ነገር ደግሞ እንደገና ያው ጎሎኦዳ ከተማ ውስጥ ቀይና አረንጓዴ ሻማ ይዞ ድልድይ ውስጥ የኦነግ አርበኞች ቀን የሚለውን አክብሬአለሁ ማለቱ ይሄንን ቃል ሲሰጥ ሰምቻለሁ።።

በወቅቱ የኦነግ አባል ነኝ ብሎ ነበር እና አባል በመሆኑ ያደረገው ነገር ምን ነበር ይሄ ሰውዬ

እኔ በዛን ወቅት ሲናገር የሰማሁት እንግዲህ ጊዜው ደግሞ በጣም ሩቅ ስለሆነ አሁን ለማስታወስ መቼም በጣም ከባድ ነው እና ግን ሲናገር ኦነግ አባል ሆኖ በዛን ጊዜ ውስጥ ያው ቀይ ሻማና አረንጓዴ ሻማ ይዞ ድልድይ ስር የኦነግ አርበኞች ቀን ብሎ ማክበሩን ሲናገር ነበር የማውቀው

እሺ ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

አበቃቸሁ ጥያቄ

አዎ

መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ይቀጥል

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስለቀኛ ጥያቄ

እኔነኝ ያከበርኩት ነው ያለው

አይደለም ስማቸውን ባልጠቀሰው ከጓደኞቼ ጋር ነው ያለው

ከጓደኞቼ ጋር ምን አደረገ አከበረና

እሱ እኔ ያደረገውን አላውቅም ቀይ ሻማ አናአረንጓዴ ሻማ ይዘን ድልድይ ስር የኦነግ አርበኞች ቀን እናከብራለን ብሎን አከበርን ብሎ ሲናገር እኔ የሰማሁት

አከበርን ብቻ ነው ያለው

አዎ ይሄንን ነው የሰማሁት

ይሄንን ቃል ለማን ነው የሰጠው

ለፖሊስ ለአለማያ ወረዳ ፖሊስ ነበር ያን ጊዜ እኛም የተጋበዝንበት የአለማያ ወረዳ ፖሊስ ነው በታዛቢነት እንድንሰማ እኛ እንትን የተባልነው

ከአንተ እና ከእሱ ማን በፊት ገባ እዛ ጣቢያ ምርመራ ክፍሉ

እኛ ነው የገባነው መጀመሪያ እኔ ነኝ የገባሁት እኔ ገብቼ እሱ ተጠራ

እሱ ተጠራ

አዎ

ከአንተ ጋር ማን ነበር

ሌሎች አባሎች ነበሩ እንደእኔው በዚህ ጉዳይ ላይ የተጋበዙ

ስንት ነበራችሁ

እኛ በዛን ጊዜ ውስጥ ሶስት ነበርን

ስማቸውን ታውቀዋለህ

አዎ አውቃለሁ አንደኛው አድማሱ ይባላል አንደኛው ደግሞ ዚያድ ይባላል

ዚያድ ይባላል አሁን ፖሊሱ ይሄንን ቃል ብትፈልግ መስጠት ትችላለህ ብትፈልግ አለመስጠት ትችላለህ ይሄ የምትሰጠው ቃል በሌላ ፍ/ቤት ማስረጃ ሆኖ ይቀርብብሃል ብሎ ሲነግረው ሰምተሃል

እኔ ምንም የሰማሁት ነገር የለም አንድም ነገር ቃሉን ብቻ እዛ ቆሞ እኛ በታዛቢነት እንድንሰማ ነው እሱ የሚናገረውን ነገር ብቻ እንድንሰማ ነው

አደለም ይሄንን ብሎ ሲነግረው ሰምተሃል አልሰማህም

አልሰማሁም እኔ

እግዚአብሔር ይስጥህ

4/72

አበቃችሁ መስቀለኛ ጥያቄ ድጋሚ ጥያቄ አለ ዐ/ህግ የላችሁም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አብዱረህማን ባሌን በምንነት ነው የምታውቀው

እኔ በግምት ያን ቀን ብቻ ነው ያየሁት

ያየከው

ያየሁት አዎ

እንጂ ምንም አታውቅም

ምን እንደሆነም አላየሁትም አዎ እኔ ለ10 ደቂቃ ነው ለ20 ደቂቃ ነው

በታዛቢነት ነው የጠሩህ

በታዛቢነት አዎ

ከዛ ምን አለ እሱ

ቃሉን ሲሰጥ ብቻ እቺ አሁን የተናገርኩትን ቃል ሲሰጥ ብቻ ነው ሌላ ምንም የሰማሁት ነገር የለም

የሰማከው

አዎ በቃ

እሺ እናመሰግኖታለን ጨርሰዋል ከኋላ ይቀመጡ ሌላ ማን ይጠራ ዐ/ህግ

አብዲ አደም

አብዲ ስንተኛ ነው እሺ ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር ቀርቧል መሀላ ፈጽሟል

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ።

አማርኛ ትችላለህ በደንብ

473

እችላለሁ

ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አብዲ አደም

ሥራ - የመንግስት ሰራተኛ

አድራሻ- ሐረማያ ከተማ 01 ቀበሌ የቤት ቁጥር ------

ኑሮዬ አለማያ ነው ስራዬ ሐረር ነው

የምታውቃቸው ተከሳሾች አሉ እዚህ ውስጥ የምታውቃቸውን እስቲ አሳየን ተከሳሾች

የሉም እኔ የማውቃቸው የሉም እዚህ

እንዴት እርግጠኛ ሆንክ ሳታይ

እኔ እዚህ ውስጥ

አይተህ አረጋግጥ ቁምና መጀመሪያ እይ ሁሉንም ዞረህ እይ ቀስ ብለህ ለምንድን ነው የመጣከው ዛሬ

እኔ የመጣሁት በአነግ አባሎች ላይ ቃሌን ሰጥቼ ነበር ከአሁን በፊት ማለት ነው

ለምስክርነት ነው ማለት ነው

አዎ እና በምስክርነት ሳይሆን እኔ የኮሚኒቲ ፖሊሲ ነበርኩ በዛ ቀበሌ ማለት ነው ሰፈር ስገመግም ነበር

ምን ነበርክ የፖሊስ

ኮሚኒቲ ፖሊሲ ማለት ነው ይሄ የሰፈር ጥበቃ ማለት ነው

ኮሚኒቲ ፖሊሲ

አዎ ፖሊስን ሰፈር ውስጥ ተባብረን ለመስራት ማለት ነው

ጥሩ እሺ በዛ ጉዳይ ነው የመጣከው

አዎ

እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

እኔ አሁንም የማውቃቸው

ቆይ ቆይ አዳምጥ ጥያቄ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

በነማን ላይ ነው ለምስክርነት የመጣከው

እኔ አሁን ጀማል አሊ የሚባለው

ቆይ ተቃውሞ አለ

ይሄ ምስክር በአንድ ሰው ላይ ይመሰክራል ተብሎ ነው ጭብጥ የተያዘው ስለዚህ በነማን ላይ ተብሎ ሊጠየቅብን አይገባም በቃ ጭብጡ የለየነው በእንዲህ ያለ ቁጥር ላይ ይመሰክራል ተብሎ ጭብጡን አስይዟል ከዛ ውጪ ሊጠየቅብን አይገባም

እሺ እዚህ ላይ መልስ ዐ/ህግ

እኛ በተራ ቁጥር 8 ላይ ለፍ/ቤቱ የምስክሮች ዝርዝር ማለት ነው አብዲ አደም ኡስማን የሚባለው አንተ ነህ አይደለም

ነኝ

እሱ በአንድ ሰው ላይ ሳይሆን በሶስት ሰዎች ላይ ነው የሚመሰክረው

በተራ ቁጥር ስንት

8 ላይ

እሺ

እና እሳቸው ያሉት ነገር ከዚህ ጋር የሚያያዝ ስላልሆነ እነማን ናቸው የሚለውን ነገር ከዚህ የተነሳ ነው

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር ፩ የፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

1/75

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል ማስረጃ ዝርዝሩ በግልፅ የተለየ ስለሆነ ስለዚህ ሶስት ሰው ስለሚያሳይ ጭብጡ የሶስት ሰዎችን 49ኛ፣ 50ኛ እና 51ኛ ተከሳሾች ላይ ይላል ስለዚህ ይቀጥል ተብሏል ቀጥሉ።

አብዲ አደም

አቤት

በነማን ላይ ነው ምስክርነት ልትሰጥ የመጣከው

እኔ ጀማል መሀመዴ አሁን ጀማል አሊ የሚባለው ላይ እና ፉአድ አብዱላሂ ኡስማን የሚባለው ላይ ነው መጀመሪያ እዛ ቃሌን የሰጠሁት ማለት ነው እና መሀመድ አባድር የሚባለው ላይ ነው ሶስት ሰዎች ላይ ነው እኔ ቃሌን የሰጠሁት ማለት ነው

እነዚህ ብቻ ናቸው ተጨማሪ ካለ አስታውስ

አላስታውስም ሶስቱ ናቸው

እስቲ ድገምልን

ጀማል መሀመዴ፣ ፉአድ አብዱላሂ ኡስማኔ እና አባድር መሀመድ የሚባለው ነው

የተከበረው ፍ/ቤት አሁን የምናሳስበው ምንድን ነው ከዚህ በፊት የሰጠው የምስክርነት ቃል አለ ለፖሊስ ምስክርነት ቃልህን ሰጥተህ ነበር ሰጥቻለሁ ብለሃል ከዚህ በፊት

አዎ እኔ የሰጠሁት ሶስቱ ሰዎች ላይ ነው የሰጠሁት ፋይሌን እኮ ጠዋትም እዛ ዐ/ህግ ቢሮ አይቼዋለሁ የቀረበልኝን አይቼአለሁ ስማቸውን ሳይ ስማቸው እኔ እዛ ላይ ቃሌ የተቀመጠው ትክክል አይደለም ብዬ እዛም ከዐ/ህግ ጋራ ራሴ እዛ ተከራክሬአለሁ እኔ እዛ ላይ ደግሞ ያለው ፊርማ የራሴ ፊርማ አይደለም እኔ እዛ ላይ አልፃፍኩም የእኔም ፊርማ እዛ ላይ አላኖርኩም አሁን ሳየው እዛ ላይ ፊርማው የእኔ የተለየ ነው እንጂ እኔ የሰጠሁት በሶስት ሰዎች ላይ ነው ቃሌን የሰጠሁት ማለት ነው

ጀማል ማን ነው የአባቱ ስም

ጀማል መሀመዴ ነው ወይም ጀማል አሊ ይባላል

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ

1176

ጀማል መሀመዴ

አሞ ጀማል መሀመድ ይባላል

ፉአድስ

ፉአድ አብዱላሂ ኡስማን ይባላል

አብዱላሂ

አብዱላሂ ኡስማን

አባድር መሀመድ

አሞ

ጥሩ እሺ ዐ/ህግ የምትሉት ነገር ካለ እዩና

እሺ ከዚህ በፊት የምስክርነት ቃል ሰጥተህ አልፈረምክም

እኔ አልፈረምኩም

ቃል አልሰጠህም የምስክርነት ቃል

ቃል ሰጥቻለሁ እኔ ቃል የሰጠሁት ያየሁትን ነው በዛን ጊዜ በነሱ በሌሉበት ነው ያወራነው ወይም ግምገማ ግምገማ ላይ ሆነን ነው ማለት ነው ያወራሁት እኔ እንጂ ይሄ ትክክለኛ ብዬ እኔ ያስቀመጥኩት ሰዎች ሶስቱ ሰዎች ናቸው

እሺ ማን ማን ብለህ ነው ቃል የሰጠከው

እኔ ጀማል መሀመዴ፣ ፉአድ አብዱላሂ ኡስማን እና አባድር መሀመድ የሚባሉ ናቸው

እና አንተ ቃል የሰጠከው እዚህ በሌሉ ሰዎች ላይ ነው ማለት ነው

አሞ አሁን አንደኛው ተይዟል አሁን ተይዞ እስር ላይ ነው ያለው

ማን ነው እሱ

ጀማል መሀመዴ

ሀ፯፯

እዚህ ውስጥ የለም

እዚህ ውስጥ የለም ሐረር መምሪያ ፖሊስ ጣቢያ ነው አሁን ያለው ማለት ነው ተይዞ

ምናልባት ፍ/ቤቱ ምንም ምስክር አልሰጠሁም በነዚህ ሰዎች እኛ በያዝነው ጭብጥ ላይ ፍ/ቤት በሰጠው ላይ ከዚህ በፊት ቀድሞ ፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ምስክርነት ቃል ላይ አልሰጠሁም አልፈረምኩም እያለ ስለሆነ እዚህ ደግሞ እኛ ጋር የተፈረመበትና በእሱ በሚገልፀው አድራሻና በሚገልፀው ስሙን በነገረና በሰጠው አድራሻ መሰረት የተፃፈና የተያዘ ስላለ ይሄ መሆን አለመሆኑን አላውቅም ስላለ እየመራን እንድንጠይቀው እንዲፈቀድልን ነው የምናሳስበው

መቃወሚያ አላችሁ እሺ መቃወሚያው ይመዝገብ

አንደኛ ዋናው በመጀመሪያ መሪ ጥያቄ አይፈቀድም ህጉ ራሱ 37 ይከለክላል መሪ ጥያቄ እንደው ፈጽሞ አይፈቀድም ሌላው ሰውዬው እኔ እገሌ በእገሌ ላይ በተባሉት ላይ ቀርቤ መስክሬአለሁ ጠዋትም ዐ/ህግ ተጠይቄ ፊርማዬን አይቼ አይደለም ብዬ ከእነሱም ጋር ተከራክሬአለሁ እና አይደለኝም ብሎ እያረጋገጠ ግድ በማያውቀው ሰው ላይ መስክር ተብሎ በዚህ ትልቅ ችሎት ላይ ሊጠየቅ እንዲህ አይነት ጥያቄም ሊቀርብም አይገባም ጥያቄውም አግባብ አይደለም ፍ/ቤቱ ይዳኝ

የምንለው አለ

እሺ

እኛ ይሄንን ብለሃል እያልን እያስገደድን አይደለም አላልኩም ብያለሁ እያለ አልመሰከርኩም እያለ ይሄንን አለመመስከሩንና የእሱ ፊርማ አለመሆኑን እና እዚህ ላይ ያለውን ቃል አለመስጠቱን ያረጋግጥልን እንዲያረጋግጥ መሪ ጥያቄ እንጠይቅ ነው ያልነው ይሄንን እንዲያረጋግጥልን ነው የጠየቅነው

ፊርማውን እንዲያረጋግጥ

እዚህ ላይ የምስክርነት ቃሉን በእነዚህ ሰዎች ላይ መስጠት አለመስጠቱን አልሰጠሁም እኔ አይቼዋለሁ እያለ ነው አሁን ዳኛው ያየውና በፍ/ቤት በችሎቱ ፊት ችሎት ፐፐሊክ ነው የሰጠውም የምስክርነት ቃል እኛ ጋር አለ እያልን ነው ለትክክለኛ ፍትህ ይቅረብና እምቢ ይበል 137 ንኡስ አንቀጽ 2 ደግሞ በምስክሩ አላውቅም ባለ ጊዜ ዐ/ህግ ወይም ደግሞ ምስክሮቹን

ሀገ

ያቀረበው አካል ፍ/ቤቱን ጠይቆ ፍ/ቤቱ ሊፈቅድለት እንደሚችል ህጉ በግልፅ ይደነግጋል አይከለክልም ስለዚህ ይሄ ሰውዬ ይሄንን የምስክርነት ቃል አልሰጠሁም እያለን ነው እኔ የሰጠሁት አለ እያለ ነው ሌላ ቦታ ስም እየነገረን ነው ያለው እኛ ጋ ደግሞ የሰጠው የምስክርነት ቃል እዚህ ጋ አለ ስለዚህ አንድ በአንድ እየነገርነው እነዚህ ላይ አልሰጠህም ወይ ሰጠህ ብለን ልንጠይቅ ነው ስለዚህ ይሄ በህጉም ላይ በግልፅ የተቀመጠ እና ያልተከለከለ ነው ምስክሩም ሙሉ ለሙሉ አላውቅም እያለ አስጠቂ ስለሆነ ይሄ እንዲፈቀድልን ነው የምንጠይቀው::

የፖሊስ ቃሉን ስጡን ስጡት ለምስክሩ እስቲ ተመልከተው ከላይ እና ፊርማውን እየው ጠዋት ያየከው ነው ስምህን እየው ከዛ ፊርማህን እየው

አዎ

እና የአንተ ነው አይደለም የሚለውን ታረጋግጣለህ

ፊርማው የእኔ አይደለም

የአንተ አይደለም ይሄንን ታረጋግጣለህ ለፍ/ቤት ጥሩ እሺ አሁን አምጣው እስቲ አምጡት አብዲ አደም ኡስማን ነህ አደለም

አዎ

አብዲ በዩሱፍ ዳውድ ላይ ምስክርነት አልሰጠህም እንዴ ለፖሊስ

እኔ አልሰጠሁም

አልሰጠህም በመሀመድ አባድርስ

ሰጥቻለሁ

በመሀመድ አባድር

አዎ

ነው በአባድር መሀመድ

መሀመድ አባድር ላይ ነው

ኮ/ግ

መሀመድ አባድር ላይ

አዎ ፉአድ አብዱላሂ

እሺ በመሀመድ ኡመሬስ

መሀመድ ኡመሬ አልሰጠሁም እኔ

አልሰጠህም

አዎ

ፉአድ አብዱላሂ

አዎ

እዚህ ላይ ሰጥተሃል

አዎ

አህመድ ሙመድስ

አህመድ ሙመድም ነበር አዎ

ነበረ

ነበር እንጂ እኔ በእሱ ላይ ቃል አልሰጠሁም

እ

እኔ አህመድ ሙመድ የሚባለው ታስሮ የተለቀቀ ነው በዛን ጊዜ ማለት ነው

እሺ ጥሩ ጃፈር ኡመርስ

ጃፈር ኡመር ላይ አልሰጠሁም እኔ

በመሀመድ አባድር ላይ ግን ሰጠህ

አዎ እዛ አዎ ተናግሬአለሁ እሱን

ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር

ነገ ዋ

የት ነው ይሄንን ቃል የሰጠከው ያኔ

ያን ጊዜ አሁን እንዴት መሰሎት ትክክል በአማርኛ አይደለም የተፃፈው እዛም ቃላት ጠየቁኝ እኔ ራሱ በዛን ጊዜ ኮሚቴ ነበርኩ ማለት ነው እዛ ውስጥ ያንን ነገር ለመገምገም የተቀመጥኩኝ ነኝ እኔ ከፖሊስ ከቀበሌ መስተዳድሮች ጋራ አብረን ተቀምጠን ነው እየጠራን ስንገመግም የነበረው እንጂ እኔ ምስክር አይደለሁም በዛ ላይ እነሱን ስገመግም የነበርኩ ነኝ ግመገማ ላይ ነበርን እኛ እንጂ ቃሌን ምስክር ትክክለኛ አየሁ ብዬ የሰጠሁት እነዛ ናቸው ስናገሩ የሰሙት ግን ሌሎች ናቸው እንጂ እኔ አይደለሁም

በጀማል መሀመዴ እና በፉአድ አብዱላሂ እና በመሀመድ አባድር

አዎ በሶስቱ ላይ እኔ ትክክለኛ

ቀኑንስ ታውቀዋለህ መቼ ቃል እንደሰጠህ

ቀኑን አላስታውስም

አታስታውስም አመተ ምህረቱንስ

አመተ ምህረቱ 79 መሆኑን አውቀዋለሁ

ስንት

79 ማነው 97 ማለት ነው

97

አዎ

ዛሬ 2002 ነው

ዛሬ 2002 ነው አዎ

በ97 ነው ሰጠሁ የምትለው

አዎ 97 ነው ሲንቀሳቀስ የነበረው ማለት ነው

በምን እንደተፃፈ ትዝ ይልሃል የአንተ ምስክርነት ቃልህ ፖሊስ የተቀበለህ

እኔ ፊርማ ላይ ነው

ፈርመሃል

እኔ አልፈረምኩም ተለያየን የዛን ጊዜ ሌሎቹ ግን ከእኛ ጋር የነበሩ

በ1997 ነው ቃል የሰጠከው ምስክርነት የሰጠከው ለፖሊስ

አይደለም አሁን አንድ አመት ከምናምን ነው

አሃ ቃልህን ከሰጠህ

አዎ ይሄንን ግምገማ ያካሄድንበት ጊዜ ማለት ነው

ምስክርነት ቃል ከሰጠህ አንድ አመት ሆኖታል

አዎ

በ2001 ማለት ነው

አዎ እንደዛ አካባቢ

ቦታውስ የት ነው የሰጠከው

እዛ ሰፈር ውስጥ ነው

የት ሰፈር

እዛ 01 ቀበሌ ማለት ነው ቀጠና 7 ላይ

የት የት አካባቢ

አለማያ

አለማያ

አዎ

የት ነበር የምትሰራው አንተ የምን ሰራተኛ ነህ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቅጅ ነው

493

እኔ ሐረር ውሃና ፍሳሽ ነኝ

የመንግስት ሰራተኛ ነህ

አዎ

ትዳር አለህ አደለ

አለኝ አዎ

ትምህርትስ እስከ ስንት ተምረሃል

ትምህርት እስከ 8 ተምሬአለሁ ወይም 8 አላለፍኩም 7ኛ ላይ ነኝ

7ኛ ላይ

አዎ

እስቲ ወረቀት ስጡትና እስቲ ስምህን ፃፍ እና ፈርም ፈርም እስቲ

ስምህ ማን ነው

አብዲ አደም

አብዲ

አዎ

ስምህን ስትጽፍ ታዲያ እንዴት ነው አድርገህ የምትጽፈው

እ

አብዲ

አብዲ አዎ ግራኝ ነኝ እኔ እንደዛ ነው የምፅፈው

አብዲን በትክክል ፃፍ እስቲ

እኔ እኮ ምስክር አልሆንኩም ሶስቱ ላይ ቃሌን ነው የሰጠሁት እኔ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ ፌ/ቤት ቁ ፫
የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

2184

እኮ በምንነት በምንድን ነው ቃልህን የምትሰጠው በምክርነት ነው

በዛን ጊዜ አደለም

በምንነት ነው ቃል የሰጠከው

ዩሱፍ ዳውድ የሚባለው እዛ ሲወራ ነበር እንጂ እኔ ምስክር አይደለሁም

በየትኛውም ጉዳይ ላይ ምስክር አይደለህም አንተ

ሶስቱ ላይ ነው እኔ የመሰከርኩት የዛን ጊዜ ሶስቱ ላይ አንዱ አሁን የተያዘው ሌሎቹ አልተያዙም

እሺ ይሄንን መልሱ ለዐ/ህግ ስጧቸው እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበት ብይን ሰጥቷል የግራቀኙ ክርክር እየመሩ ለመጠየቅ ምስክሩ አስጠቂ ነው በሚል የተነሳ ነጥብ አለ በዐ/ህግ በኩል በተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ በኩል ደግሞ ህጉ በግልፅ የከለከለው ነገር ነው የመምራት ጥያቄ እና ሊፈቀድ አይገባውም ነው ፍ/ቤቱ የተሰጠውን የምስክር ቃል ፊርማ የምስክሩን ፊርማ እንደዚሁም በፖሊስ የተሰጠውን ቃል ለመመልከት ሞክሯል በይዘቱ ዛሬ የቀረበው ምስክር መሰከርኩ የሚላቸው አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ስም ተመልክቷል በሌላ በኩል ደግሞ ምስክርነት የሰጠሁት ከእነዚህ ውጪ ያሉ ሰዎች ናቸው የሚል ነገር አለ ዞሮ ዞሮ ግን ምስክርነት የሰጠበት በፖሊስ የተያዘ ቃል በመኖሩ ሲጠየቅም በአንዳንዱ ላይ እያረጋገጠ በሌላው በኩል ደግሞ ያለማረጋገጠ አዝማሚያ ፍ/ቤቱ ስለተረዳና ስለተገነዘበ አስጠቂ ምስክር መሆኑን ፍ/ቤቱ ስለሚረዳ ይህ ሲሆን ዐ/ህግ እየመራ ጥያቄ ማቅረብ እንዲችል ይፈቀዳል በኢትዮጵያ በህግ ስርዓትም የተከለከለም አይደለም በግልፅ በአዲሶቹ ስነ-ስርዓት ህጎችም እየተፈቀደ ያለ ስለሆነ እየመሩ የፖሊስ ቃሉን ይዘው እየመሩ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ ፈቅዷል።

አቶ አብዲ

አቤት

መሀመድ ኡመርን ታውቀዋለህ

አውቀዋለሁ አዎ

ቁ 195

የት ነው ያለው

ድምጽ ትንሽ

እስር ቤት ነው እዚህ እስር ቤት ነው ያለው

አሁን እዚህ አዳራሽ ውስጥ አለ

ታረጋግጣለህ

እዚህ አዳራሽ ውስጥ አለ ወይ

አለ አሥ

እስቲ አሳየን

ማን ነው ያልከው ቆይ እስቲ አንዴ

መሀመድ ኡመሬ

እስቲ አሳየን መሀመድ ኡመሬን እዚህ ቁምና ባለህበት ቁምና ከዚህ ሆነህ አሳየን ስንተኛ ተራ ላይ ነው ያለከው 49 እሺ 49ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለውን መሀመድ ኡመሬን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ቀጥል ጥያቄ

ዩሱፍ ዳውድንስ ታውቀዋለህ

ዩሱፍ ዳውድን

እ

አላውቀውም

ከዚህ በፊት አታውቀውም

አሥ

አሁንም አታውቀውም

ሌሎቹን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

486

ዩሱፍ ዳውድን

ዩሱፍ ዳውድ አላውቅም

አታውቀውም

ዩሱፍ ዳውድ እኔ የማውቀው አልገባም እያልኳችሁ እኮ ነው አልገቡም ሌሎቹ

ጥያቄውን ብቻ መልስ

አላውቀውም

እሺ ሌላ ጥያቄ

ጃፈር ኡመርንስ

ጃፈር ኡመርን አውቀዋለሁ

የት ነው ያለው

እዚህ ነው ያለው

እስቲ አሳየን

እስቲ አሳየን እስቲ ብድግ በል ማን ነው ስምህ ስንተኛ ነህ 50 እሺ ይቀጥሉ ጥያቄ ዐ/ህግ

እነሱን በተመለከተ ከዚህ በፊት የምስክርነት ቃል ለፖሊስ አልሰጠህም

አልሰጠሁም

መሀመድ ኡመሬን በተመለከተ ዩሱፍ ዳውድንም በተመለከተ ጃፈር ኡመርንም በተመለከተ ከዚህ በፊት የምስክርነት ቃልህን አልሰጠህም

አልሰጠሁም

ማንበብ መፃፍ ትችላለህ

እችላለሁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

487

ስራህ ምን ነበር

ስራ ቢንቢ ሰራተኛ ነኝ

አሁንስ

አሁንም ቢንቢ ሰራተኛ ነኝ

የመንግስት ሰራተኛ ነህ

አዎ

እና በእነዚህ ሰዎች ላይ የሰጠከው የምስክርነት ቃል ከዚህ በፊት የለም

እ

በእነዚህ ሰዎች ላይ ለፖሊስ የሰጠከው የምስክርነት ቃል ከዚህ በፊት የለም

የለም

ስለ እነሱ የምታውቀው ነገር የለም

የለም ስለ እነሱ የማውቀው ነገር የለም

ጨርሰናል

እሺ ጥያቄ ትጠይቃላችሁ እንዴ የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ትጠይቃላችሁ እንዴ

እኛ አንጠይቀውም

እሺ ድጋሚ ጥያቄም አይኖርም የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄም የለም እሺ እናመሰግናለን ጨርሰሃል መሄድ ትችላለህ ማን ይጠራ ዐ/ህግ 26ኛ ማን ነው

አብዲ አህመድ

አብዲን ጥሩ መሀላ ፈጽሟል

26ኛ የዐ/ህግ ምስክር

1198

ስም - አብዲ ሙመድ አብዱላሂ

ሥራ - አርሶ አደር

አድራሻ-

ቆይ እስቲ አንዴ ዐ/ህግ

ስምህ ማን ነው

አብዲ ሙመድ

እኛ የጠራነው 26ኛ አብዲ አህመድ ሼክ

ይሄ አብዲ ሙመድ አብዱላሂ

አብዲ አህመድ ሼካ ነህ ነኝ አለ

አደለሁም አለ

አንተ ማን ነህ በለው አብዲ ሙመድ አብዲላሂ

አብዲ አህመድ ሼካ የለም አሁን

13ኛ ምስክር አብዲ ሙመድ ከእሳቸው በፊት ሌላ ምስክር ይሰማልን ስለተባለ ሌላው ምስክር እንዲቀርብ ታዟል ማን ነው አሁን የሚቀርብላችሁ

78ኛ

78ኛ አድማሱ አደሜ እሺ መሀላ አስፈጽሙ

በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ።።

78ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አድማሱ አለሙ አያሌው

ሥራ - 01 ቀበሌ ፀሐፊ ነበርኩ በወቅቱ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፍ/ቤት ቁጥር 4 የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

489

አድራሻ- አለማያ 01 ቀበሌ

ዛሬ ለምን መጡ እዚህ

ለደረጃ ምስክርነት

ደረጃ ምስክርነት በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት

በአብዲ ባሊ

በአብዲ ባሊ ሌላስ በዚህ ብቻ ነው የሚመሰክሩት

በዚህ ብቻ ነው

እስቲ አሳዩን እዚህ ውስጥ አለ

ይኖራል እንግዲህ

እስቲ አሳዩ ተነሱና 1ኛ ተከሳሽን በችሎት ለይተው አሳይተዋል ጥሩ ፀብ ዝምድና አሎት ከእሱ ጋር

የለኝም

ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እስቲ አብዲን በተመለከተ የሚያውቁትን በደረጃ ምስክርነት የሚያውቁትን ለፍ/ቤቱ ያስረዱልን

አብዲ ባሌን በተመለከተ የማውቀው በአለማያ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ በፍላጎቱ ቃሉን ሲሰጥ እኛንም የቀበሌ ፀጥታ ሃላፊ ስለሆንኩ ተጠርቼ በወቅቱ እንዳዳምጥ ተደርጌ ነበር በወቅቱ በዛን ጊዜ እና እሱ በወቅቱ ያለ ምንም ተፅእኖ ለፖሊሶች ቃሉን ሲሰጥና የኦነግ አባል መሆኑን እንደገና ከጎሎኦዳ ወደ አወዳይ በመምጣት ከውኑ ስማቸውን የጠቀሳቸው አለ አሁን የረሳኋቸው ስላሉ ከእነሱ ጋር በመሆን አወዳይ ውስጥ የኦነግ እንትኖችን ይመለምሉ እንደነበር እንዲሁም እንደገና የኦነግን ካሴት እንዳዩ ሲሳው የኦነግ ሻማ አረንጓዴ እና ቢጫ የኦነግ ጀግኖች ቀን በማለት የኦነግ ድልድይ ስር አብርተው እንዳከበሩ እና የቪዮዬ እና የኦነግን ሬዲዮ

ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

4/9/0

እያዳመጡ የኦነግን መመልመል እንደያዙና የኦነግ ሙሉ አባል ነኝ ብሎ ቃሉን ሲሰጥ በወቅቱ አዳምጬ ሰምቻለሁ::

መቼ ነበር ይሄ የሆነው

የሆነው 1977 ታህሳስ ወር አካባቢ ቀኑን ባላውቀው እዛ አካባቢ ነው

ስንት አመት ይሆነዋል

አምስት አመት

ዛሬ ስንት ነው ይሄ አመተ ምህረት አሁን ያለንበት

አሁን 2002 ነው

አምስት አመቱ ነው ብለዋል መቼ ነው ታዲያ

1997 ነው ነገሩ

ቦታውስ

ቦታው አለማያ ፖሊስ ጣቢያ

ዋና ጥያቄ ጨርሰናል

አበቃችሁ

አዎ

መስቀለኛ ጥያቄ ካለ እንደዚሁ ይቀጥል ለተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

እሱ የሰጠው ቃል ላይ ፈረመ

ፈርሜበታለሁ

አደለም እሱ ፈረመ ወይ

ሀ/ግ/ነ

ፈርሚአል በወቅቱ ተነቦለት እኛ ሰምተን አዳምጩ ፈርሚአል በወቅቱ

እርሶም ፈረሙ ታዲያ

በጀርባው የእሱን ቃል መስጠቱን መስማቴን ፈርሜአለሁ

እርሶም ፈርመዋል

አዎ

እሺ ይበቃል

አበቃችሁ እሺ ድጋሚ ጥያቄ አለ ድጋሚ ጥያቄ የለም የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄም አይኖርም እሺ እናመሰግናታለን ከኋላ ይቀመጡ ማን ይጠራ

የማሳስበው ጠዋት የቀረቡ ምስክሮች የቀረቡ በጣም በርካታ ናቸው ቅደም ተከተል አስይዘናል እና ፖሊስ ኮሚሽን ይጠራልንና ይዘው እንዲያቀርቡ አስረው እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ የተሰጠ ስለነበረ ምስክሮቹም እንደዚሁ ለቀዋቸውም ከሆነ ወይም ካሉ ደግሞ ይምጡልንና ይጠየቁልን

እስቲ ፖሊስ ኮሚሽኖችን ጥሩ ምስክሮቹ የሉም እንዴ እዚህ አካባቢ እስቲ ጥሯቸው

ግዛው ባሩድ

እሺ ቀጣይ ምስክር ቀርቧል መሀላ አስፈጽሙት

በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ::

ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ግዛው ባሩዳ

ሥራ - የግል ስራ

አድራሻ- አለማያ 01 ቀበሌ የቤት ቁጥር አዲስ

ለምስክርነት ነው የመጣከው

አዎ

4/92

በማን ጉዳይ

በአብዱለሚድ

እሺ አለ እዚህ ውስጥ አብዱልሃሚድ መሀመድ እሺ ና ተመለስ ጥሩ ከምስክርነቱ በፊት የጎላው ሁለት ወንበር አጠጋጓቸው ከዚህ ከፊት ያሉት ሶስት ሶስት ሰው ከጎላ ይቀመጥ ፊት ያሉት ብቻ የልጁ እናት እዛ በሩ ላይ አድርጓት ሌላ ወንበር ስጧት እሺ ጥያቄ ቀጥል ዐ/ህግ 23ኛ ተከሳሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ምስክሩ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

አቶ ግዛው የመጣሁት ለምስክርነት ነው ተከሳሽንም ለይተሃል ስለሱ የምታውቀውን ለፍ/ቤቱ ቢያስረዱልን።

ያው ወንድሜ ---------- ረስቶ ከመውጣቱ በፊት እንደማንኛውም የኦነግ አባል ነበር ከዛ በኋላ ግን ታድሶ ይግባ አይግባ የማውቀው ነገር የለም ኦነግ ከተበተነ በኋላ ከዛም ያው በአለማያ ይኖር ነበር እና ያው ብዙ ጓደኞችም የለውም ከሰውም አይቀላቀልም ያው ብቻውን ነው ሲሄድ ብዙ ጊዜ የማየው እና ይሄንን ነው ስለ እሱ የማውቀው

በፊት ምን ነበር

ድምጽህን ከፍ አድርግ

ኦነግ ቻርተሩን ረግጦ ከመውጣቱ በፊት የኦነግ አባል ነበር

መቼ በስንት ዓመተ ምህረት

---------- ሰዓቱ ግን እርግጠኛ አይደለሁም ቀን እና ሰዓቱን

ስንት አመት ይሆነዋል

ያው አሁን ካለው መንግስት ጋር --------- ድርጅት ጋር አብሮ በነበረ ሰዓት ማለት ከዛ በኋላ ያው ባለመስማማት ለህገ መንግስቱ አልገዛም ብሎ ረግጦ ወጣ በዛን ሰዓት

የት ነበር ይሄ አሁን የምትለው ነገር የተፈጸመው ኦነግ የነበረው የት አካባቢ ነበር

493

እሱ

አዎ

አለማያ ነበር

ምንድን ነበር እስቲ ያደረገው ነገር ካለ ለፍ/ቤቱ አስረዳ

እኔ ምንም ያደረገውን ነገር አላውቅም

አነግ መሆኑን እንዴት አወቅህ

አባል ነበር የዛን ጊዜ ነበር አለማያም መጥቶ ነበር የአነግ ድርጅት አባል ነው

ከዛ በኋላስ

ከዛ በኋላ ያው መጥቶ አለማያ እየኖረ ነው አለማያ ነበር ከዛ በኋላ እንግዲህ ድርጅቱ ከፈረሰ በኋላ ማለት ነው አለማያ ነበር

አለማያ ምን ይሰራ ነበር

ምንም ስራ የለውም በፊት እንትን ነበር መኪና አለው ሹፌር ነበር በኋላም መኪናውን እንግዲህ የት እንዳደረገ አላውቅም እንዲሁ ነበር የሚኖረው ስራውን ምን እንደሚሰራ አላውቅም

አመተ ምህረቱን ማስታወስ አልቻልክም

እስቲ በእሱ ላይ የአነግ አባል በነበረ ሰዓት በምታውቅ ጊዜ ማለት ነው ምን ምን ያደረገው ነገር አለ

ምንም ያደረገውን እኔ አላውቅም

ስለ ሁኔታው ስለ እሱ እንቅስቃሴ ከዚህ በፊት የምስክርነት ቃል ሰጥተሃል አደለም

አዎ

ስለተፈጠረው ነገር አስታውስና ምን ምን ሲያደርግ የነበረ መሆኑንና ምንድን ነው የምታውቀው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፫ ፬ ፫ ፫ ፫

እኔ የእነሱ አባል ሆኖ ከእነሱ ጋር እንደሚንቀሳቀስ እዛ ነበሩ ካምፕ ነበራቸው እኛ ጋ

መቼ

በዛን ሰዓት ማለት ነው

መቼ ነው የዛን ሰዓት ማለት

ያው 1983 ኢሃዲግ ከገባ ጀምሮ ማለት ነው

ኢሃዲግ ከገባ ጀምሮ

አዎ

እስከ መቼ ድረስ ነበር አባል ሆኖ ሲንቀሳቀስ የምታውቀው

ኦነግ ቻርተሩን ረግጦ እስከወጣበት ሰዓት ድረስ ነው

መቼ ነው ቻርተር ረግጦ የወጣው

እንግዲህ ሰዓቱ ረጅም ነው ዘንግቼዋለሁ እኔ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሰዓቱን

-------- የምስክርነት ቃል ስትሰጥ ምን ነበርክ

እኔ

አዎ

የ01 ቀበሌ ፀጥታ ዘርፍ ሃላፊ ነበርኩ

እሺ አሁን ምንድን ነው የምትሰራው

አሁን ደግሞ የምሰራው የግል ስራ ነው የምሰራው

መቼ ነው የተውከው ይሄንን ወደ ግል ስራ የዞርከው ከቀበሌ ፀጥታና ዘርፍ ፍትህ

አሁን በዚህ አመት

በዚህ አመት

ሀሳፕ

አዎ

እሺ ታዲያ አንተ በወቅቱ የቀበሌ ፀጥታ ዘርፍ ከነበርክ በጉዳዩ ላይ የተሻለ ቅርበት አለህ ማለት ነው ይሄ ከሆነ ታዲያ በዛን ሰዓት ከ1983 ጀምሮ ብለከናል እሱ እንቅስቃሴ የነበረበት አነግ ረግጦ እስከወጣበት ቀኑን እስካልገለጽከው ጊዜ ምን ሲያደርግና በአባልነት ምን ሲያደርግና ምን ሲፈጥር የነበረ መሆኑን የሰማከው ያኔ በወቅቱ

በወቅቱ ያኔ አባል ኖሮ ከእነሱ ጋር እንደሚሰራ ብቻ ነው የማውቀው እንጂ ምንም የሰራውን ስራ እኔ አላየሁም

ምንድን ነው የሚሰራው አባል ሆኖ የሚሰራው ስራ ምንድን ነው

ማለትም እኔ በቅርብ ከእነሱ ጋር ስላልነበርኩኝ ይሄን ይሰራል ብዬ መናገር ይከብደኛል

የሰማከውስ ነገር አለ በእሱ ላይ

ምንም አልሰማሁም እኔ

አነግ ምንድን ነው አላማው ምንድን ነው የሚሰራው እሺ በጥቅሉ

በወቅቱ እንግዲህ የኦሮሞን ህዝብ

ተቃውሞ ካላችሁ ተቃውሞ አለን በሉ ቆይ ቆይ አንዴ ተቃውሞ ተነስቷል ተቃውሞው ይመዝገብ

ዐ/ህግ ካቀረቡት ክስ ጭብጥ እየወጡ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩን መጠየቅ የያዙት እሳቸው በግልጽ አመተ ምህረቱን ጠቅሰው ክስ አቅርበዋል ምስክሩ እየመሰከረ ያለው አነግ ቻርተር ከመርገጡ በፊት ነው የማውቀው ብሎ በግልፅ ተናግሯል ከዚህ ውጪ ያለውን ነገር እንደማያውቁ ነው ምስክሩ እየተናገሩ ያሉት እና እያስገደዱ ምስክሩን መምራቱ አግባብ አይደለም ብለን ነው የምንቃወመው::

እሺ በእናንተ በኩል

አንደኛ መቼ አነግ ረግጦ ወጣ ብዬ በምጠይቀው ሰዓት አያውቀውም ጊዜውን ከአነግ ጋር መንቀሳቀስ የጀመረበትን ጊዜ ብቻ ነው እየገለጸ ያለው ሁለተኛ ከአነግ ጋር ሲንቀሳቀስና ሲሰራ

ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

61796

አውቃለሁ ነው ያለው አነግ ምንድን ነው የሚሰራው ብዬ ነው የጠየኩት ስለዚህ ቆየ ባለው ጊዜአት ውስጥ ከ1983 ጀምሮ በእሱ አቆጣጠር ማለት ነው አነግ ረግጦ እስከወጣበት ድረስ እንደ አነግ ሲንቀሳቀስ አውቃለሁ ብሏል በዛን ጊዜ ምን እያደረገ ምን ሲሰራ እና ምን ሲንቀሳቀስ እንደነበረ ነው የጠየኩት ምንም የሚመራው ነገር የለም እንደገና ደግሞ እስከ አሁን ቅርብ አንድ አመት ድረስ የቀበሌው የፍትህና ፀጥታ ዘርፍ ሃላፊ እንደነበረ ነግሮኛል በዚህ አመት ነው አንድ አመት ሆኖኛል ወደ ግል ስራ ከገባሁ ብሎኛል ስለዚህ በእነዚህ ወቅቶች የምታውቀው ነገር ምን አለ እያልኩ እየጠየኩት ነው ምንም የመራሁት ነገር የለም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ምስክሩ የሚያውቀውን በ137 መሰረት እንዲያስረዳ እየጠየኩ ነው አነግ ምንድን ነው እያልኩ ነው።

መልስ መስጫ አያስፈልገውም ሰማን እኮ ተቃውሚችሁን ሰማን የእነሱን መልስ ሰማን ከዛ የፍ/ቤቱ ስራ ነው የሚቀረው ይበቃል። እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሯል ሌላ ጥያቄ ካላችሁ ቀጥሉ

እሺ አቶ ግዛው አነግ ቻርተሩን ረግጦ ከወጣ በኋላ ከዛ በኋላ ያለውን እንቅስቃሴ ያውቃሉ

አይ አላውቅም አነግ ከእንግዲህ ከተበተነ በኋላ ያለው ያው ዝም ብሎ መንግስትን የመበጥበጥና የዱሩዬ ስራ ነው የሚሰራው

ወደዚህ ድምጽ እሺ ቀጥል

እንግዲህ የአነግ አላማ ሁላችንም እንደምናውቀው ህዝብን መበጥበጥና አልባሌ ነገሮችን መስራት የልማት እንቅፋት መሆን ነው እስቲል እስከ አሁን ድረስ የዱሩዬ ስራ ነው የሽፍታ ስራ እየሰራ ያለው በስም ለኦሮሞ ህዝብ ቆምኩ ነው የሚለው እና ያው ይሄንን ነው እንግዲህ የማውቀው

የእኔን ጥያቄ የመለስክልኝ አልመሰለኝም የእኔን ጥያቄ ተረድተከኝ ከሆነ አነግ ቻርተሩን ከወጣ በኋላ አብዱልሃሚድን አንተ የፍትህና የፀጥታ ዘርፍ ሆነህ እስከሰራህበት ጊዜ ድረስ ምን አይነት እንቅስቃሴ ነበር ሲያደርግ የነበረው

እንግዲህ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ሲያደርግ እኔ በተጨባጭ ያየሁት ነገር የለም ከህብረተሰብ ጋር አይቀላቀልም ያው ከሰዎች ጋ እንዲህ ቆይና የለውም ሲወጣና ሲገባ ያው ነው የማውቀው ስራ የለውም ይሄንኑ ብቻ ነው ስለሱ የማውቀው ይሄንን ይሰራል ብዬ ሲሰራ ያየሁት ነገር የለም።

የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ሃሳገ

የተከበረው ፍ/ቤት የምናሳስበው ምንድን ነው አሁንም መልሰው አነግ ቻርተሩን ረግጦ ከመውጣቱ በፊት ያለውን ብቻ ነው ምስክሩ

ጥያቄ ጠይቁ

አይ ለፍ/ቤቱ የምናሳስበው ነው ከዛ በኋላ ያለውን ለፖሊስ ቃሉን ሰጥቷል ፍ/ቤት እንዲያይልን ምን ምን እንደነበረ ስለዚህ ፍ/ቤቱ ይይልንና አስጠቂ ምስክር ስለሆነ መሪ ጥያቄ እንድንጠይቅ ይፈቀድልን ነው

እስቲ እንመልከተው ለፖሊስ ሰጥተሃል ቃልህን

አዎ

መቼ ነው የሰጠከው ታስታውሳለህ

በ2001

በ2001

አዎ

ስለ መቼ ጊዜ ነው የተናገርከው ያኔ በ2001 ቃልህን ስትሰጥ

ያኔ ቃሌን ስሰጥ

በ2001 ቃል ሰጠህ አደል

አዎ

ስለምን ጉድ በመቼ ጊዜ ስለተፈፀመ ነገር ነው የተናገርከው

በቃ ያው ያንኑ ጊዜ ያለውን ነው እኔ ስለሱ

የመቼ ጊዜ

አዎ ስለ እሱ ምን ታውቃለህ ብለው ነው የጠየቁኝ ስለእሱ ምን ታውቃለህ ሲሉኝ ያው ይሄንኑ አሁን የተናገርኩት ነው የተናገርኩት

ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፍ/ቤት ቁጥር 4

የምትሉት ነገር አለ ተመሳሳይ ነው የቅድሙ አይነት ክርክር እየመራን እንጠይቅ ነው አስጠቂ ምስክር ነው ለማለት ነው

የተከበረው ፍ/ቤት አሁንም ፍ/ቤቱ እኮ ባደረገው ማጣሪያ ተከሳሹ እዛም ላይ የሰጠሁት ቃል ------ ምስክሩ ይሄንኑ አሁን ያልኩትን ነው ብሏል ሌላው ደግሞ መቼ ነው ለሚለው ጊዜ ይሄ ፖሊሲንግ ጉዳይ እኮ ነው አመተ ምህረቱን በትክክል በሰውየው ባያስታውስና እዛ ላይ የሰጠው ቃል የተናገርኩት ይሄንን ነው ካለ ሌላ ሊገደድ የሚገባበት ምክንያት የለውም ምስክሩ ዐ/ህግ ባይሆን በስነ-ስርዓቱ ማድረግ የሚገባውን እንጂ ማድረግ የሚችለው ምስክሩን ከሚናገረው ወይም ከተናገረው ንግግር ውጪ እንዲመሰክር ማስገደድ የራሱን ምስክር

ፈርመሀል

እኔ አልፈረምኩም

ቆይ እሺ ፍ/ቤቱ ያው በተመሳሳይ ቀደም ሲል የሰጠው ትእዛዝ ስላለ በዛው መሰረት የምስክሩ ዐ/ሕግ የተሰጠውን ቃል መሰረት አድርገው እየመሩ እንዲጠይቁ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል በዚህ መሰረት ጥያቄ ይቀርባል መልስ ትሰጣለህ ይቀጥሉ

አቶ ግዛው ተከሣሹ ኦነግ ቻርተሩን እረግጦ ከወጣ በኋላ ወደ ትግል ገብቷል አልገባም

እኔ አላውቅም አላየሁትም

እግሩስ በጥይት አልተመታም

ትንሽ ድምፅ

እግሩን በጥይት አልተመታም

እግሩን እንግዲህ በጥይት ይመታ በምን ይመታ አላውቅም ያው ትንሽ ያነክሳል

ያነክሳል

አዎ በጥይት ይመታ በተፈጥሮ አደጋ ይሁን እንግዲህ በእግዚያብሔር በሽታ ይሁን እኔ አላውቅም አላየሁትም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

ሀ፻፯

ይሄንን በተመለከተ ተከሣሹ ከዚህ በፊት ቻርተሩ ከተበተነ በኋላ ወደ ትግል ገብቶ እግሩ መመታቱን ለፖሊስ ሰጥተካል አልሰጠክም ቃልህን ገልፀህ

ይሄንኑ ነው እኔ ያልኩት

ገልፀህ ሰተካል አልሰጠክም

ማለትም ስለዚህ ጉዳይ ስጠየቅ የተናገርኩት

አይደለም

ይሄንኑ ነው ከቻርተሩ በኋላ እዛ መጥቶ ነው ያለው እንግዲህ ታድሶ ወስዷል ወይ ይውሰድ አይውሰድ እኔ አላውቅም እና ያው

ማንበብ ትችላለህ

እ

ማንበብ እና መፃፍ ትችላለህ

እችላለሁ

ከዚህ በፊት ለፖሊስ የምስክርነትህን ቃል ሰጥተካል አይደለ እንዴ

አዎ

እዛ ላይ ተከሣሹ ቻርተሩን እረግጦ -- ከወጣ በኋላ ወደ ትግል ገብቶ እግሩ በትግል ላይ እያለ እግሩ ተመቷል ብለህ ሰጥተካል አልሰጠክም ቃልህን

እግሩን ተመቷል ካልኩማ እኔም በትግሉ ውስጥ እዛ ከእሱ ጐን ተሰልፌያለሁ ማለት እኮ ነው አይቻለሁ ሲመታ ማለት ነው

አይደለም ይሄንን መልስልኝ በለህል አላልክም

እኔ አላልኩም

አላልክም

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፩ ሀሩሪ የፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

300

እኔ በምን እንደተመታ አላውቅም በተፈጥሮ አደጋ ወይ በጥይትም ይሁን አላውቅም ግን እንደሚያነክስ አውቃለሁ

እሺ ጥያቄ ጨርሰናል

እሺ ጥያቄ በቅታል አላችሁ እሺ

ግዛው

አቤት

አንተ የፍትህ እና ፀጥታ ዘርፍ ሆነህ እየሰራህ ባለህበት ጊዜ

እሺ

ወደ ማህበረሰቡ ከተቀላቀለ በኋላ ማለት ነው ከተቀላቀለም በኋላ ይሄ የአሁኑ ተከሣሽ አነግ የአነግ የትጥቅ ትግል እና የአነግ ፖሊስ ትክክለኛ ነው እያለ በሐረማያ አካባቢ ለሚኖረው ማህበረሰብ ሲቀሰቅስ የነበረ መሆኑን በምስክርነት ቃል ላይ ከዚህ በፊት ተጠይቀህ ለፖሊስ ጣቢያ ሰጥተካል ወይንስ አልሰጠክም

አልሰጠሁም

ምንም አልሰጠክም

እኔ አልሰጠሁም

እሺ በቃ ጨርሰናል

አበቃችሁ

መስቀለኛ ጥያቄ አላችሁ መስቀለኛ ጥያቄ የለም ድጋሜ ጥያቄም የለም የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄም የለም እናመሰግናለን ከኋላ ቁሜ በል ቀጣይ ማን ይጠራላችሁ

26ኛው ምስክር መጥቶ ከሆነ ይረጋገጥልን አብዲ አህመድ መጥቶ ከሆነ

እ

አብዲ አህመድ

301

ይሄ ቅድም 26ኛው ነው አይደለ

አይደለም

እሺ አብዲ አህመድ 13ኛው

አዎ

እሺ ቀጣይ የዐ/ሕግ ምስክር ቀረቡ መሀላ አስፈፅሙት መሀላ ፈፅሚል ቅድም እሺ አብዲ ሙመድ የአያት ስም ማነው በለው

ቀጣይ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - አብዲ ሙመድ አብዱላሂ

ስራ - ገበሬ

ቀበሌ - ሐረማያ 01

ጥሩ ለምስክርነት ነው የመጣከው በማን ጉዳይ

መሀመድ ኡመሬ እና አሊይ አብዱሌ

አሳየን 2ቱንም ና ምስክሩ ወደ እዚህ ይምጣ እስቲ ጠይቅ አስተርጓሚ

አልይ አብዱሌ ነው

ስንተኛ ተራ ነው ዐ/ሕግ

49ኛ እና 47ኛ

49ኛ እና 47ኛ

47ኛ

47ኛ

አዎ

የኦሮሚያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ...

502

ጥሩ አሁን ካሳየካቸው ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ መሀመድ

የለኝም

እሺ ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለሀል ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

ምንድነው ስለ እነሱ የምታውቀውን ነገር ለፍ/ቤት አስረዳ እስቲ ለምስክርነት የመጣህበትን

በ1998 ዘር እየዘራን ነበር 2 ሰዎች የአልዬ አብዱሌ እርሻ ውስጥ አየሁት 9 ሰአት ሲሆን ወደ ከተማ ሄዱ 2ኛ ቀን ሳያቸው አሁንም እዛ ውስጥ አየሁት ከእዛ በኋላ ካየሁ በኋላ እሺ ከ1 ሳምንት በኋላ ካየሁ በኋላ ከጠረጠርኩ በኋላ የአልይ አብዲሌ እርሻን የሚጠብቅ ሰው ልጅ እነዚህ ሰዎች ምንድናቸው ብዬ ጠየኩት የኦነግ ካድሬዎች ናቸው ብሎ ነገረኝ እኔ ከእዛ መጥቼ መሀመድ ኡመሬ የቀበሌው አስተዳደር ነበረ እንደዚህ አይነት ተብያለሁ እና ሂድ እና እነዚህን ሰዎች አጣራ ብዬ ነገርኩት እስከ እዚህ ነው የማውቀው

ከእዛ በኋላ ምን አደረገ እሱ በለው

ከእዛ በኋላ እነዚህ ሰዎች ከእዛ አካባቢ ጠፉ

እሱ በወቅቱ ምን አደረገ እንደዛ ብለህ ስትነግረው ምን አደረገ እሱ

ምን እርምጃ እንደወሰደ -----

አልይንስ በለው

አልይን እሱ ከእነሱ ጋር

ስለ እሱ ምንድነው የምታውቀው

እሱ እርሻ ውስጥ ማየቴ ነው እንጂ እሱን አጠገብ አላየሁም

እሱ የት ነበር ያን ጊዜ

አሊይ ብዙ እርሻ ነው ያላቸው እና ----

ይዟቸው የት ነው ሄዱት በለው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

503

ከእኔ እርሻ ጋር ዳር ለዳር ነበርን

የት ነው ቦታው ቦታው

ሐረማያ አካባቢ ነው ገንደ ቦዬ የምትባል አካባቢ ገንደሙደ የሚባል

በዛን ጊዜ የየካቸው ሰዎች የአነግ ካድሬ መሆናቸውን ማን ነው የነገረህ በለው

አሊይ ጋር የሚቀመጥ ልጅ ነው የነገረኝ

ምን የተለየ ነገር አይተህ ነው ልትጠይቅ የቻልከው እነዚህ ሰዎች ምንድናቸው ብለህ ለመጠየቅ ምን አለ

እነዚህ ሰዎች ስራ አይሰሩም

እሺ

እዛ ይውላሉ ልክ 9 ሰአት ሲሆን ወደ ከተማ ይሄዳሉ 2ተኛ ቀንም ሳየው እንደዛ ሲሆኑ ተጠራጥሬ ነው

ምን እያደረጉ ነበር

እስከ 9 ሰአት እዛው ውስጥ ነው ዞር ዞር ብለው ነው የሚውሉት እንጂ ምንም የሚሰሩ ነገር የለም

ምን ያህል ሆነው ነው

ወደ አንድ ሳምንት --

አይ ምን ያህል ሆነው ነው የሰዎቹ ብዛት ምን ያህል ነው

2 ሰዎች ናቸው

2ቱ ብቻ የተለየ ነገር ያደረጉት ነገር አለ ወይ ወይም የያዙት ነገር አለ ወይ ምን ይዘዋል

አይ የተለየ -- ነገር አላየሁም

504

እሺ ልጁ የጠየከው ሰው እነዚህ የኦነግ ካድሬዎች ናቸው በሎ ሲልህ አንተ የተረዳከው ነገር አለ ወይ

በዛን ሰአት የተማሪዎችም ብጥብጥ ስለነበረ እኔም ለእራሴ ጥርጣሬ ውስጥ ገባሁ ከእዛን አንፃር ተነስቼ ነው

ጨርሰናል

አበቃችሁ መስቀለኛ ጥያቄ ይኖራል

ለተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

አቶ አብዲ አንተ ሰዎቹ ዝም ብለው 2 ሰዎች አየሁ አንድ ልጅ ጠየኩ ትላለህ የጠየከው ልጅ ሰንት አመት እድሜ ይሆናል

በግምት 8 አመት ይሆናል

8 አመት ይሆነዋል ይበቃናል --

እሺ አበቃችሁ ጥሩ ድጋሜ ጥያቄ አለ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

ተምረሀል እንዴ

ትቃወማላችሁ

አዎ

እሺ አስመዝግቡ መቃወሚያውን

እኛ ባነሳነው ጥያቄ ላይ ነው

ድጋሜ ጥያቄ የሚጠየቀው በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ በተነሳ ጉዳይ ነው እኛ በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ያነሳነው የጠየከው ልጅ እድሜው ሰንት አመት ነው ያን እድሜው በሚመለከት ይጠይቁ ስለሌላ ጥያቄ የታለፈ ጥያቄ ነው ሊጠይቁ አይገባም ህጉም ስርአቱም አይፈቅድም

505

ዐ/ሕግ የምትሉት አለ አንስታችሁታል ጥሩ ጥያቄው ተነስቷል ተብሏል ስለዚህ ጥያቄ የለም ማለት ነው ድጋሜ ጥያቄ የለም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ተምረሀል ወይ በለው እስቲ ትምህርት ተምረሀል እስከ ስንት ተምረሀል

እስከ 10 ተምሬያለሁ

እስከ 10

አዎ

ጊዜ መቁጠር ስለ ቀን ስለ አመተ ምህረት ስለሁሉም ታውቃለህ በደንብ

እነዚህ አሁን ይጠፋብኛል ለይቼ በደንብ አላውቀውም

እሺ እናመሰግንሀለን ቆይ አንዴ አንዴ ቆይ አንተ እርሻ ውስጥ ያየከው ማንን ነው በለው እስቲ

ያንን ልጁን እና እነዛን ሰዎች ናቸው

ማን ናቸው እነሱ

ይሄ ልጁ የአነግ ካድሬ ናቸው ብሎ የነገረኝ ሰዎች ናቸው እና እሱ እና ልጁ

አሁን የለየካቸው እዚህ ማለት ነው

ይሄ አልይ አብዱለሂ የሚባለው የእርሻው ባለቤት ነው ይሄ መሀመድ ኡመሬ የሚባለውም ደግሞ ቀበሌ ሊቀመንበር የነበረው ነው ለእሱ የነገርኩት ነው

እዛው ነው ያያቸው

አዎ

አልይ አብዱሌ እርሻው ውስጥ አይተሀቸዋል እንዲ መሀመድ ኡመሬስ

መሀመድ ኡመሬ ማለት ሊቀመንበር ነው ቤቱ ሄጀ ነው የነገርኩት እንደዚህ አይነት ሰዎች አለ ብዬ

506

ጥሩ አልይ አብዱሌ ከሰዎቹ ጋር ነበር እንዴ ይሄ አሁን ልጁ ያሳየህ ልጆች ጋር

አብሮ አልነበረም

ግን እሱ እርሻ ውስጥ አይተካቸዋል

አዎ በእርሱ እርሻ ውስጥ አይቻለሁ

እሺ እናመሰግንሀለን ከኋላ ቁጭ በል እሺ ምስክርነቱ በዚሁ እናቆመዋለን ዐ/ሕግ አበቃችሁ ምስክሮች ዛሬ የመጡትን

እሺ ዛሬ የመጡት ይበቁናል ነገር ግን ለፍ/ቤቱ ማሳሰብ የምንፈልገው አለ

ጥሩ ዛሬ የመጡት አልቀዋል

ዛሬ የመጡት አላለቁም

ስንት ናቸው የመጡት ዛሬ ጠቅላላ

አጠቃላይ የመጡት 19 ምስክሮች ነበሩ

ስንት ተሰሙ

ከጠኋት ላይ 5 ሰምተናል አሁን ከሰአት በኋላ ስንት እንደሆነ በትክክል መቁጠር አልቻልኩኝም ማስታወስ አልቻልኩም ነገር ግን ምስክሮች በርካታ መጥተው ከመጡት ምስክሮች ውስጥ አሁን የሉም እየተባልን ነው ያለነው ምስክሮቹን ፖሊስ አስሮ እንዲያቀርብ ነበር ትእዛዝ የተሰጠው አሁንም ቢሆን የተረፉት ምስክሮች ደግሞ በዚሁ ሄደው ይቀራሉ የሚል ስጋት አለ

ፖሊስ ኮምሽን የታሉ

ስለሆነም አሁን የተሰሙት እናያቀርባቸዋለን ይታዩልን እና አሁን ያሉት በትክክል ተቆጥረው እንትን እንዲሉ ለነገ ጠኋት አቆይተው እንዲያቀርቧቸው ትእዛዝ ይሰጥልን

ቀሪ ምስክሮቹን ጥሯቸው

የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

507

ከዚህ በተጨማሪ ፖሊስ ኮምሽን እራሱ ጠኋት መጥቶ ያቀረባቸውን ምስክሮች ቆጥሮ 19 ምስክሮች በአጠቃላይ ማቅረቡን ተነግሮናል ስለዚህ የቀረቡት ምስክሮች እና ያልተሰሙት ተለይተው የተቀሩት እንዲመጡ ትእዛዝ እንዲሰጥልን ለነገ እንዲያቀርቧቸው ይደረግልን

መገርሳ የእርሶስ ዩሱፍ

አልይ

አልይ የአንቺ ስም ማነው በላት ፋጡማ አሁን ሰአት ትንሽ ሄዷል በላቸው ስለመጣችሁ እናመሰግናለን ጠኋት በጠኋት ኑ እንዳትቀሩ ሌላ ዛሬ መጥቶ የቀረ አለ ወይ እስቲ ፖሊስ ኮምሽንን ጥሯቸው ፖሊስ ኮምሽን ጥሩት እሱን ፖሊስ ኮምሽንን ጥራው ለምንድነው የሚሄደው አህመድ የእርሶስ አባባ አደም የእርሶስ ባሾ እሺ የእርሶስ ኡስማን ሌላ ያልተጠራ አለ እሺ ጥሩ ሌላ የቀረ አለ ምስክር ፖሊስ ኮምሽን

የለም

እሺ ዐ/ሕግ ማሳሰቢያ ለፍ/ቤት አቅርበዋል ምስክሮች አቅርባቹሀል ግን ባልታወቀ ምክንያት ወደ እዚህ እንዲመጡ አልተደረገም የሚል ነገር አለ እና በአቀራረብ ምንድነው እዚህ ከመጡ በኋላ ለምንድነው ምስክሮቹን ከዚህ የምታርቋቸው

ምንም ነገር የራቁ የሉም -- ጠኋት የሚሰሩት ናቸው የሄዱት እና

የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም 26ኛ እና 23ኛ ጠኋት መጥተው ያየናቸው ምስክሮች

ለምንድነው እጅ ያወጣከው ኧ

50

የመ/ቁ. - 04486

ቀን - ጥር 20/2002 ዓ/ም

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰዒድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ ተሰይመናል

ከሳሽ - ዐ/ህግ እያሱ መኮንን እና አረጋይ እንደሻው ቀርበዋል

ተከሳሽ - እነ አብዱረህማን ባሌ 69 ተከሳሾች ከማረሚያ ቤት ቀርበዋል

ሁለቱ በዋስ ያሉት ቀርበዋል አንድ ተከሳሽ ክሱ ተቋርጧል ሌላ በሞት ምክንያት ማረጋገጫ እየተጠበቀበት ያለ መዝገብ ነው በትላንት የችሎት ውሎ 11 የዐ/ህግ ምስክሮች ተሰምተዋል ሌሎች 8 የዐ/ህግ ምስክሮች እንደዚሁ በችሎት መቅረባቸው ተረጋግጦ በዚህ ቀን እንዲቀርቡ በችሎት ተነግሯቸው ስለነበር ቀሪ ምስክሮችና ሌላ ምስክር ካለ መስማት ነው ችሎት ዛሬ የሚቀጥለው ስለዚህ ያልተሰሙ ምስክሮችን መስማት ችሎቱ ይቀጥላል በሌላ በኩል በተከሳሾች በጠበቃ በኩል የቀረበው ማን ነው አስመዝግቡ

አድማሱ መለሰ ኢብራሂም መሀመድ ለ23ኛ፣ 37ኛ፣ 38ኛ

ጠበቆች ቀርበዋል ማን ይጠራላቸሁ ዐ/ህግ

15ኛ ምስክር አሊዩ አብዱላሂ

በአላህ ስም እውነት ለመናገር እምላለሁ።

15ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አሊዩ አብዱላሂ

ሥራ - የመንግስት ሰራተኛ

አድራሻ- አለማያ ከተማ

የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ቢሮ ቁጥር 2

309

ዛሬ ለምንድን ነው የመጣከው

ለምስክርነት ነው የመጣሁት

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ባለፈው የተደረገው ላይ እዚህ ያሉ ሰዎች አሉ

እሺ ተነሳና ታሳየናለህ የምታውቃቸውን አስተናባሪዎች

ከሴቶቹም አይተሃል ከሴቶቹ

የዛን ጊዜ ኦፕሬሽን በተደረገበት ሰዓት እሷም ነበረች

ማንኛዋ

ታውቃታለህ አታውቃትም ብቻ በለው

አውቃታለሁ

እሺ በቃ ይበቃል አሁን ካሳየካቸው ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ

ዝምድና ያለኝ አለ

ከማን ጋር ነው ዝምድና ያለህ

ዝምድና ያሉኝ ሰዎች አሉ ግን ፀብ የለኝም

ከእነዚህ አሁን ካሳየካቸው ጋር ዝምድና አለህ

አዎ አለኝ

ከእሷ ጋር ዝምድና አለህ አሁን ከዘሀራ ጋር

ጎረቤት ናት እሷ

ዝምድና አለህ ወይ ነው የተባልከው

ዝምድና የለኝም

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፡ ፡ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

6/10

ከሌሎቹስ ጋር

ከመሀመድና ከአሊዩ ጋር ነው ዝምድና ያለኝ

ምንድን ነው ዝምድናህ ከመሀመድ እና ከአሊዩ ጋር

የአጎትማማች ልጆች ነን

አሊዩስ ያልከው

የአክስቴ ልጅ ነው

እሺ ሌሎቹስ ከሌሎቹ ጋር ዝምድና የለህም

አለኝ

እኮ ንገረና

ይሄኛውም የአክስቴ ልጅ ነው

የትኛው

ጀማል

እሺ ሌላ

ጃፈርም እንደዛው ነው

እሺ ምንድን ነው ከእሱ ጋር ዝምድናህ

ያው የአክስት ልጅ ነው

እሺ ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እሺ አቶ አሊዩ ዛሬ የመጣከው ለምንድን ነው እሺ ለምስክርነት ነው ብለሃል እስቲ ምንድን ነው የምታስረዳው በነዚህ በሰዎችህ ተከሳሾች ላይ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቀጠሮ ክፍል

511

የማውቀው በዛን ሰዓት ኦፕሬሽን በተደረገበት ሰዓት እኔ በዛን ሰዓት የፀጥታ ዘርፍ የኦፂድ አባል ነኝ ኦፕሬሽን በተደረገበት ሰዓት ተጠራን ግምገማ የየራሳችን ጀምረን ነው የተደረገው ሁሉም ህዝብ በነበረበት ሰዓት በዛን ሰዓት የየራሱን ሁሉም ሰው የየራሱን ችግር አስቀመጠ መሀመድ አባድር የተባለው እኛ ሰፈር ይቀመጥ ነበር አሊዩ ጋር ይኖር ነበር ይሄ አሊዩ ጋር ሆኖ ይሰራ ነበር እሱ ጋር ይሰራ ነበር

ማን

ከዛ በኋላ እሱን ትቶ ሄደ ሀይስኩል ሄዶ ተምሮ መጣ እየተማረ ሀይስኩል ደረሰ ከዛ በኋላ ረብሻ በሚነሳበት ሰዓት ነገሮች አጠናከረ እሱ ነገሩ ተጠናክሮ ሲታወቅ ግምገማ ሲታወቅ አጠገብ አጠገባችን ስለነበረ ሀይስኩል ስለነበረ ሁሉም የየራሱን ችግር አስቀመጠ አሊዩም የራሱን አስቀመጠ ይሄ ልጅ አንተ ጋር ነበር እንዴት ኦነግ አንተ ጋር አስቀመጥክ ብሎ ተጠየቀ አሁን በዛን ጊዜ እኔ ጋር ይቀመጥ ነበር ከእኔ ጋር ትቶ ሄዷል ከተማረ በኋላ ነው አሁን ተመልሶ የመጣው አንድ ቀን ሁለት ሰው ይዞ መጣ እኔ ጋር ከእኔ ጋ ከመጡ በኋላ እኔን አነጋግሮኝ ከሄዱ በኋላ ኦነግ መሆናቸውን አወኩት እነዛ ሰዎች ኦነጎች ናቸው እነዚህ አነጋግረውኝ ሄዱ አለ አገርስ እንዴት አደረግህ ተብሎ ሲጠየቅ ስለ አገር አላውቅም ስለራሴ ግን ይሄንን ነው የማውቀው ብሎ ተናገረ በዛን ግምገማ ወቅት ይሄንን መልስ ሰጠ እሱ መሀመድ ኡመሬ የፀጥታ ሃላፊ ነበር ማታ ፀጥታ እየሄድን እንቆጣጠር ነበር ሮንድ እየወጣን ማታ ማታ እንቆጣጠር ነበር ሁሉም ጊዜ እንከታተል ነበር በዛን ሰዓት አብዲ ሙመድ የሚባለው ትላንትና ለምስክርነት የመጣው ሁለት ሰዎች የአሊዩ ቆትቾ እርሻ እዛ ውስጥ ነበሩ አሊዩ እሱ ጋር አልነበረም የእርሻው ባለቤት አልነበረም ወደ ሀይስኩል ወደዚህ መጣ እነዚህን ሰዎች ተጠራጥሬ ሄጀ ለመሀመድ ነገርኩት አንተ ስትነግረኝ መሀመድ መሀመድ ሄጀ አጣሁ ብሎ መልሱን ሲመልስልኝ ይሄንንም ሰምቻለሁ በሌላ መንገድ ጀማልና ጃፈር እንደዚህ አይነት ሰዎች በእነዛ አይነት ሰዎች የተደራጁ ነበሩ ለመተጋገዝ የተደራጁ ነበር በእነዛ ውስጥ የመሀመድ አባድር በዛ አካባቢ ስለሚንቀሳቀስ መንግስት ይሄ አደረጃጀት መንግስት ተጠራጠረ ትክክለኛ ነው ትክክለኛ አይደለም በማለት ተጠራጠረ በዛ የተነሳ ትኩረት ተሰጠበት በዛ ምክንያት ሊያዙ ቻለ

አሁን የነገርከን ድርጊት መቼ ነው የተከሰተው

በ1998 አካባቢ

5/12

ወሩና ቀኑ ትዝ ይልሀል

አላስታውስም ወሩና ቀኑን አላስታውስም

የት ነው ቦታው

ሐረማያ

እሺ አሊዩ ቤት ተቀመጠ ያልከን መሀመድ አባድር ምንድን ነው መሀመድ አባድር

እሱ ጋር ተቀምጦ መሬት ይቆፍር ነበር ብር ይከፈለው ነበር በዛን ወቅት

ምንድን ነው ያደረገው ታዲያ ምን አጥፍቶ ነው

አሁን ይሄ ግምገማ ከተደረሰበት በኋላ

ምን ተደረሰበት

እነዚህን አነጎች ይዞ ሰፈር ውስጥ መንቀሳቀሱ ከተደረሰበት በኋላ

እሱስ ምንድን ነው

ከዛ በኋላ እሱም አነግ ሆነ

ማን ቤት ነበር እሱ ተቀምጦ የነበረው

አሊዩ ጋር እንደሚቀመጥ ነው የሚታወቀው

እሺ አሊዩ ጋር ነው የሚቀመጠው ብለከናል አሊዩ ቤተሰብ አለው እንዴ

አለው

ሚስት አለው

አዎ ሚስትም አለው

ማን ናት ሚስቱ

ዘሀራ ትባላለች

የፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ 4 ክፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

513

አሊዩ ሚስቱ ዘሀራ ናት ብለከናል እሱ ቤት መሀመድ ተቀምጧል እያልከን ነበር መሀመድ አባድር የተባለው ደግሞ ኦነግ ነው አልከን እኔ ያነጋገሩኝ ጊዜ ነበር ብለካል ማን ነው ያነጋገረህ አንተን ያነጋገረህ ሰው የለም ቅድም አነጋግረውኛል እኔን ያልከው የለም ያናገረህ ሰው የለም ምንም አንተን

በግምገማ ላይ ነው ያነጋገሩን

እነማን አነጋገሩህ

አሊዩ መሀመድ

ምን ብለው አነጋገሩህ

በዚህ በአባድር የተነሳ ኦነጎችን ይዞ በሚንቀሳቀስ አንተ ቤት የሚቀመጠው እንዴት ነው ተብሎ ኦነግ ነው ይሄ ሰውዬ አንተ ኦነግን አሸሸገህ እዚህ ታስቀምጣለህ በመባል

ማን ነው እንደዚህ በመባል ያነጋገረህ አንተን ማን ነው ስም ነው እኮ

ሙዘይድና ዳንኤል ይባላሉ ከላይ የመጡ ሰዎች

እሺ አሁን ከዚህ ካስነሳካቸው ሰዎች ውስጥ ማለት ነው አሊዩ የትኛው ነው እሺ አሊዩ እሱ ነው ባለቤቱ ደግሞ ዘሀራ እሷ ናት ብለከናል ሌሎቹስ ምን አድርገው ነው

ቆይ ቆይ አስተርጓሚ ምንድን ነው በግል ነገር አቁሙ ተብላችኋል

አስተርጓሚው የማስተርጎም ችግር እንዳለበት እየተረዳን ነው እና አንደኛ አስተርጓሚ ሲተረጎሙ በደንብ እያዳመጡ ይተርጉሙልን ሁለተኛ ሰውየው እነዚህን በዚህ በዚህ ነው የማውቃቸው እንዲህ እንዲህ ነው ብሎ አስረድቷል የሚያውቀውን ታሪክ አስረድቷል ስለዚህ አሁን እነገሌ ምንድን ናቸው እነሱ እኮ ይሄ ሰውዬ እኮ ግምገማ ላይ ሲናገሩ ሰማሁ ነው በቃ ሰውየው ይሄንን ምስክር እየመሰከረ ያለው ስብሰባ ተደርጎ በግምገማ ላይ ስላለ ነገር ነው እየመሰከረ ያለው ከዛ ውጪ ያለ ነገር ካለ መጠየቅ ነው ስለ ግምገማ ብቻ ነው የመሰከረው ምንድን ነው የምታውቀው እየተባለ ከመሰከረው ጭብጥ ውጭ ሊጠየቅ አይገባም

እሺ በእናንተ በኩል

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቋሚ ችሎት

5141

በእኛ በኩል አንደኛ ምስክሩ በግሉንም የሚያውቀውን ነገር እንዲነግረን ወደመጠየቁ እየሄድን ነው እንደገና ደግሞ የፍ/ቤቱ ነው እንጂ ምስክርነት ቃሉን የሚመዘግበው አስጠይቁ ልንባል አይገባም ሁለተኛ በእነሱስ ላይ ምን ታውቃለህ ብለን እየጠየቅን የማያውቀው ነገር ካለ አላውቅም በእነሱ ላይ ብሎ ሊመልስልን የሚገባው የቀረበው ምስክር እንጂ ተከላካይ ጠበቃ አይደሉም ስለዚህ እኛ እዚህ ላይ ግራ ተጋብተናል ምስክራችን የሚያውቀውን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያውቀውን እየጠየቅነው ነው መጠየቃችንን እንቀጥላለን::

በቀጥታ ትላንትና በተሰጠው ማሳሰቢያ መሰረት የግል ነገሮቻቸውን ቀጥታ የሚባለውን ሳትጨምር ሳትቀንስ መናገር መቻል አለብህ ሁሉም ሰው እዚህ ቋንቋ የሚሰማም ሰው ስላለ ወደሌላ ነገር እንዳይሄድ በእናንተ በኩል ግን የተነሳው ጥያቄ አግባብ ነው ጥያቄው መቀጠል አለበት ተቃውሞ ውድቅ ብለናል ጥያቄው ይቀጥል::

እሺ አመሰግናለሁ ግምገማው ያደረግነው የተደራጁ ስለነበሩ ለማጣራት ነው ብለከናል ቅድም ከግምገማው በኋላ ምን የተደራጁ መሆኑን ነው ያወቃችሁት ምንድን ነው ያጣራችሁት ውጤቱስ ምን ነበር

እንደ-------- ደረጃ ጥነኛ የሚባል ነበር በዛን ወቅት በአካባቢው የነበሩ ወጣቶች ተደራጁ ነበር የበዓል ልብስም ተከራይቶ ነበር በዓል የሚያሳይ በዛ ጥነኛ ላይ በዛ አካባቢ ስለተጠራጠረ መሀመድ አባድር የተባለው ወደ 7 8 አካባቢ ስለተቀመጠ ሰው ጋ የተቀመጠ ስለሆነ በሀይስኩል አካባቢም ተማሪዎች ረብሻ ስለተነሳ በዛን ሰዓት እኛም ከመንግስት ጋር የምንሰራ ሰዎች ሁሉም ነገር በዛን ሰዓት ጥርጣሬ ነበር በዛን ሰዓት ትእይንቱ ይሄ የተደራጀው ትክክልኛ ነው ትክክለኛ አይደለም በማለት ትኩረት ውስጥ ገባ

የተደራጀው ታዲያ ምን ሆኖ ተገኘ

የተበላሸ ሆኖ ተገኘ

ምንድን ነው የተበላሸ ሆኖ ተገኘ ምን ሆኖ ተገኘ የተበላሸው

እከሌ እከሌ ተብሎ ተጣርቶ ባንደርስበትም በዛን ሰዓት እነዚህ የተደራጁት ያው እዛም እዛም የተገኙ ስለነበረ በዛን ሰዓት ይሄ

ምንድን ነው የተገኙት ምን ሆነው ነው የተገኙት

5/6

እነዚህ ያደራጁ ሰዎች እነዚህ ሰዎች ጋር በነዚህ የተደራጁ መሆናቸውን ተገኙ የአባ አባል ሆነው ተገኙ

ምንድን ነው ያለው

አባል ሆነው ተገኙ

የምን

የአባ

የአባ አባል ሆነው ተገኙ

አ

ማዴ ነው የእነሱ ድርጅት

ቆይ ቆይ አባ ብለሃል አላልክም

አላለም

ታዲያ ለምን አልክ አንተ

አባች ማዴ የሚባል አደራጁት

የምን አባል ናቸው በለው የምን አባል ናቸው የምን ድርጅት አባል ናቸው ድርጅቱን አታውቀውም ማዴ ምንድን ነው በለው

የእነሱን ሃሳብ የሚያንቀሳቅስ ሰፈር ውስጥ

የማንን ሃሳብ

የአባች ሃሳብ

ምናልባት አስተርጓሚ ላይ ችግር ካልተፈጠረ በስተቀር ንኡስ ኮሚቴ ነገር ነው እያለ ያለው

ቀጥሉ አሁን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ፌ/ሪፐብሊክ ክፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

5/16

ይሄ የተቋቋመው ድርጅት አባዎ ያቋቋመው ድርጅት አልከን ያቋቋመበት አላማው ለምንድን ነበር

የራሳቸውን ሃሳብ ለማንቀሳቀስ ነው ያቋቋሙት

ሀይስኩል አካባቢ ረብሻ ነበር እያልከን ነው ሀይስኩል አካባቢ የነበረው ረብሻ የምን ረብሻ ነው

አባዎች በተማሪ ውስጥ ሃሳቡን በማቀላቀል በተማሪዎች ውስጥ ብጥበጣ ለማስነሳት አገሪቱ ይታወቃል መንገዱ ያጥርልናል ብለው በተማሪዎች ስለገባ ይታወቃል አገርም ይታወቃል በሁሉም አካባቢ ይታወቅ ነበር

የተከበረው ፍ/ቤት አንድ የምንጠይቀው ነገር አለ እነዚህ አሁን ያስነሳካቸው ተከሳሾች አሉ እና እከሌ እከሌ ብሎ ይጠቁምልን በስም እየጠራ ለመጠየቅ ያመቸናል እና ይህንን ቢያደርግልን

ስማቸውን እንዲነግር ነው

አዎ ይሄ እከሌ ነው ይሄ እከሌ ነው እያለ

ቅድም አረጋግጠዋል እኮ ስማቸውን ለፍ/ቤት አረጋግጠዋል

እሺ ተረጋግጦ ከሆነ

እሷ ማን ናት ዘሀራ ነሽ እነዛ ከኋላ ያሉትስ ጀማልና

መሀመድ ኡመሬ

መሀመድ ኡመሬ፣ ጀማል አደም፣ እሳቸውስ

አሊዩ አብዱላሂ

ከዛ ከኋላ ያለውስ

ጃፈር

ቅድምም ብለዋል አሁንም በድጋሚ ይሽው

መሀመድ ኡመሬ የፀጥታ ዘርፍ ሃላፊ ነበር

የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

517

ቆይ እስቲ አንዴ

አሁን መጨረሻ አሁን ያልከው ምንድን ነው በለው

ጥያቄ አታብዙብኝ ይላል

ፍ/ቤት መሆንህን ዘነጋህ ወይ ቀኑን ሙሉ ልትጠየቅ ትችላለህ

ይቅርታ

ስራ ነው የ ምትሰራው ይሄ ትልቅ ቦታ ነው በል እሺ ይቅርታ ስላልክ ቁጭ በል

መሀመድ ኡመሬ የፀጥታ ዘርፍ ሃላፊ ነበር ከእኛ ጋርም አብሮ ይሰራ ነበር ብለሃል እና እሱ ታዲያ የፀጥታ ዘርፍ ሃላፊ ሆኖ በሚሰራበት ጊዜ ምንድን ነው ያደረገው ነገር ምንድን ነው ያደረገው ወይም ያላደረገው ነገር የሰራው ወይም መስራት ሲገባው ያልሰራው ነገር ካለ ንገረን

የቀበሌ አስተዳደር ነበር በዛን አካባቢ የእኛ ሰፈር ነዋሪ ነበር ቀጠናውም በእኛ ሰፈር አካባቢ ነበር እኛን የሚያንቀሳቅስም በሳምንት ሁለት ጊዜ እንደዚህ ይንቀሳቀሳል ተራው በዛ ነው የሚደርሰን እንወጣለን ፖሊስ ጋር እንሄዳለን ስም እንጽፋለን ከዛ እንወጣለን የእኛ አላማ ሰላም አውርደን እነዚህ እረብሻ የሚፈጥሩ እንደነ አባዎ አይነትን መያዝ ነው ይሄ ነው የእኛ አላማ በዚህ አይነት እያለ ወደ በኋላ ላይ ኦፕሬሽን በተደረገበት ሰዓት ይሄ አብዲ ሙመድ የተባለውን ትላንትና ምስክር የነበረው መሀመድ ኡመሬ ሁለት ሰዎች የአሊዩ ቆቲኞ እርሻ ውስጥ እያሉ አሊዩ ግን አጠገቡ አልነበረም አይቼ ወደ ሀይስኩል ያያሉ ከዚህ እነዚህ ሰዎች አባዎ ነው ብዬ ተጠራጥሬ ሄጄ ነገርኩ ይሄንን ሃሳብ ነገረን ኦፕሬሽን ላይ ነበር እኛ አብረን እየተንቀሳቀስን ነበር ይሄ እንደዚህ ብሎ ሲነግረው ሄጄ አጣሁት እንደዚህ አይነት መልስ ስሰጠው አየሁ ሰምቻለሁ በሌላ በኩል እንደሚሰራ አውቃለሁ

በሌላ በኩል የሚሰራው ምንድን ነው

እኛ መድቦ በመንቀሳቀስ

እናንተን መድቦ ለፀጥታ ዘርፍ ከተንቀሳቀሰ ምን ነገር ፈጥሮ ነው ታዲያ የተከሰሰው ምን ጥፋት አለው እንደዛ ማድረግ

ትግባባላችሁ ቆይ አንዴ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅጥር ግቢ

518

የተከበረው ፍ/ቤት የገባውን ስለሚያውቅ ምን አጥፍቶ ነው የተከሰሰው ምን አጥፍቶ እንደተከሰሰ ሰውየው ራሱ ስለተጠራበት ምስክርነት እንጂ ሰውየው እኮ ግልጽ ነው እርሻ ውስጥ ሰዎች ታዩ ተብሎ ተጠቆመ ያም መቶ ተነገረን ከዛ ውጭ እኛ ጋር እየተንቀሳቀሰ ያለ ነው እንጂ ምንም ሲያደርግ አላየሁም ብሎ አረጋገጠ መስክሯል ምን ስላደረገ ነው የተከሰሰው እንዴት አድርጎ እንደከሰሰው የሚያውቀው ዐ/ህግ እሱ ስለመጣበት ምስክርነት ብቻ ነው ሊጠየቅ የሚገባው የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ የሞያ ጥያቄ እኮ ነው

በእናንተ በኩል

በእኛ በኩል ምንድን ነው በሌላ በኩል ተንቀሳቀሰ እያለ ነው በሌላ በኩል የተንቀሳቀሰው ነገር ካለ እንዲነግረን እያደረግን ነው ያን ነገር በምንጠይቀው ሰኣት እኛ ለሰላማዊ እንቅስቃሴ አሰማራን እያለ ነው ታዲያ ምን ያደረገው ነገር አለ አይ ምንም አላደረገም ይሄ ነው ብሎ እንዲያረጋግጥልን ነው እሳቸው አረጋገጠ አሱ እንጂ እሱ ከዚህ ውጪ አላደረገም ብሎ አላረጋገጠም እንዲያረጋግጥልን እየጠየቅን ነው እኛ ፍትህ ፍለጋ ነው በተለይ ደግሞ እንደዚህ አይነት የሽብርተኝነትና እንደዚህ መሰል ማነሳሳት ወንጀሎች በቀጥታ አንድ ለአንድ እንደ ስድብ እንዲህ ሲል ሰማሁት የሚባሉ አይደሉም ስላልሆኑ ትክክለኛ ፍትህ ፍለጋ ምን እንደነበረ ስለሁኔታው በግልጽ እንዲያስረዳን ነው የጠየቅነው::

ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበታል ዐ/ህግ በጥያቄ አቀራረብ ፍ/ቤቱ የተመለከተው የአቀራረብ እና የቃላት አጠቃቀም ላይ ነው ጥፋት የሚለው ላይ ማዘንበሉ በቀጥታ ክሱ የቀረበው ነገር ይታወቃል ዐ/ህግ ማስመስከር ያለባችሁን ነገር ስለምታውቁ ቀጥታ ወደዛ ነገር ላይ የሚያተኩር ጥያቄ መነሻ ማድረግ በጥያቄ አቀራረብ ላይ ስህተት አለው እሱ ታርሞ ግን ምስክሩ የሚያውቀውን ነገር ከተጠየቀ ከቀረበበት ጉዳይ ጋር ቢጠየቅ አግባብ ነው መነፈግም የሌለበት ነገር ስለሆነ በዚህ መልክ ተስተካክሎ ጥያቄው ይቀጥል ምን አደረገ በሚለው ጠይቁት

እሺ እናመሰግናለን ጥያቄአችንን እናስተካክልና በአንድ በኩል እኛን እያሰማራ እያንቀሳቀሰ ነው ብለሃል በሌላ በኩል ደግሞ ሌላ ነገር ይፈጽማል ብለከናል በሌላ በኩል የፈጸመው ነገር ካለ ያንን ነገር ንገረን

አሁን በዚህ ላይ ችግር ይሄ ሰውየው ሄደ ነግሮት ሄዶ ያየው ለእኛ ለምን አላስተላለፍክም የሚል በዚህ ላይ ትችት ተሰንዝሏል ይሄ ነው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ፌ/ሪፐብሊክ ጋምቤላ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

519

ሰውየው ሄዶ መረጃውን ስለደበቃችሁ ነው ማለት ነው

ዝም አለ እሱ ሄዶ ከዛ እንዳጣ ዝም አለ ዝም ማለት አልነበረበትም ተብሎ ተነሳበት

እሺ አመሰግናለሁ ሌላው ነገር የምጠይቀው ጀማል አደምስ ምንድን ነው ያደረገው

በእያንዳንዱ በዚህ በአደረጃጀት ላይ እንደአጠቃላይ ነው የተናገርኩት

አይ ጀማል የጀማል አደም ስራ ምንድን ነበር ምንድን ነው የፈጸመው ያደረገው ድርጊቱን ጀማል አደምን በተመለከተ ንገረን አጠቃላይ ነገሩን ቅድም ነግረከናል እናመሰግናለን

ቅድም እንደ አጠቃላይ አስቀምጫለሁ አሁን ግን ወደ ውስጥ ጠለቅ ብዬም አሁን ይሄ ይሄ ነው ብዬ የምናገረው ነገር የለኝም ምንድን ነው ቅድም እንደአጠቃላይ ካስቀመጥከው ውስጥ የጀማል አደም ተሳትፎ ምን ነበር ንገረን

የባህል ልብስ የሚከራይ ነበር በዛ ውስጥ እሱን ያንን ልብስ እንደሚያከራይ ነው ያንን ነገር ሲጠየቅም ያንን ልብስ ውስጥ ፍቃደኝነት አለመሆን ይታያል ይሄ ይሄ ነው

ባህል ነው በዓል

የባህል ልብስ

ባህል የምን ባህል ልብስ

የኦሮሞ ባህል ልብስ ነው ሰው ሲያገባ መግዛት ስለማይቻል ከኪራይ ነው የሚጠቀሙት

እሱን አይደለም መጠየቅ የፈለኩት እሱን አይደለም ቅድም እንደአጠቃላይ ተናግሬአለሁ ያልከን ነገር ምንድን ነው መሀመድ አባድር የተባለውን የኦነግ እንደዚህ አይነት ነገር አመራር እዛ አካባቢ ድርጅት ነበር ረብሻ ነበር እያልክ ነው የነገርከን እዛ ረብሻ በነበረበት ቀን መሀመድ አባድርን በተመለከተ ጀማል አደም ምን ሲያደርግ ነበር ይህንን በተመለከተ ጀማል አደም እንዲህ አድርጓል እንዲህ አላደረገም በልና ንገረን በግልጽ

እኔ በወቅቱ ጀማል ይሄንን አጠፋ ብዬ የምናገረው ራሴ የማውቀው ነገር የለም እግዚአብሔርም ሃቅን ነው የሚፈልገው እኔ

የሰማከውስ ነገር የለም ወይ

520

በመንግስት በኩልም በዚህ በልብስ በኩል ነው ፍቃደኛ አለመሆን የታየበት እንጂ እሱ ተቆጣ እኔም ተጠያቂነት አለብኝ እና ሌላ ነገር ስሰራ ካየሁ እኔም ራሴ ማለፍ የለብኝምና አላየሁም

የሰማከው ነገር የለም ወይ

ቆይ እስቲ አንዴ ቆይ እስቲ ቆይ በለው

የተከበረው ፍ/ቤት ተጠየቀ እኔ የማውቀውም ስለ እሱ የሰማሁትም ነገር የለም ብሎ ደመደመ በቃ ከደመደመ በኋላ እንደገና የሰማከው ነገር የለም ወይ

ሰማን በእናንተ በኩል

የተከበረው ፍ/ቤት ምንድን ነው ይሄንን ጥያቄ ግድ መመስከር አለበት ማለት እኮ አይደለም የሚያውቀውን ምስክር ተጠየቀ መልስ ሰጠ

ለምንድን ነው የሚደግሙት ሰማን አይድገሙት ሰማን አደለ አንዴ ብቻ ነው ማሳሰብ ያለባችሁ በእናንተ በኩል

ምናልባት ያለመስማት ችግር ከሆነ ፍ/ቤቱ ያርማቸዋል ብዬ አስባለሁ ምስክሩን የሰማከው ነገር ካለ ብለን ስንለው እኔ በአላህ ስም ነው ያየሁት ነገር የለም ብሎ ተናገረ አይ ያየከው ነገር አለ እያልኩ ሳይሆን የሰማከው ነገር ነው ያልኩህ ብዬ በድጋሚ ጠየኩት እንጂ እሱ የሰማሁት ነገር የለም የሚል ነገር ማረጋገጫ አልሰጠኝ አልሰሙ ከሆነ ፍ/ቤቱ ያርማቸዋል ብዬ አስባለሁኝ አመሰግናለሁ::

በቃ ይበቃል እኮ አልን እኛም እንሰማለን እኮ መልስ አሁን ስድብ አለ እንዴ እዚህ መሀል ላይ

የመስማት ችግር ነው የማዳመጥ ችግር ነው እየተባለ እኮ ነው

እርሶ ኖታ የሚተረጉሙት እኮ በዐ/ህግ ኩል የተሰነዘረው የመስማት ችግር በሚል የሚለው ትንሽ የሰው መብት የሚነካ ነገር ስለሆነ እሱ መታረም አለበት ስህተት ነው ፍ/ቤቱ በማስጠንቀቂያ ያልፈዋል በሌላ በኩል ግን ጥያቄው የተጠየቀው የሰማከውን ነገር ተብሎ አልተመለሰም በጭራሽ አልተመለሰም ፍ/ቤቱም ይሰማል ይከታተላል እያዳመጣችሁ የማትከታተሉ ከሆነ ፍ/ቤቱ የችሎቱን ስርዓት የማስከበር ሃላፊነት አለበት እርምጃ እንወስዳለን ይሄንን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ይጠይቀዋል የሰማከው ነገር አለ ወይ ያየከው ሳይሆን የሰማከው ነገር

521

የሰማሁት

ነገር አለ የለም ብቻ

የሰማሁት አለ

በቃ እሺ የሰማሁት ነገር አለ ጠይቁት

እሺ የሰማከውን ነገር ንገረን

ይሄ የባህል ልብስ መጥቶ ሲጠየቅ ትክክለኛ መልስ አይመልስልንም እነዚህን ነው በብዛት የሰማሁት

ትክክለኛ መልስ አይመልስልንም ማለት ምን እያለ ነው የሚመልሰው

አይሰጥም

ለምን

ይሀራያል ብር ካልሰጣችሁ አልሰጥም ይላል

እሺ ዋና ጥያቄ

አበቃችሁ አላችሁ መስቀለኛ ጥያቄ የላችሁም ጥያቄ

አለን

እሺ ቀጥሉ

መሀመድ ኡመሬ ጋር አብረን እንንቀሳቀስ ነበር ሰምቶ ዝም አለ የምትለው አንተስ አብረህ አልሰማህም ወይ

አውቆ ዝም አለ ያልነው ነገሩ የተሰራው ረጅም ጊዜ ነበር ከአንድ ሶስት አመት በፊት ነበር እንደዛ ሆኖ ተገናኝተን ይሄንን ነገር መገናኘታችን በአፕሬሽኑ ሰዓት ነው ይሄንን ነገር እርስ በእርሳችን መነጋገራችን የዛን ጊዜ ነው ይሄ ነገር የተነሳው ደግሞ ወደዛ ርቀት ነበረው እኔ ለራሴ ሰምቼ ዝም ያልኩት ነገር የለም

በግምገማው ለኣት ነው ይሄ ነገር የተነሳው

622

የተነሳው በግምገማ ነው

የሱን ተቀበሉ ወይ አለመንገሬ ትክክል ነው ብሎ የሱን ተቀበሉ ወይ

አሞ አንስቷል የሱን

ይበቃናል

ይበቃችኋል ድጋሚ ጥያቄ አለ ዐ/ህግ

ድጋሚ ጥያቄ የለንም

የላችሁም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

እስኪ ቅድም ስለመረዳጃ ማህበር ያነሳከው ነገር አለ ይህ መረዳጃ ማህበር የምን መደራጃ ማህበር ነው

ይሄ መደራጀት እንደ ኦሮሞ ባህል የኦሮሞ የመደራጀት ጥነኛ የሚባል

ጥነኛ ምንድን ነው

ለወጣቶች ለማግባት የደረሱ ማለት ነው ከዛ በፊት እንደባህል አጥር ማጠር እርሻ በጉሩፕ ሆኖ መስራት በእንደዚህ አይነት ላይ በስራና በሰርግም እንደዚህ አይነት ባህል አለ ይሄ አደረጃጀት በዚህ በኩልም አለ

እና የባህል የመረዳጃ ማህበር ነው ወይ

ከዚህ አደረጃጀት ላይ ጥርጣሬ አለን

ጥርጣሬው እንዳለ ይሁንና ይሄ የተባለው መረዳጃ ማህበር ለዛ አላማ የቆመ ነው ወይ ለመረዳዳት የቆመ ነው ወይ ለምንጠይቀው ጥያቄ ብቻ መልስ ስጥ

ለዛ ለመደራጀት ብቻ ሆኖ አልተገኘም

ምን ሆኖ ተገኘ

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ቁጥር 4 የፌደራሉ ከፍተኛው ፍ/ቤት

523

የተደባለቀ ሆኖ ተገኘ

ምንድን ነው የተደባለቀበት

የአባዎች ማዴም ተገኘበት

ምንድን ነው ማዴ

አባዎች የሚያካሂዱትን ሃሳብ ከውስጥ እጅ እንዳለበት ጥርጣሬ ነበር

እስኪ ጥያቄውን ግልጽ አድርገውና እዛ ማህበር ውስጥ የኦነግን ሃሳብ የሚያራምዱ ሰዎች ነበሩ ልትለን ፈልገህ ነው ወይ

አከሌ ብዬ አሁን ባልገልጽም ግን የዛን ጊዜ መሀመድ አባድር የሚባል ግን ይሄንን ሃሳብ ውስጡ ነበር

እነዚህስ ነበራቸው ወይ እነዚህስ የኦነግን ሃሳብ ያራምዱ ነበር ወይ

እነሱን ይሄንን ሃሳብ ሲያንቀሳቅሱ አላየሁም

ዘሀራ ምን አደረገች ነበር ቅድም ያልከን

እቺ ዘሀራ እቺ የሰራችውን አላየሁም የአሊዩ ሚስት መሆኗን አውቃለሁ መሀመድ አባድር እነሱ ጋር መቀመጡን አውቃለሁ እሷ የሰራችውን ነገር እኔ አላውቀውም

ጃፈር ነው እንዴ ስምህ አንተ ጃፈርስ በለው

የሰፈር ልጅ ነው ይሄ ጥነኛ የተገናኙ ሰው ስለነበረ በዚህ አካሄድ የነበረ ነው

በየት አካሄድ

ምን አደረገ ነው ታዲያ የምትለው አጠፋ የምትለው ነገር የለም

አሁን እሱም ይሄ ይሄ አጥፍቷል ብዬ የምናገረው ነገር የለኝም አንተ የምታውቀው ምንድን ነው

እኔ የሱ ነገር የሰማሁት ያየሁትም ነገር የለኝም

እሺ ጃፈርን ለምን ታዲያ አነሳከው ስሙን ለምን ጠቀምከው

ያልኩት ይሄ ጥነኛ አብሮ የነበሩ ሰዎች ቅድም የተናገርኩት ሃሳቦች መንግስት መጠርጠሩ ይታወቅ ነበር ከዚህ አንፃር አሁን የሰማሁት ጀማል ልብሱን ስለሚያከራይ አመትባሉን በሚያከብሩበት ሰዓት መጥተው ሲጠይቁት ጠንከር ብሎ መልስ ስለሚሆንባቸው ጠንካራ ንግግር መልስ ስለሚሰጣቸው እንደዚህ አይነት አንዳንድ ሃሜት ይሰማል ጥነኛ አብሮ ስለነበረ አብሮ መግለጼ ነው እከሌ እከሌ ማለቴ አይደለም

ጥሩ ንግግሩ ምንድን ነው በለው ጠንከር ያለው ንግግር

ልብስ አልሰጥም ለማከራየት ነው የገዛሁት

አንተ እሱ የሚለውን እንዳለ ለእኛ አድርስ ምንድን ነው ሲያደርግ የነበረው ተቃውሞ ጠንካራ ቃል ይናገር ነበር የሚባለውስ ምንድን ነው

አልሰጥም በማለት እስከመጨረሻ አልሰጥም በማለት ተከራዩ እንጂ አልሰጥም በማለት እስከወደፀብ ይሄዳል

እና ጠንካራ የምትለው ነገር አልሰጣችሁም ካልተከራያችሁኝ ይሄ ለማከራየት ነው ያዘጋጀሁት ነው

ከዚህ አንፃር በመጣላት ደረጃ ስለደረሱ ለዚህ ብዬ ነው

ተከራዩ አልሰጣችሁም በሚል ተጣሉ

አንዳንዴ እንደዚህ አይነት አዎ ግጭት ይከሰታል ሲጠይቁት

እነሱ ለምንድን ነበር የሚጠይቁት

ባህል ለማሳየትና አመት በአሉትን ለማክበር ነው

እሱ ደግሞ ምን ነበር የሚላችሁ

ሁሌ እንዴት እንሰጣለን ብለው ነው እንጂ

የማን ነው ልብሱ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

525

ይሄ ልብስ የዛ የጉሩፑ ነው የጥነኛው

የትኛው ግሩፕ የትኛው ጥነኛ

ይሄ የተደራጁ አሉ አደለ

የመረዳጃ ማህበር

አዎ

የመረዳጃ ማህበሩ

አዎ

ነው ወይስ አይደለም

ጥነኛ ያልከው ምንድን ነው ትርጉሙ ማዴ ካልከው ጋር ይለያል ወይ

ከዛ ጋር የተለየ ነው

ምንድን ነው ይሄኛው የሚለየው

ይሄ ጥነኛ የሚለው ለበጎ ነበር እርሻ መተጋገዝ አጥር ማጠር ለዚህ የሚውል ነው

ለዚህ የሚውል ነው

ይሄ የተለያየ ሃሳብ የለውም

ልብሱ ቅድም ያልከው የሙሽራ ልብስ በነፃ ነው እንዴ የሚሰጠው በነፃ ለመስጠት ነው የተቀመጠው የድርጅቱ ነው ያልከው

ለውጪ ሰው ይከራያል እዛው ማህበሩ ውስጥ ላለው ግን በነፃ ነው የሚወስዱት

ጥሩ እሺ እናመሰግናለን ከጎላ ቀጭላ ቀልቲምን ይጠራላችሁ ዐ/ህግ

ዩሱፍ አሜ

ስንተኛ ነው ዩሱፍ አሜን ጥሩት

526

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ::

ምን ፈልገው ነው ጠይቋቸው ምን ፈልገው ነው በላቸው

አሞኛል ነው የሚሉት

እሺ አስወጧቸውና መልሷቸው መሀላ አስፈጸምከው

የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ዩሱፍ አሜ

ሥራ - አርሶ አደር ነው

አድራሻ- ሐረማያ አካባቢ

ለምንድን ነው የመጣከው

ለምስክርነት

ማን ላይ ነው የምትመሰክረው

አሊዩና እነ መሀመድ ኡመሬ ላይ ነው ልመሰክር የመጣሁት

ታውቃቸዋለህ ወይ

አዎ አውቃቸዋለሁ

ተነስና አሳየን እስቲ በስም ንገረን

እቺ ዘሀራ ትባላለች

እሺ እያየህ ከኋላ ያለውን

አሊዩ ይባላል

ከዛስ ከኋላ ያለው

መሀመድ ኡመሬ ይባላል

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ክፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፩

627

ይሄ መሀል ያለው

ጀማል አደም ይባላል

ከእነሱ ጋር ተጣልተሃል እንዴ

የለኝም

ዝምድናም የለህም

የለኝም ሰፈር ነው

እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እነዚህ አሁን ያሳየከን ተከሳሾች ያደረጉት ነገር ምንድን ነው

እነዚህ ያስነሳካቸው ሰዎች ፖሊስና የአካባቢው ፀጥታ ዘርፎች አስነስቶን እነሱ የሚገመገሙበት ቦታ ወስደን እኛም ተገምግመን እኔም በዛን ሰዓት አባል ነኝ

የምን አባል

እኔ የድርጅቱ አባል ነኝ

የትኛው ድርጅት

የመንግስት አባል ነኝ

እነሱ እኛ ላይ እኛም ተገማግመን እነሱም እኛ ላይ ተጠርተው ተገመገሙ ከዛ አንፃር በዛ ግምገማ ላይ እነሱ የሰጡት ሃሳብ ይዤንን ነገር የሰማሁት ነገር አለ እኔ አሁን ለመናገር የመጣሁት የዛን ቀን የእነሱን ንግግር የሰማሁትን ነገር ነው ለመናገር የመጣሁት

እሺ እሱን ንገረን

እኔ የሰማሁት አሊዩ ቆቲኞ የሚባለው ላይ እሱ ላይ ግምገማ ሲካሄድ እኔ የሰማሁት መሀመድ አባድር የተባለው ከአሁን በፊት እሱ ጋር ሰርቼ ስናሩን እኔም አውቀዋለሁ በዛ ከዛ በኋላ በዚህ ግምገማ ላይ በዛን ጊዜ እሱ ሲጠየቅ አዎ እውነት ነው እንደልጄ ሆኖ እኔ ጋር ይሰራ ነበር

529

ብሎ ሲናገር እየሄዱ ሲጠየቅ ይሄ ሰውዬ የኦነግ መስመር ውስጥ ሁለት ሰዎች ይዞ የእሱ ቤት መምጣቱን እሱ ራሱ የተናገረው ነው እኔንም አደራጅቶኛል ከነቤተሰቦቼ ሌላ ሰዎችስ ከአንተ ጋር ተደራጁ እነማን ናቸው ተብሎ ሲጠየቅ ሌላ ሰው የለም ይሄንን ቃል ተናግሯል ከአንድም በላይ ሁለቴ ተናግሯል ይሄንን ከተናገረ በኋላ አሁን አንተ የሰጠከው ሃሳብ አለአንዳች ማፊት ከዱላም አለዱላ

ቆይ አንዴ

አሁን ይቀጥሉ ይቀዳ እንቀጥል አሁን ከመጨረሻ ላይ ይቀጥሉ በላቸው

አለምንም ድብደባ ይዜንን ሀሳብ መስጠት ይዜ ሀሳብ ላይ ፍ/ቤት የሚያደርስ ነው እወቅ ፖሊሶችንን እና የዛን ጊዜ የነበሩ ፀጥታ ዘርፎች የዛን ጊዜ እሱን አሳወቁት በአልይ በኩል የማውቀው ይሄንን ነው

እሺ እዚህ ላይ አልይ ላይ እየጨረስን ብንሄድ አልይ ኮቲቼ ማለት ማነው የትኛው ነው አለ እዚህ

አልይ ኮቲቾ የሚባለው ---

እንዲቀረፅ በማይኩ ይነገርልኝ ነው ያልኩት አልይ ኮቲቾ ማለት አልይ አብዱሌህ የሚባለው ሰው ነው ብሎ እያረጋገጠ ስለነበረ ነው

አልይ ኮቲቾ የሚባለው እራሱ ነው አልይ አብዱሌም ይባላል

አልተቀረፀም ነው ጥያቄው

ጥሩ እሺ ቀጥሉ

መሀመድ አባድር የሚባለው እቤቱ አሳድረው ነበረ እንደ ልጅም አድርጌ አሳድጌዋለሁኝ ብሎኛል በለከናል እንደገና ከእዛም በላይ ደግሞ እኔንም ከእነ ቤተሰቦቼ አደራጅቶኛል ብሎ ተናግሯል ብለከናል 2ቱ ሰዎችንም ይዞ መጣ ብለከናል መሀመድ አባድር ምንድነው

129

በእላን ሰአት የተማሪዎች ብጥበጣ ነበረ ይሄ ሰውዬ እኛም አንድ ሰፈር ነበርን ይሄ መሀመድ ኡመር የተባለው ይሄ ሰውዬ ልጁ እኔ እንደ ሰራተኛ ነበር የምቆጥረው መሀመድ አባድር መሀመድ አባድር የተባለው እንደ ሰራተኛ ነበር እኔ እኔም እራሴ የማይ የነበረ በግምገማ ወቅት ግን ኦነግ መሆኑን እኔም እራሴ ከእላ በኋላ አወቅሁ ከእላ ባለቤቱ ደግሞ ሰውዬው በዝርዝር አንድ በአንድ አስቀመጠ

እኔንም ከእነ ቤተሰቦቼ አደራጅቶኛል በሏል ለምንድነው ያደራጃችሁ በምን ውስጥ ነው ያደራጃችሁ

በምን ላይ ነው የተደራጀ ተብሎ ሲጠየቅ ተደራጅቻለሁ ከማለት ውጪ በምን ላይ ነው የተደራጀ ተብሎ ሲጠየቅ ባለመናገሩ ሊታሰርም ችሏል መታሰርም አለበት ተባለ

እነዚህን 2 ሰዎች ይዞ መጥቶ ነበር ብለከናል እነዛ 2ቱ ሰዎች ምንድናቸው

የኦነግ ሰዎች ናቸው

እስቲ ጊዜው መቼ ነው ይሄንን አደረኩ ያለበት ጊዜ እንደዚህ ---

እኔ አሁን እረስቻለሁ ቢያንስ ግን ከ1998 አካባቢ ይሆናል አንድ አራት አመት አምስት በዚላ

ወሩንስ ታስታውሳለህ ወይ ቀኑን

አላስታውስም

ቀን

ቀንም አላስታውስም

የት ሀገር ነው የት ቦታ ነው ሀገሩስ ቦታው

ገንደቡቴ የሚባል አካባቢ ነው ትምህርት ቤቱ ስር ነው

ወረዳው ወይም የሚጠራበት ስም ካለ

01 ቀበሌ ተብሎ ነው የሚጠራው

530

እሺ አሁን ደግሞ ቀጥለህ ሌሎቹን ያስነሳካቸው ላይ ንገረን በለው ዘሀራስ ዘሀራ ዘሀራ ምንድነው ያደረገችው

እኔ እና እስክ ባለቤቴ ተደራጅተናል ብሎ እሱ በተናገረው ላይ ይሄን ሲናገር ስለሰማሁ ነው ከእዚህ አንፃር ነው እንጂ

የማን ናት ሚስት

እዛ ቀንም እሷ እዛ ግምገማ ላይም አልቀረበችም

የማን ናት ሚስት

የአልይ አብዱሌ ሚስት ናት

እሺ ሌሎቹስ ሌሎቹስ አሁን ያስነሳካቸው ውስጥ ጀማል አደምስ ምንድው ያደረገው

ይሄ ጀማል አደም በእዛ በግምገማ ሰአት ከህዝቡ ጋር ሆነን ስንገማገም እኛጋም አላመጡም አምጡልን ስንላቸው ወስደው ወደ እስር ወሰዱት እነዛ ሰዎች ከተገማገምን በኋላ አብረን እንጠይቃለን ብለን ስንጠይቃቸው እናመጣለን አሉን አላመጡም በዛው ወደ ሌላ ሄዱ ከእዛ አንፃር በእዛን ጊዜ ስሙ ተነስቶበት የተነሳበት ሀሳቦች ጥሌኛ መደራጀት አለ ከዚህ አንፃር ይሄ የተደራጀው ጥሌኛ ማፅዳት አለብን በማለት ይሄንን ሀሳብ በዚህ ሀሳብ ተይዟል በእሱ በኩል የማውቀው ከዚህ ጋር የተያያዘ ሀሳብ አብሮ የሚሄድ ስለሆነ ይሄ ነው በመሀመድ ኡመሬ በኩልም

ቆይ ቆይ ጀማል አደም ተደራጅቷል ያልከን የምን ድርጅት ነው

ጥሌኛ

ጥሌኛ ምንድነው

ወጣቶች በሰፈር ውስጥ አንድ ላይ ተደራጅተው የበአል ልብስ በአንድ ላይ ገዝተው በሙሽራ ጊዜ እና በአንድ አንድ በአላትም ጊዜ ከዚህ አንፃር ይሄ መሀመድ አባድር ሀሳብ በዚህ ላይ የሚያካሂደው ይሄ ሀሳብ እነዚህ ልጆች ላይስማም ሳይኖር አይቀርም እነዚ ልጆች ማፅዳት አለብን ከማለት ከእዛ አንፃር ልጆቹንም ተጠየቁ ከእዛ በኋላም እነዚህ ልጆች እነዚህ ልጆች ከእነ መሀመድ አባድር ጋርም የሚሄዱ ናቸው አንድ ሰፈር ውስጥ ስለነበሩ አብረው የሚሄዱ ናቸው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

531

እኔ የማውቀው እነዚህ ሰዎች የእኔ ሰፈር ስለሆኑ እንደ ወንድሞቼም አብረን የምንኖር ስለሆነ እኔ ያልሰማሁት ነገር እነሱ ላይ አሁን እነሱ ላይ የማስቀምጠው ነገር የሰማውም የማስቀረው ነገር የለኝም ያልሰማሁትን ደግሞ እነሱ ላይ የማስቀምጠው ነገር የለኝም ከዚህ አንፃር እግዚያብሔርን እፈራለሁ

ቆይ አሁን ቅድም አልይ ላይ ስትመሰክር መሀመድ አባድር የተባለው የኦነግ አባል ነው ያደራጅ ነበር ብለከናል መሀመድ አባድር --- አደም ጋር አብሮ ከእነ ጀማል አደም ጋር አብሮ ነበረ ነው ያልከኝ ቅድም ወይንስ ምንድነው የእኑሱ ሀሳብ እዛ እነኛ ውስጥ ነበረ እያልከን ነው ወይ

ይሄ መሀመድ አባድር ከሁሉም ጋር ነበረ እዛ ሰፈር ውስጥ አብሮ ያልነበረ ሰው አልነበረም ከሁሉም ጋር ነበረ

መሀመድ አባድር እዛ ሰፈር ላይ --- ለምንድን ነበረ ምን እያደረገ ነበረ አላማው ምን ነበረ

እኛም ከአሁን በፊት የምናውቀው ያው ሰርቶ እንደሚያድር ነው ከእዛ በኋላ ግን መጨረሻ ላይ በግምገማ ምክንያት ይሄ ነገር ለህዝቡ እራሱ ግልፅ የወጣው ከእዛ በኋላ እኛም እራሳችን ተረዳን እኛ እራሳችንም ብንጐዳም በእዛ ቀበሌ ውስጥ እኛ የምንቀሳቀስ ሰዎች እንኳን በእዛ አንፃር እንኳን እግዚያብሔር አወጣን ከእዛ ጀምሮ እስካሁን ድረስ እስከ አሁን ድረስም እየተከታተልን ያለውም ቀን እና ለሊትም እየሰራን ነው

ኦኬ

ይሄ ነው

እሺ መሀመድ ኡመርን በተመለከተ ደግሞ ንገረን

መሀመድ ኡመሬ የቀበሌ አስተዳደር ፀጥታ ነው ቀን እና ለሊት ፀሀይ እና ዝናብ ሳንል ቀን ለሊት ሙሉ ከፖሊሶች ጋር ሆነን ሮንድ ስንዞር እናድራለን አሁን እየሄድን እየሄድን ይሄ ከእዛ በኋላ ይሄ ግምገማ መጣ ከመጣ በኋላ ይሄ ግምገማ ከመጣ በኋላ ነገሩ መሀመድ ኡመሬን የማነካ ሆነ አብዲ ሙመድ የተባለው የሆነ ሰዎች የአሊይ ቆቲቾ እርሻ ውስጥ በማዳበሪያ የሆነ ነገር አንጠልጥሎ እዛ ላይ አድርጐ እዛ ላይ ሰቅሎ ሁለት ሰዎች እዛ ቆመው አየሁት እነኚህን ሰዎች ጠርጥሮ ተከታትሎ ሌላ ሰው ተሸታቹሎ ጠይቆ አነግ መሆናቸውን አውቆ ለዚህ ለቀበሌው አስተዳደር መሀመድ ኡመሬ ለተባለው እንደዚህ አይነት ነገር ነው በቦታው

532

የተጠራጠርኩት አንተን ነው የሚመለከተው ሂድ እና ተከታትለህ ድረስበት እንደዚህ አይነት ነገር አለ ብዬ ነገርኩት በማለት እውነት ነው አንተ ነግረከኛል እኔ ደግሞ ሄጀ ሳየው አላየሁም አጣሁት በማለት መሀመድ ኡመሬ ኦሶ አይተህ እየሰማህ አውቀህ ነው የተውከው በማለት ተይዞ ታሰረ መሀመድ ኡመሬ እኔ በእዛን ወቅት ሄጀ ተከታትዬ በወቅቱ የነበረ --ችን ይገር ሄጀ አጣሁት በእዛን ሰአት ይሄንን ሀሳብ እሱም ሲሰጥ ነበረ ይሄንን ነው እኔ የሰማሁት እግዜሀርም ያውቀኝ

ማነው ሄጀ ነግሬ ሳትሰራ ቀረህ ብሎ ያለው ማነው -- የነገረው ሰው ለሱ ማነው

እነዚህ ያገማገሙ ሰዎች ናቸው

ስማቸውን አታውቃቸውም

አንዱ ሙዘይን ይባላል

አንዱ ዳንኤል ይባላል

ዳንኤልና ሙዘይን ናቸው ወይ ነግረንህል ያሉት

አይደለም

እ

ለመሀመድ ኡመሬ የነገረው አብዲ ነው አብዲ ለመሀመድ ኡመሬ ሰምቶ ነገሩን ተጠራጥሮ ሄዶ ለመሀመድ ኡመሬ የቀበሌ አስተዳደር ፀጥታ አስለሆነ ሂድ እና እይ ይመለከትህል ነገሩን ተከታትለህ ድረስበት ብዬ ብሎ ነገረው አንተ የነገርከኝ ለአት

በቃ እሱን እሱን ሰምተናል መቼ ነው

እኔ በእዛው በግምገማ ሰአት ነው የሰማሁት

ቅድም የነገርከን ጊዜ ነው ወይ

አዎ በዛው ጊዜ ነው

ቦታውስ

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 2

533

እርሻው የአልይ እርሻ ነው

ቅድም የነገርከን ቦታ ነው ወይ

እርሻ እና ቤቱ ይለያያል

አንድ ቀበሌ ነው

ሌላ የምታውቀውን ነገር ትነግረናለክ ወይ

እኔ ያየሁ እና የሰማሁት ነገር

ሌላ የምትጨምረው ነገር አለ ወይንስ የለም

ተጨማሪ አሁን ከነገርከን ተጨማሪ ካለ ከነገርከን ነገር በተጨማሪ ሌላም ነገር አለ ወይ

ጨርሻለሁ

አበቃችሁ እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አላችሁ

ማነው ስሙ የሱፍ አዎ

አቶ የሱፍ

ይሄ መሀመድን ይሄን ቃል ተናገረ የምትለው ----- ምርመራ ----

እዛው ግምገማ ላይ እራሱ ፖሊስም አለ እዛው እራሱ ቃልም ይፃፍ ነበር

--- ማጣራትም ነው

አዎ

ይበቃናል ኤው ------- መሀመድ ኡመሬን --- መሀመድ ኡመሬም ሰዎች ይገቹ ሄጂ ሰዎቹን አጣኋቸው ሄጂ ብሄድ አጣኋቸው ብሎ ያለው ቀጥታ እሱ ከቀበሌው ከከተማው ---

የተወሰነ ይርቃል

ምን ያህል እስቲ እንደው በሰአት ተምነው

6341

አንድ ሰአትም አያስኬድም ቅርበት አለው አንድ ሰፈር ነው

የት ሀገር ነው -------

ጫት ምናምን እርሻዎች አሉ

እርሻዎች አሉ

ይበቃቹሀል እሺ መስቀለኛ ጥያቄ በቃን ተብሏል ድጋሜ ጥያቄ ካለ በዐ/ሕግ በኩል የለም የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ እሺ የፍ/ቤቱ መጣሪያ ጥያቄም የለም እናመሰግንዎታለን ይመለሱ በላቸው ማን ይጠራላችሁ ዐ/ሕግ

9ኛ ምስክራችን ፋጡማ የሱፍ

ወ/ሮ ፋጡማ መሀላ ፈፅመዋል

9ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ፋጡማ ዩሱፍ

ስራ - የቤት እመቤት

አድራሻ - ሐረማያ አካባቢ

ለምስክርነት ነው

አዎ

በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት

ዩሱፍ ዳውድ የሚባል ላይ ነው

እስቲ ተነስተው ያሳዩናል ሌላ የለም

ሌላ የለኝም

ሌላ የለም እሺ ይቀመጡ ይምጡና

በኦሮሚያ ፌዴራላዊ ዲ/ፀ/ግዛት ... የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

536

ዩሱፍ ዳውድ ስንተኛ ነህ ስንተኛ ተራ ላይ 51ኛ አይደለ እሺ 51ኛ ተከሣሽ ዩሱፍ ዳውድን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ ለምስክርነት ነው ምንድነው የምታስረጂው በእሱ ላይ ምንድነው የምታውቂው

እሱ ላይ የማውቀው ነገር መሀመድ አባድር አባዎ ከዩሱፍ ዳውድ ጋር የእኔ እቤት መጥቶ ከትምህርት ቤት መጥቶ ትምህርት ቤት መጡ ሚሸን መጡ ከእዛ በኋላ ያው ሉሉ አድርገው ሄዱ የኔ ባል ትልቅ ሰው ነው እኔም ትልቅ ሰው ነኝ የእኔ ልጅም የለም የእናንተ እኩያ እኔ ጋርም አትምጡ ከእኔ ሂዱ ይሄንን ነው የማውቀው

ይሄ መሀመድ አባድር የተባለው አባዎ እና ዩሱፍ ዳውድ መጥተው ሉሉ አድረጉ ማለት ምን ማለት ነው

ሉሉ ማለት ያው ጫት ቅመው

ማን ቤት ነው ጫት የቃሙት

የእኔ እቤት ነው የቃሙት

ታዲያ አንቺ እቤት ከቃሙ ለምንድነው አትምጡብኝ ያልሻቸው

ይሄ መሀመድ አባድር ኦነግ ስለሆነ ከእዛ አንባር ተነስቼ ነው የተቆጣሁት

በሚቅሙ ሰአት ምን ይሉ ነበር የሰማሽው ነገር አለ

መሀመድ አባድር የተባለው እኛ ነፃ አልወጣንም

እ

ሲል ነበር

--ቦታው የት ነው

ሐረማያ

መቼ ነው

በኢፌዲሪ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጋምቤላ ክልላዊ መንግስት የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

536

ቆይቷል

ምን ያህል ይሆነዋል በግምት

ወይም አራት አመት ወይም ደግሞ አምስት አመት ይሆናል

ምንድነው ነፃ አልወጣንም ማለት

እሺ ተመልሷል ምንድነው ያሉት መልሱ ምንድነው

እ

ምንድነው ያሉት አሁን ያሉት

እኔ አላወኩም

አላወኩም ብለዋል እሺ ሌላ ጥያቄ

ይሄ መሀመድ አባድር የተባለው አባዎ ነው ብለሻል

አዎ

ዩሱፍ ዳውድ ታዲያ ከእሱ ጋር ምን ነበር የሚያደርገው

አብረው ሲሄዱ ነው የማየው እኔ ምን እንዳደረገ አላየሁም

ታዲያ አንቺ እቤት ሲመጡ አትምጡብኝ ያልሽበት ምክንያቱ ምንድነው

መሀመድ አባድርን ስለጠላሁት ከእሱ ጋር እንዳትመጡብኝ አልኩ

ምን ስለሆነ ነው የጠላሽው ለምንድነው

መሀመድ አባድር አባዎ ስለሆነ ነው የጠላሁት

የሚነጋገሩትን በሙሉ ሰምተሻል እንዴ አንቺ

እኔ ቤት ውስጥ ወዲያ ወዲህ ስሯሯጥ ነው እና ስራዬን ነው የምሰራው ማንም ልጆችም ስላሌለኝ እቺን ቃል ብቻ ነው የሰማሁት

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 4

537

ምን የምትለውን ቃል

እኛ ነፃነት አልወጣንም የሚለውን ቃል ብቻ ነው የሰማሁት

አበቃችሁ እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አላችሁ ትጠይቃላችሁ

አንጠይቃቸውም

እ የላችሁም እሺ ድጋሜ ጥያቄም አይኖርም የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄም የለም እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ ማን ይጠራላችሁ

ማሻ አደም 77ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ማሾ አደም 77 የዐ/ሕግ ምስክር

37ኛው

77ኛ

77ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ማሾ አደም

ስራ - አርሶ አደር

አድራሻ - አወዳይ

ለምስክርነት ነው ወይ የመጡት

አዎ

በማን ላይ

ሻሚ ኢብራሂም

ያሳዩናል ሻሚ ኢብራሂምን ተነስተው ተነሱ እና ያሳዩን

የለም

ከሁሉም ከሌቶቹም ከወንጀቹም ምንም የለም

የፌዴራሊ ዲሞክራሲያ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 1

539

እኔ ሌላ አላውቀውም የማውቀው አለ ግን እሱ ላይ የማውቀው ነገር የለም

ማንን ነው የምታውቀው

ቆይ ቆይ ቆይ ቆይ እስቲ አንዴ ቆይ ቆይ ቆይ አሁን ማንን ለየህ በለው እስቲ አንተ አስተርጉም ባክህን የታለ

አሜ ኢብራሂም

እሺ ሌላ የምታውቀው አለ ሌላ የምታውቀው አለ

ሌላ አሉ የማውቃቸው

እኮ አሳየና

ከእኛ ከተማ የመጡትን

አይደለም እዚህ ውስጥ የምታውቀው አለ ወይ እዚህ ከተከሰሱት ውስጥ

ከእኛ ከተማ የመጡትን አውቃቸዋለሁ

ጥሩ እሺ ና ቆይ ጥሩ ከአንተ ከተማ የመጡትን ሌሎች የምታውቃቸው ሰዎች እዚህ ውስጥ አሉ ወይ በለው

ብዙ አሉ

ጥሩ ስለ እነዛ ሰዎች የምታውቀው ነገር አለ ወይ ለፍ/ቤቱ የምትነግረው ዛሬ በምስክርነት እሺ የመጨረሻው ይደገም እኔ በአይኔ ብለህ ያልከው

በአይኔ ካየሁት በስተቀር ቁራን ጨብጬ ውሸት አልናገርም

ጥሩ አሁን ባልከው እምነት መሰረት በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

ሻም ኢብራሂም ላይ

እሺ ስንተኛ ተራ ላይ ነው

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ

539

ስንተኛ ሻም ስንተኛ ነህ 26ኛ

25ኛ

25ኛ ተከሣሽን በችሎት ለይቶ ሻም ኢብራሂም አብደላ ጥሩ እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ ካየሁት በስተቀረ አልመሰክርም ብለሀል

ቆይ ቆይ ቆይ አንዴ ቆይ ምንድነው

የተከበረው ፍ/ቤት ዐ/ሕግ በክሳቸው ላይ 77ኛ ምስክርን የጠሩት በምስክርነታቸው ላይ በ22ተኛ ተከሣሽ ላይ ይመሰክርልኛል ነው እንጂ በ25ኛ ተከሣሽ ላይ ይመሰክርልኛል ብለው ያላሉ ስለሆነ ከጭብጣቸው ውጪ ነው ከጭብጥ ውጪ ደግሞ የመጣ ምስክረ ሊሰማም አይገባውም

እሺ ዐ/ሕግ

አዎ ምናልባት ፍ/ቤቱ እየጠየኩ ነበረ አሁን እንትኑን ምስክራችንን በቀጥታ ያየሁትን ብቻ ነው የምመሰክረው እያለ ነው ከዚህም ሌላ ሰው ካለ ልጠይቅ ነው የሰማው ካለ ማለት ነው በ2ኛ ደረጃ ደግሞ ለፍ/ቤቱ 77ኛን ምስክር በሚመለከት የምናሳስበው በዚህ በክስ ዝርዝራችን ላይ ከጠቀስነው በተጨማሪም ይሄንኛው ምስክር በ22ኛ ብለን ነው እዛ ላይ ጭብጣችን ላይ የያዝነው ነገር ግን በ25ኛ ሻሚ ኢብራሂም ላይ እንዲመሰክርልን ነው ለፍ/ቤቱ ጭብጥ የምናሲዘው ምክንያቱም ከሁለት ነገር አንፃር ነው የምናሳስበው ለፍ/ቤቱ 1ኛ በ137 ላይ ምስክር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ስለሚያውቀው ነገር እንዲመሰክር ስነ ስርአት ህጉ ይፈቅዳል ስለዚህ የጭብጣችን አካል ነው የምናደርገው 2ኛ እንደገና ደግሞ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ በተጨማሪ ማስረጃነት በ145 ንዑስ አንቀፅ 143 ንዑስ አንቀፅ 2ትም ላይ ዐ/ሕጉ ሊጠይቅ እንደሚችል ህጉ ይደነግጋል እንደገና ደግሞ ከዚህም በተጨማሪ ወንጀሉ ሽብርተኝነት ማነሳሳት ከመሆኑ አንፃር እጅግ በርካታ ተከሣሾች እና ምስክሮች ከመኖራቸው አንፃር የትኛው ምስክር በየትኛው ተከሣሽ ላይ ለይቶ ይመሰክራል የሚለውን እጅግ አድካሚ ስራ ስለነበረ መጀመሪያ ለይተን ለማቅረብ ተቸግረናል ስለዚህ ይሄንኛውን ተከሣሽ ይሄንኛውን ምስክር በሚመለከት አሁን ባሳሰብኳቸው ምክንያቶች በ25ኛ እና በ25 ተከሣሽ እና በጠቀስነው በ22ኛ ላይ እንዲመሰክርልን ነው በዚህ መልኩ ጭብጥ እንዲያዝልን ይፈቀድልን ነው የምናሳስበው

የተከበረው

እሺ አስመዝግቡ

ጭብጥ ከላይ -- ክስ ቀርቦ ጭብጥ በግልፅ ቀርቦ በ22ኛ ተከሣሽ ላይ ይመሰክራል ተብሎ ፍ/ቤቱም በዚሁ መሰረት ነው ጠርቶ ያመጣው ይሄ ምስክር መመስከር ያለበት በ22ኛ ነው ይሄ 145 መቶ ምናምን የሚባለው 145 ተጨማሪ ምስክር ወይም ያይለታል ወይም አያይለትም ከዚህ ከመጀመሪያ ምስክር ጋር ግንኙት የለውም ተጨማሪ ምስክር ፍ/ቤትን ማስፈቀድ ሌላ ጥያቄ ነው በዚህ ጭብጥ ላይ የሚሄድ አይደለም 2ኛ ደግሞ የፍ/ቤቱ ጠርቶ ያመጣው ምስክር በ22ኛ ላይ እንዲመሰክር ነው በቃ ስለ 25ኛ የተነሳ ነገር የለም ይሄ ክስ ተነጥሎ ቀርቦ ቢሆን በ25ኛ አልነበረም ማለት ነው ስለዚህ ባልነበረ ባልተያዘ ጭብጥ ላይ ሊመሰክር አይገባውም ሊመሰክርብን አይገባም

በቀረበው አቶ ማሾ አደም 77ኛ የዐ/ሕግ ምስክርን በተመለከተ ነው ክርክሩ የተነሳው በጭብጥ የተያዘው ላይ የዐ/ሕግ ክስ ዝርዝር የጭብጥ ማስረጃ በእያንዳንዱ ምስክሮች የሚያስረዱት በማን ላይ እንደሚያስረዱ ተከሣሾ የተመለከተበት ነው በሌላ በኩል የተነሱት ክርክሮች በዐ/ሕግ በኩል የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ቁጥር በተጨማሪ ማስረጃ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ እና በክስ አቀራረብ ደግሞ ከጉዳዩ ስፋት እና ምስክሮችን ከመለየት አንፃር ያለውን በአሰራር ችግር መነሻ በማድረግ የቀረቡ ክርክሮች ነው በተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ በኩል ደግሞ በህጉ ይሄ ተቀባይነት የለውም በግልፅ በተቀመጠው ጭብጥ የተጠራ ምስክር ነው ይሄንን አላውቅም ካለ ምስክርነቱ በፍ/ቤት ሊሰማ አይገባም የሚል ነው ፍ/ቤቱ 2ቱንም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቷል በህጉ በወንጀለኛ በተጨማሪ ማስረጃ የተደነገገውን ድንጋጌ እና በክስ አቀራረብ በመለየት በኩል የቀረቡትን በፍሬ ነገር በማስረጃ አደረጃጀት የቀረቡትን 2 ተያያዥ ክርክሮችን በተመለከተ ፍ/ቤቱ አልተቀበላቸውም በሌላ በኩል ግን የቀረበው 77ኛ የዐ/ሕግ ምስክር በዚህ ፍ/ቤት ተከሰው ከቀረቡት ተከሣሾች የሚያውቁትን ለይቶ በችሎት አሳይቷል በዚህ ፍ/ቤት ደግሞ የተከሰሰ ሰው ስለሆነ የቀረበውም ምስክር ደግሞ በዚህ ችሎት ተከሶ የቀረበውን ተከሣሽ አውቃለሁ በእሱ ላይ ነው የምመሰክረው ስላለ ይህ ምስክር በፍ/ቤት ሳይሰማ ሊመለስ ይገባል ብሎ ማለት ስለማይቻል መመስከር አለበት በሚያውቀው ጉዳይ ላይ በዚህ ፍ/ቤት ተብሏል ስለዚህ ፍ/ቤቱ ምስክርነቱን መስማት ይቀጥላል በ25ኛ ተከሣሽ ላይ ማለት ነው ስለዚህ በዚሁ መሰረት ምስክርነቱ ይቀጥላል

ከእሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ በለው እስቲ ከማሾ ጋር

የለኝም

እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ ማሾ ምንድነው እስቲ በሻሚ ላይ የምታስረዳው የምታውቀው ምንድነው እስቲ ንገረን

ይሄ ሻሚ እኔ ያ ቀበሌ አስተዳደር በመሆኔ ቀበሌዎቹን ህዝቡን ለመቆጣጠር በምንሄድበት ሰአት ለግምገማም በምንሄድበት ሰአት ለሰላም በምንሄድበት ሰአት ከእኛ ጎላ እኛ ውስጥም ጥርጣሬ አስገብቶ እየተከታተልን ይሄንን ነገር ደርሰንበት ይሄ የእነሱ መስመር የአባዎ ጫያ ቁጭ ብሎ የእነሱ ጫሳ የእኛን ጫሳ በመበጥበጥ ይሄንን በማወቁ ይሄንን አውቀዋለሁ

ጫሳ ምንድነው በለው እስቲ ጫሳ ኦሮምኛ ነው አይደል ተርጉምልን አንተ

ያው የተ ማለት ጓደኛ ማለት ነው የተሳሰረ አንድ ላይ የተሳሰረ ማለት ነው ፊንቀባስ የተባለም ኦነግ ከአሁን በፊት ከአወዳይ ውስጥ ፈንጂም ያወጣው እሱው ጋር አብረው እሱ እቤት ተይዘዋል

ከሻሚ ቤት

አብሮት እንደተቀመጠ ከሻሚ ጋር አብሮ ነበረ

እህ ስለዚህ ሻሚ ምንድነው ማለት ነው

አባዎ ነው

መቼ ነው

እኛ ሰላም ብዬ ብለን እያወቅን እያለን እስከሚደረስበት ድረስ በሰላማዊ ሰው ነው የምናውቀው ከተደረሰበት በኋላ ነው ይሄንን ነገር ሁሉ የታወቀው

አሁን ይሄ የምትለን እኔ የጠየኩህ ይሄ የምትለን ጊዜው መቼ ነው በስንት አመተ ምህረት ነው ይሄ አባዎ መሆኑን ደርሳችሁበት እንደዚህ በቁጥጥር ስር -- መቼ ነው

እኔ አሁን ስላልተማርኩ አመተ ምህረቱን ይዜን ያህል ነው ብዬ ለመናገር

በግምት ምን ያህል ይሆነዋል ገምት በዚህ ምን

ቢያንስ በግምት ከ1 6 አመት በፊት ነበረ ከእዛ ከተባለ በኋላ ከ2 አመት በኋላ አዋጅ ወጣ እና በፖሊስ ተይዞ ቁጥጥር ስር ዋለ

መቼ ነው ቁጥጥር ስር የዋለው መቼ ነው በቁጥጥር ስር የዋለው

ታስሮ ከወጣ በኋላ በእንደዚሁ ሀሳብ ውስጥ እይተራመደ ነው ያለው

የት ነው ቦታው

አወዳይ

ስለዚህ አሁን አንተ ሻሚ ላይ የምትለውን ብለከናል በቀጥታ የማውቀውን ነው ብለካል ከሻሚ ሌላ ቀጥታ አንተ ከምታውቀው ውጪ እዚህ ውስጥ ካሉ የሰማከው አለ ወይ

መቃወሚያ አላችሁ መቃወሚያ አለ እሺ አስመዝግቡ

የተከበረው ፍ/ቤት በ25ኛ ላይ በቻ ተብሎ ብይን ሰጥቷል ይህ ፍ/ቤት የፍ/ቤት ብይን ነው እኮ

እሺ

በእናንተ በኩል

ፍ/ቤቱ የ22ኛ ተከሣሽ ላይ በ22ኛ ተከሣሽ ላይ ምስክራችን እንደሆነ ቀደም ብሎ ገልፀናል ነገር ግን ምስክሩ አለየም ነበረ ያለየውም ምንድነው ምሎ እኔ የማውቀውን ብቻ በአይኔ ያየሁትን ነው የምመሰክረው በአይኔ ያየሁት እከሌ ነው ብሏል የሰማከው ማን ላይ እንደሆነ አልተናገረም በዚህ እረገድ የሰማሁት በእከሌ ላይ ነው ብሎ ስላለየን እንጂ ፍ/ቤቱ 22ኛ ተከሣሽ ላይ አያሰማም ብሎ አልከለከለንም ሳንጠቀስ የነበረውን የ25ኛን በሚመለከት ብይን ተሰጥቶ ተፈቀደልን እንጂ 22ኛው ውድቅ ይደረግ አልተባለም እኛም ውድቅ ይደረግም ብለን አላሳሰብንም

ተጨማሪ

እሺ

5/13

ፍ/ቤቱም ብይን ሲሰጥ ምናልባት ካልሰማሁ እታረማለሁኝ በ25ኛ ተከሣሽ ላይ እንዲመሰክር ተፈቀደ እንጂ በእሱ ላይ ብቻ እንዲመሰክር ከእሱ ውጭ እንዳይመሰክር የሚል እገዳ ፍ/ቤቱ የጣለ አልመሰለኝም ስለዚህ ተቃውሚቸው ውድቅ እንዲደረግልን እጠይቃለሁ

ዐ/ሕግ አላችሁ የምትጠይቋቸው

ሌላ ጥያቄ ቀጥሉ እናንተ እኛ እንጠይቅ በኋላ ፍ/ቤት አስፈላጊ ከሆነ በፍ/ቤቱ የሚታይ ይሆናል

ማለት ጥያቄያችን ውድቅ ተደርጐ ተቃውሞው ተቀባይነት አጊኝቶ የእኛ ውድቅ ተደርጐ ማለት ነው

ፍ/ቤቱ ብይን አልሰጠም ሌላ ጥያቄ ካላችሁ ሌላ ጥያቄ ቀጥሉ አሁን

ከዚሁ ጥያቄ ተያይዞ ነዋ የምንጠይቀው እንጂ ሌላ ጥያቄ የለንም

የላችሁም

ከጥያቄው የተነሳ ነው የምንጠይቀው

ጥሩ

ይሄ ከተፈቀደልን እንጠይቀው

ጥሩ እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮ ብይኑ ማታ እንደተባለው የመገደብ ነገር የለውም 25ኛ ላይ ስላለ በ25ኛ ላይ ይቀጥል ነው ዞሮ ዞሮ ግን ምስክር ሲመሰክር የሚያውቁት ነገር እያሰቡ ከሚናገሩት ጋር የሚወሰን የሰው ልጅ አስተሳሰብ አይምሮ ስለሆነ የሚመጣው ስለዚህ ሊሰፋም ሊጠብም ይችላል ብዙውን ጊዜ ይሄ የተለመደ ነው ፍ/ቤትም በሌላ ደግሞ ሰፋ ያለ ነገር ከተገኘ የመሰከረውን መነሻ እየተደረገ ጥያቄ የመጠየቅ ነገር የተፈቀደ ነገር ነው ባለው ህግ ስርአትም በየትኛውም ሀገር ይኼው ነው ያለው ልምዱ ስለዚህ ጥያቄው የሚያውቀው የሰማው ነገር ካለ በሚል ነው ጥያቄው ይቀጥል እና ፍ/ቤቱ ደግሞ ያጣራል ይቀጥሉ አሁን

እሺ እናመሰግናለን ቅድም ምያለሁኝ ቁራኝ/ይዤ ምያለሁኝ የምመሰክረው ያየሁትን ብቻ ነው ብለሀል አሁን ቁርአን ይዘህ ምለሀል አሁን ደግሞ የሰማከውም ነገር ካለ ንገረን በሌሎቹ ተከሣሾች ላይ የሰማከውን ብቻ

እኔ በጆሮዬ የሰማሁ አስገምጋሚው የሰማሁት እጀና የምትባለው እኔ ስለ እጀና ምንድነው የምታውቀው ተብዬ ተጠይቄ ይዤ ስለ እሷ ምንም የማውቀው ነገር የለም ብዬ የመለስኩት ነገር አለ

ሌሎችስ ስለ እሷ ምን አሉ የሰማከው ነገር ካለ ንገረን

ሰው ከአባዎ ጋር እንደዚህ እንደዚህ እንደዚህ የላሉ እኔ ግን የደረስኩበት ነገር እንደ ግሌ የለም

እስቲ እንደዚህ እንደዚህ ያሉትን ነገር ከአባዎ ጋር ንገረን ምንድነው እንደዚህ እንደዚህ እኛ አይገባንም እኮ

በእንደዛ ምክንያት ተይዛ በዚህ ምክንያት ተይዛለች ሲባል ነው የሰማሁት

እሺ ሌላ ጥያቄ

ጀና የትኛዋ ናት አሳየኝ

ተነሳ ተነሳ እና በለው

ጥሩ እሺ ሌላ ጥያቄ

እሷስ ስትናገር የሰማከው ነገር አለ

የለኝም

ቅድምም አላውቅም ብሏል

ስለ ጀና ከዚህ በፊት የሰጠከው ምስክርነት የለም በእሷ ላይ አንተ በቀጥታ አውቃለሁ ብለህ ወይንም ደግሞ ሰዎች በእሷ ላይ ይዤንን ነገር ጀና እንዲህ ናት በሚል

አይ እኔ የለኝም በስህተት ከተባፈ እንጂ እኔ አላውቅም

በእሷ ላይ ሙሉ የምስክርነት ቃል ሰጥተህ አልፈረምክም የፈረምከው ነገር የለም በእሷ ላይ ለብቻ

ኑና ቅረቡ ተብለን አሁንም እንደተጠራን አይነት ናና ፈርም ተብዬ ፈረምኩት እንጂ እኔ ምን እንደሆነ የማውቀው ነገር የለም

ምናልባት ለፍ/ቤቱ እዚህ ጋር ማሳሰብ የምንፈልገው ምስክሩ ከዚህ ከ22ኛ ከ25ኛ ከሻሚ ውጪም ጀናን በሚመለከት የሰጠው ሙሉ የምስክርነት ቃል ስላለ እዚህ ላይ ደግሞ ዝም ብዬ ፈረምኩ እያለን ስለሆነ ይሄንን በሚመለከት አስጠቂ ምስክር ስለሆነ እሷን በሚመለከት የሚያውቀው እና የሰማው መኖር አለመኖሩን እየመራን እንድንጠይቀው በድጋሜ እንዲፈቀድልን ነው እኛ የምንጠይቀው

እሺ በእናንተ በኩል

እኔ ስለ ጀና ታሰረች መባልን እንጂ ሌላ ምንም ነገር የሰማሁትም የማውቀውም የለም ብሎ ደምድሞ ጨርሷል እነሱም ይሄንን ምስክር ደምድሞ እየጨረሰ እያለ ምንድነው የሚመራው መሪ ጥያቄ በመጀመሪያ ጥያቄ ላይ እንደውም አይፈቀድም መሪ ጥያቄ በማይፈቀድበት እሱ ምንም አላውቅም ብሎ ደምድሞ በዚጋው ነገር ላይ ሊጠየቅበት አይገባም

አላችሁ የምትሉት

አዎ እዚህ ላይ

እሺ ምንድነው

መሪ ጥያቄ በዋና ጥያቄ ላይ ጭራሽ አይፈቀድም የሚል ፍፁማዊ ክልከላ የለውም ፍ/ቤቱን አስፈቅዶ ዐ/ሕግ ወይንም ተከላካይ ጠበቆች እንዲጠይቁ ይፈቀዳል የሚል የህግ ድጋፍ አለ አሁን እያደረግን ያለነው የስነ ስርአት ህጉን ተመርኩዘን ፍ/ቤቱን አስፈቅደን እንድንጠይቅ ይፈቀድልን ብለን ነው ያልነው እና እንዲፈቀድልን እንጠይቃለን በዚህም ላይ ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ ምስክሩ ማለት ነው ስለ እሷ አልሰጠሁም አላውቅም ሳይሆን ያለው ስለ እሷ ልክ እንደዛሬው ተጠርቼ የሆነ ነገር ተደርጉልኝ ፈርሜያለሁ ሁላ ቃል በቃል እያለ ነው የሰማሁትን እና እነዚህ ነገሮች የሚያሳዩት ምስክሩ በተለይ በዐ/ሕግ የዐ/ሕግ ምስክር ቢሆንም በዐ/ሕግ ዋና ጠያቂ ላይ ይሄንን ጭብጥ በተመለከ ኮስታዊትነስ ወይንም ደግሞ አስጠቂ መሆኑን ነው የሚያሳየው ስለሆነም እኛ አሁን ሌላ ነገር ይፈጠር ሳይሆን አብራርተን አረግጠን ስላለመስጠቱ እንዲያረጋግጥልን ነው ሀሰተኛ ምስክር የሚባለውም ከዚህ በኋላ የሚመጣ ጥያቄ የመሳሰሉት እንጂ ቀጥታ አላውቅም ስላለ እንዲሁ ተድበስብሶ የሚቀር አይደለም ፍ/ቤቱ አጣርቶቶ አስፈላጊው ከሆነ 2ቱም ላይ የፈረመው አለ ፍ/ቤቱም ሊያየው ይችላል ይሄ ትክክለኛ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥም የሚያስገድደን ነው ስነ ስርአት ህጉ 137 ንዑስ አንቀፅ 2ትም ላይ

5416

ይሄንን ነገር በዋና ጥያቄ ላይ ሊቀርብ የሚችል መሆኑ ክስታይል በሆነ ጊዜ በግልፅ የደነገገው ነው ክልከላም የለ እንደውም ኮስታይል መሆኑን እስካሳየን ድረስ ፈቃጅ ነው ስለሆነም ፍ/ቤቱ ይሄንን ተንተርሶ በዚህ ላይ ብይን እንዲሰጥልን

ለምስክሩ አሳዩት ፊርማው የእሱ መሆኑን እስቲ ፊርማው ያንተ መሆኑን ታረጋግጣለህ ለፍ/ቤት ፈርመሀል እንዴ ያኔ በለው ፊርማው ያንተ ነው ወይ በለው ሌላ ነገር አይደለም ነው

ወይንስ አይደለም

እኔ ትምህርት የለኝም እንደዚህ መፈረምም አልችልም

ጥሩ ማሾ አደዊ ነህ አደም

አደም

አደም

ማህተም ስላለበት እረጋ ብለህ እይ በለው ምን አልክ እሺ ጥሩ መለየት አልቻልኩም ነው መልሱላቸው ለዐ/ሕግ

እኔ በዛን ጊዜ

እ

በእሷ ጉዳይ ምን ታውቃለህ

ጥሩ ጥሩ ጥሩ ቆይ ቆይ ቆይ ያኔ ግን ቃል ሰጥተሀል በለው

ይሄንን ቃሌን እንዴት እንደሰጠሁ ልነግርህ ፈለግሁ

ጥሩ ነው አይ እሱ አይደለም አሁን የተፈለገው ቆይ ቃል መስጠትህ ብቻ ነው ይበቃል በተነሳው የግራ ቀኞችሁ ክርክር ላይ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል በትላንቱ ውሎ ችሎትም በተመሳሳይ በፖሊስ የተሰጡ በፖሊስ መዛግብት የገቡ ቃሎች ምስክሮች አናውቅም የሚል ስላለ ወደ አስጠቂነት ወደ ሚለው ትርጉም በማያዝ በስጠቂ ምስክረ ደግሞ ትላንት በብይን ላይ እንደተባለው ህጉ ግልፅ ክልከላ አያደርግም በሌሎች የኢትዮጲያ ህጐችም ይህ አይነቱ ነገር ባለው የማስረጃ አደረጃጀት አይተፈቀደ ያለበት ሁኔታ አለ ከዚህ አንፃር በአስጠቂነት በይዘቱ

ፍ/ቤቱ ያመነባቸውን እየተፈቀደ በግራ ቀኙ ክርክር እንዲደረግባቸው ሊፈቀድ ይችላል በዚሁ ትላንትም የተሰራበት ስለሆነ ዛሬም በዚሁ አስጠቂ ምስክርነት ዐ/ሕግ እየመሩ ጥያቄ እንዲጠይቁ በማለት ብይን ሰጥቷል በዚሁ ይቀጥል ጥያቄው

እሺ ማሾ ስንት ቀን የምስክርነት ቃል ሰጠህ

አንዱ ነው የሰጠሁት

በማን ላይ በማን ላይ

በሻም እና እኔ የማውቀውን ነው የምናገረው

እኮ የምታውቀውን ንገረን ነው ያልኩህ

ስለ እሷ ጉዳይ ለእናንተ የምነግረው የተጠየኩት ቀጠራ አራት ውስጥ ነበረች ቀጠና አንድ ውስጥ እሷ ከተመለሰች በኋላ አጭር ጊዜ ነበረ እስከ አሁን የደረስኩበት ነገር የለም ለወደፊቱ ግን ከደረስኩበት ነው እንጂ

ቆይ አሁን አንድ ቀን ሰጥቻለሁ ብለሀል በማን ያኔ ምስክር የሰጠከው ቃል በማን ላይ ነው የመሰከርከው በእከሌ ላይ ብለህ ለይልን

ሻም ኢብራሂም ላይ ብቻ ነው

እሺ ጀና መሀመድ ላይ የምስክርነት ቃል አልሰጠክም ሰጥቻለሁ ወይም አልሰጠሁም በለን

አልሰጠሁም

የኦነግ ደጋፊ ሆና ሰዎችን ለመቀስቀስ የህገ መንገስቱ እንቅፋት መሆንዋን አውቃለሁኝ ብለህ ለፖሊስ ቃል አልሰጠክም ወይ ጀናን በተመለከተ

እኔ አልሰጠሁም

እሺ በአወዳይ ከተማ በዞን 1 ፍ/ቤት በዞን 2 ውስጥ የኦነግ ሴል ናት ብለህ

እኔ አላህ ያውቀኛል ምንም የማውቀው ነገር የለም

እናመሰግናለን ጨረሰናል

አበቃችሁ

አዎ

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥል ከተማከራችሁ

የተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

እርሶ ፖሊስ ጣቢያ ቃል ሰጥቻለሁ ብለዋል ፖሊስ ጣቢያ ቃል ሲሰጡ

አዎ

እዛ ግምገማው ጋር ማለት ነው ቃል ሲሰጡ ቃሉ የተፃፈው በላቲን ቋንቋ በኦሮምኛ ነው የተፃፈው ወይስ በአማርኛ ነው

እኔ ሁቱንም ስላልተማርኩ በምን እንደተፃፈ አላውቅም

የሚፈርሙትስ በምንድነው

እኔ ዝም በዬ እንደዚህ ይገፍ ነው እንደዚህ እንደዚህ የማደርገው

እንጂ

እኔ ለትምህርት ያህል የማውቀው በደርግ ጊዜ መሰረተ ትምህርት ትንሽ ነው የተማርኩት ምንም ትምህርት የለኝም

ይበቃናል

ይበቃቹሀል ድጋሜ ጥያቄ አለ ድጋሜ ጥያቄም የለም

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ሻም ላይ በተመለከተ ሻም አባዎ ወይንም አነግ ነው ብለህ ቃልህን ሰጥተካል እና እሱ አነግ ስለመሆኑ እንዴት ነው ያወቅከው

እኔ ያወኩት የቀበሌው አስተዳደር በመሆኔ እኔ እሱ ላይ አላየሁም ብዬ ለእሱ እራሱ ስከራከር ነበርኩ እኔ እሱ ላይ በኋላ ሻመን የቻልኩት ከፊጠሳስ ጋር ከተገናኘ በኋላ ነው

ፊጠባስ ምንድነው

ሰው ነው እዚህ እስክ እዚህ ድረስም ታስሮ ነበረ ፈንጂ ከአወዳይ የወጣ ጊዜ

አወዳይ ፈንጅ የወሰደ ሰው ነው እንደዛ ነው ወይ በለው ግልፅ አድርገው

አዎ

እሱ ማነው

ፊንጠባስ ነው

ታዲያ ሻሚስ ምንድነው የሚያደርገው

እሱ ጋር በመሆኑ እኔም አምኜ ከዚህ አንፃር ነው በዚህ ላረጋግጥ የቻልኩት

ከእሱ ጋር በመሆኑ ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው ከእሱ ጋር ስለሄደ ማለትህ ነው

ከእሱ ጋር ሆኖ ቅስቀሳ በማድረጉ

እሱ ማን ነበር ስሙ ያኛው

ፊንጠባስ

ከፊንጠባስ ጋር ሆኖ ሻሚ ቅስቀሳ ሲያደርግ አይተሃል ወይ

አዎ

ምን ብሎ ነበር የቀሰቀሰው

እናንተ ከነዚህ ሰዎች ጋር የምታደርጉት እኛ ሰዎች ትተከን ከጠላት ጋር ትንቀሳቀሳላችሁ

ይሄንን ማን ነው ያላችሁ

ሻም

ለማን ነው ያለው

እሱ ያላቸው ሰዎች ሰፈር አሉ

የኦሮሚያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምዕራብ ሸዋ ዞን ጨሆ ክፍተኛው ፍ/ቤት

550

እስኪ ምንድን ነው ያላቸው ድገምልን

የእኛን ሰው ትታችሁ ከጠላት ጋር እንዴት ትሄዳላችሁ

ማን ነው የእነሱ ሰው ማን ነው ጠላቱስ

አባዎ

አሁን እነሱ ቀስቀሰዋቸዋል የተባሉት ሰዎች ምን የሚሰሩ ሰዎች ናቸው ስራቸው ምንድን ነው

ያው ነዋሪው ህዝብ ነው

አንተ ነበርክ ወይ እሱ እንደዛ ብሎ ሲቀሰቅስ አንተ ከተቀስቃሾቹ ውስጥ ነበርክ ወይ

እኔም ራሴ ስላለኝ ነው እራሴን ስላለኝ ነው

እነዛ ሰዎች ውስጥ ነበርክ ወይ ሲቀሰቀሱ የነበሩት ውስጥ

እኔ ከእነሱ ጋር አልነበርኩም

በግልስ እንደዛ ብሎ ቀስቅሶሃል ወይ

አዎ እኔን ብሎኛል ከዛ ተነስቼ ነው እኔ ለራሴም

እስኪ ድገመው ጥያቄውን እና

ከብት የማይሰማው ቦታ ይተኛል እኔማ ያልሆነ ነገር እንዴት እቀበላለሁ

እሱ እንዳለ ሆኖ ለጥያቄ ብቻ መልስ ስጥ አንተን ቀስቅሶሃል ወይ አንተን እንደዛ ብሎ ቀስቅሶሃል ወይ

ስላለኝ ነው ቁራኑን ጨብጬ ልል የቻልኩት

ምንድን ነው ያለህ

በዝናብና በጨለማ ከነዚህ ሰዎች ጋር መሮጥ ምንድን ነው አለኝ

ብሎሃል ከነማን ጋር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጋምቤላ ክልል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

ለምን ከመንግስት ጋር እንደዚህ ትሮጣላችሁ ለምን ከእኛ ጋር አትሆኑም

እሺ እንደዛ ብሎ ከመቀስቀስ ውጭ ሌላ ያደረገው ነገር አለ

የለም

ምንም አላደረገም

እኛ ፀጥታ ዘርፎች ባለንበት ሰዓትም እነሱ ሰውን በጉልበት ለመዝረፍ ሮጠው ሄደው ይዜም ፖሊስም ደርሶ እስከ እዛ ደረጃ የሚሄድበት ነገር ነበር

ሻሚ ቀስቅሷል ከመንግስት ጋር ለሊትም ቀንም አትሩጡ ብሎናል እና የተለያዩ ቃላቶች ተናግሯል ብለህ ተናግረሃል ከዚህ ውጭ ያደረገው ነገር አለ ወይ እሱን በግልፅ አስቀምጥልን በአጭሩ

እኔ ከዚህ ውጭ የማውቀው ነገር የለም

ምንድን ነው ታዲያ አሁን ደርሰንበት ነበር ያልከው ከፖሊስ ጋር ሆነን

ፊንጠባስና ቦና ከተባለው ጋር የነዚህ ሃባዎ ሰዎች እኛ የሰፈሩን ሰው በመበጥበጥ ከፖሊስ ጋ ሆነን ይዜንን ነገር ደረስንበት ትዕዛዝ ወጥቶ በእንደዚህ ምክንያት በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ቻሉ

አሁን በጠቀስካቸው ፊንጠባስና ቦና ጋር ሻሚ ሄዶ ይበጠብጥ ነበር ወይ

ስለበጠበጠ ነው እሱ ላይ ልመሰክርም የቻልኩት

እንዴት አድርጎ ነው የበጠበጠው

ጀማል አብዱልቃድር የተባለው የዛ የፀጥታ ዘርፍ ከእኛ ጋር ነበር ብቻውን ሰርቶ ሲሄድ ከዛ በሩጫ ለህይወቱ ራሱ ለትንሽ ነው የተረፈው

ምን

በቢላዋ ሊገድሉት ሮጦ በሩጫ አመለጠ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ ፣ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፣

552

ለምንድን ነው ሊገድሉት የነበረው የግል ጥላቻ ነው ፖሊስ ከህግ ጉዳይ ጋ በተያያዘ መልኩ ነው

ከእኛ ጋ ስለሚሰራ እሱ ከእኛ ፀጥታ ጋር እንዲሰራ ስለማይፈልጉ ለዛ ነው ሊገድሉት የሄዱት

እሱ ነበረበት ወይ የዛን ቀን ሻሚ

ከእሱ ጋር የሚቅሙ ሰዎችን ነው አብሮ የዛን ቀን

እሱ ነበር ወይ

የዛን ቀን እሱ የለም

ያን ቀን ካልነበረ ታዲያ የት ነው የበጠበጠው

ልል የቻልኩበት እነዚህ አካባቢን የሚበጠብጥ ሰዎች ማራቅ ነው እንጂ ያለበት እንዴት ሊያስጠጋ ቻለ እንዴት አብሮ ሊሄድ ቻለ

ስላስጠጋቸው ብቻ ነው ወይስ የበጠበጠው በተሰየ የበጠበጠው ነገር አለ ወይ በለው እስቲ ግልጽ አድርገው

እኔ እንደግሉ ይሄንን አደረገ ብዬ አሁን የምናገረው ነገር የለኝም

በጥብቂል ወይስ አልበጠበጠም

ከዚህ በላይ ረብሻ የለም

በጥብቂል ወይስ አልበጠበጠም እሱ ከእነሱ ጋር በመሆን አብሮ

በጥብቂል

እንዴት አድርጎ ነው የበጠበጠው እሱን ነው የፈለግነው ግልጽ አድርገው ወይ ግልጽ እንዲሆንልህ ይሄውልህ እነ ፊና እነ ቦና የሚባሉ ሰዎች ይበጠብጡ ነበር በስምም አንድ ሰው ጠርተህ እሱ ከእኛ ጋር እንደሚሰራ ሊመቱት ፈልገው ነበር ያልከው ሁኔታ አለ በአንድ በኩል ደግሞ ያን ጊዜ እሱ ከእነሱ ጋር አልነበረም እንዲህ ልል የቻልኩት እነሱን ስለሚያስጠጋቸው ነው ብለህ ለማብራራት የሞከርከው ነገር አለ እና እሱ በግሉ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ሆኖ የበጠበጠበት ሁኔታ አለ ወይ ከበጠበጠ የት አካባቢ ነው የበጠበጠው እሱን ንገረን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

553

እኔ በግልም ላሳምን ብዬ እሱ ጋ ሄድኩት

ወደዛ አትግባ

አላምን በማለቱ ከዚህ አንዣር ነው ልል የቻልኩት

እንጂ እሱ አልበጠበጠም ማለት ነው ከእነሱ ጋር ሆኖ ግልጽ አድርገው እስቲ

በጥብጧል

እንዴት አድርጎ ነው የበጠበጠው እሱን ንገረን

እኔ የቀበሌ አስተዳደር እንደመሆኔ የፀጥታ ዘርፍ በመሆኔ መጠን ይሄ ሰውዬ ከዚህ ሰውዬ ጋር መንቀሳቀስም የለብህም ሰፈር እየበጠበጠ ነው አቁም ብዬው ማቆም የለብኝም ብሎ በአቋሙ በመሄዱ ከዚህ አንዣር ይሄ ሰውዬ እኔ እንደራሴ እንደበጠበጠ አድርጌ ነው የምወስደው

አቋሙ እንዳለ ሆኖ ከነዚህ ሰዎች ጋር ሆኖ ሰፈሩ ወይ አገሩን የበጠበጠበት ሁኔታ ነበር ወይ እነዛ ሲበጠብጡ ሰው ሲመቱ ሲዘርፉ የተለያየ ነገር ሲያደርጉ

ይሄንን በአይኔ ያየሁት ነገር የለም

የለም

ከስንት እስከ ስንት በአካባቢው የፀጥታ ዘርፍ ሃላፊነት ሰርተሃል ስንት አመት ሰርተሃል በፀጥታ ዘርፍ

ወደ 11 አመት ይሆነኛል የሰራሁት

ሻሚ በስንት አመት ውስጥ ነው በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ አንተ በምትረዳው መልክ በጠበጠ እያልክ የምትናገረው

ያው ፅፌ ስላልያዝኩት በዚህን ቀን ነው በዚህ ነው ብዬ አሁን ልናገር ፅፌ ስላልያዝኩት አልችልም

አመቱን በግምት ለአንድ አመት ለሁለት አመት ለአንድ ወር

554

እኔ እንደዚህ ሳስበው ቢያንስ ከአሁን እንደዚህ ሶስት አመት አራት አመት እንደዚህ ይሆነኛል ብዬ እገምታለሁ

ይሄ በግምት ነው

አዎ

እናመሰግናለን ጨርሰሃል መሄድ ትችላለህ። ማን ይጠራላችሁ ዐ/ህግ ቆይ ምንድን ነው እጅ እዛ ጋ የቋንቋ ተነሳ እስቲ መሀላ ፈጸሙ

የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አደም ዩሱፍ ኢብራሂም

ሥራ - ቀን ሰራተኛ

አድራሻ- አወዳይ

ዛሬ ለምስክርነት ነው ወይ የመጡት

አዎ

በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት

ጃፈር ማመድ ፋ የሚባል

በእሱ ላይ ነው

አዎ

በነማን ላይ ነው

ጃፈር መሀመድ እና ጀማል ጠቃ

ጥሩ ሌላ አለ

ጀማል ከድር የሚባለው

ጥሩ ታውቃቸዋለህ በአይን

555

አዎ አውቀዋለሁ

ለያቸው ተነስና ተነሳና አሳየን

ጃፈር መሀመድ የለም

ረጋ ብለው እዚህ ውስጥ ያሉት በሁለት በኩል ነው ሰዎቹ ያሉት ተከሳሾች እያንዳንዱን ጊዜ ወስደህ ማየት ትችላለህ

ጀማል ጢቃ የሚባል ከፖሊስ ጋር የእሱ ቤት ሄድኩ ግን በደንብ በአይን

አሁን የተነሳው ማን ነው ስሙ

ጀማል ከድር ነው

እሺ ሌላ ማን ነው ያልከው ሌላ

ጃፈር መሀመድም የሚባለው የለም

ሌላ ሶስቱን ነው ጀማል ጢቃ ጀማል ከድርና ጃፈር መሀመድ እነሱን ነው የምታውቀው እሺ ቁጭ በል

አዎ

ጥያቄ አለ

ጥሩ አሁን ከዚህ ካሳየከው ጋር ፀብ ዝምድና አለህ ወይ ከጀማል ከድር ጋር

ምንም የለኝም

ጥሩ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

ጥያቄአችን ሶስት ተከሳሾችን ጠቅሶ አንደኛውን በአካል አመላክቷል አንደኛው የለም እዚህ ብሏል አንደኛው አለ ያየሁት ለአንድ ቀን ስለሆነ ግን አሁን መለየት አልቻልኩም እያለ ነው ስለዚህ ተከሳሹ እዚህ ካለ በፍ/ቤት ቢጠራልን

556

ጀማል ጢቃ ማን ነው በሉት

ጀማል ጢቃ የሚባለው በአይን ባየው አላውቀውም

እሺ ጃፈር መሀመድንስ በአይን ብታየው ታውቀዋለህ ወይ

ጃፈር መሀመድ በደንብ አውቃለሁ ሰፈሬ ነው እዚህም መንግስት እጅም አልገባም እሱን በደንብ አውቀዋለሁ የለም

ጥሩ ጃፈር መሀመድ አለ እዚህ ውስጥ ጀማል ጢቃ አለ እዚህ ውስጥ ጃፈር መሀመድ ጃፈር መሀመድም ጀማል ጢቃም እዚህ ውስጥ የሉም ማን ነው ስምህ ጀማል ሀምዛ ስንተኛ ተራ ላይ ነው ያለከው 9ኛ ጀማል ሀምዛ ቂልቤ ጀማል ጢቃ አንተ ነህ አደለህም ጥሩ ታውቀዋለህ ወይ ይሄንን ሰውዬ

አዎ አውቀዋለሁ

ማን ነው ስሙ በማን ስም ነው የምታውቀው

እኛ በጀማል ጢቃ ነው የምናውቀው

ታውቀዋለህ እሱን እሺ ጃፈር መሀመድ የለም ጥሩ ጀማል ጢቃ በሚል 9ኛ ተከሳሽን በችሎት አውቀዋለሁ ብሎ በችሎት ለይቶ አረጋግጧል በሌላ በኩል ጀማል ከድርን ለይቷል ጃፈር መሀመድ ግን እዚህ መሀል የለም ተብሏል ጥሩ ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ

እሺ ይሄ ጀማል ጢቃ የሚባለው ምንድን ነው ያደረገው ወይም ጀማል ሀምዛ ምንድን ነው ያደረገው

ተቃውሞ አለን

ስርዓት አድርግ ባክህ አንተ ስነ-ስርዓት አድርግ በደንብ እየው ሂድና በለው ቀረብ በልና እየው አንተም ወጣ በል ቆይ ቆይ አንተ ለምን አታስተረጉምም ንገራቸው እሱ ነው ወይ ጀማል ጢቃ

ጀማል ጢቃ በአይኔ አላየሁም የእሱ ቤት ግን ሄጃለሁ

ጥሩ ይሄንን በማን ስም ነው የምታውቀው

በጀማል ነው የማውቀው

557

ጀማል ማን

የማን እንደሆነ አላውቅም

ግን ታውቀዋለህ

የሰፈር ሰው ነው አውቀዋለሁ

ልትመሰክርም መጥተሃል በእሱ ላይ

አልመጣሁም

ተመለስ ወደኋላ ቁም እዛው ቆይ ጀማል ጢቃ ነው ብለሃል ቅድም ለፍ/ቤቱ

ጀማል ጢቃ ነው አላልኩም ጀማል ነው አልኩት

ጥሩ በጀማልነቱ ታውቀዋለህ የአባቱን ስም አታውቀውም

አላውቀውም

ጥሩ በእሱ ላይ ትመሰክራለህ

አይ ምንም የማውቀው ነገር የለም እሱ ላይ

ጥሩ በ9ኛ ተከሳሽ ጀማል ጢቃ ሳይሆን ጀማል በሚል ስም ነው የማውቀው ብሏል አውቀዋለሁ ግን በእሱ ላይ ልመሰክር አልመጣሁም ብሏል እሺ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ ዐ/ህግ

እሺ ጀማል ከድርን በተመለከተ ምንድን ነው የምታውቀው

ቆይ እስቲ ዐ/ህግ አንዴ ጀማል ጢቃ የሚባል አለ እንዴ ሌላ አቁም ባክህ አንተ አስተርጉም ንገረው ና ወደዚህ ለምንድን ነው ፍ/ቤቱ አቁም ሲልህ የማታቆመው ለምን ትረብሻለህ

የእኔ ስላልሆነ ግራ ተጋብቼ ነው በህይወቴ ላይ እየተፈረደ ስለሆነ ነው

እየረበሸክ ነው ያለከው እሱ አይደለም

ደንግጬ ነው እና ይቅርታ አድርጉልኝ

አውቀህ ነው የምትረብሸው በለው ፍ/ቤት ደግሞ ይቀጣሃል

554

ይቅርታ አድርጉልኝ

እሺ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ

ክቡር ፍ/ቤቱ የጀመረውን ጥያቄ ቢጨርስልን ነው ማለት ጀማል ጢቃ እዚህ ውስጥ ካለ ራሱን

የለም ጀማል ጢቃ

ኦሮሞኛ ይነገር ተብሎ ነው

በኦሮምኛ ጀማል ጢቃ የሚባል አለ እዚህ ውስጥ

ጀማል ከድር የሚባል አለ

ሌላ ጀማል ሌላ እሺ አንተ ቁጭ በል ሌላ ጀማል እሺ አንተ ማን ነው ጀማል ተነሳ ጀማል ነው አደለ ታዲያ ለምን ዝም አልክ እናስታውሳለን እኮ እኛ እሺ ቁጭ በል ያኛው ከኋላ ጀማል ከድር እሺ ሌላ ጀማል ነበር አደለ ጀማል የለም እዚህ ውስጥ አለ አንድ ጀማል አሞ አንተ ጀማል ነህ ቁጭ በል አንተ ጥሩ ቀጥሉ ዐ/ህግ

ጀማል ከድር ምንድን ነው ያደረገው እስቲ ንገረን

ይሄ ጀማል ከድር እኔ የማውቀው ቀን ሰፈር ውስጥ አይታይም ሽርጡን ተሸፋፍኖ ተጠርጣሪ መሆኑን ነው የማውቀው

የምን ተጠርጣሪ

የኦነግ ተጠርጣሪ መሆኑን ነው የማውቀው

ቀን ሰፈር ውስጥ የማይታየው ለሊት ሽርጥ የሚከናነበው ለምንድን ነው

ቀንና ለሊት መንግስት እሱን እንደሚፈልግ ነው የማውቀው

ለምንድን ነው የሚፈልገው

ተጠርጣሪ ነው

የኦነግ

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቁጥር 4

359

አም

ታዲያ ይህንን ሊጠረጠርና ሊፈለግበት የቻለበት ምክንያት ምን ስላደረገ ነው

ሰውን ሰብስቦ ያነጋግራቸዋል በማለት ተጠርጥሮ ነው ይሄንን ነው የማውቀው

ምንድን ነው የሚያነጋግራቸው

ሰውን የመቀየር ሁኔታ ነው

ወደምንድን ነው የሚቀይራቸው

ወደ ኦነግ እንዲቀየር

አንተ ይህንን ስለማድረጉ የምታውቀውን ንገረኝ እስቲ ታውቃለህ ወይ በግልጽ

እኔ የዛን ሰፈር አጠቃላይ ነኝ እና ከዚህ ውጭ የማውቀው ነገር የለም

ይህንን ማድረጉን ግን ታውቃለህ ወይ

ይሄ ግልጽና ግልጽ ነው በደንብ አውቀዋለሁ

መቼ ነው

ቢያንስ አመት ይሆናል

አመት ይሆነዋል

ከዛ በፊት

ከአመት በፊት እሺ የት ቦታ ነው

አንደኛ ዞን

አንደኛ ዞን የት ነው አባቲ ስሙ ማን ይባላል

አወዳይ አንደኛ ዞን

አበቃችሁ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፖሊስ ኮሚሽን የምርመራ ቡድን

560

ጨርሰናል አም

መስቀለኛ ጥያቄ አለ ጠይቁ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

አቶ አደም ግልጽ ነው የሚሉት ከምን ተነስተው ነው ምን አዩ ተጠርጣሪ ነው የሚሉት ከምን የተነሳ ነው የጠረጠሩት

ከአንዱም ሁለት በላይ ከፖሊስ ጋር ሆነው እሱ በመፈለጉ በመጥፋቱ ነው

በመፈለጉ በመጥፋቱ ነው እንጂ ምንም ሲያደርግ አላየህማ

የሰራውን ነገር ያየሁት ነገር የለም

የሰሙት ነገር የለም

ሰውን እንደሚቀሰቅስ እሰማለሁ

ማን ነገሮት

እኔ የቀበሌው አስተዳደር ስለሆንኩ በተለያየ መንገድ ኢንፎርሜሽን ይደርሰኛል

እንጂ እርሶ በተጨባጭ የሚያውቁት ነገር የለም

በተጨባጭ ይሄ ይሄ ሰርቷል ብዬ አሁን የምናገረው ነገር የለኝም

ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ለዐ/ህግ ድጋሚ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ድጋሚ የለንም

የላችሁም

አም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ምንድን ነው የስራ ድርሻዎት

361

ከዛን ጀምሮ እስከ አሁን እዚህ ድረስ የዞን ሃላፊ ነኝ

በዚህ በዞን ሃላፊነቶ ምንድን ነው አንድ የስራ ሃላፊነቶ ምንድን ነው ፀጥታ የስራ ሃላፊነቶት ነው ለምሳሌ በላቸው

የህግ ኮሚቴ ውስጥም አባል ነኝ

የምን ኮሚቴ

የህግ ኮሚቴ

የህግ ኮሚቴ በዚህ ጊዜ አሁን እርሶ አሁን በሃላፊነት እስከ አሁን አለሁ ብለዋል ጀማልን ምንድን ነው እርሶ በሃላፊነት ደረሰኝ ያሉት ኢንፎርሜሽን ያሉት ነገር ምንድን ነው ይሄ ኢንፎርሜሽን እንደ ሃላፊነቶ የተቀበሉት ያመኑበት መረጃ ምንድን ነው እና በአካባቢውስ የደረሰ ችግር ምንድን ነው

ይሄ ሰውዬ አነግ ነው የአነግ ደጋፊ ነው ተጠንቀቁ ራሳችሁን ጠብቁ የሚል በተለያየ ጊዜ ኢንፎርሜሽን ይደርሰናል

ማን ነው ስሙ ያሉት

ጀማል ከድር

ይሄ ነው መረጃ ያሉት

አዎ ይሄ ነው

ምን እርምጃ ወሰዱ እርሶ ትልቅ ሃላፊነት ነው ምን እርምጃ ወሰዱ

ብዙ እርምጃ የወሰድኩት ነገር አለ ይሄ እሱ ግን ፊልገን አጣን እኛ ውጪ ሆነን እሱ ላይ የወሰድኩት ነገር የለም ስላጣን ነው እና የወሰድኩት እርምጃዎች የለም ይሄንን ነው የማውቀው

የደረሰ ችግርስ አለ አካባቢያችሁ ላይ በጀማል

የለም

562

እሺ ይሄንን ጀማል ጢቃን ግን አላወቁትም ጀማል ጢቃ ብለው እሱ አይደለም ያሉት ጀማል ብቻ መሆኑን ነው የሚያውቁት

ይሄ ጀማል ጢቃ የሚባል ዞን አራት ውስጥ የሚኖር ነው ሄደን ልንይዝ ሄደን ከቤት አጣን ቤቱን ሄድኩት እንጂ አላገኘሁትም በአይን አላየሁም ከፍ/ቤቱ ትእዛዝ ወጥቶ ከዛ በኋላ በፍለጋም በምንሄድበት ሰዓት አጣን እና በአይን አላየሁትም

እሺ እናመሰግኖታለን እሺ በዚሁ ሰዓት ስለደረሰ ዐ/ህግ ምስክርነት መስማቱን በዚሁ እናቆማለን የምስክርነት መስማት ሂደቱ ከቀትር በኋላ ጀማል ተቀመጥ ከቀትር በኋላ ይቀጥላል ዐ/ህግ ቀሪ ምስክሮቹን ከቀትር በኋላ እንሰማለን ዐቃቤ ህጉና የሰሙ ላይ የተነሳ አንድ ክርክር አለ እሱንም ዛሬ ከሰዓት ከደረሰ ይሆናል ካልሆነም ምስክርነቱ ካላለቀ ደሚቀጥል ከሆነ ከምስክርነቱ በኋላ የምናየው ይሆናል ከቀትር በኋላ እንገናኛለን።

563

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 20/5/2002

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ ከቀትር በኋላ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ አረጋይ እንደሻውና እያሱ መኮንን ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ በአካል የሚቀርቡት ተከሳሾች በሙሉ ከማረሚያ ቤት 69ም ቀርበዋል ማረሚያ ቤት አረጋግጧል።

ከቀትር በፊት የተጀመረውን ምስክርነት መስማት ሂደት በዚሁ ይቀጥላል አስተርጓሚውም አለ ማን ይጠራላችሁ ዐ/ህግ

75ኛ የዐ/ህግ ምስክር ኡስማን አደም

ኡስማን አደምን ጥሩ

75ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ኡስማን አደም በሎ

ሥራ - አርሶ አደር

አድራሻ- አወዳይ

ለምንድን ነው የመጡት ለምስክርነት ነው

አም

በማን ላይ

ጀማል ጢቃ ቤት

ሌላ

ይሄንን ነው የማውቀው

በጀማል ጢቃ ላይ ብቻ ነው ለመመስከር የመጡት

አዎ

ጥሩ ያውቁታል ጀማል ጢቃን

አዎ አውቀዋለሁ

እዚህ አለ ዛሬ እስቲ አሳዩን ካለ ተዋቸው እንደተመቻቸው እዚህም ከሆኑ ቆመው ማየትም ይችላሉ በላቸው ቀና ቀና በሉላቸው እየዞሩ እዩ በላቸው አሁን የለዩት ማን ነው በላቸው

ጀማል ጢቃ ነው

በዚህ ስም ነው የሚያውቁት

አዎ

እርግጠኛ ኖት

በትክክል አውቀዋለሁ የእሱ ቤት ሄደን ነው ያየሁት አውቀዋለሁ

እርግጠኛ ኖት ወይ

አንድ ሰፈር ነን አውቀዋለሁ

ጀማል ጢቃ ነው የሚባለው

ጀማል ጢቃ ነው የሚባለው ወንድሙ ደግሞ ሁሴን ከድር ይባላል

ፀብ ዝምድና አሎት ወይ ከእሱ ጋር

ምንም ነገር የለንም

እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

565

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

ክቡር ፍ/ቤት የምናሳስበው ነገር አለ ጠዋት ምስክርነት ቃል ሲሰጥ ጀማል ጢቃ የሚባል አለ የለም እየተባለ ሲጠየቅ ማንም

እሺ ፍ/ቤቱ ግንዛቤ እንዲይዝ ነው እናመሰግናለን

እሺ ዛሬ ምንድን ነው የሚያስረዱት እሱ ላይ ምንድን ነው የሚያውቁት

አባዎ ነው ኑና ታዘቡ ተብለን ተጠርተን የእሱ ቤት ተቀመጥን

እሺ ከዛስ

ከዛ በኋላ አላውቀውም

በአባዎ ነው ተብሎ ቤቱ ምንድን ነው ያደረጋችሁት

ተፈተሸ

ታዲያ ምን አገኛችሁ ስትፈትሹ

ሁለት ካርቶን ኪኒኖች ተገኘ

ምን የሚሆን ኪኒን ነው

እሽግ ነው አልተከፈተም

እኮ ለምን አላማ የተቀመጠ መድሃኒት ነው

ያው ኪኒን ነው ተብሎ ማንሳቱ ነው እንጂ ለምን እንደሆነ እኔ አላወኩም

ምን ሊደረግ ነው ሲባል ሰሙ

እናንተ ታዘቡ ተብለን እኛ እዛ ቁጭ ብለን ከማየት ውጭ ይሄ ኪኒን ነው ተብሎ እሽግ ካርቶኖች ሲያወጡ ነው እኛ ያየነው

እሺ ሌላስ ምን አገኛችሁ

566

ሌላ አላየንም

አባዎ ነው ተብሎ እንደተፈተሸ ነግረውናል ምን ጥርጣሬ ስለነበር ነበር የፈተሻችሁት ምን ፍለጋ ነበር የተፈተሸው

ኢንፎርሜሽን ደረሰን ከአባዎ ጋር ግንኙነት እንዳለ ከዛ ውስጥ ወረቀቶችና መርፌዎች እንደነበረ ተነገረን ከዛ ተነስቶ ነው

የማን መርፌና ወረቀቶች መኖሩ ተነግሯችሁ የሄዳችሁት

የምን እንደሆነ አላወኩም

የማን ተብሎ ነው የተነገራችሁ መረጃ ተነገረን ያልከውን ኢንፎርሜሽን ደረሰን ያልከውን

ከፍ/ቤት ትዕዛዝ ወረቀት አውጥተው መጡ እናንተ ሽማግሌዎች ኑና ታዘቡ ቤቱ ሲፈተሽ ተብለን እኛ እዛ ስናይ ነው ይሄ ሲወጣ ያየነው

ወረቀቱ የምን ወረቀት ነበር ተገኘ የተባለው

ወረቀቱን ከማየት ውጭ አላነበብኩትም እና አላየሁም

ወረቀቱን ያዩት ሰዎች ምንድን ነው ብለው ነገሮት ወይም የሚያነቡት ሰዎች

አባዎ ከማለት ውጭ የሰማሁት ሌላ ነገር የለም

መድሃኒቱ ወዴት የሚላክ ነበር ተባለ

አላወኩም

መቼ ነው

አሁን ቆይተናል ጊዜውን በደንብ አላውቀውም

ገምተው ይንገሩን ምን ያህል ጊዜ ይሆናል ስንት አመት ይሆነዋል

እኔ አሁን በውሸት ካልተናገርኩ በስተቀር ይሄንን ያህል ነው ብዬ መናገር አልችልም

የት ቦታ ነው

567

አወዳይ

ሌላስ ተከሳሹ ያደረገው ነገር ከዛ ይሄ ከመፈተሹ በፊት እዛ አካባቢ ላይ ሲያደርግ የነበረውን ነገር የሰሙት ነገር ካለ ፍተሻ ከመያዙ በፊት

እኔ ምንም አላውቅም

ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ቃል ሰጥተው ነበር ወይ

አሁን የተናገርኩትን ነው የሰጠሁት የዛን ጊዜም እዛ እኔ አባዎ ነው የሚል ነው እዛም ቃል የሰጠሁት

ያ አባዎ ነው የሚል ነው

እነሱ ይሄ አባዎ ነው ኑና እዩ ስላሉን እዛ ቁጭ ብለን ስናይ ነበር ይሄንን ቃል ነው እዛም ሄጀ የተናገርኩት

አይ ከዚህ ውጭ ሌላ የሰጡት ቃል የለም ወይ

እኔ ይሄንን ያህል ነው የሰጠሁት

ተከሳሹ የህክምና ባለሞያ ነው እንዴ

የለውም

ምንድን ነው ታዲያ የሚሸጠው ስራው ምንድን ነው

ይነግዳል

ምን

ልብስ ይነግዳል

ታዲያ ልብስ የሚነግድ ከሆነ መድሃኒት ምን ሊያደርግለት አስቀመጠ በእሽግ የታሸገ ትልቅ መድሃኒት

ተቃውሞ አላችሁ እሺ መቃወሚያ

569

ይሄ ከእሱ እውቅና ውጪ ነው እንዴት አስቀመጠ የሚል ጥያቄ ሊጠየቁ አይገባም ሰውየው ስለሚያውቁት ነው ሊመሰክሩ የመጡት የልብስ ነጋዴ ስለነበረ እንዴት መድሃኒት አስቀመጠ እንዲህ አይነት ጥያቄ ሊነሳ አይገባም ይሄ የሞያ ጥያቄ ነው

እሺ በእናንተ በኩል

እኔ ምስክሩ የእኛ ምስክር ነው እንጂ የመከላከያ ምስክር አይደለም የእኛን ምስክር ደግሞ መሪ ባልሆነ መልኩ እና ምስክሩን በማይጎዳ መልኩ ምስክሩ የሚያውቀውን ነገር ማን መቼ የት እንዴት የሚሉትን ነገሮች የመጠየቅ ህጋዊ መብት አለን ስለዚህ ያቀረቡት ተቃውሞ ውድቅ ተደርጎ ጥያቄአችንን ልንቀጥል እንዲፈቀድልን ነው።

ጥያቄው የተያያዘ ስለሆነም መከልከልም የሌለበት ነው ይቀጥል ጥያቄው

አመሰግናለሁ እርሶ

ድገሙላቸው ጥያቀውን ድገምላቸው

እሱ ልብስ ነጋዴ ነው ብለውኛል ከዛም የሚሰራው ይሄንን ነው አሁን እዛ ደግሞ የታሸገ መድሃኒት ተገኘ እያሉ ነው መድሃኒቱን ለምን አስቀምጦት ነው ተባለ

አላወኩም

የደረሳችሁ ጥርጣሬ ማለት ነው መረጃ ደርሷችሁ ሄዳችሁ ምን ተብላችሁ ነው ጥርጣሬው የደረሳችሁ

ትቃወማላችሁ እሺ

እኚህ ሰውዬ የፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ወጥቶ ና ታዘብ ተብለው ነው እንጂ ጥርጣሬ ጥቆማ ደርሶኝ ሄጃለሁ ብለው አልመሰከሩም

እሺ በእናንተ በኩል

በእኛ በኩል ደግሞ ቅድም ምስክሩ መረጃ ደርሶን እኛሉ ነበር መረጃ ደርሶን እንደዚህ አይነት ጥርጣሬ መረጃ ደርሶን ነው ወደዛ ቦታ ታዘቡ ያተባልነው እያሉ ነበር ይሄንን እሳቸው ምስክሩ ሲሉ ስለሰማሁ ነው

564

እስቲ ሌላ ሌላ ጥያቄ

እሺ መድሃኒት ተገኝቷል ብለዋል የማን ነው መድሃኒቱ

ከእሱ ቤት ውስጥ መገኘቱን ነው እንጂ የማን እንደሆነ እኔ ከእሱ ቤት ውስጥ መገኘቱን በአይኔ አይቻለሁ

እሺ በአይኖት አይተዋል የማን ነው ሲባልስ ሰሙ

የጆማል ጢቃ ነው ቤቱም የሱ ነው ሲባል ነው የሰማሁት

እሺ መድሃኒቱን ምን የሚያደርጉበት ነው ሲባል ሰሙ እሺ

አላወኩም

ይሄንን በሚመለከት ለፖሊስ ጣቢያ ቀርበው የሰጡት ቃል የለም ይሄ መድሃኒቱን በሚመለከት ለዚህ እንደዚህ ነው ብለው የሰጡት ቃል እርሶ የሚያውቁትን

እነሱ ለአባዎች ያደርሳል ሲሉ ሰማሁ ይሄንን ነው የተናገርኩት

እሺ ጨርሻለሁ

አበቃችሁ መስቀለኛ ጥያቄ አለ አማክሩትና የሚጠቅም ነገር ካለ ጠይቁለት ካልሆነም

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

አቶ ኡስማን እሱ ቤት ተገኘ ያሉት ስንት ክፍል ነው ቤቱ

ሁለት ክፍል ነው

ከየትኛው ክፍል ተገኘ

ከአንዷ ክላስ ነው የተገኘው

እነማን ናና ታዘብ አሎትና ነው እዛ የተገኙት እነማን ናቸው ታዘብ ያሉህ

ሻምበል ናስር የሚባሉ ናቸው

ተከሳሽም ነበር እንዴ ሲፈተሽ ቤቱ

የፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ኢ ጋ ... ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ...

5/10

የለም

እሱ በሌለበት ነው

ሚስቱ ነው ያለችው

እንጂ እሱ ቤት ውስጥ የለም

እሱ የለም

ይበቃናል

ይበቃችኋል ድጋሚ ጥያቄ አለ ዐ/ህግ

የለንም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ እሺ እናመሰግናታለን መሄድ ይችላሉ

66ኛው ምስክር አህመድ ሀሩን

አህመድ ሀሩን እሺ ቀጣይ የዐ/ህግ ምስክር ቀርቧል መሀላ ፈጽመዋል

66ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - አህመድ ሀሩን ከሊፍ

ሥራ - አስተዳደርና ፀጥታ የአወዳይ ከተማ ውስጥ

አድራሻ- አወዳይ

ለምስክርነት ነው የመጡት

አዎ

በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ቆይ እስቲ ስመሰማቱ በፊት ነው

አዎ

571

እሺ ምንድን ነው ቆይ ምስክሩ እዚህ መኖር አለበት የለበትም ከመጠራታቸው በፊት ታዲያ አትጠይቁም ነበር

ያው ቃለ መሀላ እንደፈጸሙ ----------

አንዴ ምስክሩ ውጭ ሁኑ እሺ ቀጥሉ ምንድን ነው

ይህ ምስክር 66ኛው ምስክር ይመሰክራል ብለን በክስ ቻርጃችን ላይ ያቀረብነው ማስረጃ ዝርዝር ላይ በ14ኛ ተከሳሽ ላይ ነው

14ኛ

አዎ በ14ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ ነው የሚለው ግን ምስክሩ 14ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ ሳይሆን ከጀማል ከድር ወይም ደግሞ ጀማል ጢቃ ከሚባለውም ላይ ይመሰክራል ስለዚህ እንደጭብጥ ለማስያዝ ነው አሁን እዚህ ያለነው እና እሱን በተመለከተ እንደጭብጥ እንድናስይዝ ከመመስከሩ በፊት እንዲፈቀድልን

እሺ ጥሩ ምስክሩን ጥሩት በማን ላይ ልትመሰክር ነው የመጣከው

ጀማል ከድርና ጀማል ጢቃ

ሌላ

እነዚህ ሁለቱ ናቸው

ሁለቱን ታውቃቸዋለህ

ጀማል ከድርን አውቀዋለሁ አሁንም ባየው አውቀዋለሁ

ጀማል ጢቃስ

በታዛቢነት ቤቱ በሄድኩበትም እሱ ቤት

ማን ቤት ነው የሄዳችሁት

የጀማል ጢቃ ቤት

እሺ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቃጭ

572

በታዛቢነት በሄድኩት ሰዓትም እሱ ቤት አልነበረም እና ባየውም ይቸግረኛል

ጥሩ ጀማል ከድርን ግን ቢያዩት ያውቁታል

አሁንም ባየው አወጣዋለሁ

እስቲ ካለ ይለዩልን ይነሱና ጥሩ ጀማል ጢቃን ግን ስላላዩት አያውቁትም እዚህ ቢኖርም አይለዩትም

ከመስማት ያለፈ በአይን ስላላየሁት አላውቀውም

ጥሩ ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

ጀማል ከድር ምንድን ነው ያደረገው በእሱ ላይ ልትመሰክር የመጣከው ነገር ምንድን ነው

ጀማል ከድር በ11:00 ሰኣት ላይ ተጠርቼ በፍ/ቤቱ ትእዛዝ በታዛቢነት ሄጀ የእሱን ቤት ፈትሸን እሱ በዛን ወቅት ተይዞ ከዛ በፊትም እሱ ህዝብ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ህዝቡን የሚያደራጅ ነበር ከዛ በፊትም ይጠረጠር ነበር ታስሮም ነበር ቀን አይታይም ማታ ብቻ ነው የሚንቀሳቀሰው በእንደዚህ አይነት ጉዳይ ላይ አውቀዋለሁ ስብሰባ በምንጠራበት ሰዓትም አይመጣም የመንግስት እስትራቴጂ ውስጥ የቀበሌ መስተዳድሮች በሚያይበት ሰዓትም አይወድም በዚህ ነው የማውቀው እሱን

መቼ ነው ጊዜው ይሄ ነገር የሆነበት ጊዜ

በ1998 ነው ቤቱ የተፈተሸው

ቦታውስ አገሩ የት ነው ይሄ ነገር የተፈጸመበት

አወዳይ ቀጠኛ አንድ

በፍ/ቤቱ ትእዛዝ ቤቱን ለምንድን ነው የፈተሻችሁት

በፍ/ቤቱ ትእዛዝ ነው ቤቱ እንዲፈተሽ የተደረገው ከዞን የመጣ ፖሊሶችም ነበሩ ከአወዳይ ፖሊሶች ጋር ሆነን

673

ለምንድን ነው ፍተሻው ምንም መሰረት ያደረገ ነው አላማው ምንድን ነበር

ከአሁን በፊትም ተጠርጣሪ ስለነበረ ነው ከአሁን በፊትም ታስሮ የወጣ ነበር

የተጠረጠረበት ነገር ምንድን ነው ተጠርጣሪነቱ በምን ላይ ነው

ሰፈር ውስጥ እየሄደ ሰውን ማደራጀት ነው

ለምንድን ነው የሚያደራጀው

ለአባዎች ያደራጃል

ለአባዎች ምንድን ነው የሚያደራጀው

የእነሱ አባል ሆኖ ሰውን ያደራጃል

ቤቱ ሲፈተሽ ምን ተገኘ በቤቱ ፍተሻ ላይ ምን ተገኘ ምን ታዘባችሁና አያችሁ

ሲፈተሽ ከዛ ቤት ውስጥ ምንም አላየንም

በምን አወክ የኦነግ ወይም የአባዎ አባል ነው ያልከን በምንድን ነው ልታውቅ የቻልከው አባል መሆኑን ያወከው

የቀበሌ መስተዳደሮች በሚንቀሳቀሱት ሰዓትም አይወድም ስብሰባ በሚጠራበት ሰዓትም አይመጣም በግሉ የሚሰራም ስራ የለም ቀንም አይንቀሳቀስም ከዚህ አንፃር ተደርሶበት ነው ከዚህ አንፃር ተነስቶ ነው ሊጠረጠር የቻለው ከዚህ ተነስቶ ነው ከፍ/ቤትም ትእዛዝ ወጥቶ ቤቱ ሊፈተሽ የቻለው

እና ከዚህ ጥርጣሬ በመነሳት አረጋገጣችሁ ወይ አባልነቱን

አዎ

ጨርሻለሁ

አበቃችሁ ጥያቄ

ይቅርታ እስቲ ጀማል ጢቃንስ በተመለከተ

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፍትህ ሚኒስቴር ፍ/ቤት ቁጥር ፭

ቀጥሉ ጥያቄ

ጀማል ጢቃንስ በተመለከተ ያው በመልክ ባየው አላውቅም ቤቱ ሲፈተሽ ግን ታዝቤያለሁ ብለሀል እና ቤቱ የተፈተሸበት ምክንያት ለምንድን ነበረ

መርፌ እና 2 ካርቶን ኪኒኖች አይቻለሁ ሲወጣ --

ለምንድነው ቤቱ የተፈተሸበት ምክንያት ምንድነው በምን ተጠርጥሮ ነው

ለምን እንደተጠረጠረ አላወኩም ግን እኛ በታዛቢነት ተጠራን ይሄን 2 ካርቶን ኪኒን እና መርፌዎች ሲወጣ በአይኔ አይቻለሁ

ከዚህ ሌላስ ያየከው እቃ የለም በፍተሻ የተገኘ

አንድ አንድ ዶክመንት ከዚህ ከጀማል ጢቃ ቤት አንዳንድ ዶክመንትም አጊኝተናል የተለያየ ስም ያለበት

የምን ስም ያለበት

የቆየ ስለሆነ አሁን አላስታውስም ግን የተለያየ ስም የለበት

እንደው በአጠቃላይ ግን የዶክመንቱ ይዘት ምንድን ነበር አጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ነው የምትለን ነገር የዶክመንቱን ይዘት ቢቆይም አጠቃላይ ይዘቱ አይጠፋህም

ያልታወቀ ሰዎች ስም ነው እዛ እኛ ያየነው

የሰዎቹ ስም ለምን አላማ የተዘጋጀ ነበር

አላችሁ መቃወሚያ እሺ መቃወሚያ

እኔ ለምን እንደሆነ አላውቅም ያልታወቀ ሰዎች ስም ነው ያየሁት ብሎ ደምድሟል ስለዚህ ለምን አላማ ለምን አላማ እንደሆነማ አላውቅም ብሎ እኮ ደምድሟል ለምን አላማ ወረቀቱ ለምን እንደተፃፈ ምን እንደሆነ አላውቅም የስም ዝርዝር ብቻ ነው ያየሁት ነው የሚለው ያየውን ነው የሚመሰክረው ስለ አላማው ማወቅ እንዴት ይችላል እሱ ያየውን ለታዛቢነት ነው የሄደው እንደዚህ አይነት ጥያቄ ሊቀርብበት አይገባውም የተከበረው ፍ/ቤት

እሺ በእናንተ በኩል

576

እሺ በእኛ በኩል ምንድነው ምስክሩ እያለ ያለው ዶክመንቶች አይቻለሁኝ እነዛ ዶክመንቶች ግን አሁን ይዘታቸው ምን እንደሆነ አላስታውስም ብሎ ጥቅል ነገራቸው ምንድነው ስንለው የሰዎች ስም ዝርዝር ነው የተደራጀ ነው አለኝ የእነዚህ የሰዎቹ ስም ዝርዝር በጥቅሉ ለምን አላማ የተዘጋጀ ነበረ ብዬ ጠየኩት እንጂ እሱ አላውቅም አላለኝም ካለም አሁን ሊለኝ ይችላል እና ገና ምስክሩ ሊል ይችላል እየተባለ ከሆነ አግባብ አይመስለኝም እና ጥያቄያቸው አሁንም ውድቅ ተደርጐ ጥያቄያችንን እንድንቀጥል ተገቢ ጥያቄም ይመስለኛል እና እንድንቀጥል ይፈቀድልን ነው

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበታል ይሄ ተያያዥነት ያለው ነገር ነው ገና ምስክሩ ሊል የሚችለው እንዲህ ይላል ብሎ ብዙ ጥያቄዎችን ማቋረጥ ያስቸግራል እና ጥያቄው ፕሮፐር ነው ይቀጥል ብለናል

አመሰግናለሁ

ድገሙለት እና በአጭር አድርጉት እና ድገሙለት ግን

እሺ የሰዎች ስም ዝርዝር አይቻለሁ ብለሀል እዛ የተገኘው ዶክመንት ላይ የሰዎቹ ስም ዝርዝር እንደው በአጠቃላይ እንደዉ ለምን የተመዘገበ ይመስልሀል

እኔ በዛን ጊዜ የተረዳው በእኛ ቀበሌ ውስጥ እነዚህ ሰዎቹ ስም ዝርዝራቸው በእኛ ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ እንዳልሆኑ ነው ያረጋገጥኩት

እሺ መርፌ እና 2 ካርቶን ኪኒኖች እሽግ እንትን ውስጥ ተገኙ ብለከናለ እነዚህ ለምን አላማ ሊውሉ የተዘጋጁ ነበር ሲባል ሰማህ

እሱ የህክምና ባለሞያ አይደለም ፋርማሲ የለውም ታሞ እቤት አልተኛም እና ይሄ ነገር ከአሁን በፊትም ይጠረጠር ነበረ ይሄንን ነው በዚህ ነገር ላይ እኔ የታዘብኩት

የሚጠረጠረው ለምን ለምን አላማ ያውለዋል እየተባለ ነበረ

ይልካል ተብሎ ይጠረጠራል

ለማን ይልካል ተብሎ

ለአባዎች ይልካል

576

አኬ ጨርሻለሁ ክቡር ፍ/ቤት ምናልባት የምናሳስበው ነገር

ቆይ ይለቅ እና

እዚሁ ላይ ስለሆነ ነው

እሺ ምንድነው

ጀማል ጢቃ የሚባለው ተከሣሽ እዚሁ ስላለ ስንተኛ ተከሣሽ እንደሆነ ተረጋገጦ በእሱ ስር እንዲመዘገብ ለሪከሪዲንጉ ሲስተም እንዲ--

ሲያልቅ እሱን ማሳሰቢያ ምስክርነቱ ካለቀ በኋላ

እሺ እሺ

ፍ/ቤቱም የያዘው ነገር ስለሆነ ነው እሺ መስቀለኛ ጥያቄ አላችሁ

አዎ

ለተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

ኤው -- 2 ካርቶን መድሀኒት የያዘ ነው ተብሎ እና መርፌዎች አጊኝተናል በለሀል ሲመረመር አይተናብ ብለሀል ማን ነገረህ ይሄንን ይልቅ በዚህ ሀገር ሊመጣ ወደ እገሌ ጋር ሊላክ ነው ብሎ ማን ነገረህ ነው ግምትህን ነው

ቆይ አንዴ አንዴ ቆይ ይቀጥል ይሄ ሰውዬ ታሞ እቤት አልተኛም

ይሄ ሰውዬ ታሞ እቤት አልተኛም 2 ካርቶን ሙሉ ለምን እቤት አስቀመጠ ከአሁን በፊትም ይጠረጠር ነበረ ነው የሚለው

ይሄ የአንተ ግምት ነው ወይ

አዎ እኔ እንደ እራሴ የማስበው ይሄንን ነው

ነው እንጂ በተጨባጭ ያወከው ነገር የለም

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

577

ከአሁን በፊትም ታስሮ ነበረ

ታስሮ ምን ሆነ

ከአሁን በፊት ታስሮ ወጣ ነው የሰማሁት

ታስሮ ወጣ የሚባል ወሬ ሰማህ እቤቱ ሄደህ ያንን ነገር ሲገኝ ከማየት ውጪ ምን ታውቃለህ አንተ

እኔ ከእዛ በፊትም እሱን አላውቅም አሁንም አላውቀውም እሱ የእሱ እቤት መሄዱን ነው የማውቀው

ሌላ ጥያቄ

ኤው ማነው 12ኛ ጀማል ከድርን በሚመለከት ጀማል ከድር

አንዱ ቆይ ጀማል ከድር የአያት ስም ማነው ጀማል ከድር ማን ሳኒ ቀጥሉ

እሺ ጀማል ከድር ሰኒን በሚመለከት ጀማል ከድርን ቀን ቀን ስራ አይሰራም ቀበሌ ሰብሰባም አይመጣም ከሚል ውጪ ጀማል እንዲህ ወንጀል ፈፅሟል ወይንም እንዲህ አድርጓል የሚል አንተ አልሰማህ አላየህ ምንድነው ጥርጣሬ ልታሳድር የቻልከው

እኔ የማውቀው ሰው የመታ አላየሁም ስብሰባ ሲጠራ በቀበሌ መስተዳደር ለመንግስት ስራ በሚጠራበት ሰአት የማይመጣ ሰውዬ እሱ ይሄንን እራሱ እኔ እንደ እራሴ እንደ ወንጀል ነው የምቆጥረው

እኮ ስብሰባ ስላልመጣ ብቻ

ቀን አይንቀሳቀስም ማታ እየተንቀሳቀሰ ህዝቡን ያደራጃል ከዚህ ተነስተን ነው ይሄን የተደረሰበት ነው

ይሄን አንተ በምን አወቅህ አየኸው ወይ አንተ በአይንህ

አዎ አይቻለሁ

ማንን ሲያደራጅ

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ፍ/ቤት ቁጥር 4

579

ሰፈር ውስጥ ህዝቡን ሲያደራጅ አይቻለሁ

እነማንን

በዛን ሰአት እኔ የፀጥታ የእነዛ የፀጥታ ዘርፍ ውስጥ ስለነበርኩ በወቅቱ ተበታተኑብን አሁን እገሌ እገሌ ብዬ የያዝኩት ነገር የለም

ይቀጥል ጥያቄ

ምኑን ነው ተበታትነዋል ይምትላቸው እነዛ ተደራጁ የምትላቸውን ነው

ኢንፎርሜሽን ነው የደረሰን ተደራጀ የተባለበት ቦታ ስንደርስ አላገኘንም

ወሬ ነዋ የሰማከው

ኢንፎርሜሽን ሰምተን ከእዛ በኋላ ስንደርስ ተበተኑብን

ስለዚህ አላየከውማ

አዎ በአይኔ አላየሁም

ይበቀናል

አበቃችሁ እሺ ድጋሜ ጥያቄ አላችሁ እሺ የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

የዐ/ሕግ ድጋሜ ጥያቄ

ጀማል ከድርን በተመለከተ እናንተን ሲያዩ ተበተኑ ያልከው የህግ አካላት መሆናችሁን ሲያውቁ ነው ወይ የተበተኑት እንደመጣችሁ ሲያውቁ ነው ወይ

በተጨባጭ እኛን ያውቃሉ ብዎ ከእዛ አንፃር ነው ሊበተኑ የቻሉት

እናንተን ፈርተውነው ማለት ነው እናንተን

አዎ

ጨርሻለሁ

እሺ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት

579

የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ ካለ የምስክሩ መልስ

ጀማል እስቲ ተነስ በለው ጀማል ማን ነው የአባትህ ስም ጀማል ከድር አህመድ አህመድ እሺ ቁጭ በል አንተስ ጀማል ከድር ሳኒ ጥሩ ቀደም ሲል በ75ኛ የዐ/ሕግ ምስክር በ15ኛ በ18ኛ ተራ ቁጥር ስለ ጀማል ጢቃ ብለው የመሰከሩት 34ኛ ተከሣሽ መሆኑ ተረጋግጧል በተመሳሳይ በአሁኑ ምስክርነት እየተሰጠበት ያለው በዚሁ በ34ኛ እና በ29ኛ ተከሣሾች ላይ መሆኑ ተመዝግቧል ማጣሪያ ጥያቄው ይቀጥላል

እ ጀማል ከድር ቀን ቀን አይንቀሳቀስም ማታ ማታ ሽርጥ ለብሶ ይንቀሳቀሳል በእዛ የተነሳ ይጠረጠራል ብለከናል

አዎ

ስለዚህ ይሄ ጀማል ከድር ሳኒ ተጠርጥሮ ክትትል ሲደረግበት ምን ተገኘበት

በተጨባጭ የተደረሰበት ይሄ ነው ብዬ አሁን የማስቀምጠው ነገር የለም እሺ ጀማል ከድር ሳኒ እየሄደ ሰው ይቀሰቅሳል ያደራጃል ያልከው ነገር አለ ያደራጃቸውን ሰዎች አይተካል ወይ ወይ ሲያደራጅ አይተካል ወይ

እኛ የቀበሌ መስተዳደሮች መሆናችንን ስለሚያውቁ እኛ ተደራጀ የተባለበት ቦታ ስንደርስ ይበተኑብናል እና አከሌ ብዬ አሁን ለማስቀመጥ ይቸግረኛል

ምን ብሎ እንደቀሰቀሰስ ያየከው ወይ የሰማከው ነገር አለ ወይ

የዚህን መንግስት አትስሙ አትስሙ ብሎ ህዝቡን እንደሚቀሰቅስ ይሄንን ነው የሰማሁት

ማነው ይሄንን ያለው

የእኛም አባል አለን ከህብረተሰቡ ውስጥ አባል አለ እና ከእነዛ ይደርሱናል

እነማን ናቸው የነገሩህ ማስታወስ የምትችል ከሆነ እኔ እሱም ቢሆን እኔን እንደ ግሌ ምንም ያደረገኝ ነገር የለም

የግልህን ነገር አይደለም የተጠየከው የተጠየከው ምን ብሎ እንደቀሰቀሰ ነው እና ተነግሮህ ከሆነ ማን እንደነገረህ

5 80

ያው ኢንፎርሜሽን ይደርስናል ከሴቶችም ከወንዶችም በተለያየ መንገድ ይደርሱናል

እንጂ በተጨባጭ የደረሳችሁበት ነገር የለም ከኢንፎርሜሽን በስተቀር

በተጨባጭ ቤትም ስንፈትሽም ያው የተጨባጭ ያየነው ነገር የተገኘ ነገር የለም

እሺ የጀማል ጢቃን ቤት ስትፈትሹ መድሀኒት እና ዶክመንቶት ተገኝተዋል ብለሀል ዶክመንቱ ላይ በላዩ ላይ የተፃፈ ስለምንድነው ተብሎ ነው ሰዎቹ የተዘረዘሩት እዚህ ላይ የተፃፈ ነገር አይተካል ወይ በለው በእነሱ ላይ

እኔ ተምሬም አላውቅም ግን ያንን አላየሁም እና ፖሊስ እጅ ነበረ የስም ዝርዝሮቹን ብቻ ነው ያየሁት

ካልተማርክ የስም ዝርዝር መሆኑን በምን ታውቃለህ የመድሀኒቱ ዝርዝርስ ቢሆን በምን ትለያለህ በለው

የመድሀኒት ስም እና ይዜ የተለያየ ነው ያስታውቃል

በምንድነው የለየከው አልተማርክም አይደለ ወይ በለው

ያው መድሀኒቱ እሽግ ነው እኔ አማርኛ ነው የሚቸግረኝ እንጂ ላቲን ስለማውቀው አንዳንድ ስሞች ሲያነሱም እሰማለሁ

የሰዎቹ ስም ዝርዝር በምንድነው የተፃፈው

በላቲን ነው የተፃፈው

እና ትችላለህ ማለት ነው ላቲን ማንበብ በለው

አዎ አውቀዋለሁ

እንዴት ነው ያወከው አልተማርክም አይደለም

እቺን የማንበብ ያህል አውቃለሁ

እና የማንበብ ያህል ስታውቅ በእነሱ ላይ በላቲን ተፅፎ ከሆነ ምንድነው የሚለው እርእሱ

58

እኔ የርእሱን አላየሁም የሰዎቹ ግን በእኛ ቀበሌ ውስጥ የሌሉት ስም ዝርዝሮች ከሆነ ይዤንን ነው የለየሁት ማነው ያነበበላችሁ እሱን

ከፖሊሱ ጋር ሆነን አብረን ነው ያነበብነው

በዚህ ነው ይዤ ሰዎች ስም ዝርዝር ነው ብሎ ያረጋገጥከው በለው

አዎ

እሺ እናመሰግንዎታለን ከኋላ ይቀመጡ ማን ይጠራ ጥሩ አጀንዳ እንይዛለን በቀጣይ ምስክሮቹን ለመስማት ማለት ነው ችሎቱ ስለ አጀንዳ አያያዝ የተነጋገረውን አሁን የሚቀጥለው አጀንዳ ምስክሮች እንዲቀርቡ ለየካቲት 3 እሮብ ነው ቀጠሮ

ት እ ዛ ዝ

ቀጠሮ አይቀየርም የካቲት 3 ነው የእኛ አጀንዳ ወደ ፊት መስተካከልም አለበት ተነጋግረን እስከምናስተካክል የካቲት 3 አጀንዳ ይዘናል መለወጥ የማይቻለው የጋራ አጀንዳ ስለሆነ ነው የካቲት 3 ምስክሮቻችሁን አቅርቡ እሮብ እለት ነው የካቲት 3 በሌላ በኩል እስከ ከየካቲት 3 በፊት ሪፈር የተባለ

አይ የተጠየቀበት አለ ከየካቲት 3 በፊት ማረሚያ ቤት እና ፖሊስ አሳክመው እንዲመልሱ ፍ/ቤቱ አዟል በሌላ በኩል የስም በተመለከተ የአንድ ማመልከቻ ቀርቧል አህመዲን ኢብራሂም የሚባል ሰው መኪና ስለሸጠ ስሙ ይስተካከልልኝ የሚል አቤቱታ ግለሰብ አቅርቦ ነው እሱ የፃፈው አህመዲን ነኝ ነው የሚለው አህመዲን ኢብራሂም ሀሰን እንግዲህ ከ ከምርመራ በዝገብ ከፖሊስ ሆነ ከሌላ ከሚገኘው መረጃ ይረጋገጥና በፅሁፍ አስተያየት ይቅረብበት ክሱ ማመልከቻው ላይ ነው የፖሊስ መቻቻል ላይ ይዤ ሰው በየትኛው ስም እንደሚታወቅ ቢቻልም ከፖሊስ ጋር ሆናችሁ ከአካባቢው ሄዳሩ እና ለፍ/ቤት ይቅረብ ከእዛ በኋላ ትእዛዝ ይሰጣል ለየካቲት

59

ምንድነው በግል እዚህ ድሬዳዋ ልታከም ያልከው ነህ በግሌ ወጥቼ ልታከም ብሏል ማረሚያ ቤት አጃቢ በመመደብ በግሉ አሳክሞ እንዲመልሰው ታዟል የካቲት 3 ለአስተርጓሚው በዚህ መዝገብ ለስተረጉመው ማነው ስምህ ሰዲን አብዱራህማን አንዳርጌ በ2ቱ ቀናት በሙሉ ችሎት ያስተረጉመበት በደንቡ መሰረት እበል እንዲከፈለው ታዟል ይፃፍ ብለናል ለየካቲት 3 ተቀጥሮ ችሎቱ በዚሁ ስራውን አብቅቷል የዛሬን

ማ/ተ

የመ/ቁ - 04486

ቀን - 25/6/2002

ዳኞች - ሀብታሙ ወርቁ

- ሰኢድ ሀሰን
- ዩሱፍ መሀመድ ተሰይመናል

ከሳሽ - የፌደራል ዐ/ህግ አረጋይ እንደሻው ቀርበዋል

ተከሳሾች - እነ አብዱረህማን ባሌ ጎጆ ከማረሚያ ቤት 69 ተከሳሾች ቀርበዋል

ማን ናት ህክምና የሄደችዋ ሌሎቹ ቀርበዋል በዋስ ያላችሁ ቀርበዋል ተቀመጡ መዝገቡ የተቀጠረው የዐ/ህግ ማስረጃ ምስክሮች ካሉ ለመስማት ነው በዚህ መሰረት ምስክሮች መኖራቸው ስለተረጋገጠ ምስክርነቱን መስማት ፍ/ቤት ይቀጥላል ማን ይጠራላችሁ ዐ/ህግ

ለፍ/ቤቱ ግን ፋጤ አህመድ ፃድቅ እቺ 8ኛዋ በእሷም ላይ የሚመሰክሩ ምስክሮች የቀረቡ አሉ

ግልጽ ነው እሺ

እሱ ከግምት እንዲገባልን ነው ከቀሩት ምስክሮች

ለመለየት ነው እሺ

ለአሁን ግን 36ኛ የዐ/ህግ ምስክር ዩሱፍ መሀመድ ይቅረብ

39ኛ

36ኛ

ዩሱፍ መሀመድን ጥሩ

የዐ/ህግ የመጀመሪያው ለዛሬ የተቀጠረ 36ኛ ምስክር በሚመሰክሩባቸው የ43ኛ እና 64ኛ ተከሳሾች ላይ በምን ጉዳይ እንደሚመሰክሩ ጭብጥ እንዲያዝልን እናመለክታለን

ጥሩ ዐ/ህግ የምትሉት አለ

384

ከዚህ በፊትም ለፍ/ቤቱ እንዳስረዳነው ጭብጣችን እንደ ክስ አመሰራረታችን የሚያስረዱ ናቸው ስለዚህ በዚሁ በ43ኛ እና በ64ኛ ተከሳሾች ላይ እንደ ክስ አመሰራረታችን የሚያስረዳ ምስክር ነው።

እሺ ምስክሩን ጥሩት አስተርጓሚ 36ኛ የዐ/ህግ ምስክር ቀርቧል አማርኛ ይችላሉ በደንብ ይችላሉ

36ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ዩሱፍ መሀመድ

አድራሻ- ቡርቃ ቀበሌ ጎሎዳ ወረዳ

ዛሬ ለምንድን ነው የመጡት ለምስክርነት ነው

አዎ

ለምስክርነት ነው

አዎ

በማን ጉዳይ ላይ ነው ምስክርነት የ ሚሰጡት

መሀመድ እና ኡስማኤልና አህመድ ኡስማኤል

ጥሩ ያውቋቸዋል ቢያዩዋቸው

እኔ አንድ ቀን ስላየኋቸው በመልካቸው አለያቸውም

በመልክ አይለዩዋቸውም

አዎ

ጥሩ አሁን ይነሱና እዚህ መህል የሚያውቁት ሰው ካለ ይለዩልናል የሚያውቁትን ብቻ ገብቶታል አደለ ቀስ ብሎው እያዩ የሚያውቋቸውን ይለያሉ ይቀመጡ አሁን ያሳዩትን ሰዎች በስም ያውቋቸዋል ወይ

አዎ

586

እስቲ እዚህ ጋ ያለው ማን ነው ስሙ

ይሄ ባሌ ይባላል

ባሌ

አዎ

በቅጽል ስሙ ነው የማውቀው

በቅጽል ስሙ ማን ነው ስምህ አብዱረህማን ባሌ እዛ ጋ ያሳዩትስ

ያኛው

አዎ

ስሙ ጠፋብኝ እሱ

ስሙ ጠፋኝ እሺ ያኛውስ

ያኛው እዛ ያልኩት እሱ ነው ፖሊሱ ጋር የቆመው

ማን ነው ዳኛ

ዳኛ

ዳና

አዎ

ማን ነው ስምህ አመዲን

አዎ

ስምህ ማን ነው አልክ መሀመድ ኑር ጮክ በል እስቲ ስም ማን ነው

መሀሙድ ሻሩ

ከነዚህ ጋር ፀብ ዝምድና አለሎት እንዴ እርሶ

የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ቁጥር ፫

586

የለኝም

የሎትም

አዎ

ጥሩ ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እሺ አቶ ዩሱፍ በስም አውቃቸዋለሁ ያሏቸው ከእነዚህ ውስጥ ካስነሳካቸው ውስጥ ናቸው እንዴ

አይደሉም

ምናልባት ስማቸው እስቲ ማን ነው በትክክል በስም ልመሰክርባቸው መጣሁ ያሉትን ስማቸውን ጥሩልን

መሀመድ ኑር እና አህመድ ኡስማኤል አንድ ቀን ያየኋቸው እነሱን

አሁን በሚሏቸው በጠሯቸው ሰዎች ላይ ምንድን ነው የሚያስረዱት

መሀመድ ኑር ኡስማኤል ለመርማሪ ፖሊስ ቃሉን ሲሰጥ ነው እኔ አጠገቡ ቁጭ ብዬ የሰማሁት

መቼ ነው

በ1989 አካባቢ ይመስለኛል

በስንት ዓመተ ምህረት እስኪ

1988 አካባቢ

ስንት ዓመት ይሆነዋል

ሁለት አመት

ሁለት አመት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ ፖሊስ ኮሚሽን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

597

አዎ

አሁን ስንት አመተ ምህረት ላይ ነው ያለነው

2002

2002 ታዲያ የዛሬ ሁለት አመት ከሆነ ስንት አመተ ምህረት ነው የሚሆነው

1998

መቁጠር ይችላሉ እንዴ ጊዜ ቀን መቁጠር ይችላሉ

እኔ በደንብ አልችልም

በደንብ አይችሉም

አዎ

የዛሬ ሁለት አመት ይሆናል ብለውኛል የዛሬ ሁለት አመት ምንድን ነው የተፈጠረው ምንድን ነው ያዩት ያወቁት ምን ሲሉ ነው እነዚህ ስማቸው የጠሯቸው ግለሰቦች

በጎሎዳ ወረዳ ሚኖ በሚባል ቦታ ለመርማሪ ፖሊስ ቃላቸውን ሲሰጡ

ምን ብለው ቃላቸውን ሰጡ

ይሄ መሀመድ ኑር ኡስማኤል መጀመሪያ የህዝባዊ ሚኒሻ እንደነበረ ከዛ በኋላ ኦነጎች በአካባቢው ሲመጡ ሀረቦረኒ ላይ ፉንጋስ ለሚባለው የኦነግ መሪ እጁን መስጠቱንና ከዛ በኋላ ከእነሱ ተመልሶ ወደ ሚኒሻ እንዳይገባ ለእነሱ ረዳት ሆኖ ከላይ ህዝቦች እህል ወተት እየተላላከላቸው ከእነሱ ጋር ሲሰራ እንደቆየ ቃሉን ሲሰጥ አይቻለሁ

እሺ ያንኛውስ ደግሞ ማን ነው ያለት ደግሞ አንደኛው አሁን የነገረው መሀመድ ነው አደለ ያንኛው ደግሞ ማን ነው ስሙ

አህመድ

እሺ አህመድስ

588

አህመድ ኡስማንን በዛን ወቅት ከኦነጎች መሪዎች ጋር ---------- ግንኙነት እንዳለውና እህል አምስት እህል ሶስት ኩንታል ቁስለኛ ደግሞ ለ7 ቀን አስታሞ 500 ብር እንዲያስታምሙበት ---------- ሰጥቶ እንደሄደ ወተት ከህዝቡ እየሰበሰበ ለእነሱ እንደሚያቀብል ቃሉን ሲሰጥ ሰምቻለሁ

ለነማን እንደሚያቀብል

ለነ ብራሳ ዳዲ

እነ ቢራሳ ዳዲ ማለት ምንድን ነው የሚሰሩት ምንድን ናቸው

ኦነግ ናቸው

ኦነግ ናቸው ቁስለኛ ብለውናል የምን ቁስለኛ ነው

በመንግስት ሰራዊት የተመታ የኦነግ ቁስለኛ

እሺ እነሱን ቁስለኞች ምን ሲያደርግ ነበር ነው ያሉት

ለ7 ቀን አጠገቡ ቁጭ ብዬ አስታምማ ከዛ ስሄድም ለብራሳ ዳዲ የሚያስታምሙበት 500 ብር ስጥ በኋላ እንመልስልሃለን ስጡኝ ብሎ ሰጥቻቸው ሄጃለሁ ብሎ ቃሉን ሲሰጥ ሰምቻለሁ እና ከዛ በኋላ ሶስት ኩንታል ማሽላ ሰብስቦ መስጠቱን ቃሉን ሲሰጥ ሰምቻለሁ

እስቲ እነዚህ አሁን ቅድም የነበሩን አሁን በሁለቱም ሰዎች ላይ በአህመድ እና በመሀመድ ላይ እንደዚህ ብሎ ለፖሊስ ቃላቸውን ሲሰጡ ሰምቻለሁ ብለው መስክረዋል እነዚህ ያስነሳካቸውን ሰዎች ደግሞ አውቃቸዋለሁ ብለው የሚያውቋቸውን ሲባሉ አስነስተዋቸዋል በምንድን ነው የሚያውቋቸው እነዚህ ያስነሷቸውን ሰዎች እስቲ አሁን ባሌ ያሉትንም በምን እንደሚያውቋት ለፍ/ቤቱ አስረዱ

እነዚህ የተነሱትን ሰዎች እኔ በወሬ የኦነግ ተባባሪዎች ናቸው ተብለው ነው የተያዙት የሚሉት ነው እንጂ እኔ ቃላቸውንም ሲሰጡ ይዤያቸው ነገር ሲሰጡም አላውቃቸውም እኔ ወሬ የሰማሁትን ብቻ ነው

እነዚህ ያስነሷቸው ማለት ነው

589

አዎ

እነዚህ አሁን ቅድም በስም ነው የማውቃቸው ብለው ለፍ/ቤቱ ያስረዱት ማለት ነው እነዛን ሰዎች ከዛን ቀን በፊት ያውቋቸዋል እንዴ የምስክርነት ቃል ከመስጠታቸው በፊት ያውቋቸው ነበር እንዴ

የእኔ መኖሪያ እና የእነሱ መኖሪያ ወደ 105 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ናቸው እኔ ለስራ እዛ አካባቢ ሄጄ ነው እንዲ ፖሊሱ እኔ ጋ አምጥቶ ቃላቸውን የተቀበለው አላውቃቸውም 105 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው ያለነው

ከዛን ቀን በኋላስ ደግመው አይተዋቸዋል እንዴ እርሶ

አላየኋቸውም

ጨርሻለሁ

እሺ ቀጥል መስቀለኛ ጥያቄ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

በእናንተ እና በእነሱ መካከል የ105 ኪሎ ሜትር እንዳለ በምስክርነት አሁን ተናግረዋል ስለዚህ እርሶ ምን ሊያደርጉ ሄደው ነው ቃላቸውን ሲሰጡ የሰሙት

እኔ እዛ ቤት ለመስራት

አደለም ቃላቸውን ሲሰጡ ሰምቻለሁ ብለዋል አደለም ምን ሊያደርጉ ሄዱ 105 ኪሎ ሜትር ድረስ ቃል ሲናገሩ እርሶ ምን ሊያደርጉ ሄዱ

ቤት እዛ ላይ ለስራ ነው የሄድኩት እዛ ቦታ ያ ወረዳ አሁን የሚቋቋም አዲስ ከተማ ስለሆነ ስራ ፕሮጀክት ነበር ያንን ፕሮጀክት ለመስራት ወስጄ ነው እዛ ቦታ የሄድኩት

ፖሊስ ጣቢያ ለምን ሄዱ

የሚሰራው እዛው ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ስለሆነ እኔ ከስራ እረፍት ቁጭ ስል እኔ ብቻ አይደለሁም አንድ መሀመድ ኑር የሚባል ዛሬ አልመጣም እንጂ ከእኔ ጋር ነበር ፖሊሱ እኛ ጥላ የተቀመጥንበት ቦታ ጠርቶ መጥቶ አዳምጡ ብሎን እኮ ነው

እኮ እርሶ ስራዎትን ይሰራሉ ወይስ ለፖሊስ ቃል የሚሰጠውን ሰው በሙሉ እየተከታተሉ ያዳምጡ ነበር በዛን ቀን እንዴት ለይተው ሊያስታውሱ ቻሉ

ይሄ እንግዲህ የፖሊስ የእነዚህ ሰዎች የደረጃ ምስክር ትሆናላችሁ ብሎ ነው አዳምጡ ብሎን ነው እኛ የተቀመጥንበት ቦታ እንጂ እኔ የፖሊስ ተከታታይ አይደለሁም

ስለዚህ አዳምጡ ተብለው ሲያዳምጡ እነዚህ ሰዎች ተገደው ቃላቸውን ይስጡ አይስጡ የሚያውቁት ነገር አለ

ተገደው እንዳልሰጡ አውቃለሁ አብረን ቁጭ ብለን ጫት እየቃምን ነው የተናገሩት

በምን አወቁ እርሶ

አንድ ላይ ነው ቁጭ ብለን የተቀመጥነው ጫት ስንቅም አንድ ቦታ ተሰብስበን በአንድ ጥላ ስር ምንም ተጽዕኖ ሳይኖር እስቲ አንተ ራስህን አጋልጥ ተብሎ የሰራውን በሙሉ ሲናገር ነው የሰማሁት ግዳጅ እኔ አላየሁኝም

ጫት መቃም ተፅእኖ አለመኖሩን ያሳያል እንዴ

ጫት መቃም ተፅእኖ አለመኖሩን አያሳይም

ተቃውሞ አላችሁ ቆይ እስቲ አንዴ እሺ አስመዝግቡ

ተቃውሞ አለን ተቃውሞአችንም ምንድን ነው ምንም አይነት ግዴታ የለም አብረን በሰላም በነፃነት ቁጭ ብለን እያወራን ነበር ብለዋል ስለዚህ ጫት መቃም መገደድ ነው አደለም የሚለውን ለፍ/ቤቱ የሚተው ጥያቄ ስለሆነ ይሄንን ጥያቄ ተቃውሞ አለን

እሺ ጥያቄውን እናሻሽላለን እርሶ ስራዎትን ትተው ነው ቁጭ ብለው የሚያዳምጡት

ተቃውሞ አላችሁ

አዎ

እስቲ

ይሄንንም በሚመለከት እኔ የፖሊስ ተከታታይ አይደለሁም እዛ ቦታ ስራ እየሰራሁ ነበር ፖሊስ ና የደረጃ ምስክር ትሆናለህ ብሎ ስላለኝ ደረጃ ምስክር ሆኛለሁ ብለዋል ስለዚህ ደግሞ እንደገና ስራዎትን ትተው ለምን እየተባሉ ሊጠየቁብን አይገባም

እዚህ ላይ ሃሳብ አላችሁ

የተከበረው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ነገር ምስክሩ እንደክሱ ያስረዳሉ የተባሉ ናቸው እንደዛም ሆኖ እንደክሳቸው አደለም እያስረዱ ያሉት የስሚ ስሚ ነው እንደክሱ ማስረዳት ማለት በድርጊቱ ላይ በቀጥታ ቢሳተፉ ነው

አሁን በተባለው መቃወሚያው

አዎ ስለዚህ የስሚ ስሚም ራሱም ሆኖ መረጃው ግን የሰሙበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ስለሚያስፈልግ ነው የሰሙበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ መንደርደሪያ ጥያቄዎችን ነው እያቀረብንለት ያለነው

እሺ ተነጋግረንበታል ይሄ ጥያቄ ይቀጥል አይደጋገም ግን ጥያቄዎች አይደጋገሙ

እሺ ጥያቄው ይደገምልኝ

ጥያቄውን ድገምላቸው በአጭሩ

ጥያቄውን እርሶ ከዛ በኋላ ከሰሙ በኋላ ወዴት ሄዱ

ወደስራ ነው የሄድኩት

ስራ አቋርጠው ነው የሰሙት

5:00 ሰዓት ጠዋት ስራ ጀምሬ 6:00 ሰዓት ላይ ለእረፍት ቁጭ እንዳልን ነው

እሱን ተናግረዋል ቅድም

እሺ የሰጡት ቃል ስለመመዝገቡ እና አለመመዝገቡ አይተዋል የዛኔ

አዎ መመዝገቡን አውቃለሁ

አይተዋል

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥር 4 ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

592

ወ

ዛን ነው የመዘገበው ቃላቸውን

ፖሊስ

ጫት እየቃማችሁ ነበር

አዎ እኛ ጥላ ያለንበት ቦታ ነው ይዞ የመጣው

ስለዚህ በምን ላይ ነው እየመዘገበ የነበረው እዛ ቁጭ ብላችሁ እየቃማችሁ

ወረቀት ላይ ወረቀት አለ

ምናልባት ጨዋታ ነው ወይ ቃል መስጠት ነው እየተጨዋወታች ነው ወይንስ ቃል እየሰጡ ነበር

ይሄ ጥያቄ እኔ የምጠየቀው አይደለም ይጫወት ይስራ ፖሊሱን ነው መጠየቅ ያለበት እኔ ይሄንን ጥያቄ ልመልሰው አልችልም

ቃል ሲሰጥ ይመዘገብ ነበር

አዎ

እሺ ሌላ ጥያቄ

ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በ105 ኪሎ ሜትር ሲኖሩ ከዛ በፊት አያውቋቸውም

አዎ

አላውቃቸውም ብለዋል

እሺ ከዛ በኋላ አልተገናኛችሁም

አዎ

ድርጊቱንም ሲፈጽሙ አላዩም እርሶ

አላየሁም ብዬአለሁ

593

ጨርሻለሁ እሺ

ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ዐ/ህግ

የለንም

የላችሁም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

መሀመድ ኑር አህመድ አህመድ ኡስማኤል መተኮ እናንተ ሶስታችሁ ቁጭ በሉ እርሶ ይሄንንስ ያውቁታል ወይ እዚህ የቆመውን ቀረብ ብለው እዩት መጀመሪያ ይሄኛውን ይችላሉ በደንብ ያስታውሱታል

አዎ

በዛን ወቅት እሱ ነው ቃል የሰጠው የሚያስታውሱት ሰው አሁን በምን አስታወሱት ቁጭ ብለው ተረጋግተው ይንገሩን እየተቀረጸ ነው

እሺ መጀመሪያ ሲመጣ መጀመሪያ የመጣው የቱ ነው

አዎ እሱ ነው

እሱ እሺ ያኛውስ

ሁሉንም አስታውሻለሁ

ጥሩ አሁን ቃል ሲሰጡ የዛን እለት ባሏት ደቂቃ አየሁ ያሏቸው ሰዎች እነዚህ ሁለቱ ናቸው ማስታወስ ይችላሉ አሁን

አዎ

እርግጠኛ ኖት

አዎ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

ጥሩ ቃሉ ላይ ተፈርሟል እንዴ ፖሊስ ከተቀበለ በኋላ ተፈርሟል እንዴ

እነሱ እዚህ ቦታ ትዝ አይለኝም ይፈርሙ አይፈርሙ

አያስታውሱም

አላስታውስም

ጥሩ ያኔ በወቅቱ እርሶ ቅድም የመገደድ ሁኔታ የለም ብለዋል ግን እነሱ የሚናገሩት ነገር ነበር እንዴ ግዳጅን በተመለከተ ወይም አንሰጥም ቃሌን ይሉ ነበር እንዴ

የለም

የለም

አዎ አንደኛው ይሄ ኡስማኤል መተኮ የሚባለው ከፖሊሱ ጋር ያንን ብር ቁስለኛውን ጫካ አይደለም ቤትህ ነው አስቀምጠህ ያስታመምከው ብሎ ሲጠይቀው ቤቱ አይደለም ካራሚስ ማዶ ነው በዚህ በሁለቱ እና በዚህች በሁለቱ ነጥብ ብቻ ላይ ነው ሲከራከሩ የሰማሁት

እንጂ ሌላ ነገር የለም

አዎ

እሺ እናመሰግኖታለን መሄድ ይችላሉ ከኋላ ይቀመጡ ሌላ ምስክር ማን ይጠራላችሁ ዐ/ህግ

በድሪ አብዱልከሪም 38ኛ የዐ/ህግ ምስክር 67ኛ ተከሳሽ ላይ የሚመሰክር ነው

በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም እምላለሁ።።

እሺ እዚህ ይምጡ ይቀመጡ አማርኛ ይችላሉ

አዎ እችላለሁ

በደንብ

አዎ

38ኛ የዐ/ህግ ምስክር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፡

545

ስም - በድሪ አብዱልከሪም

ሥራ - የመንግስት ሰራተኛ

አድራሻ- ሎጎአዳ ወረዳ

ለምስክርነት ነው የመጡት

አዎ

በማን ጉዳይ ላይ ነው የሚመሰክሩት

በአቶ አህመድ አብራሂም

በአቶ አህመድ

አብራሂም አብዱላ

ጥሩ ያውቋቸዋል አቶ ኢብራሂም አብዱላ ዋሪዬ በመልክ ያውቋቸዋል ይለዩዋቸዋል

ያው ጊዜው አንድ አመት በፊት ነው በመልክ ባለያቸውም እኔ ሌላ የስእል ማስረጃ አለኝ የቪዲዮ ማስረጃ

ጥሩ እዚህ መሀላ ተነስተው ይለያሉ ተነስተው

ባለያቸውም ግን ማስረጃ አለኝ እኔ

ግድ የለም አሁን ተነሱና ካሉ ይሞክሩ ይምጡ ይቀመጡ አሁን ካሉት ስሙን ከጠቀሱት ሰው ጋር ፀብ ዝምድና አሎት እንዴ

የለኝም

የሎትም ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እሺ አቶ በድሪ ዛሬ የመጣሁት በኢብራሂም አብዱላ ዋሪዬ ላይ ልመሰክር ነው ብለዋል

አዎ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁ ፫ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

596

እስቲ ምንድን ነው ያዩት ምንድን ነው የሚያውቁት እስቲ ይንገሩን

እኔ ያየሁት ፖሊስ ጣቢያ የኦነግ አባል መሆኑን በራሱ ድምጹን ቃሉን ሲሰጥ

መቼ ነው

ከ1988 ጀምሮ እስከ በጥርጣሬ እስከተያዘበት 2001 ድረስ በአባልነት ማገልገሉንና እንደውም መሳሪያ ተሰጥቶት መሳሪያውን ቤቱ ውስጥ ቆፍሮ መደበቁን ድምጽ ቃሉን ሲሰጥ ነው የሰማሁት በጆሮዬ

ቆይ የምን አባል ሆኖ ሲያገለግል ነው መሳሪያ የተሰጠው

የኦነግ አባል ነው

እሺ የኦነግ አባል ሆኖ ሲያገለግል እንደነበረ ቃል ሰጠ

አዎ

ከዛስ

ከዛ በዛው ራሱን ------- ተከታትለን ፖሊሶቹን ወስዶ የደበቀበት ቦታ ሄዶ መሳሪያውን አውጥቶ ሁለት መሳሪያ አንድ ባለ አንድ እግር ክላሽ ታጣፊ ከ30 ጥይት ጋር አንድ ኤስ ኬ ኤስ ከ4 ጥይት ጋር ከቤቱ ውስጥ ቆፍሮ አውጥቶ ለፖሊሶች ሲያስረክብ በአይኔ አይቻለሁ ማለት ነው

መሳሪያም ሲያስረክብ በአይኔ አይቻለሁ ብለዋል መጀመሪያ ቃል የሰጠው የት ቦታ ነበር የት ነው ቃል የሰጠው

ፖሊስ ጣቢያ ነው

ምን የሚባል ወረዳ ነው የት አካባቢ ነው እስቲ ይግለጹልን

ቁንቢ ወረዳ ነው ወረዳው አሁን ቁንቢ ወረዳ ሚኖ ከተማ ላይ ነው እዛው ነው ፖሊስ ያለው

የት ነው የት አካባቢ ነው ቦታው ያለው አጠቃላይ ዞኑ ምናምን

ምስራቅ ሐረርጌ ድሮ ጎሎዳ ነበር አሁን ቁንቢ ወረዳ ሚኖ ከተማ ነው

597

እሺ እዚህ ሚኖ ከተማ ላይ ቃል ሰጠ አሉን ከዛስ ቃል ከሰጠበት ቦታ ይሄ ቅድም የነገሩን ሁለት መሳሪያ ያሳያችሁ ወይም

ተቃውሞ አላችሁ እሺ ይመዝገብ

የተከበሩ ዐ/ህግ ሁሉም ምስክሮቻቸው እንደ ክሱ ጭብጥ የሚያስረዱ መሆናቸውን ነው ያስመዘገቡት ስለዚህ እንደክሱ ጭብጥ ለማስረዳት አጠቃላይ ሁኔታውን መጠየቅ እንጂ ሁለት መሳሪያ ካሉ የሚቀጥለው ጥያቄ ተመልሷል ማለት ነው ሁለት መሳሪያዎች ነው የተገኙ እያሉ ነው ይሄ ደግሞ እንደክሱ ጭብጥ ማስረዳት ሳይሆን እንደመምራት ነው ለዚህ ፍ/ቤቱ ይሄንን ጥያቄ እንዳይመለስ ውድቅ እንዲያደርግልን ነው

እሺ ለፍ/ቤቱ የምንገልጸው እንደውም መሳሪያውን አንድ ታጣፊ ክላሽና አንድ ኤስ ኬ ኤስ ብሎ ራሱ ገልጾታል ከእኔ ቀድሞ ማለት ነው ያ መሳሪያ የት ተያዘ እያልኩኝ እየጠየኩት ነው ስለዚህ ምንም አልመራሁም ከእኔ ቀድሞ ነው የመሳሪያውን ዝርዝር ሁላ የተናገረው እኔ ምናልባት በስም መጥራቱን ትቼ ሁለት ስላልኩ

ፍ/ቤቱ ጥያቄው ይቀጥል ብሏል

እሺ አሁን የገለጽክልንን ታጣፊ ክላሽና ኤስ ኬ ኤስ መሳሪያ መርቶ ያሳያቸው የት ነው

ከሚኖ ከተማ 2:00 ሰዓት ርቀት ነው በእግር ጉዞ ቡርቃ ነገያ የሚባል ቀበሌ ውስጥ ነው

እሺ ከሚኖ የ2:00 ሰዓት መንገድ የሚኬድበት ቡርቃ ነገያ የሚባል ቦታ ወስዶ አሳያችሁ

አዎ

ቅድም ሰውየውም ባላውቀውም ፊልም አለ ስትል ነበር የምን ፊልም ነው

የቪዲዮ ካሜራ ነው

ምንድን ነው ምን የተደረገ ነው

ቪዲዮ ካሜራ ቦታውን ቆፍሮ አውጥቶ ለፖሊሶች ሲሰጥ

ምን ምን ሲሰጥ

መሳሪያውን

599

የቱን መሳሪያ

አንድ ክላሽ ባለአንድ እግር ታጣፊ እና አንድ ኤስ ኬ ኤስ

ማን የሰጠው መሳሪያ ነው እሱ መሳሪያ

ከአነግ ነው የወሰድኩኝ ብሎ ራሱ ተናግሯል

አበቃችሁ ጥያቄ

መሳሪያዎቹ እነዛ ያሳያችሁ መሳሪያዎች የት ደረሱ መጨረሻ ላይ

ፖሊስ ነው ይዞ የሄደው

ጨርሰናል

መስቀለኛ ጥያቄ አለ ተከላካይ ጠበቃ ቆይ አንዴ

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

አቶ በድሪ አብዱልከሪም ዛሬ ለምስክርነት ነው የመጡት በምን ስራ ነው የሚተዳደሩት

እኔ የመንግስት ሰራተኛ ነኝ

ስለዚህ አንድን ተከሳሽ ቃሉን ሲሰጥ ቦታ ወስዶ ሲመራ ቪዲዮ ሲቀረጽ ይዤንን ሁሉ ስራ መስራት ምንድን ነው የምሰራው ነው ያሉኝ

እኔ ለስራ ጉዳይ ነው እዛ አካባቢ ያለሁት

ምንድን ነው የሚሰሩት ነው ያልኩት

የመንግስት ሰራተኛ ነኝ ብለዋል

የመንግስት ሰራተኛ ነኝ

ስለዚህ ይዤንን ሁሉ ጊዜ ሲያሳልፉ በመንግስት ስራ ላይ ሳይገኙ ነው እንዴት ሊገኙ ቻሉ እሺ

ነኝ በስራ ላይ ነኝ

ስራዎት ----------

አጋጣሚ ነው እዛ የተገናኘነው እንጂ እኔ ለስራ ነው እዛ ያለሁት ሁኔታውን ሳይ እንደምጠየቅም አውቃለሁ በኋላ በምስክርነት

አደለም አቶ በድሪ ላስቁሞትና ጥያቄዬን አልመለሱልኝም ይሄንን ሁሉ ድርጊት ለመከታተል አንድ የመንግስት ሰራተኛ ስራውን ትቶ ሊንቀሳቀስ ይችላል እርሶ እንዴት ይሄንን ሊያደርጉ ቻሉ ነው የእኔ ጥያቄ

ይሄንን ላደርግ የቻልኩት እኔ ምስክር ሲሰጥ በምስክርነት ይቀርባል

ቆይ እስቲ አንዴ አንዴ ቆይ መቃወሚያ ስለተነሳ መቃወሚያውን እናድምጥ

ማንኛውም ሰው ፍትህን የመርዳት ግዴታ አለበት ይኼ ሰው የመንግስት ሰራተኛ ነው ስራዬ አይደለም ነገር ግን ስለምጠየቅ በወቅቱ 2:00 ሰዓት የፈጀም ቢሆን አይቻለሁ እያሉ ነው ለምን አዩ እየተባሉ እየደጋገሙ ሊጠየቁብን አይገባም::

እሺ ጥሩ እዚህ ላይ የምትሉት አለ

ጥያቄው ብይን ይሰጠው ፍ/ቤቱ

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበታል በሁለት መልክ ነው በማሳሰቢያም በአጠቃላይ በአመራሩ ላይ ጥያቄዎቹ አንደኛ ወደ ጭብጡ ዙሪያ የሚያነጣጥሩ ይሁኑ ሁለተኛ የሚጠየቁት ጥያቄዎች ተገኝቻለሁ ብለዋል ለምሳሌ ምስክሩ የመንግስት ሰራተኛ ነው ስለዚህ እዛ የተገኘበትን ምክንያት ለመጠየቅ ከተፈለገ በአጭር ጥያቄም ማቅረብ ይቻላል እና አቀራረቡ ይቀየርና ጥያቄውን ፈጠን ብላችሁ ማቅረብ የምትችሉበትን ሁኔታ እየተከተላችሁ ጥያቄ አቅርቡ ተስተካክሎ ይቅረብ ጥያቄ በአጭሩ::

እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ተቀብለናል ብይኑን ቅድም ምስክርነት ሲሰጡ የቪዲዮ ካሴት ነው አለኝ ያሉት

አዎ

እርሶ ጋ ነው ያለው

600

አዎ እኔ ጋር ነው ያለው

እንዴት እርሶ እጅ ሊገባ ቻለ

ሰራተኛ ነኝ ባለሞያ ነኝ ደግሞ እኔ

የምን

የካሜራ

ሆነ ብለው እርሶ ጋ ለምን ያዙት ካሴቱን

ሆነ ብሎ አይደለም የመስሪያ ቤቱ ሰራተኛ ስለሆንኩ ዶክመንቱ በእኔ እጅ ነው ያለው

የመስሪያ ቤቱ ንብረት ነው ወይስ የእርሶ

አዎ የመስሪያ ቤቱ ንብረት ነው

ስለዚህ ተከሳሹ ድርጊቱን ፈጸምኩ ብሎ ሲያወራ ተገዶ ይሁን አይሁን የሚያውቁት ነገር አለ

ፈጸምኩ ብሎ ሲያወራ በራሴ ብቻ ነው የሰማሁት ቪዲዮ መከታተል የጀመርኩት ስለሰማሁ ምስክርነቱን አወኩ ከዛ ቀጥሎ ነው በቪዲዮ እንትን ማለት የጀመርኩት እንጂ

እሺ ምስክርነት አሁን ለምስክርነት ሲመጡ ለህግ ለመከባበር ማስታወስ እንዳለቦት ተናግረዋል ይሄ ጥሬ ነው ስለዚህ በወቅቱ ያዩትን ተከሳሽ በቪዲዮ ቀርጸው ያስቀሩትን ተከሳሽ እንዴት ከዚህ ውስጥ መለየት ያቅቶታል

ስለማንተዋወቅና ቅርብነት የለንም

ቪዲዮ ካሴቱ በእጄ አለ ብለውኛል እኮ

አዎ

ስለዚህ አሁን እንዴት ሊለዩት አይችሉም

ካሴቱንም ደጋግሜ

አልቻልኩም መለየት ለጊዜው ብለዋል ሌላ ጥያቄ

601

ጨርሻለሁ

አላችሁ ድጋሚ ጥያቄ ዐ/ህግ

የዐ/ህግ ድጋሚ ጥያቄ

ይሄንን ቪዲዮ ካሴት ያሉትን ከፍተው ያዩታል እንዴ እርሶ በቀን በቀን እየከፈቱ ያዩታል ሰውየው መልኩን

ደጋግሜ አልከፈትኩም አሁን ለምስክርነት ስጠራ ነው አንስቼ ያመጣሁት

አሁን ይዘውታል እንዴ የታለ እስቲ

አለ አዎ እዚህ ውጪ ነው ያለው

ምናልባት ፍ/ቤቱ ለትክክልኛ ፍትህ አሰጣጥ ይሄንን የቪዲዮ ማስረጃ ቢያየው የተሻለ ይመስለኛል

አበቃችሁ አደለ

ጨርሰናል

ጥሩ እሺ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ

ኢብራሂም አብዱላ ዋሪዬ አሁን ስሙ ተጠርቶ በችሎት የተነሳውን ተከሳሽ ታስታውሰዋለህ በችሎት እስቲ እየውና

አዎ

እሱ ነው

---------- እንጂ ጠርጥሬው ነበር

አሁን በደንብ አየከው

አዎ

602

አረጋገጥክ እሱ ነው

አዎ

ሰፋ ብሎብሃል

አዎ

የሰውነት ለውጥ

ወፈረ አዎ

ሌላ ምን ለውጥ አየህበት

የእስልምና ምልክትም ትንሽ ግንባሩ ላይ በደንብ ይታያል አሁን ጎላ ብሎ በዛን ጊዜ እንደዚህ አይደለም

አልነበረም ስለዚህ አሁን በእርግጠኛ እሱ ነው

አዎ

ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ነው

ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ነው የሚሰሩት የት

ጎሎዳ

ቦረዳ

አዎ

በዚህ ምክንያት ነው አሁን ያሉት ቪዲዮም ሌላውም በዚህ የስራ ሃላፊነቶት ነው ሊያዩም ሊያስቀምጡም በእጅትም ሊገኝ የቻለው

አዎ

በስራ ምክንያት ማለት ነው

603

በስራ ምክንያት አዎ

አሁንም በማስታወቂያ ስራ ላይ ነው ያሉት

አዎ

በዚህ ጉዳይ ተጠርተው ነው ሊገኙ የቻሉት በአጠቃላይ

አሁን

አዎ አይ በፊትም ያዩት በዚህ ስራ ላይ

በፊት ፖሊስ ጣቢያ ድምጹን ቃላቸውን ሲሰጡ ነው የሰማሁት እና ስሰማ አዳመጥክ አደለም አዎ ሰማሁ ብዬ እኔም መስማቴን ስነግራቸው እንደምስክርነት ተነገረኝ ለምስክርነት በኋላ እንደምቀርብ ከተነገረኝ በኋላ እዛ ---------- ስንገናኝ ተከታተልኩ ማለት ነው በካሜራ

ጥሩ ነው ከዛ በኋላ የካሜራ ባለሞያ ስለሆኑ እና የማስታወቂያ ስራ ሃላፊነት ስላለቦት በካሜራም ተከታትዬ አግዤ ይሄንን ነገር ተከታትያለሁ ነው

አዎ

በመንግስት ሃላፊነትም በተጨማሪም ደግሞ እንደማንኛውም ሰው ፍትህን ለመርዳት ምስክርትነ ለመሆን ማለት ነው እንደዛ ነው ለማለት የፈለጉት

አዎ እንደዛ ነው ለማለት የፈለኩት

አሁን ማንኛውም የማስታወቂያ ስራ ዶክመንት እርሶ እጅ ነው ያለው የወረዳዋ

ማንኛውም አዎ የተቀረጸና የሰራነው

አዎ

አዎ የሰራነው

እርሶ እጅ ነው የሚገኘው

አዎ

ቅድም ያሉት ነገር ለማስታወቂያ አሁን እንዳሉት ለዛው ስራ ተብሎ ነው አብረው የሄዱት

ለማስታወቂያው ሳይሆን እኔ እዛው ስለነበርኩ ሲሄዱ ነው ተገናኝተን

አብረው ተከትለው ሄዱ ቃሉን ስለሰጠ ከዛ ተከትለው

አዎ ተከትዬ ሄድኩኝ

ተጽፏል ቃሉ ላይ ተፈርሟል ያስታውሳሉ

አዎ

መፈረሙን ያስታውሳሉ

አዎ

ይሄ ቪዲዮ ክር አሁንም አለ እንዴ እጆት ላይ

አዎ

የተቀዳው

ካሴቱን ይዣለሁ አዎ

የት አለ

እዚህ ውስጥ ነው ያለው

እስቲ ይስጡን

ላምጣው

እስቲ አምጡላቸው ይቀመጥ ያመጡት እቃ የት ነው ያደረጉት ፌስታል ወይ ቦርሳ ቶሎ በሉ ቪዲዮ የተቀረጸው እሳዩላይ የተፃፈ ነገር አለው እንዴ ከላይ

ከላይ የተፃፈ አለ አዎ

ምን ይላል

605

ቁጥር አንድ እና ቁጥር ሁለት የሚል ተፅፎበታል

ሌላ መግለጫ አልተፃፈበትም

አልተፃፈበትም

ከየት እንደመጣ ምንጩ ምን እንደሆነ ዘገባ የለውም ከላይ

ምንም የለውም

የለውም

ሌላ የልማት ስራዎች ስላሉበት ካሴቱ 3፡10 ሰዓት ነው

ጥሩ

ስለዚህ በቁጥር ብቻ ነው የሚለየው እንጂ

ጥሩ የ3፡00 ሰዓት ካሴት ነው

አዎ የ3፡00 ሰዓት ነው

እዛ ውስጥ ምን ምን እንደተያዘ እርሶ ያስታውሳሉ ካዩት በቃል

ሁሉንም

ምን ምን አለበት ውስጡ

የልማት ስራዎች ናቸው

አሉ

አዎ መንገድ የሚሰራበትና ችግኝ ተከላ ብዙ ነገር አለ

አለበት በተጨማሪ ይሄ አሁን ምስክርነት የሰጡበት ነገር አለ

አዎ

እነዚህን ነገሮች ይይዛል

606

አዎ

ማስታወቂያው ጽ/ቤቱ ወይም ቢሮው ፈቅዶ ነው ይዘው የመጡት እርሶ ወደዚህ ፍ/ቤት ድንገት ከተጠየቀ ብለው ነው

አዎ ከተጠየኩኝ ሰው ገጠር ውስጥ በነበረና እዚህ በነበረበት ጊዜ ምስሉ እኩል ስለማይመሳሰል ከተጠየኩኝ ማስረጃ ይሆናል ብዬ ነው አስፈቅጀ ነው ያመጣሁት

በነማን ጉዳይ የተቀዳ ካሴት ነው ያሉት

አይ

መግለጫ የለውም ጠቅላላ የወረዳው ነው

ምንም የለውም

የምን ወረዳ ማስታወቂያ ቢሮ ነው

የጎሎዳ

የጎሎዳ

ወረዳ

የጎሎዳ ወረዳ ማስታወቂያ ቢሮ ንብረት የሆነ አንድ ካሴት ነው የ3:00 ሰዓት ካሴት

አዎ

ጥሩ ፍ/ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ ትፈልጉታላችሁ እንዴ ካሴቱን

አዎ

ሌላ ቅጂም የላችሁም

ሌላ ቅጂ የለንም

በአንድ ኮፒ ነው ያለው

አንድ ብቻ ነው

የፌዴራሊ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር ፡ ፡

607

ጥሩ ይሄንን የተባለውን ካሴት ፍ/ቤቱ በማስረጃነት ስለሚመለከተው በመጣበት ሁኔታ በተለመደው የመንግስት ንብረት ማስረከብ ሂደት ተጠብቆ ለፍ/ቤቱ ሬጅስትራር አሁን ያስረክባሉ

እሺ

ገብቶታል አደለ

አዎ

ሬጅስትራር ጽ/ቤት ይሄዱና ለአስተዳደር ይረካከባሉ በምትፈልጉበት ጊዜ ይወስዳሉ ወይም ደግሞ ቀሪው ወደፊት ተሰርቶ እናንተ ዋናውን የምትወስዱበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ ያመቻቻል ለአሁን ግን ዛሬ በመጣበት ሁኔታ ለሬጅስትራር እንዲያስረክቡ ፍ/ቤቱ አዟል እዛ ይሄዳሉ በዚሁ ምስክርነቶን አብቅተዋል መሄድ ይችላሉ እናመሰግናለን::

እሺ አመሰግናለሁ

ቀጣይ ምስክር ማን ይጠራ ዐ/ህግ

ሞጌ አብዱላሂ የዐ/ህግ 51ኛ ምስክር

ማን ሞጌ

ሞጌ አብዱላሂ

ሞጌ አብዱላሂ በስንተኛ ላይ ነው ስንተኛ ምስክር ነው

የዐ/ህግ የክስ ቻርጅ ላይ 51ኛ ምስክር

በስንተኛ ላይ ነው

በ1ኛ በአብዱረሃማን ባሌ በ8ኛ ፋጥሽ የምትባለው ታማለች የተባለችው እና 14ኛ ተከሳሾች ላይ በሶስቱ ላይ ነው የሚያስረዳው

እሺ ጥሩ ሞጌ አብዱላሂ ይጠራ አስተርጓሚ የለም እንዴ ምንዳ

በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ::

608

51ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ስም - ሞጌ አብዱላሂ

አድራሻ- ምስራቅ ሐረርጌ ጎሎዳ ወረዳ

ለምስክርነት ነው የመጣከው

የዐ/ህግ ምስክር ሆኜ

በማን በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

አብዱረሃማን ባሌ ላይ እና ኢብራሂም ደሬሳ ላይ ነው

ኢብራሂም ደሬሳ እና አብዱረሃማን ባሌ ሌላ

ፋጥሽ

ጥሩ በእነዚህ ላይ ነው የምትመሰክረው

አዎ

ተጣልተሃል እንዴ ከእነዚህ ጋር ዝምድና አለህ

የለኝም

ጥሩ እነዚህን ሰዎች አሁን ለይ እስቲ ተነስና እዚህ መሀል ካሉ እሺ ና ቁጭ በል በለው ማን ነው ስምህ አንተ ኢብራሂም ማን ሁሴን ጥሩ ዐ/ህግ ዋና ጥያቄ መቀጠል ይችላሉ

የዐ/ህግ ዋና ጥያቄ

እሺ ሞጌ ፋጥሽ በምትባለዋም ላይ እመሰክራለሁ ብለሃል ፋጥሽን አየሃት እንዴ እዚህ ውስጥ

አሁን አላየኋትም አላወኩም

እሺ አሁን አላየኋትም ብለሃል አሁን ሁለቱ የለየካቸው ሰዎች አሉ ትለያቸዋለህ በስም ማን ማን ናቸው

ይሄ አብዱረሃማን ባሌ ይባላል

ያንኛውስ

ያ ኢብራሂም ደሬሳ ይባላል

ኢብራሂም ደሬሳ እሺ በእነሱ ላይ የምታስረዳው ምንድን ነው

በ1998

ትንሽ ድምጽጎን ከፍ አድርገው

ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት ሲሆን ከተማሪዎች ጋር ጉዞ በቁጥር የማይታወቁ ተማሪዎች ጋር ሆኖ መሳሪያ ታጥቆ የሚሄድ ሚኒሻ ከእነሱ ጋር ስር ተከትለው ጠብቅ አትወጣም ትሞታለህ ጠብቅ ብለው ሲሉት የእኛም ፋጥሽ መጥተህ ነው ወይ የምትሄደው አንተም አትሄድም ቁም እያሉ ሲሉት በዚህም በዚህም ተማሪዎችን አድርገው አንተም አትወጣም እሱንም ወደታች መሳሪያውን ዘቅዝቆ ህግ ካወቃችሁ ቁሙልኝ ወደዛ ከላዬ ላይ ብሎ ከስሬ ቅሩ ብሎ ሲላቸው እነሱም ደግሞ ወደእሱ ሲጠጉ

ማን ነው ከስሬ ቅሩ ሲል የነበረው

መሀዲ መሀመዶ አብዱላሂ ይባላል

መሀዲ መሀመዶ አብዱላሂ ማን ነው ምንድን ነው የሚሰራው

ሚኒሻ የሚኒሻ ዘርፍ ነው

እሺ እሱ የሚኒሻ ዘርፍ ነው እሱ በህግ አምላክ የሚለው ማንን ነበር

አብዱረሃማን ባሌ እና ይሄ ኢብራሂም ደሬሳ እና ብዙ ተማሪዎችም የማላውቃቸው ቁጥራቸውን

እሺ ምን አድርግ ሲሉ ነው እሱ በህግ አምላክ ሲል የነበረው

ፋጥሽ የእኛ ልጅን መተህ አትሄድም አትወጣም ብለው እያሉት ነበር

እሺ ከፋጥሽ ጋር በምን እንደተጣሉ ወይም ለምን እንደመታት የምተውቀው ነገር አለ ወይ ይሄንን ሚኒሻ በምን ምክንያት ነው የምታውቀው ነገር አለ ወይ

ጠዋት ፋጥሽን አግኝተው ይሄ ነገር አያስፈልግም አቁሚ ብለው ሲሏት

ምኑን ነው አያስፈልግም አቁሚ ብዋት የነበረው ፋጥሽን

እሱ ሚኒሻ ዘርፍ ስለሆነ ይሄ ቅስቀሳ ምናምን ነገር አይሆንም

የምን ቅስቀሳ ነው አይሆንም ያለው

የቡርቃ ውስጥ ያለ ተማሪዎችን እየቀሰቀሱ ነበር

ምን ብለው ነው የሚቀሰቅሱት

ከመንግስት ቅስቀሳ ያደርጉ ነበር ወደ መንግስት ነው

ምንድን ነው ግልጽ አድርግልን እንደዚህ እንደዚህ ብለህ ግለጽ

የአባዎ ማለት የኦነግ ሰራዊት የእሱን ተገንብቶ ቅስቀሳ ያደርጉ የነበረ ነው

እነማን ናቸው በአባዎ በኦነግ ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ የነበሩት

አብዱረሃማን ባሌ ደሬሳ እና ፋጥሽ ናቸው

እንግዲህ ከዚህ በኋላ ይሄ ታጣቂውን ምን አድርግ ነበር ሲሉት የነበረው ሁለቱ

እኔ በዛን ሰዓት የጤና ጣቢያ ጥበቃ ሰራተኛ ነበርኩኝ ስሩ እየተከተሉ ቁም ሲሉት የዛን ሰዓት እኔ አልፈውኝ እንዳለፉ አልፈውኝ ትንሽ እንደሄዱ ሁለት ጥይት ወደ ሰማይ ተተኮሰ ከዛ በኋላ ሲበታተኑ የወረዳው ፖሊስም መጥቶ አንዳንዱን ሰዎች ይዘው በህግ ጥላ ስር አውለው ሌሎቹ ተበታትነው ሲጠፉ እኔ ይሄንን ነው የማውቀው በ1998 ዓ/ም ነው

ይሄ በ1998 ያልከው ወሩ እና ጊዜውን ታስታውሰዋለህ ወይ

ቀኑንና ወሩን አላስታውሰውም ሰዓቱን ግን አስታውሰዋለሁ ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት ላይ ነው

እሺ በ1998 ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት ላይ ነው ብለሃል ወሩና ጊዜውን አላስታውስም ብለሃል ከዚህ ጊዜስ በኋላ ከዚህ ሚኒሻውን ተዉ ሲላቸው እነሱ ፋጥሽን መታት ባትሄድም እያሉ አንባጓሮ

611

የፈጠሩ መሆኑን ሁለቱ ክሌሎች ተማሪዎች ጋር ሆነ ነግረከናል ሰበቡ ያው ቅድም የዘረዘርክልን ነው ነገር ግን ከዛ በኋላ ከዛን እለት በኋላስ ምን እንቅስቃሴ እንደነበራቸው የምታወቀውን -------

አላችሁ መቃወሚያ እሺ መቃወሚያ

በክሳቸው ላይ በ2ኛ ክስ በ1ኛ በ8ኛ እና በ12ኛ ተከሳሾች ላይ

14ኛ እሺ

ከዛ በኋላ ስለተደረገው ክስ አልቀረበባቸውም በእለቱ ስለተፈጸመው ምስክራቸው አስረድተዋል ይሄ ጥያቄ ሊጠየቅም ሊመለስም አይገባውም

እሺ በእናንተ በኩል ዐ/ህግ

ተከሳሹ በእለቱ የነበረውን ሁኔታ ተናግሯል በ1998 ወሩ እና ጊዜውን አላውቀውም ብሏል እንግዲህ 1998 መስከረም ይሁን ጥቅምት ይሁን ህዳር ይሁን አይታወቅም ከዛስ በኋላ እሱ ከሚለቀን በኋላ ባሉት ጊዜአት ውስጥ ምን አይነት እንቅስቃሴ ያደርጉ እንደነበረ እንዲያስረዳልን ነው ለፍ/ቤቱ በቀጥታ የሚያውቀውን ነገር እንዲያስረዳ

እሺ ፍ/ቤቱ ተነጋግሮበታል ጥያቄው ይቀጥል እስቲ ፈጠን አድርጉት

አንተ ያልከን አሁን 1998 ላይ ነው ከ1998 በኋላስ የእነዚህ የሁለቱን ተከሳሾች ድርጊት ወይም ደግሞ እንቅስቃሴአቸው ምን ይመስል ነበር ምንድን ነው -------- ከዛን ቀን በኋላ ሚኒሻውን ካባረሩ በኋላ

አብራሂም ደሬሳ የአባዎ ወታደር የኦነግ ሰራዊት መሆኑን ሰምቻለሁ ከዛ በኋላ አብዱረሃማን ባሌ እና ፋጥሽ ደግሞ ከህብረተሰቡ ላይ ገንዘብ እየሰበሰቡ ሲወስዱ አውቃለሁ

ለማን ነው የሚወስዱት

አባዎ የሚባሉት ሰራዊቶች ላይ

ጨርሰናል

እሺ መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ይቀጥል አማክሯቸው ምክርም ከፈለጉ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር

6/12

የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

እርሶ እና እነ አብዱረሃማን በአንድ ከተማ ውስጥ ነው እንዴ የሚኖሩት

አዎ አንድ ከተማ ውስጥ ነው የምንኖረው

ዐ/ህጉ ሲጠይቆት ከዛ በኋላ ስለፈጸመው ድርጊት እየነገሩን ነበር እና በዚህ ጉዳይ ላይ ሌላ ፍ/ቤት ቀርበው ምስክርነት ሰጥተው ነበር

አዎ ሰጥቻለሁ ፍ/ቤት

የት ፍ/ቤት ነው የሰጡት

የወረዳው ፍ/ቤት

የወረዳው ፍ/ቤት ላይ የሰጡት ምስክርነት እና አሁን የሰጡት ምስክርነት አንድ ነው ወይ

የበፊትም የአሁኑም ልክ ነው የፊቱም የአሁኑም ቃሌ ልክ ነው ያው ሰማሁ ብያለሁ

ሌላ ጥያቄ

እሺ ተቀጡ እንዴ በዛ ምስክርነቶት እዛው ፍ/ቤት

ተቃውሞ አላችሁ

አዎ

እሺ ተቃውሞ

በዚህ ጉዳይ ላይ በሌላ ፍ/ቤት ቀርበው አልተቀጡም የተቀጡም ከሆነ በመቃወሚያቸው ላይ አንስተው እንትን ይባል ነበር እኛም ከተቀጡ የምንቀበለው ነገር ስለዚህ ጊዜ ማጥፋት ብቻ ነው ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ ነው በዚህ ጉዳይ ተቀጡ እያሉ መጠየቅ በሌላ ጉዳይ በሌላ ክስተት ሊሆን ይችላል በዚህ ጉዳይና በዚህ ክስ ግን እዚህ ፍ/ቤት ነው የቀረቡት

እሺ አጭር አድርጉት በእናንተ በኩል መጀመሪያ

በእኛ በኩል የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ መስክሬአለሁ ሌላ ፍ/ቤት በዚሁ ጉዳይ ላይ መስክሬአለሁ ሌላ ፍ/ቤት ተብሏል

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

63

ስለዚህ ውጤቱን እየጠየቅነው ነው

አዎ ተቀጥተውበታል እሳቸውም ስለሚያውቁ ነው

እሺ አጭር አድርጉትና ጠይቁ ጥያቄው ይቀጥል

እሺ ምንድን ነው የተቀጡት የተቀጡትን ያስታውሳሉ

ታውቃለህ አታውቅም

ምንም እንደተቀጣው ምንም አላውቅም እኔ መጥቼ ምስክርነት ቃሌ ብቻ መስጠቴን ነው

እሺ በቃ አላውቅም ብለዋል

የዛን ቀን ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ቀን ከጠዋት ላይ ፋጡማን ተይ ሲላት ነበር ሚኒሻው ብለዋል የት አካባቢ ነው እንደዚህ ያላት

ቦታው የት ነው

ቡርቃ ከተማ ውስጥ ሁለተኛው ቁጥር 2 መንደር ነው

ቡርቃ ቅድምም ተናግረዋል

እርሶ የት ነበሩ ታዲያ በወቅቱ ይዜንን ነገር ሲላት

እኔ የዛን ሰዓት ያየሁት ይዜንን ሰማሁ የፋጥሽን ጉዳይ ሰማሁ እንጂ ምክንያቱ ለዚህ የሆነው የእሱ ጉዳዩ ከዛ የተነሳ ነው ሰማሁ እንጂ እኔ አላየሁም ሰማሁ ነው

ሰማሁ ነው እሺ ሰማሁ ነው አላዩም ማለት ነው ሌላው ገንዘብን መሰብሰብ በተመለከተ ገንዘብ ሲሰበስቡ በአይኖት አይተዋል

እሱንም ሰማሁ እንጂ አላየሁም

ሰማሁ ነው ያሉት ቅድመመመ

በቃ ጨርሰናል

እሺ ድጋሚ ጥያቄ አለ ዐ/ህግ

6/4

የለንም

እሺ

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ፋጥሽን ማን ነው የመታት በለው

መሀዲ መታት ብለው ነው ያሉት

በምንድን ነው የመታት

ሰማሁ እንጂ አላውቅም

መታት ሲባል ሰማህ

አዎ

እነዚህስ ምን አደረጉ ታዲያ

የሰው ልጅ መተህ ትሄዳለህ ወይ ቁም አንተ አንተም ትሞታለህ አትሄድም ብለው ሲሉ ነበር እሱ መሳሪያ ይዞ ሲሄድ እነሱ ደግሞ ድንጋይ ይዘው ይከተሉት ነበር እሱ ደግሞ

--------- የሄደውን ሰው ለማስቆም ነው ጥረታቸው

በዛኑ ሰዓት እነሱ ልጅቷ የተመታችበትና ይሄ ነገር የሆነበት ቦታ እሩቅ ቦታ ነው ልዩነት አለው በጣም ከተማ ውስጥ ይሁን እንጂ የተለያየ ቦታ ነው

ታዲያ ቅድም ከምን ጋር ነው ያገናኘከው

እኔ ያየሁትን ነው የተናገርኩት

ከምን ጋር አገናኝተህ ነው ያየኸው

---------- ሰው መታ ደሰው የመታውን ሰው ሰዎች ተከተሉት ሌላ ምን ሚስጥር ነበረው ይሄንን ነው ያየኸው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፓብሊክ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4

6/5

ምንም ነገር እኔ ሚስጥሩን አላውቅም ግን እነሱ እየተከተሉት ሲሄዱ ጠዋት ነው ያየሁት የዛን ሰዓት

ምናልባት እነ አብዱረሃማን ባሌ በኦነግ ስር ተደራጅተዋል ብለሃል እሱን በምን አወቅህ በለው

ሰማሁ

ከማን ነው የሰማከው

ከህብረተሰቡ እና ከሰው ነው የሰማሁት

እንጂ ኦነግ ሆነው አላየካቸውም አንተ

አላየኋቸውም እኔ ሰማሁ እንጂ

እሺ እናመሰግንሃለን መሄድ ትችላለህ ጨርሰሃል ማን ይጠራ ሌላ ዐ/ህግ

ሀሰን አወል 63ኛ የዐ/ህግ ምስክር

ኢብራሂም አብደላ ዋርዬ ይሄ ሰው

እኛ በ8ኛ እና በ14ኛ ተከሣሽ ላይ ነው ግን 8ኛ ተከሣሽ ፋጥሽ የምትባለው የለችም ስለዚህ

19ኛ

8ኛ 8ኛ ፋጥሽ የምትባለው

8 የሚቀጥለው ማን ነው

ምስክሩ 63ኛ ምስክር ነው

አይደለም 1 8 19 ነው 14ኛ ነው

14

እርግጠኛ ነህ

ቆይ ቆይ አንድ ጊዜ ቼክ ላድርገው እሺ አዎ

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍ/ቤት ቁጥር 2 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

616

19ኛ

14

14ኛ

አዎ

ጥሩ ቀጣይ 4ኛ የዐ/ሕግ ምስክር በዛሬው እለት ቀርበዋል

4ኛ(14) የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - ሀሰን አወል

አድራሻ - ጮሎጋ ወረዳ ቡርቃ ከተማ ነው የመጣሁት

እሺ ለምስክርነት ነው የመጣከው

አዎ

በማን ላይ ነው የምትመሰክረው

አብዱራህማን ባሌ ኢበራሂም ሁሴን ፋጥሽ ላይ

ጥሩ ከእነሱ ጋር ፀብ ዝምድና አለህ

የለኝም

እስቲ ካሉ እዚህ ውስጥ አሳይ ተነስና ፈጠን በል በለው እስቲ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ አጭር

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ ሀሰን በፋጥሽም ላይ እመሰክራለሁ ብለሀል ፋጥሽ አለች እንዴ እነዚህ ከሴቶች ውስጥ

እሺ ዐ/ሕግ አለየም እኮ ስለዚህ ቀጥሉ ጥያቄ የለችም ማለት ነው

እሺ የለችም አሁን የለየክልን 2 ተከሣሾች አሉ እስቲ አማርኛ ትችላለህ እንዴ እሺ የለየክልን 2 ተከሣሾች አሉ ምን አድርገው ነው የተከሰሱት እስቲ የምታውቀው ነገር ካለ ለፍ/ቤቱ አስረዳልን

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ጋፋት ወረዳ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፕሮሰስ

6/7

እነዚህ ሰዎች በ1998 ዓ/ም

እሺ

ከጠጂቱ 4፡00 ሰአት አካባቢ ቡርቃ ከተማ ውስጥ ማህዲ መሀመዶ የሚባል ሰው የወረዳው የሚኒሻ ዘርፍ ሀላፊ የሆነ ሰው እሱን ድንጋይ ይዘው እሱን ሲያባርሩ ደረስኩ እሱ ሙሉ ትጥቅ ይዟል መሳሪያም ይዟል በእጁ የወያኔ መልክተኛ ብለው ከተማ ውስጥ ሲያባርሩ ድንጋይ እየወረወሩ አይቻለሁ

ብቻቸውን ናቸው ብቻቸውን ነበሩ

ቁጥራቸው የማይታወቁ 40 ወይም 50 በላይ የሆኑ ብዙ ልጆች ነበሩ

ነበሩ

አዎ

በምን ምክንያት ነው በምን ሰበብ ነው ሚኒሻውን አንተ የወያኔ መልክተኛ ነህ ብለው በድንጋይ ሲያባርሩት ያየከው

እዛ ምክንያቱ የተነሳው ፋጥሽን ይዜ ነገር ጥሩ አይደለም ጥሩ አይደለም ብሎ ሲል

ምኑ ነው ጥሩ አይደለም ብሎ ያላት ማነውስ እንዲህ ብሎ ያለው

መሀዲ ነው

መሀዲ ማለት ምንድነው

ሚኒሻ ዘርፍ ሀላፊ ነው

እሺ ሚኒሻው መሀዲ ፋጥሽን ይዜ ነገር ጥሩ አይደለም ብሎ ያላት ምንድነው ምን ስታደርግ ነው ምንድነው ነገሩ

በመንግስት ላይ ሰዎችን እየሰበሰበች ልጆችን እያነሳሳች ስድብ ይሳደባሉ በመንግስት ላይ ነው

ምን ብላ ነበር የምታነሳሳው እሷስ ምን ነበረች በወቅቱ

በእዛ --- የተማሪዎች እንቅስቃሴ ነበረ እዛ

6/8

የምን እንቅስቃሴ ምንድነው ምን አይነት እንቅስቃሴ ነው እንቅስቃሴውን ለይልን

በመንግስት ላይ እረብሻ ማስነሳት

እሺ በመንግስት ላይ እረብሻ ማስነሳት ነው

አዎ

ያንን ነገር ነው ፋጥሽን ተይ የተባለችው ብለሀል ፋጥሽ ሰዎቹን ወይንም ተማሪዎቹን ወይም ልጆቹን ምን እያለች ነበር የምታስነሳው ቃል በቃል እንዲህ በሉ እያለች የምትለውን ነገር ንገረን

አባዎ ከዚህ አነግ ከዚህ መንግስት ያስተዳድር ይሄ መንግስት ይፍረስ እያሉ ነበረ የሚሉት

እሺ ይሄ መንግስት ይፍረስ አባዎ ያስተዳድር እያለች ትል ነበረ ብለሀል ይሄንን ነገር ተይ ስላለ ነው እሱን በድንጋይ ያባረሩት ብለሀል እነሱ ምነ ነበሩ እነሱ ይሄ እነዚህ 2ቱ ተከሣሾች በወቅቱ የፋጥሽን ሚና እና ፋጥሽ ስታደርግ የነበረውን ነገርከን እነሱ በድንጋይ ሲያባርሩት ነበር ብለሀል ምን ምንድናቸው እነሱ

እሱን እያባረሩ ሲመጡ በድንጋይ ተው እናንተ ሰዎች ምን አደረገ ይሄ ሰውዬ ብዬ ስላቸው ዝም በል አንተ እራስህ የተገዛህ ነህ ብለው አስፈራሩኝ እኔንም

እሺ እሱ ብቻውን ነው እነሱ በርካታ ናቸው ብለሀል ታዲያ መጨረሻው ምን ሆነ ለበርካታ ሆነው ሲያባርሩት ምን ሆነ መጨረሻው

እያባረሩት ስለሆነ ከስሩ አልቀርም ሲሉት 2 ጥይት ተኮሰ እና ወደ ሰማይ ከእዛን ለአት ከስሩ ቀሩለት ነው እሱ እየተናገረ ነበረ እግዚያብሔርን ፍሩ ህግ ካወቃችሁ ከእኔ ስር ቅሩ እያለ ነበረ የሚሄድ የነበረው

እሺ

እዛ 2 ጥይት ተኮሰ እና ከስሩ ቀሩለት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲ/ሪ ፐብሊክ ፍ/ቤት ቁጥር 4

619

እሺ 2 ጥይት ተኮሰ ከስሩ ቀሩለት ብለከናል ከእዛስ በኋላ ተከሳሾቹ ምን ሲያደርጉ ነው የምታውቃቸው ከእዛን እለት በኋላስ ባለው ጊዜ እነዚህ 2ቱ ተከሣሾች እንቅስቃሴያቸው ምን ይመስል ነበር ምን ነበረ የሚያደርጉት

እኔ የማውቀው አብራሂም ሁሴን ወይንም አብራሂም ደረሳ ይባላል የኦነግ ሰራዊት ሆኖ እያለ ከብዙ ሰራዊት አባሎች ጋር እጁን ለመንግስት ሰጥቶ እስር እቤት እንደነበረ አውቃለሁ ነው

ይሄንኛውስ አብዱራህማን ባሌስ --- መሆኑን ነው የምታውቀው

አብዱራህማን ባሌ ከእዛ ከተማሪዎቹ እንቅስቃሴ በኋላ አላየሁትም ከእዛን በኋላም ታስሮ ነበረ ትንሽ በእስር ላይ ቆይቶ ነበረ ከእዛ በምንም አይነት እረብሻ ውስጥም ሆነ ነገር ውስጥ ሲሳተፍ አላየሁትም ተማሪ ነው

እ

ተማሪ ነው በምንም አይነት እረብሻ ውስጥ ሲሳተፍ አላየሁትም ከእዛ በኋላ

ዐ/ሕግ ድገሙለት ጥያቄውን

ጥያቄውን ድገሙለት አልተመለሰም እኮ

ጥያቄው ምንድነው ያልኩት

ቆይ ቆይ ቆይ እኛ እንጠይቀዋለን

ስለ እሱስ ምን ታውቃለህ ከእዛ በኋላ በለው በቀላሉ ስለ አብዱራህማን ባሌ ምን ታውቃለህ

አሁን መስክሯል እኮ ከእዛ ከተማሪዎቹ ብጥብጥ ወዲያ ምንም ነገር ውስጥ መንቀሳቀሱን አላውቅም

ከእዛ በኋላ

አም አላውቅም

እሺ ሌላ ጥያቄ

620

ከእዛ በፊትስ ከእዛ በፊት ምን ያደርግ ነበር ከእረብሻው በፊት የሚኒሻ ዘርፍ ሀላፊውን ካባረሩት በፊት ምን አይነት እንቅስቃሴ ነበረው

እኔ የማውቀው በዚሁ የተማሪዎቹ እረብሻ ውጪ ምንም የማውቀው ነገር የለም ግን ከሰው እንደሰማሁት ገንዘብ እየሰበሰበ ለኦነግ ሰራዊት ይሰጣል ሲባል ሰምቻለሁ

አበቃችሁ

ጨርሰናል

መስቀለኛ ጥያቄ አለ እሺ ይቀጥል

የተከሣሾች ተከላካይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ

የአብዱራህማንን ኢብራሂምን እና ፋጤን እዛው ከተማ ነው የሚያውቋቸው

አዎ እዛው ነው የማውቃቸው

በ---------

አዎ ከዚህ ነገር ጉዳይ በፊት አዎ

ከእዛን በኋላ በሰላም ሲኖሩ ነው የሚያውቋቸው

ከእዛ በኋላማ እንዳልኩት ነው

እሺ ስለዚህ ገንዘብም መሰብሰብ አለመሰ በወሬ እንጂ ሲሰበስቡ አይተው አያውቁም

ብለዋል ሰማሁ እኮ ስላሉ

አዎ አላየሁም

---- አብዱራህማንን በተመለከተም ፍ/ቤት --- መስክረዋል አይደለም

አዎ የወረዳው ፍ/ቤት ቂርቤ የእነሱ ጉዳይ እዚህ አይደለም የሚታየው ወደ ፌደራል ነው ብለው ወደ እዚህ አሸጋግረውኛል

ኢብራሂምም ኢብራሂምም ላይ መስክረዋል የዛኔ

አዎ

በ3ቱም ላይ

ስለዚህ ኢብራሂም በሰላም እጁን ለመንግስት ሰጥቶ መኖሩንም ያውቃሉ

አዎ በመንግስት እጅ መሆኑን አውቃለሁ

አበቃችሁ ድጋሜ ጥያቄ አለ ዐ/ሕግ

የለንም

የለም

የለንም

የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄም የለም እናመሰግንሀለን መመለስ ትችላለህ ማን ይጠራ ዐ/ሕግ

64ኛ የዐ/ሕግ ምስክር አደም መሀመድ

ስንት ስልሳ

አራተኛ ምስክር

አደም

አደም መሀመድ

መሀመድ

አዎ

በስንተኛ ላይ ነው

በ1ኛ በ5ኛ የለችም እንጂ በ8ኛ በ11ኛ እና በ14ኛ ተከሣሾች ላይ

ምስክሩን ጥሯቸው መሀላ አስፈፅሚቸው ምስክሩ መሀላ ፈፅመዋል አማርኛ ይችላሉ አቶ አደም

622

አልችልም

እሺ በአስተርጓሚ እየተረዱ

64ኛ የዐ/ሕግ ምስክር

ስም - አደም መሀመድ

አድራሻ - ጉሎልዳ ወረዳ

ለምስክርነት ነው የቀረቡት

የዐ/ሕግ ምስክር ሆኜ ነው የቀረብኩት

በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት

አብዱራህማን ባሌ

ሌላ

ፋጥሽ አሜ

ሌላ

ከማል አልይ

ሌላ

ሌይሳ ቦኬ ዙቤር

ዙቤር ሌላ

ኢብራሂም ገለታ ላይ ምስክር ልሆን ነው የመጣሁት

ጥሩ በእነዚህ ላይ ነው የሚመሰክሩት

አዎ

ፀብ ዝምድና አለዎት ከእነሱ ጋር

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ቁጥር 4 ፌዴራላዊ ዲ/ሪፐብሊክ

623

የለኝም

እስቲ አሳዩን እነዚህን ሰዎችን እሺ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ እስቲ ዐ/ሕግ

የዐ/ሕግ ዋና ጥያቄ

እሺ አደም አሁን ያስነሳካቸው እነማን እነማን እንደሆኑ ትነግረናለህ እሱ ማን ነው

አብዱራህማን ባሌ

እሺ ያንኛውንስ

ዙቤር

ዙቤር ሌላስ 11ኛ ተከሣሽ እሺ ያንኛውስ

ዙቤር ማን ነው ቆይ ቆይ ቆይ 1ኛ ተከሣሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል እስቲ እጅህን አውጣ ዙቤር ዙቤር ማን ነህ ስንተኛ ነው 11ኛ

11ኛ ተከሣሽ

አሥ እሺ 11ኛ ተከሣሽን በችሎት ለይቶ አሳይቷል ከማል ማን ስንተኛ ነህ 5ኛ ተከሣሽንም በችሎት ለይቶ አሳይቷል ኢብራሂም 14ኛ ተከሣሽንም በችሎት ለይቶ አሳይቷል 14ኛ ተከሣሽ ጥያቄ ቀጥሉዋ

እሺ እነዚህን 4 ሰዎች ለይተክልናል እስቲ ምን እንዳደረጉ ነው የምታውቀው እስቲ አንድ በአንድ ያደረጉትን ነገር ከጊዜው ጀምረህ እስቲ ንገረን

ከ1998 ዓ/ም እስከ 2001 ድረስ

እሺ

የአባሥ ማለት የኦነግ ሰራዊት ሆነው

እ

አባል ሆነው ሲንቀሳቀሱ ነበረ በእኛ ወረዳ ውስጥ